መድረሱቻችን በመጽሐፍ ቅዱስ ዕይታ



በኃይሉ ተርኑት

መድረስቻችን በመጽሐፍ ቅዱስ ስዳታ

በኃይሉ ቸርነት

ራዕይ አሳታሚ
አዲስ አበባ 1997 ዓ.ም.

መድረኮቻችን
በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

ይህንን መጽሐፍ ያለ ደራሲው ፈቃድ ማባዛት
ወይም እንደገና ማሰተም በሕግ የተከለከለ ነው።

© Hailu Cherenet 2004

ራዕይ አሳታሚ
የፖ. ሳ. ቁ 2332
አዲስ አበባ

RP 17

ይህችን መጽሐፍ ዘወትር በአገልግሎቴ ዋጋ ከፍለው አብረውኝ ስቆሙት ባለቤቴና ልጆቼ መታወሻነት አበረክታለሁኝ::

ይህ መጽሐፍ የተጻፈው ምእመን ፊት ስሚቆሙና ስሚያቆሙ ነው:: ለእጥቢያ ቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች፥ ለመድረክ (ፑልፒት ኮሚቴ እባላት፥ ለሰባኪዎችና ስመዘምራን ነው:: መምህር ኃይሉ ቸርነት «ምስባክ» የሚል አዲስ ቃልም እያስተማረን ነው:: መድረክ የሚለው ቃል ቲያትረኞች ያልሆኑትን ነኝ የሚሉበት፥ ፓስቲስኞች እራሳቸውን ከሚያስተዋውቁበት ቦታ የተለየ መሆኑን ሲያስተምረን ይህንን ቃል የተጠቀመ ይመስለኛል::

እንድ ሥራ ላይ ስንመደብ ሥራውን በሚገባ ስመሥራት እንድንችል ለለዚያ ሥራ የሚለጥ ኮርስ ካለ ያን ኮርስ መውሰድ ጥሩ ነገር ነው:: ለምንመደብበት ኮሚቴ ሁሉ ኮርስ ቢኖር ጥሩ ነው:: ዛሬ አብዛኛው ነገር የሚስማውና የሚጠፋውም መድረክ ላይ በእዲሱ ቃል በምስባኩ ላይ በሚቆመት ነው:: በዚህ መጽሐፍ ላይ የቀረበው አውነት ምስባኩ ላይ የሚያቆመና የሚቆመት መወሰድ ያለባቸው ኮርስ ነው ብየ አምናለሁኝ:: በባለሙያ የተጻፈ ነው:: ወንድም ኃይሉ ቸርነት የመድረክ አገልጋይና መምህርም ነው::

ሽማግሌዎች ሆይ የእግዚአብሔርን መንጋ እንድትጠብቁ፥ እንድትመገቡ (በመድረኩ ላይ በምታቆሙት ሰው እማከኝነት) እንድትመሩት የወንድማችንን ምክር ገንዘብ አድርጉ:: በየግላችሁ እንድ እንድ ምዕራፍ አንብባችሁ በየስበሰባችሁ በሕብረት በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ የየራሳችሁን ጥያቄዎችም አክላችሁ እንድትወያዩ ያስፈልጋል::

ያሰብን ተግዳሮት ከፍተኛ ነው:: እካሔዳችን ግን ተመጣጣኝ እይደለም:: በተሰይ የእሁድ ጠዋት የእምልኮ ጊዜ ምእመኑ የሚማርበት ዋና ጊዜ ነው:: «ሕዝቤ እውቀት ከማጣት የተነሳ ጠፍቷል»(ሆሴ 4:6) ያለውን ልብ ልንል ይገባል:: አምላኩን እንደሚገባ ያወቀ ሕዝብ ባወቀው መጠን ያመልከዋል:: ይከተለዋል:: ስለዚህ ምስባኩ ላይ የሚቆመ አገልጋዮች ማንነት፥ ቅድሰና፥ዝግጅት ፥ ስጦታው፥ ችሎታው ሕዝቡን ስማነጽ ወላኝ ነው::

ሚሊዮን በለጠ

መድረኮቻችን በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ

ማውጫ

መቅድም..... 9

መግቢያ.....13

ክፍል አንድ መድረኮቻችን በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ.....16

1.1 በቃሉ የተፈጠረ አዲስ ሕብረተሰብ
1.2 ክርስቶስ የምስባኩ ማዕከል
1.3 የምስባኩ ተቀዳሚ ዓላማ
1.4 ምስባኩ ሰቃሉ ተገዥ
1.5 በምስባኩ ሰመቆም
1.6 ምስባኩ ሰእነማን?
1.7 ምስባኩ እንዲዋብ
1.8 ምስባኩ እንዲጠበቅ

ክፍል ሁለት ትኩረት የሚሹ የመድረክ አገልግሎቶቻችን.....48

2.1 የመድረክ ትርጉምና ምንነት
2.2 የመድረክ ክብር
2.3 ፕሮግራም መሪዎችና መድረኮቻችን
2.4 ዘማሪያንና መድረኮቻችን
2.5 የቡድን ዘማሪያንና መድረኮቻችን
2.6 የሙዚቃ ቅንብርና መድረኮቻችን
2.7 ስባኪያንና መድረኮቻችን
2.8 መባና መድረኮቻችን
2.9 ማስታወቂያዎችና መድረኮቻችን

ክፍል 3 የምስባክ (ፑልፒት) ኮሚቴ.....107

3.1 የምስባክ ኮሜቴ ስምን?
3.2 ውጤታማ የምስባክ ኮሚቴ
3.3 የመጋቢው ሚና
3.4 የምስባክ ኮሚቴና የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ
3.5 የምስባክ ኮሚቴና ባስ እደራንት
3.6 የምስባክ ኮሚቴ እንደ ባስራአይ
3.7 የምስባክ ኮሜቴ እንደ ጠባቂ

ክፍል አራት የመእመኑ ምላሽ ሰመድረኩ.....140

4.1 ምእመኑ እንደ አምላኪ
4.2 ምእመኑ እንደ ተመጋቢ
4.3 ምእመኑ እንደ ተባባሪ
4.4 ምእመኑ እንደ ታራሚ
4.5 ምእምኑ እንደ ገምጋሚ
4.6 ምእመኑ እንደ ጋላፊ
4.7 ምእመኑ እንደ ጠያቂ

ማጠቃለያ

ምስጋና

ከሁሉ በማስቀደም ይህችን አነስተኛ መጽሐፍ ለመጻፍ ረድኤቱን ያበዛልኝን አምላክ እመሰግናለሁኝ። መንፈሳዊ ጽሁፍን ለማዘጋጀት ሲነሱ ከችሎታ ይልቅ ችሮታው፥ ከብልሃት ይልቅ ምሪት እንዲሁም ከጉልበት ይልቅ ረድኤት ተፈላጊ መሆኑን እንድማር ዕድል ስለ ሰጠኝ ምስጋና ይድረሰው። ታየኝ የምለውን በእኔ ሁኔታ ለመግለጥ ባደረግሁት ጥረት የእኔነቴ አሻራ ያረፈባቸውን ጽሁፌቼን በትዕግስት እንብበው ገንቢ እርማት የሰጡኝን ወገኖች ጌታ አብዝቶ ይባርካቸው እላለሁኝ።

ወንድሜን ጋሽ ሚሊየን በለጠ አንዳስብ ያበገደዱኝን ጥያቄዎች በመጠየቅ እንዲሁም የዚህን መጽሐፍ ረቂቅ አንብቦ ገንቢ አስተያየት ስለሰጠኝ አመሰግናለሁኝ። ፓስተር ሥዩም ገብረጻዲቅ ከድርብርብ የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት እንዲሁም ከራሱ የዕረፍት ጊዜ ቆርሶ ረቂቁን አንብቦ ገንቢ ሃሳብ ስለ ሰጠኝና ሰላበረታታኝ ጌታ ይባርከው።

ፓስተር ተሰፋዬ ጋቢሶም እንደዚሁ ከድርብርብ የመጋቢነት ኃላፊነቱ ባሻገር የእኔን የጊዜ ገደብ አክብሮ፥ ጊዜ ውስዶ ረቂቁን አንብቦ ስለ ሰጠኝ ገንቢ ምላሽ ምስጋናዬ ከፍተኛ ነው። በተጨማሪ ሞራሌን የሚገነባና በጽሁፍ ሥራ እንድገፋበት የሰጠኝን ወንድማዊ የአጋር ማበረታቻ ምንጊዜም አልረሳውም።

ወንድሜ ገዛኸኝ ሙሌ ጋሼ እያለ እያሞካሸ፥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ በተባ ብዕሩ የኔን የጎለደፈ ጽሁፍ ለማቃናት የበኩሉን ባያዋጣ ጽሁፌ ዛሬ የያዘውን መልክ አይዝም ነበር። እርሱንም ጌታ ይባርክልኝ። ወንድሜ ዶ/ር ግርማ ተሰፋዬ ረቂቁን አንብቦ አያቸው ያለኝ ነገሮች በርግጥም ሊታዩ የሚገባቸው ነበሩ። ወገኖች!! ቁጭ ብለን ሰንወያይ የሰጠኝን ገንቢ ሃሳብ በምን

ልተምነው እችላለሁ? ጌታ ይባርክህ። ወዳጄ ሰሎሞን ጥላሁን በበኩሉ ረቂቁን እንብቦ ግልጽነት የጎደላቸውን አባባሎች አሻሚ የሆኑ ነገሮችን ባያሳየኝ መጽሐፏ እንደ አሁኑ አትሆንም። አህቴ ሰላም አስጥፋኖስም ረቂቁን በማረም ያደረገችው አስተዋጽኦ ታላቅ ነው ጌታ ይባርካት። ወዳጀና የሙያ አጋሬ ውድነህ አንዳይላሉ ጥያቄየን በመመለስ፥ ይህች መጽሐፍ እንዲህ ዓይነት ቅርጽ እንዲኖራት የሰጠኝ ማበረታቻ የሚረሳ አይደለም።

የመጽሐፉን የሽፋን ስዕል ውብ እድርጎ ያዘጋጀውን ሰዓሊ መጋቢ ይድነቃቸው ለገሠን ከልብ እመሰግናለሁኝ። ከሺ ቃላት አንድ ስዕል የተበላውን አውነታ አስረግጦልኛል። ጌታ ይባርከው። በልፋታቸው ይህችን መጽሐፍ እዚህ ያደረሷትን ወገኖቼን ሁሉ ጌታ ይባርካቸው።

ስለ መጽሐፉ አስተያየት ቢኖራችሁ በፖ.ሣ.ቁ 101488 አዲስ አበባ ብላችሁ መጻፍ ትችላላችሁ።

ኃይሉ ቸርነት
መሠረተ ክርስቶስ ኮሌጅ
አዲስ አበባ

መቅድም

ነገር ግን ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን (1ቆሮ 14 ÷ 40)።

የምናመልከውና የምናገለግለው አግዚአብሔር አምላካችን የነፃነትና የሥርዓት አንዲሁም የዓይነትና የእንድነት እምላክ ነው። ስለዚህም የሁክት ሳይሆን የሰላም እምላክ ነው (1ቆሮ 14:33)። ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምዕመናን እበክሮ የሚያስገነዝበው ይህንን እውነት ነው። ለምን ቢባል÷ አነርሱ በነበራቸው የግል ሥጦታ ምናልባት በነጻነት የማገልገልን ጉዳይ ትልቅ ሥፍራ ሰጥተውት የመተሳሰብንና የመተናነጽን ጉዳይ ችላ ብለው ይሆናል። ሁሉም ዓይነት የጸጋ ስጦታ አያላቸው የአጠቃቀም ሥርዓትና የዓላማ አንድነት የጎደላቸው ይመስላል። በዚህ ምክንያት የጋራ በሆነ የማምለኪያና የመገልገያ ቦታቸው÷ መድረካቸው ሁሉን በአገባብና በሥርዓት ያደርጉ ዘንድ በጥብቅ እንደተመከሩ ማየት እንችላለን።

በተሰጠው ተራ በአገባቡና በሥርዓቱ እየቆመ÷ አገልጋይ የጠለለና ኩልል ያለ መለክታዊ መልእክት በሚናገርበት የአገልግሎት ቦታ እንግዳ ለው ቢገባና ቢታዘብ ሊናር የሚችለውን እጋንታዊ ምላሽ ሐዋርያው ጳውሎስ ጽፎልናል። ምላሹም በእውነት አግዚአብሔር በመካከላቸው ነው እያለ በፊቱ ወድቆ ለአግዚአብሔር መስገድ ነው (1ኛ ቆሮ 14:25)።

አግባብና ሥርዓት የጎደለው ያልታረመና ለመታረም ያልተዘጋጀ የመድረክ አገልግሎትን እንግዳ ሰው ቢያይ ÷ የሚሰማው የእግዚአብሔር ሕልውና ሳይሆን የአገልጋዮች የአሠራር ችግር ነው። አናም ወድቆ ለአግዚአብሔር መስገዱ ይቀርና ሌላ ጊዜ ወደዚያ ሥፍራ ላሰመመለስ ወስኖ ሊሔድ ይችላል። በዚህ ዓይነት መንገድ እስከዛሬ የደረሰብንን የነፍስ ኪሳራ ለመገመት ይቻል ይሆን?

ስለ እርምት ስነጋገር ግን በቁጥር ጥቂት ያይደሉትን በአግዚአብሔር ፍርሃትና በክፍተኛ የኃላፊነት ወይም የተጠያቂነት ስሜት ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ በማገልገል ላይ ያሉትን አየታረመ ለመማር የተዘጋጀ ልብ ያላቸውን ቅን አገልጋዮች ማስታወስ ተገቢ ነው። ማስታወስ

ብቻ ሳይሆን በርቱ ማለትም ያስፈልጋል። በአግዚአብሔር ማደሪያ ቤት እንዴት መኖር እንደሚገባ ማወቅ ÷ የአገልግሎቱንም ክቡርነት መረዳት እየጨመረ እንዲሄድ÷ በምለሌነታቸው የሚያስተምሩን ብዙ አሱንና እነርሱን እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርካቸው እንላለን።

መቼም÷ የመስበኪያ ቦታ የእግዚአብሔር እፍ በተባሰ ለዎች እማካይነት የአግዚአብሔር ክቡር ሃሳብ ወደ ለው የሚተላለፍበት ክቡር ቦታ ነበር። ዛሬ በቦታው የሚቆሙት ለዎች መሪ÷ ዘማሪ÷ አስተማሪ ወይም ሰባኪ ሊባሉ ይችላሉ። በዚህ ቦታ ግን እግዚአብሔርን በመፍራትና በመንቀጥቀጥ÷ ለእግዚአብሔርም ሕዝብ ሕይወት በመጠንቀቅ ያገለገሉ ነቢያትና ሐዋርያት ነቀፋ የሌለውንና በክብር የሚታወስ ተልእኮአቸውን አየተወጡ እንዳለፉ ሊዘነጋ አይገባም። መድረኩ የጌታ ነው። ጌታን በምስባኩ ቆመን የምናገለግል ሁሉ ይህንን አንርሳ። ይልቁንም ለቃሉ አገልጋዮች ሁሉ ዋና አለቃና የአገልግሎቱ ባለቤት የሆነው ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቆመበት ቦታ መሆኑ ዘውትር ሊታወስ ይገባል።

በጋራ ለማምለክ በምንለበሰብባቸው ቦታዎች ደግሞ ማረጋገጥ የሚገባን እንድ ትልቅ ጉዳይ አለ። ይህም እግዚአብሔርን ከልብ የማክበር ጉዳይ ነው። እግዚአብሔር አንደ አባት የምንወራውን ያህልና ጌታ እያልን የምንዘምርለትን ያህል ልባዊ የሆነ የአባትነት አክብሮትና የጌትነቱ ፍርሃት በአኛ ዘንድ ስለመገኘቱ ራሳችንን ሁልጊዜ መጠየቅ አሰብን። በነቢዩ ሚልኪያስ የአገልግሎት ዘመን እንደነበሩት አይሁድ ቃላችንና እገልግሎታችን ከአፍ ያላለፈ÷ ወደ ልብ ጠልቆ በተግባር ያልተደገፈና የድፍረትም አንዳይሆንብን ቆም ብለን ማሰብ ይኖርብናል (ሚል 1÷6 ና 3÷ 13)።

አሁን አሁን በጉልህ ለሚታዩት የመድረክ ላይ ግድፈቶቻችን መሠረታዊ መነሻው ምናልባት አግዚአብሔርን አልፈራ ሰውንም አላፍር ብሎ ያመጸው ልባችን ሳይሆን ይቀራል? እግዚአብሔር ራሱ ምሕረቱን በአኛ ላይ ገልጦ የተፈራ ማንነቱንም ዳግም በማሳየት አርሞን የሚፈራ ልብ ይመልስልና!! ይሻሰናልና።

ወንድማችን ኃይሉ ቸርነት መድረኮቻችን በመጽሐፍ ቅዱስ አይታ በተሰኘ መጽሐፉ በዘመናችን በስፋት አየተስተዋለ ላለው የጥንቃቄ ጉድለትና

እስከፊ ድፍረት ዓይነተኛ በሆነ የራሱ አቀራረብ እራሚ የሆነ ምክሩን ለመለገስ የበኩሱን ድርሻ እበርክቶአል የሚል እምነት አለው፥ የዚህ መቅድም ጸሐፊ። ጠንከር አድርገን የአገልግሎታችንን አያያዝ መመርመር ላለመድን ስእንዳንዶቻችን ሃሳቦቹ በአንዳንድ መልኩ ጠንከር ይሉብን ይሆናል። ቢሆንም

«ጻድቅ በምሕረት ይገሥጸኝ፥ ይዝለፈኝም።

የኃጢአተኛ ዘይት ግን ራሴን እይቅባ፤ (መዝ 141፥ 5) ማለቱ ነው የሚያዋጣን። ምክንያቱም በአገልግሎት አደባባይ ግራ የሚያጋባና ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ የሚያሳዝን ተግባር እየፈጸምን ሳለ የሰው እንደበት ከሚባርከን የአገልግሎቱ ዋናው ባለቤት፥ ጌታ፥ የሚልከውን ልኮ ቢያርመን ለነገ የምንተርፍ እንሆናለን። ስለዚህ በለፋና በለከነ እእምሮ የመጽሐፉን መልእክት ለመረዳት መለናዳቱ ይመረጣል።

ይህ ማለት በገጾቹ ላይ የሰፈሩትን አረፍተ ነገሮች ሁሉ ለመቀበል ግዴታ እንገባለን ማለትም አይደለም። የመጽሐፉ ደራሲም እንዲህ እይለንም። ሃሳቦቹን በእግዚአብሔር ቃል እይታ የቤሪያ ለዎች እንዳደረጉት «ነገሩ እንዲህ ይሆንን?» እያልን ብንመረምር ከደራሲው የልብ ትርታ ብዙ የራቅን አንሆንም ማለት ነው (የሐዋ 17፥11)።

ወንድም ኃይሉ በዚህ መጽሐፉ ÷ የምስባከ ኮሚቴንም ኃላፊነት በአጽንኦት ይጠቁማል። ኮሚቴው የአረኝነት ሥራውን በትጋት እንዲወጣም በማሳሰብ ይጮኻል። ይህ የእግዚአብሔር መድረክ የድረሱልኝ ጥሪም ይመስላል። እምን፥ ልዑል እግዚአብሔር በማዕካላዊነት ትኩረት ወለዶ ለሳምና ጤና ለጪ እንዲሁም የሚያንጽ ድምጹ ሲሰማበት በሚገባው ምስባክ ላይ ይህ ብቻ እንዲረጋገጥ ለማድረግ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ ቸልታቸውን እቁመው ጥንቃቄ መጨመር ይኖርባቸዋል። ባለማወቅ የሚያጠፉትን አለተምሮና መከሮ በማቅናት፥ ጀማሪ የመድረክ አገልጋዮችን በማለልጠንና በማበረታታት፥ የየዕለቱንም አገልግሎት ጊዜው ሳይረፍድ በመገምገምና አለፈላጊ ማስተካከያዎችን በማድረግ ትጋትን መጨመር የወቅቱ ብቻ ሳይሆን ወራትን ያለቆጠረ ጥያቄ ሳይሆን አይቀርም። ስለዚህ----------።

ሐዋርያው ጳውሎስ የአረኝነት ኃላፊነቱን ተወጥቷል። የቆሮንቶስ ምእመናን በጸጋ ስጦታዎቻቸው በነጻነት እንዲጠቀሙበት እያበረታታ ሁሉ

ግን የእግዚአብሔርን ማኅበር፥ ቤተ ክርስቲያን በሚያንጽ መንገድ፥ በአገባብና በሥርዓት፥ ይሁን ብሏቸዋል። ወንድም ኃይሉ ቸርነትም የዚህ ዘመን ኃላፊነቱን ለመወጣት ይህን መጽሐፍ አበርክቷል። ቀሪው ድርሻና ምላሽ የእኛ የአንባቢያን በተለይም በእግዚአብሔር መድረክ ላይ መቆምን የምናዘወትረው ይሆናል። በከበረውና በተቀደሰው የአገልግሎት ቦታ ላይ በማስተዋል አንድናገለግለው፥ በውጭ ያሉትን ወደ እግዚአብሔር ቤት የሚያመጣ፥ የመጡትን ደግሞ በለላም አያነጻ የሚያሳድግ መጽሐፍ ቅዱሳዊና መንፈሳዊ ሥራ አንድንሠራ ጌታ በጸጋው ይርዳን። አሜን!!

ፓስተር ተስፋዬ ጋቢሶ
ከአዋሳ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን
መስከረም 7 ቀን 1997 ዓመተ ምህረት

መግቢያ

መጽሐፍ ቅዱስ ለሁሉም ነገር የሚሆን ብርሃንን የሚለግስ መጽሐፍ ነው። በሕመም አልጋቸው ላይ ጋደም ብለው በደጃፍ የሚማቅቁትን ለማጽናናትና ለማበረታታት የመጽሐፍ ቅዱስ ገጾችን ገለጥ አድርገን እንዲህ ይላል ብለን አጽናንተናል፥ መክረናል፥ አበረታትተናል። ደግሞ እንደ ሠርግ ባለ የደስታ ጊዜ ደግሞ ይህንኑ መጽሐፍ ይዘን አብሮ ስለ መኖር ከሚለግሰው ድንቅ ምክር መሸሮችንና ታዳሚዎችን መክረንበታል። በቤተ ክርስቲያን ተሳስረን ስመኖር የሚረዳንን ደንብ ለማርቀቅ ስንፈልግም ይህንን መጽሐፍ ብንደገፍ የሚለግስን ብርሃን አኩያ የለውም ብለን ከውስጡ በወጡ ሃሳቦች ደንባችንን ቀርጸናል። አንዳንዴም ከመስመር የወጣ ልምዳችንን መልክ አሲዘንበታል።

የምንወዳቸውን ባጣንና በክፉን ጊዜ ደግሞ በልቅሶ ቤት ስሚያዝኑ መጽናናትን ከዚህ መጽሐፍ ያመጣንበት ጊዜ ጥቂት አይደለም። በተለይ ለቅሶ ቤት ይዘነው ስንቆም ደግሞ ይህ መጽሐፍ እዚህ ምን አመጣው? እዚያው ጸሎት ቤታቸው አይበቃም? እሁንስ አበዙት፥ አስከንባል ድረስ ላዘኑ ወገኖቻችን የሚበጅ ምክር፥ ለሐዘንተኞች የማጽናኛያን መልእክት ለማድረስ ከፍተነዋል። በየትኛውም የሕይወት ግስጋሴ ውስጥ ምክሩን ፈልገን ጠጋ ስንለው የሚረዳንን ጥበብ የሚያቀብል እንደዚህ ያለ መጽሐፍ የለም። አይኖርምም። ታዲያ ይህ መጽሐፍ ስለ መድረኮቻችንስ የሚለው ይኖር ይሆን? ብዬ ለአያሌ ወራት ቢዘህ ጥያቄ ላስብ ቆየሁኝ። በእኔ መረዳት መድረኮቻችን የመጽሐፍ ቅዱስን እውነትን የምናስተጋባበት፥ የእምላክን ፈቃድ የምናስታውቅበት ቦታ ናቸው።

ምስባክ ጌታችን ልዩ ልዩ ባሪያዎቹን በመጠቀም ሃሳቡን ለማስተላለፍ የመረጠው ቦታ እንደሆነ ፣ ሁላችንም በደምላላው የምናውቅ ይመስለኛል። ይሁን እንጂ ይህ አጠቃላይ ግንዛቤ ከመሪዎች ፥ ሰባኪዎች፥ መዘምራን እንዲሁም ከምእመናን እየራቀ በመድረኮቻችን ላይ የሚታዩ ነገሮች የማይጠበቁ እየሆኑ በመምጣታቸው ምናለ ብናስብበት? የሚል ልባዊ

ጥያቄዬን ጠይቄ ለመነሻ የሚሆኑ፥ ለእኔ የሚታዩኝን ጥቂት መፍትሄዎች ለማቅረብ ሙከራ እድርጌያለሁኝ። ዳሩ ግን እነዚህ መርሆዎች ያለቀላቸው፥ ፍጹምና የማይታረሙ ናቸው ብዬ አላምንም። ነገር ግን ቆም ብለን ራሳችንን እንድናይ ዕድል ይስጡናል የሚል ግምት አለኝ።

እኔና ይህንን አይታዬን የሚጋሩ ወገኖቼ ያለንበትን ሁኔታ ቆም ብለን በማየት ነገራችንን ለማረምና እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ለማድረግ ካልተጋን ቅዱሳን አይታነጹም፥ ወንጌል አይሮጥም እንዲሁም ጌታ ያዝናል የሚል ድምዳሜ አለን። ለዚህ ደግሞ መፍትሔው ለቤቱ ይገደናል የምንል ሁላችን ከምስባኩ (ከመስዊያው፥ ከፑልፒቱ ፥ ከመድረኩ) የሚፈስስውና ለሕዝባችን የሚተላለፈው ነገር በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ቅርጽና ይዘት የተቃኘ እንዲሆን የበኩላችንን ስናዋጣ ነው፥ የሚል እምነት አለን።

ይህች ትንሽ መጽሐፍ በዚህ አቅጣጫ ላለን ምኞት መነሻ የሚሆን ጥቂት ነገር ብላለች የሚል ግምት አለኝ። ከዚህ በኋላ በዚህ ርዕስ ጉዳይ ጥልቀት ያላቸው ድንቅ ጽሁፎች፥ የጠለቁ ትምህርቶች እንዲገለጡና ምስባኮቻችን (መስዊያዎቻችን፥ ፑልፒቶቻችን፥ መድረኮቻችን) ከሚታይባቸው ግዙፍ ጉድለቶች ነጻ ሆነው ሁላችንን እንዲያንጹ የሚያግዙ ድርጊቶች ይከናወናሉ የሚል ምኞትና ልባዊ ጸሎት አለኝ። አንባቢያን ጥቂት ክፍሎቿን አይተው ቅጽበታዊ አሉታዊ ምላሽ ከመስጠታቸው በፊት መጽሐፏን ከዳር እስከ ዳር በትእግስት እንዲያነቡ አጋብዛለሁኝ።

በተጨማሪም ምስባኮቻችን ይህ መጽሐፍ እንደሚላቸው ናቸው? ወይስ ሌላ ገጽታ አላቸው? የሚለውን ጥያቄ በራስም እንዲመልሱ የተረጋጋ ጊዜ ወስደው ያስቡበት። መጽሐፏ የቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ የሚቆሙትን፥ የሚያቆሙትን፥ ምስባኩ ላይ ከሚቆሙ የሚመጣውን የሚያስተናግዱ ተጋባዣቿን በየፈናቸው ቃኝታለች። ከዚያም በምስባኩ ላይ በሚቆሙት ወገኖች በህሉት ከፍላ ለማየት ትሞክራለች። ምስባኩ አምንታዊም አሉታዊ ነገሮች ሲያስተናግድ አስተውላለችና። እንደ ቃሉ በሆነ የምስባክ አገልግሎት ታንጸናል ትላለች። በተቃራኒው ከቃሉ አፈነግጠ

በምንለው የምስባክ አገልግሎት ደግሞ አሞናል የሚል ድምዳሜዋን ለአንባቢያን ታቀርባለች።

ይሁን እንጂ እይታችን በሁሉም አቅጣጫ እንከንየለሽ ነው አትልም። ስለሆነም አንባቢያን በትእግስትና በጥሞና እንብበው ይበጃል የሚሉት እንዲታረም የሚፈልጉትን ነገር እንዲሏት ትጠብቃለች። የመጽሐፏ ትኩረት በቀዳሚነት አሁድ አሁድ የሚኖረን አምልኮ ጊዜ ላይ ነው። ትንታኔዋም የሚያጠነጥነው ከጅማሬው እስከ ፍጸሜው በሚኖረው ጊዜ ላይ ነው። በተረፈ በአዘቦት ቀናት የሚኖረውንም የቅዱሳን ሕብረት እንስታ ምስባኮቻችን በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ እንዲቃኙ ማሳሰቢያ ታቀርባለች። እንግዲህ እኔ በዚህ ጥያቄ እንዳበሰ አንድ ግለሰብ የሚታየኝን ለማለት ምክሪያለሁኝ። ይህንን ጨምር ይህንን ደግሞ ቀንስ የምትሉኝን በልብ ስፋት ለማስተናገድ ሙሉ ለሙሉ ዝግጁ ነን። ጌታ ሁላችንም ፈቃዱን ፈጽመን ደስ እንድናሰኘው ይርዳን። መልካም ንባብ።

ኃይሉ ቸርነት
አዲስ አበባ መስከረም 1997

ክፍል አንድ መድረኮቻችን በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ

ጊዜው ብዙ ጥያቄ የሚጠይቅበት ነው። ጥያቄ በብዛት የሚጠይቅበት እንደዚህ ያለ ዘመን ከዚህ በፊት የታየ አይመስለኝም። በየአቅጣጫው ብዙ ጥያቄ ይጠየቃል። ጥያቄ የሚጠየቀው ግራ የሚያጋባ ድርጊት ሲፈጸም ነው። ለጥያቄ ተገቢ ምላሽ ሲጠፋ ሌላ ጥያቄ ይወለዳል። ያኔ የሕይወት እንግልት ይበዛል። የነፍስ ትግል ይጠነክራል። በተቃራኒው ሰተጠየቀው ጥያቄ ደግሞ ሁነኛ መልስ ሲገኝ እረፍት ለጠያቂው ይሆንልታል። ለሕይወት ጥያቄ ተገቢ ምላሽን የሚሰጥ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ያለ መጽሐፍ የለም። ወደፊትም አይኖርም። መጽሐፍ ቅዱስ ለሁሉም ነገር የሚሆን ብርሃንን የሚለግስ መጽሐፍ ነው።

መንፈሳዊ የሆነ ሁሉ ደግሞ ይህንን መጽሐፍ በመታዘዝ የውስጥ እምነቱን በውጫዊ ድርጊቱ ይገልጣል። የእግዚአብሔር መንፈስ በቃሉ ከተገለጠው እውነት ውጭ አይሠራም። ስለሆነም ከግላዊ ልምምድ ይልቅ በዘለቄታዊ ቃሉ የተመሠረተ ልማድ ምእመናን ያንጻል። ቃሉ እውነተኛ መተማመኛ ነው (መዝ 12:6 18:30 ምሳ30:5-6)። እንደ ቃሉ የሆነ እደራረግ ስቅዱሳን መካከል ሲለለጥን ጌታችንን ያስከብራል። ከቃሉ ውጭ የሆነ ነገር ሲያይል እኛን ያሰነቅፋል፥ የሚያመልኩት እንዴት ዓይነት እምላክ ነው? የሚል ጥያቄን ያስጠይቃል። ታዲያ በዚህ የጥያቄ ዘመን የሚያምነውም የማያምነውም ስለ መድረኮቻችን ይጠይቃል። የማያምኑት ለምኽ በጸሎት ቤቶቻችን በሚያዩት አግባብነትና ሥርዐት በጎዳላቸው ነገሮቻችን ምን ነካቸው? ብለው ሊጠይቁ ይስተዋላሉ። የወንጌል እማኞች ደግሞ ለመሆኑ መድረኮቻችን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚላቸው ናቸውን? የሚል ጥያቄን መጠየቅ ከጀመርን ዓመታት ተቆጠሩ። ሁላችንም የየበኩላችንን ጥያቄ እንጠይቃለን።

በጌታ ቤት የምንፈጽማቸው ተግባራዊ ድርጊቶች እንደ ሕያው ቃሉ መሆን ይኖርባቸዋል በሚለው እጠቃላይ መርህ ብዙ የወንጌል እማኞች ይስማማሉ። ስለሆነም ለሕብረት እምልኮአችንን የሆነ እደረጃጀት በመምረጥ መንፈሳዊ ድርጊቶቻችን እንፈጽማለን። የድርጊት ቅደም ተከተላችንን

የሚመራው የአደረጃጀት ቅርጽ እንደ ቤተ እምነቶቻችን ይለያያል። ይሁን እንጂ አብዛኛውን ጊዜ በብዙ ቤተ እምነቶች የአደራጃጀታችን ይዘቱ መሠረታዊ ልዩነት የለውም ። ምክንያቱም ለአደራረጋችን ሁላችንም ድጋፍ የምናደርገው ቃሉን ነውና። በመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ብንለያይም ስለ «አግባብና» ስለ «ሥርዐት» ያለን ልዩነት ያን ያህል የለፋ አይደለም። በተለይ በወንጌላውያን ክርስቲያኖች ዘንድ አንዲህ ዓይነቱ ልዩነት በአገራችን ያን ያህል የጎላ አይደለም። አንደውም አንዱ ቤተ እምነት ከሌላው ጋር ካለው መመሳሰል የተነሳ የልዩነት መበመር ማኖር አስከሚያበቸግር ደርሷል። ስለሆነም ስለ መድረኮቻችን የሚነሳው ጥያቄ አብዛኞቻችንን ይመለከተናል።

መጽሐፍ ቅዱስ በቅዱሳን መካከል ያለው አምልኮ የሚያንጽና የሚገነባ አንዲሆን መመረያን ይሰጣል። ስለሆነም አደረጃጀታችን ሁላችንን የሚገነባና የሚያንጽ እንዲሆን «ሁሉም በአግባብና በሥርዐት ይሁን» ይሰናል (1ኛቆሮ 14፡40)። ከላይ በተጠቀሰው የእግዚአብሔር ቃል ትዕዛዝ ላይ ሁሉት መሠታዊ መርሆዎች ተቀምጠዋል። በመድረክ ላይ ሕዝቡን ለማነጽ የሚፈስሱ ነገሮች በመጀመሪያ «አግባብነት» እንዳላቸው መጤን አለበት። «አግባብ» የሚለው ነገር የአንድን ነገር መጥቀም ሳይሆን ትከክለኛ አደራረጉንና ቦታውን አንዲሁም የሚታይ ቅርጹን ይመለከታል። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በሕብረት አምልኮአቸው ሰዓት ሲፈጸሙ ስለሚገባቸው ድርጊቶች አግባብ ያለው አደራረግ ዝርዝር መመሪያ ሐዋርያው ጳውሎስ በ(1ኛ ቆሮ 11:2-16፡ 14:34-36) አስታወቀ።

በዚያ ማህበረ ሰብ ባሕሉ ተጠብቆ ስለሚከናውን ነገር ሐዋርያው ጳውሎስ መመሪያን ከላይ በተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይሰጣል። በእነኚህ አማኞች መካከል አንዲደረጉ የታዘዙት ነገሮች አግባብነት ያላቸውና መፈጸም ያለባቸው ድርጊቶች ናቸው። እነዚያ ድርጊቶች ከሕብረቱ አምልኮ አልተገኙም ማለት ትልቅ ነገር ጎደለ ማለት ነው። ለምሳሌ «ሲጸልዩ መሸፋፈን» በዚያ ባሕል ተቀባይነት ያለው ድርጊት ነበር። ስለሆነም አለመሸፋፈን አግባብ ያልሆነ ድርጊት ነበር። ጸሎት ወይም ትንቢት ያለመሸፈን ሲከናወኑ ነውር መሆኑ ግልጽ ነበር።

በተጨማሪም ሴቶች መልእክት ሲተላለፍ «ዝም ይበሉ» ተባለ። በዚያን ጊዜ ብዙ ሴቶች ያልተማሩ ስለ ነበሩ ከመድረክ የሚነገረውን ሁሉንም አይረዱም ነበር። ስለሆነም ጥያቄ የሚሆንባቸው ነገር ሲኖር አጠገባቸው ያለውን ሰው ይጠይቁ ነበር። የጉባኤም የመድረክም ንግግር በአንዱ ክፍለ ጊዜ መስተናገዱ የአምላኪውን ትኩረት በእጅጉ የሚያዛባ አንዲሁም የተናጋሪውን መንፈስ የሚረብሽ ጉዳይ ስለ ነበር «ሴቶቹ በጉባኤ ዝም ማለታቸውና» በቤት ባሎቻቸውን መጠየቅ አግባብ ነበር። አግባብነት ያለው መመሪያ የተሰጠው አግባብ ያልሆነ ልምምድ ቤተ ክርስቲያኒቱን አናውጦ ስለ ነበር ነው። «ዝም ይበሉ» የሚለው ትዕዛዝ የአገልግሎትን ሁነኛ አጋርና ግማሽ ክፍል ማፈን አልነበረም። ይልቁንም የተሻለ አማራጭ ነበር። ሁከት እንዲወገድ ይህን ማድረግ አግባብ ነበር።

ዛሬም አግባብነት ስላላቸው ነገሮች ስንነጋገር እንዲተኮር የምንፈልገው መድረኮቻችን ውበታቸው እንዲጨምር መደረግ ያለበትን እያደረግን መወገድ ያለበትን አንድናስወግድ ነው። ምእመናን ገና ከቤታቸው «አግባብ» ያለው መስናዶ አድርገው መምጣታቸው የመድረክን ውበት ይጨምራል። ይሁንና ቤታቸው ጌታን እንደማያውቅ ሰው እየኖሩ በጸሎት ቤት ኃይማኖተኛ ቢሆኑ ጉባኤን ያስራሉ። ስለሆነም አግባበነት ባለው መንገድ ሕይወትን መንከባከብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው።

አገልጋዮችም የጊዜው ቃል÷ የጊዜው መዝሙር÷ የጊዜው ሙዚቃ÷ የጊዜው የፍቅር ስጦታ÷ የጊዜው ማስታወቂያ በመድረኩ ጊዘያቸውን ጠብቀው በአግባቡ አንዲተላለፉ ምቹ ሁኔታ መፍጠራቸው እንደ ቃሉ የሚጠበቅባቸው መሆኑን ሊረሱት አይገባም። ከላይ የተገለጹት መንፈሳዊ ድርጊቶች ከመድረኩ በጨዋነት ÷ በተአማኒነት ÷ በሐቅ÷ ራስን በመግዛት ወዘተ መተላለፋቸው ማረጋገጥ «አግባብነት» ያለው ድርጊት ነው። እነዚህንና እነዚህን የሚመስሉ መንፈሳዊ አገልግሎቶች በአግባቡ ከመድረኩ ሲፈሱ እንታነጸለን።

በመድረኮቻችን «በአግባብ» እየሆኑ ያሉትን ጎሽ በጎል በመድረካችን ሊታዩ አይገባም «አግባብ» አይደሉም ብለን የምንላቸውን ደግሞ ይታረሙ ለማለት ይህ መጽሐፍ ቀርቧል። ወገኖች!! በእኛም የዕለት ተዕለት ልምምድ

ለምሳሌ የባልና የሚስት የጓዳ ነገር አደባባይ ቢወጣ አግባብ አለመሆኑ ለአብዛኞቻችን አይወፋንም። በመድረኩ ላይም ከመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ ጋር የማይሔዱ ድርጊቶች ማከናወን የለብንም። የመጽሐፍ ቅዱሱ እውነት ይህ ሆኖ ሳለ በዛሬው ጊዜ ይህ መረዳት በብዙዎች ዘንድ አይገኝም። ስለሆነም አግባብነት የጎደላቸው አያሌ ድርጊቶች መድረኮቻችን ላይ እየተለመዱ መምጣታቸው እናያለን። ስለሆነም በዚህ ጉዳይ ለሰጋን በጊዜ እንድንታረምና አንድናስብበት ይህች መጽሐፍ መልእክቷን ታስተላልፋለች። በመድረካችን «አግባብ» ያልሆኑ ነገሮች መታየታቸው ብዙዎቻችን እንገነዘባለን። ጥያቄው ግን ለመሆኑ የቱ? የቱ? ነው አግባብ ያልሆነው? የሚል ነው። በሚመጡት ጥቂት ገጾች ላይ ተዘርዝረዋልና በጥሞና እንድትመለከቷቸው አጋብዛለሁ።

መጽሐፍ ቅዱስ በሕብረት ሳለን ለምንፈጽመው መንፈሳዊ አደራረጎቻችን ውበትና ውጤታማነት የሚሰጠን ሁለተኛው ምክር ደግሞ «በሥርዐት»(1ኛ ቆሮ 14:40) ነገሮቻችን አናድርግ የሚለውን ነው። በመድረኮቻችን የሚሆኑ ነገሮች አንደ ቃሉ በሆነ «ሥርዐት» ሲገሩ መንፈሳዊነት ይጎለብታል። ምእመናን ይታነጻሉ። የክርስቶስ አካልም ይገነባል። ከቃሉ እንደምናነበው በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ሕይወት ሥርዐት ጎድሎ፥ መንፈሳዊነት ተዛብቶ ነበር። ስለሆነም ከሰላም ይልቅ ሁከት ነገሰ «14:33» እንዲሁም በምዕራፍ 11:17-34 እንደምናነበው አንዱ ሲስከር ሌላው ተወጣ፥ አንዱ ሲጠግብ ደግሞ ሌላው ተራበ። እንዲህ ዓይነቱ ሥርዐት አልባ የሕብረት አምልኮ ከጌታ ዘንድ ቁጣን አመጣ። አንዳንዶች ታመሙ፥ ደከሙ ሌሎች ደግሞ በሞት ተቀሰፉ። ሥርዐት ሲፋሰስ መደማመጥ በአማኞች መሐል ይጠፋል። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በ(1ኛ ቆሮ 11:17-34ና 14:26-33) የሥርዐትን ተፈላጊነት ለምእመናን ያበገነዘበው። በሕብረት አምልኮ ትምህርት፥ መዝሙር፥መግለጥ፥ ልሳን፥ መተርጎም ቦታቸውን ጠብቀው በሥርዐት ካልፈሰሱ አደጋን ያመጣሉ።

ዛሬም ከመድረካችን ቅደም ተከተል ወጣቀው የሚፈሱ የፕሮግራም ዓይነቶች በቃሉ የተገራ ሥርዐትን ካልያዙ ቅዱሳንን ያስነቅፋሉ ጌታን ደግሞ ያስቆጣሉ፥ያስዝናሉም። ወገኖች!! ሁላችን ለአበላላችን ሥርዐት አለን። ወጡን ጠጥተን፥ እንጀራን በላዩ አናስከትልም ይልቁንም በሥርዐቱ አናቀናጃቸዋለን።

ስንለብበም የውሰጥ ስሬ ከቦላሌ መቅደሙ አይጠፋንም። ሥርዐቱን ብናዛባ ይላቅብናል ወይም ደግሞ የአእምሮ ሕመም እንዳጋጠመን ይታሰባል። ሥርዐት ሲፋለስ አምልኮ የሚያንጸ መሆኑን ያቆማል፤ አንደውም ፍርድን ከአምላክ ያመጣል። የቆሮንቶስ አማኞች ሥርዐት ያጣ አምልኮ ያስከተለውን ፍርድ አንብበናል። ዛሬ በቤቱ ከልክ ያለፈ ሥርዐተ አልበኝነት ሲነግስ የጌታ ዝምታ ገደብ የለሽ የሚሆን ይመስለን ይሆንን? ከቃሉ ያፈነገጠ ልምምድ እያየለ ሲመጣ የቤቱ ባለቤት ርምጃ መውሰዱ አይቀሬ ነው። ያ እንዳይሆን በአግባብና በሥርዐት እንድንኖር የመጽሐፍ ቅዱስን ምክር እንስማ።

አሁን አሁን መድረኮቻችን ላይ ፕሮግራም መሪዎቻችን ለሕዝቡ አክብሮትን የሚነፍግ ነገር አምልጦአቸው ሲወጣ ይስተዋላል። እንደማያከብሩት የሚያስገነዝቡትን አባባሎች በሚቀጥሉት ጥቂት ገጾች ታገኛ ላችሁ። መከባበርን ከጌታ ቤት የሚገፋ ድርጊት እየጎላ ሲመጣ በቸልታ ከታለፈ የወደፊቱ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ፍቅርና ትህትና ርቆት ኃይል ያጣል። ጌታችንን ያሳዝናል፥ የእኛን ሕብረት ደግሞ ይሸረሽራል። መድረኮቻችን የሰላም አምላክ በሚሰጠው ረድኤት ተልእኮአቸው የሚመራ እንዲሆን ለሥርዐት በቂ ትኩረት መሰጠት አለበት። ሥርዐት የለም ማለት ሁከት ተጋበዘ ማለት ነው። ስለሆነም በምንሰበሰብበት ቦታ ፕሮግራሞች ለውሰጣቸው የተሸከሙትን መንፈሳዊ ሰጦታ ለእኛ ያለመከልከል እንዲያደርሱ «አግባብና ሥርዐት» በሚባለው ሁነኛ ሀዲድ መጓዝ አለባቸው። ስለዚህ በአብዛኛው የፕሮግራም ይዘት ውስጥ የሚካተቱ መንፈሳዊ ነገሮቻችን አንደ ሰንሰለት መያያዝ አለባቸው። ስለሆነም ሥርዐትን የሚያዛቡ ነገሮች ይቁሙ። በመጽሐፍ ቅዱስ መነጽር ሲታዩ መቆም አለባቸው ብለን ከምንላቸው ውስጥ በዚህ አጋጣሚ ጥቂቶቹን እንጠቅሳለን ወደ ፊት በስፋት እንመለስበታለንና።

ፕሮግራም መሪዎች ፊት ፊት ሲመሩን ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል ግና ያን ማድረግ ላይሆንላቸው ስለ ቀረ የጎደለ ነገር አለ እንላለን። እንደ ቃሉ የሆነ ፕሮግራም መሪ ባለ መሆናቸው ያጎደሉብንን ሰለ አነርሱ በተጠቀሰው ከፍል ማየት ይቻላል። መሪው ለዘማሪያን አሳልፎ ከሰጠን በኋላ ሁሉም አንደ ቃሉ የማይሆንበት ጊዜ አለ። ምክንያቱም ዘማሪያን መልእክታቸውን የሚሸፍን ነገር ማስተናገድ እየጀመሩ ስለሆነ ነው። ግርዶሹ ምንድነው ካልን

ስለ እነርሱ በሚነሳው ክፍል የተዘረዘረውን የመድረኩ ፈርጅ በጥሞና ማየት ይጠይቃል። ስለሆነም በዝርዝር በቀጣይ ምዕራፎች ተጠቅሰዋልና ለዚያም ጊዜ ይበጡና ይዩት። ግርዶሽ እንዲወገድ ምን ማድረግ አለብን ሰሚለው የተሰጠውን በትእግስት ይመልከቱና ያልተነካ ካለ ያከሉበት። ከዘማሪው ቀጥሎ በፕሮግራም ቅደም ተከተሉ የሚመጡት ሰባኪያን ለመድረኩ መታወክ የበኩላቸውን አዋጥተዋል። ሰባኪዎች በሥርዐት የሚናገሩ የቃሉ አገልጋይነታቸው በተግባር ለማሳየት እቅም ሲያንሳቸው ይስተዋላል። ስለሆነም ከቃሉ አገልጋይነት ዝቅ ብለው በመድረኩ የሚታዩ ጌታን የሸፈኑ ሰባኪያን አሉና እነርሱንም እንደ ዘማሪያኑ ጌታን የከለለውን ግርዶሽ እንዲያነሱ ጽሁፉ ያስገነዝባልና ጊዜ ሰጥተው ይዩት።

መድረኩ ላይ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው የሚመጡ በሙሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለዛ ቢሳበሱ ሁላችን እንታነጻለን። ስለሆነም ስለ መባና ማስታወቂያ እንዲሁም መድረኩ ላይ ስለምናከናውናቸው አያሌ ነገሮች በአግባቡና በሥርዐት ሆነው ውበት እንዲጨምሩና እንደ ቃሉ እንዲሆኑ የቀረበውን ጥሪ በጥሞና እንይና ከቃሉ ጋር እናስተያያቸው ።

በተጨማሪም ለአምልኮ የምንመጣና ከመድረኩ የሚፈስልንን የምንቀበል ምእመናንም ቤታችንን ማስተካከል ይጠበቅብናል። አገልጋዮች ከመድረክ የሚለጡት አገልግሎት ውጤታማ የሚሆነው የምእመናን ልባዊ ተሳትፎ ሲጨመርበት መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ሁላችንም ግቢታችን ጌታን ያለማቋረጥ ካልፈለግነው የሕብረት ጊዜ ትግል ይበዛበታል። አንዳንዶቻችን በቤታችን የምንኖረው ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ኑሮ ከመድረኩ በሚፈበሰው አገልግሎት ላይ የራሱ ተጽእኖ እንደሚኖረው መዘንጋት የለበትም። ስለሆነም እኛም በአግባብና በሥርዐት እንኑር። ያለ ሥርዐት መሄዳችን አይበጅምና እንመለስ። እንዲሁም ለእርማት የተዘረዘሩ ሥርዐት ጎደል ድርጊቶችን ታግላችሁ እንብቡዋቸው

የቀረቡት ማሳሳቢያዎች ከንቱ ወቀሳ ወይስ ጉድፋችንን እንለተን እንድንዋብ የተዘጋጀ መስታወት? የሚለውን ጥያቄ እናንተም ጠይቃችሁ የበኩላችሁን መልስ ለመስጠት ሙከራ አድርጉ። በማስከተልም ከእኔ ጋር መድረክቻችን እንደ በመጽሐፍ ቅዱስ ሲታዩ እንዴት ናቸው? በማለት ጠይቁ። ለራሳችሁ መልስ ስጡ። እኔ ለዚህ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ እዚሁ

ይገኛል። ለእኔ መጸሐፍ ቅዱስንና እነርሱን ሳስተያይ ታየኝ የምለው፡ በሚከተሉት ጥቂት ገጾች አቀርባለሁኝ። የእናንተ አይታና የእኔ ከተራራቀ ባልሁት ሁሉ ካልተለማማችሁ በመግቢያው በስጠኋችሁ አድራሻ እንገናኝ። በምን መልኩ ያልኩት ሁሉ ፍጹም ነው አልልም። ግና መድረኮችን ሳያቸው መታረም እንዳለባቸው ይታየኛል። እንደኔ የበኩሉችሁን ለማዋጣት ተዘጋጁ። የሚያዋጣን በቃሉ መሠረት የሚከናወን እደራረግ ነውና (ቆላ 3:16)።

1.1 በቅዱስ ቃሉ የተፈጠረ ሕብረተሰብ

በሁለቱም የቅዱሳት መጻሕፍት ኪዳናት የእግዚአብሔር ሕዝብ የተገኘው ከቃሉ በኋላ ነው። በአዲስ ኪዳንም ይኸው እውነታ በተግባር ይታያል። ስለሆነም የቤተ ክርስቲያን ዓላማና መጽሐፍ ቅዱስ ለንል ልናተኩር የምንፈልገው የክርበቶስ ሞትና ትንሳኤ ተሰብኮ እውን የሆነችውንና ጌታ በቃሉ አማካኝነት ዘወትር የሚያንጻትንና የሚያድሳትን አካሉን የሚመለከተውን እውነታ ማለታችን ነው። በሕያውና ሠራተኛ ቃሉ የተፈጠረችው ቤተ ክርስቲያን ከቃሉ አዋጅ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አላት። በቃሉ ወደ ሕያውነት የመጣችው ቤተ ክርስቲያን በሕያውነት እንድትቀጥል እግዚአብሔር ቃሉን በመጠቀም ያጸዳታል[1] ይቀድሳታል እንዲሁም ያድሳታል። (አፌ 5:26-33)

ቤተ ክርስቲያን በቃሉ ያለ ማቋረጥ መደገፍ አለባት የሚለው መረዳት በሁሉም ክርስቲያኖች ዘንድ አይገኝም። አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ቤተ ክርስቲያን የቃሉ ደራሲ ናት ብለው ስለሚያምኑና ስለሚያስተምሩ ቤተ ክርስቲያን በቃሉ ላይ ሥልጣን እንዳላትና አድራጊ ፈጣሪ እንደሆነች እድርገው ያቀርባሉ። እርግጥ ነው፣ በሁሉቱም ኪዳኖች መጽሐፉ የተጻፈው በቀጥታ ለሚያምነው ህብረተሰብ ነው ። ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያን በቃሉ ተፈጠረች እንጂ ቃሉን አልፈጠረችውም።

[1] Hailu Cherenet Hiyaw Kibibil Addis Ababa: Commercial Printing Press, 2003.

ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን በሕያውነት የምትኖር እንዲሁም ተልእኮዋ የሚያቋርጥ ኃይል ያለው እንዲሆን ለቃሉ ተገቢውን ትኩረት መስጠት እንዳለባት መገንዘብ ያስፈልጋታል። ምክንያቱም ቃሉን ቸል ስትል ወደ ድንቁርና እና ወደ ሞት ታዘግማለችና ነው። ቃሉን እንደሚገባ በምታውጅ ቤተ ክርስቲያን ባለ ራእዮች በመላት ይታያሉ።[2] አባሎቿም በጎ ተጽእኖን የሚፈጥሩ የአዲሱ ህብረተሰብ አባላት ሆነው ስሚኖሩበት ማኅበረሰብ ጨውና ብርሃን በመሆን ያገለግላሉ። የእምላክ ፍቅር ለሰዎች በተግባር ይታያል። ስዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥተው እውነተኛውን አረፍት ይለማመዳሉ። ምክንያቱም እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል የሚፈስሰውን የፍቅር ÷ የመታዘዝና የመከባበር ግንኙነት በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው በተግባር ለማሳየት በክርስቶስ ፍቅር የተሳሰሩ የአማኞች ስብስብ ናትና።

ቤተ ክርስቲያን አንድትመሠረት በቀደምትነት የተሳኩት የእምነት አባቶች አጥቢያዊ ማንነትን እንድትላበስ የአካባቢውን መጠሪያ ለቤተ ክርስቲያን በመስጠት ተጠቀሙ። የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን (የሐዋ 8:1) ÷የእስያ ቤተ ክርስቲያን (የሐዋ 16:5) ÷ የሮም ቤተ ክርስቲያን (ሮሜ 16:5) ወዘተ.. ማለትን መረጡ። የቤተክርስቲያን ሕልውና እንዲቀጥል መንፈሳዊ ትምህርትን ቀዳሚ ሥራቸው አደረጉ።

- ከተረት የጸዳ ኑሮ (1ኛ ጢሞ 1:3-5)
- እግዚአብሔርን መምሰል (1ኛጢሞ 4:6)
- እውነተኛ መንፈላዊ ርምጃ (1ኛ ጢሞ 6:17)

ወደ ሕብረቱ የሚቀላቀሉትም ቃሉን ማዕከል ያደረገ ሕይወት እንዲመሩ ትኩረት ይደረግ ነበር። ስለሆነም ቤተክርስቲያን የጸጥታ ሥፍራ፥ የስላም መቅደስ፥ የጥርጣሬ መጥፊያ፥ የመጽናናት ሥፍራ፥ የተስፋ ማደያ፥ የጸሎት ሥፍራ እንዲሁም የማምለኪያ ቦታ ሆኗ እንድትቀጥል የምትኖረው ቃሉን ለማወጅና እንደ ቃሉ የሆነ ሕይወት በተግባር እንዲታይ መሆኑን መገንዘብ

[2] Ibid

ያሻታል። መድረኮቿ ይህንን እውነታ በጉልህ ማስተጋባት ይኖርባቸዋል። ዋና ዓላማዋም ቃሉን በማወጅ የአምላክ መንግስት እንዲሰፋ ክብሩ እንዲስራፋ ማድረግ ነውና።

የውይይት ጥያቄዎች

1. በእናንተ አይታ ቤተ ክርስቲያንን ያስገኘው ቃሉ ነው ወይስ ቃሉን ያስገኘች ቤተክርስቲያን ናት?
2. ቤተ ክርስቲያን በሕያውነት እንድትቀጥል ቃሉን ማወጅ ይኖርባታል ስንል ምን ማለታችን ነው?

1.2 ክርስቶስ የምስባኩ ማዕከል (ቆላ 3:16-17)

ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ከእርሱ ትምህርትና የመሥዋዕትነት ሥራ የተነሳ የተሳሰሩ እማኞች የእርሱን ፈለግ ተከትለው እርሱን በሕይወታቸው በመግለጥ ሌሎችን ወደዚህ ሕብረት ስመጥራት እንዲችሉ ነው። ቤተ ክርስቲያንም በመድረኳ ይህ ተቀዳሚ ዓላማ የሚተገበርበት ማንኛውም ነገር እንዲከናወን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይኖርባታል። በመድረኩ ላይ የሚከናወነውን ማንኛውንም እንቅስቃሴ የሚገዛው ይህ አውራ ሃሳብ ሲሆን ይገባል። በመከከላችን እሱ ከፍ ያለ እንደሆነ እርሱ ሁሉን ወደ እርሱ የሚስበበትበት ልዩ ሁኔታ ይፈጠራል። ክፉ ከሆነው ከዚህ ዓለም ያዳነንን÷ መልካሙን ሥራ እኛን ሆኖ ያከናወነልንን ጌታ በጉባኤያችን ለማምለክ ወይም ለማወደስ እያንዳንዱ ድርጊት ከዚህ አውራ ዓላማ ዙሪያ መቃኘት አለበት።

መጽሐፍ ቅዱስ «የጌታ መንፈስ ባለበት በዚያ አርነት አለ» (2ኛ ቆሮ 3:17) ይላል። በቤተ ክርስቲያን ምስባክ ላይ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው የሚስተናገዱ÷ የትልቁ ዓለማ ክፍሎች የሆኑ ፕሮግራሞች በሙሉ ÷ ፍስታቸውን ጠብቀው እንድን እውነት ለመግለጽ በአንድ ድምጽ ማስተጋባት አለባቸው። ያም ድምጽ «ኢየሱስ ክርስቶስ ከፍ ከፍ ሊል ይገባዋል» የሚል መሆን አለበት። ቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነላትን ጌታ ሕይወት በልዩ ልዩ የአካል ክፍሎቿ እንቅስቃሴ በተግባርና በተጨባጭ ልታሳይ ይገባልና።

ከርስቶስን ከመድረኮቿ ከፍ አድርጋ ማሳየት የተሳናት የእርሱን ቃል ለማስተጋባት አቅም ያነሳት ቤተ ክርስቲያን የእርሱ አካል ናት ለማለት ያስቸግራል። ከአድር ከዕቁብና ከሙያ ማኅበር መድረኮች የተለየ መድረክ ቤተ ክርስቲያን አሳት ብለው አገልጋዮቿም ሊናገሩ ሲያጎሉ የሚፈልጉት ክርስቶስ የአንቅስቃሴው ቁንጮ እንዲሁም የድርጊቶች ሁሉ አውራ መሆኑን ከመድረኮቿ በማስተጋባታቸው ነው። ከላይ በጠቀስናቸው ትስስሮች መያያዝ አለ። ከአድር ÷ ከዕቁብና ከሙያ ማኅበር ጋር ባለው መያያዝ ገዝፎ የሚታየው ጥቅምና መደጋገፍ ሊሆን ÷ ልዩነቱ የቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ የሚታየው መያያዝ የሕይወት ለሕይወት የሆነ ግንኙነት የቀደመበት መተሳሳር ከሁሉ በፊት ቅድሚያ የተሰጠው መሆኑ ነው።

ክርስቶስ መልኩን እንዲያንጸባርቁለት ዛሬ በዚህች ዓለም የተወው ከእርሱ የተነሳ የተሳሳሩትን አማኞች ነው። አነርሱም መድረካቸውን ሰሌላ ነገር አሳልፈው ከሰጡበት በቤቱ መብቱን የተቀማ ሐዘንተኛ ይሆናል። እርሱ እንዳያዝን ቤተ ክርስቲያን እርሱን ማዕከል ያደረገ የአገልግሎት አንቅስቃሴ ሊኖራት ይገባል። እርግጥ ነው አማኞች በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ጌታ የሚያንጸባርቅ አካሔድ በተግባር ማሳየት ይጠበቅባቸዋል። ይሁን አንጂ በጸሎት ቤት እሱን አነሰማለን ብለው ተሰብሰበው ትኩረትን ከእርሱ ወደ ልዩ ልዩ ነገሮች የሚወስድ ሁኔታ ሊፈጠር ጌታ ደስ አይለኝም። ስለሆነም ለመጸበይ አንደበታቸውን የሚከፍቱ መሪዎች ÷ በዜማ መልእክት ለማቅረብ የታደሙ ዘማሪያን ÷ የዕለቱን መልእክት ለማቅረብ የተሰናዱ ሰባኪያን እንዲሁም ታዳሚዎች የጌታ ስመ እንዲቀደስ÷ ክብሩ እንዲወደስ በየፊናቸው ተልእኮአቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል።

በአባላት የስብሰባ ጊዜ ሪፓርት ቀርቦ በጠንካራና ደካማ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አካሔድ መነጋገር ስህተትነት ባይኖረውም በመደበኛ የአምልኮ ጊዜ ላይ ግን የቤተ ክርስቲያን መድረኮች ለክስና ለአሉባልታ የተከፈተ በር ሊኖራቸው አይገባም። በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያን መድረኮች እሮሮና አምባጓሮ ለማስተናገድ የተመቻቹ መሆን የለባቸውም። እንዲሁም ከሁነኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ያፈነገጡ አስተሳሰቦችና አደራረጎችን ለመሸክም መፍቀድ የለባቸውም። መድረክ የአምላክ ÷ ቤተክርስቲያንም ይሁን የአምላክ

ንብረት በአደራ ልታስዳድር የተሾመች ወኪል መሆኗ ለአፍታም እንኳን መዘንጋት የለበትም። መድረክ በእንዲህ ዓይነት ቅዱስ ፍርሃት በክብር ሊያዝ ይገባዋል። ይህንን ስንል ለመድረኩ ያለን የተጋነነ አክብሮት የአምላክን ቦታ እንዳይወስድ መጠንቀቅ አለብን። በብሉይ ኪዳን ዘመን ንጉሥ ሰሎሞን ሕዝቡ አምላኩን የሚፈልግበት ሥፍራ ለማዘጋጅት በአባቱ በዳዊት በእግዚአብሔርም ተመረጠ። የተሰጠውን አደራ በመፈጸም ግንባታውን ካጠናቀቀ በኋላ እምላክን ወደዚህ ማደሪያ እንደዲመለከት በብዙ ፍርሃት ተማጠነ። እግዚአብሔርም በተለየ መንገድ መጥቶ ለዚህ ልመና አሺታውን በገሃድ አሳየ (1ኛ ነገ 8፡11)።

ሕዝቡም እግዚአብሔር በሚታወቃቸው መንገድ በመካከላቸው ስለተገኘ ሐሤት አደረጉ (1ኛነገ 8፡67)። ይሁን እንጂ አምላካቸውን ትተው ቦታውን ማምለክ ሊጀምሩ ከብሬ ይኖርበታል÷ ለዘለቄታውም በዚያ አሆንበታለሁ ያለውን ቤት ተወው። ሕያዉን ጌታ ትተው በድኑን ሕንጻ የሙጥኝ ሊሉ÷ የአምላክን ያህል ክብርም ሊሰጡት ጌታ ተቆጣ። አላፊ ከሆነው ነገር የተሰራውን መቅደስ ብቻ በማክበር የዘላለሙን ጌታ ገሸሽ አደረጉት። በዚህ ጊዜ ነገር መስመሩን ሲለቅ የቃል ኪዳኑ ሕዝብ ጠላቶችም መጥተው እንዲያፈርሱት ፈቀደላቸው። ክሚታይው ወደ ማይታየው÷ ክእሁኑ ይልቅ ዘለቄታውን እንዲያዩ ፈልጎአልና። እኛም ዛሬ አምላካችን በድርጊቶቻችን ቢገለጥ እሱን ትተን ድርጊቶችን ክእርሱ በላቀ ሁኔታ ክፍ ክፍ ብናደርግ ክፍተኛውን ስህተት እንፈጽማለን። ሳምራውያን ገሪዛን በሚባል ተራራ እግዚአብሔር በተለየ መንገድ ተገልጦ ያክናወነውን ታሪክ ያስታውሳሉ። ይህንንም ለልጆቻቸውና ለልጅ ልጆቻቸው አስተላልፈዋል። ይሁን እንጂ ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ በተራራው ላይ ለየት ባለ መንገድ የተገለጠውን የለማይ አምላክ ትተው ተራራውን የሙጥኝ አሉት።

እኛም ዛሬ አንድ መዝሙር ስንዘምር በተለየ መንገድ ብንባረክ ነገ ተመልሰን ያቺኑ መዝሙር የሙጥኝ ማለት ይቃጣናል። የባረከን መዝሙሩን ተጠቅሞ እኛን የነካን አምላካችን እንጂ መዝሙሩ በውስጡ የተለየ ነገር ስላላው አይደለም። ምስባኩን ልንጠነቀቅለት ይገባል ስንልም እናምልከው ማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል። ይሁን እንጂ እንደ ተራ ሥፍራ ልናየው ደግሞ አይገባንም። መድረክ የተከበረ የአምላክ መገለጫ ሥፍራ ነውና።

ደጋግመን ያነሳነው የለንበት አገልግሎት የሚከናወንበትን የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መድረክ ቢሆንም ሕዝቡ በሚሰበሰብበት መንፈሳዊ አገልግሎት በሚከናወንበት ሥፍራ ሁሉ ይህ ግንዛቤ ሊርቀን እይገባም። እያሌ ሕዝብ ለሚከማችበት÷ ሁላችን ተገናኝተን መንፈሳዊ ማዕድን ለምንካፈልበት ሥፍራ ውጫዊ ውበትና ጌጥም ሊገደን እንደሚገባ ሳናሳስብ እናልፍም። ይህንን ሃሳባችንን ወደፊት እናየዋለን። በተረፈ ግን ምስባኩ ለቆመለት ዓላማ ከምንም ይልቅ ቅድሚያን መስጠት ይኖርበታል እንላለን። የምስባኩን ተቀዳሚ ዓላማ በተመለከተ ተገቢ ግንዛቤ እንዲኖረን የሚከተለውን ሃሳብ እንመለከታለን።

የውይይት ጥያቄዎች

1. ዛሬ በቤተ ክርስቲያን መድረኮች የላቀን ሥፍራ ተሰጥቶት የምናየው ምንድነው?
2. ቤተ ክርስቲያን በመድረኳቿ የእዋጆቿ መካከለኛ ያደረገችው ምንድነው?
3. የቤተ ክርስቲያን መድረኮች እንደ ቃሉ ናቸው? ካልሆኑስ ለምን? እንዲሆኑስ ምን እናድርግ?

1.3 የምስባኩ ተቀዳሚ ዓላማ

ቀደም ብለን እንዳስገነዘብነው የሕብረት እምልኮ አውራ ዓላማ ለእምላክ ልባዊ ስግደት ማቅረብና በፊቱ ሁለንተናችንን መስጠት ነው። ቤተ ክርስቲያን ከምትኖርለት ቀዳሚው ጌታን ማምለክና ማወደስ ነው። ይህንን ያስቀደመች ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳንን መተናነጽ እንዲሁም መልእክቷን ለዓለም ማድረስ ቸል አትልም። ምስባኩም እነዚህ የቤተክርስቲያን ቋሚ ዓላማዎች ለማለካት ዓይነተኛ ሚና አለው። የምስባኩ ተቀዳሚ ዓላማ ሕዝቡን ለማነጽ ከእግዚአብሔር በልዩ ልዩ መንገድ የሚመጣውን መልእክት በየወረፋቸው የተሰለፉ አገልጋዮች ለሕዝቡ እንዲያቀርቡ ምቹ ሁኔታን መፍጠር ነው። ይሁን እንጂ ምስባኩ የአንድ አቅጣጫ መንገድ ነው ብሎ ማሰብ ልክ አይሆንም። ስለሆነም ከሕዝቡ ለእምላክ የሚቀርበውን ስግደት ለማቅረብ ምቹ ሁኔታንም ያካትታል። ከሕዝቡ ወደ ፈጣሪ የሚሔደው ልባዊ

ስጦታ እምልኮ ሲሆን ከእምላክ ወደ ህዝቡ የሚፈሰሰው ደግሞ አምላክ ሕዝቡን ለመገንባት(ለማነጽ) የሚልከው ረድኤት ነው።

በዚህ ጊዜ በዕለቱ እንግዳ ሆነው የተጋበዙ ሰዎች የምሥራቹን ቃል በመዝሙር፤ በስብከት እንዲሁም አማኞች ተሰብሰበው በሚያስተላልፉት ተግባራዊ መልእክት ለአእርሱ የሚሆነውን ለመውሰድ ዕድል ያገኛሉ። አማኞች ደግሞ መንፈሳዊ ረሃባቸውን የሚያስታግስ ምግብ ፤ ለመንፈሳዊ ጉዞአቸው የሚበጅ ምሪት ፤ ለትክክለኛ ውሳኔ የሚያበቃቸው ብርሃን ወዘተ.. የሚቀበሉበትን ዕድል በመፍጠር እምላክ እንዲከበር ማድረግ በምስባኩ በኩል የሚጠበቅ ጉዳይ ነው። በምስባኩ የሚቆሙ አገልጋዮች በተቀደሰ ሕይወታቸው ለእርሱ መገዛታቸውን ይገልጣሉ። በመልእክተኛነታቸው ደግሞ ፈቃዱን ለመፈጸም የቆሙ ባሪያዎቹ መሆናቸውን ያስረግጣሉ። ይህንን ተቀዳሚ ዓላማ የረሳ ማንኛውም የመድረክ አገልጋይ ክትክክለኛው መስመር ወጥቷል ማለት ይቻላል።

በምስባኩ ላይ በልዩ ልዩ አጀንዳ መቆም የሚሹ ቢኖሩም ተቀዳሚ ዓላማው ግን ለአገልጋዩ ታዛዥነቱን የሚያረጋግጥበት ለተቀባዩ ደግሞ የአምላክ ድምጽ የሚመጣበት መንገድ መሆኑን መረዳት ከምንም በላይ መቅደም ያለበት እውነታ ነው። የሕክምና ሳይንስ ጠቢብት በሆስፒታል ውስጥ ዋናው በሽተኛው ነው ይላሉ። ሁላችን እንደምናውቀው በብዙዎች ልፋት የተገነባው የሆስፒታል ህንጻ በውስጡ የታጠቃቸው ልዩ ልዩ መሳሪያዎች አሉት። ያ ብቻ አይደለም በልዩ ልዩ መያ የተካኑ ሐኪሞች ቢሮዎችን ሞልተው ይጠባበቃሉ። ይሁን እንጂ እንዲህ ሁሉ ሆኖ በሽተኛው ከሌለ እነዚህ በሙሉ ምንም ናቸው። ስለሆነም ሁሉንም እንዲኖሩ ያደረጋቸው ለበሽተኛው ትኩረት መስጠታቸው ነው። የምስባኩን ተቀዳሚ ጉዳይም ስናነሳ አምላክ በቤቱ የሚመጡትን እንግዶችን ለማስተናገድ ይፋዊ ግብዣ የሚያደርግበት ቦታ (የተከፈተው መንገድ) ምስባኩ መሆኑን እንገነዘባለን።

በዚህ አጋጣሚ ምስባኩን በተመለከተ ግልጽ እንዲሆንልን የሚያስፈልገው ዋና ነገር ምስባኩ ያሰው ምዕመናን ስላሉ መሆኑን ነው። ይህ ምስባክ ግን በጂአግራፊ ተጽእኖ ውስጥ የወደቀ ሃውልት ነው ብሎ ማሰብ ልክ አይሆንም። ይህ ስንል ጌታ ስማምሰክ በተሰበሰብንበት ሁሉ መሐል ቆሞ

የሚያስተባብረን ሰው ባላበት ቦታ ሁሉ አለ። መገኘቱ ጸሎት ቤት ብቻ አይደለም ማለታችን ነው። ለለሆነም የአግዚአብሔርን ህዝብ ልናገለግል በቆምንበት ሥፍራ ሁሉ ይህንን ግንዛቤ መጣል የለብንም። ምክንያቱም በሥፍራና በቦታ የማይወሰነው አምላክ ልጆቹ ባሉበት ሥፍራ ሁሉ አባታዊ ድምጹን ለማሰማትና የልጆቹንም ድምጽ ለመስማት በጎ ፈቃዱ ነውና።

ስለሆነም የአርሱ መገኘት ከሥፍራ ወይም ከሰንበት ጋር ታስሮአል የሚለው አመለካከት አግባብ አይሆንም። ይሁን እንጂ በዚህ ሥፍራ ዛሬ በሰፋት የምንነጋበርበት ሃሳብ ይፋዊ ህንጻ ይዘን በሚመሰለንና በታየን መንገድ ማምለክ ከጀመርንበት ጊዜ አንስቶ የምናያቸውን ሁኔታዎች ይሆናል። ለማምለክ ነጻነት ማግኘታችን ካምላክ የታደልነው በረከት ነው። ይህንን ነጻነታችንን ለሁላችን አንደሚያንጽ አድርጎ መጠቀም ብልህነት ነው። ይሁን እንጂ አልፎ አልፎም ቢሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊው አመላካከት የማይገዛቸው አስታዊ አዝማሚያዎች በምስባክቻችን ላይ አየታዩ መጥተዋል። እነዚህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሚዛን የጎደላቸውን አደራረጎች ለማስወገድ ስንለበለብ ተቀዳሚ ዓላማችን ምን አንደሆነ በውል መለየት አለብን። የሚገነባውን አየገነባን መፍረስ ያለበትን አንድናፈርስ ዓላማችን ለሁላችንም ጉልህ መሆን አለበት። የመለብስባችን ቀዳሚ ዓላማ አግዚአብሔር አምላክችንን በቻልነውና በሚገባን መንገድ ማክበርና ከፍ ከፍ ማድረግ ነው።

ምስባኩ ላይ ኃላፊነት ወስደው የሚቆሙ አገልጋዮች ይህንን ስማረጋገጥ ቀዳሚ ናቸው። የሁላችንም ዋና ትኩረት የሁላችን ገዥና ጌታ አግዚአብሔር ላይ ሊሆን ይገባል። አግዚአብሔርን የማያመልኩ ሰዎች ትኩረታቸው ከአግዚአብሔር ይልቅ በልዩ ልዩ ነገሮች ላይ ነው። አንዳንዶቹ ልባቸውን የሚያደርጉት በተፈጠረው ነገር ላይ ነው (ሮሜ 1:25)። ሌሎቹም ልባቸው የሚንጠለጠለው ጣዖታት ላይ ነው (የሐዋ7፤39-43) አንዳንዶችም አጋንንትና ገንዘብን ያመልካሉ(ማቴ 6:4 ራአ 9:20)። ይሁን እንጂ ክርስቲያኖች የሚሰግዱሎትና ከፍ ከፍ የሚያደርጉት አንዱን አምላክ ብቻ ሊሆን ይገባል። የምስባኩ ቀዳሚ ዓላማ አምላካችንን ከፍ ከፍ ማድረግ ብቻ እንዲሆን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ነው። በተሰጣቸው ጊዜ በሕዝቡና በአምላክ መካከል መካከለኛ የሆኑ አልጋዮች በሙሉ በከፍተኛ ድምጽ የሚያስተላልፉት

ጥሪ የተሰበሰቡ ለምች በሙሉ በልባቸው ወደ ሰማይ ግስጋሴ እንዲያደርጉ ማነሳሳት ነው።

አነርሱ ይህ ግንኙነት የሚጎለብትበትን መንገድ ያብጁ እንጂ ምዕመኑ የአነርሱን አደራረግ አያየ ገለልተኛ ተመልካች እንዲሆን መግፋት የለባቸውም። ምክንያቱም በምንሰበሰብበት ጊዜ አብረን በመያያዝና በመተናነጽ እንድንቆይ የሚያግዙን ልዩ መንፈሳዊ ስጦታዎች ይፈሳሉ (1ቆሮ 14:26)። ያኔም ከምስባኩ ብቻ ሳይሆን አርስበርስ (ኤፌ 5:19) በመሆን የሚመጣውን የጌታ በረከት ለማበተናንድ የምስባኩ ድርሻ ቀላል አይሆንም። ካህኑ መስዋዕትን ለአምላክ ሊያቀርብ አያንዳንዱ አምላኪ በመሠዊያው ላይ የሚቀርበውን ይዞ እንደሚመጣ ሁሉ ልክ እንዲሁ አማኞች በተሰበሰቡበት ስታ ለዚህ ማኅበራዊ ተሳትፎ የሚመች መንገድ መመቻቸቱን ማረጋገጥ ከምስባኩ አውራ ዓላማ ጋር ይደመራል።

የውይይት ጥያቄዎች

1. በአናንተ አይታ የምስባኩ አውራ ዓላማ ምንድነው ትላላችሁ?
2. ዛሬ በቤተክርስቲያን የምናያቸው እንቅስቃሴዎችን ይህ አውራ ዓላማ ይገዛቸዋል ትላላችሁ?
3. መጽሐፍ ቅዱሳዊው አውራ ዓላማ ጎልቶ እንዲታይ ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?

1.4 ምስባኩ ለቃሉ ተገዥ

በምስባኩ የሚከናወን ማንኛውም ድርጊት ስቃሉ የተገዛ መሆን ይኖርበታል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስቃሉ ሥልጣን ሥር ያልዋለ እንቅስቃሴ ሁሉ ከንቱ ድካም ነው። አግዚአብሔርን ያስተዋወቀን ቃሉ ቸል በተባለበት ሁኔታ እውነተኛ አምልኮ አንዴት ሊኖር ይችላል? የሚያንጽና ስአምላክ ክብርን የሚያመጣ አምልኮ አውን እንዲሆን አምልኮ ለቃሉ ተገዥ መሆኑን ማረጋገጥ አማራጭ የለውም። ምስባኩ ላይ በመቆም ይህንን ለማስፈጸም ኃላፊነት የሚወስዱ በሙሉ ይሄ ሊጠፋቸው አይገባም። ለማምለክ ስንሰበሰብ የምናደርገው ትልቁ ነገር አምላካችን ያደረገውን እውነት መተረክ ነው።

ይህንን በምንዘምረው መዝሙር ÷ በምንሰጠው ምስክርነት እንዲሁም በልዩ ልዩ ነገሮቻችን እንገልጣለን፡፡ ይህ አካሄዳችን ባሕላዊ ተጽእኖ ወድቆበት ከመስመር እንዳይወጣ መጽሐፍ ቅዱስ ቅርጽ ሊያበጅለት ይገባል፡፡ ይህ ሲባል ባሕላዊ ነጻነታችንን እናጣለን ማለት ግን አይደለም፡፡ ይልቁንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባሕልን እንላበሳለን ማለት ነው፡፡ ላለምላክ ክብርን የማያመጣው የባሕላችን ገጽታ በመጽሐፍ ቅዱሱ እውነት መቀየር ይኖርበታል፡፡

በየትኛውም ታዋቂ ጨዋታ ሕግ አለ፡፡ ሙዚቃን ለመጫወት የራሱ ህግ አለው፡፡ ልክ እንዲሁ በጸሎት ቤት የሚከናወኑ ድርጊቶችን ገዢያቸው በሁላችን ሊሰለጥን የሚገባው ቃሉ ነው፡፡ እያንዳንዱ አደራረጋችን በቃሉ መቃኘት አለበት፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ለምስባኩ እንቅስቃሴ ቅርጽን አንዲያበጅለት ምስባኩ ሙሉ ለሙሉ ለቃሉ ሥልጣን ያደረ መሆን አለበት፡፡ ስለሆነም በመድረኩ ላይ ቆመን የምንጸልይ ቢሆን÷ የምንዘምር እንዲሁም ቃሉን የምናውጅ የሁላችን አደራረጎች ለቃሉ ሥልጣን የጎላ እውቅናን መስጠት አለባቸው፡፡ አዲስ ኪዳን በተጻፈበት በግሪክኛ ቋንቋ ማወደስ ና ማክበር ብለን እኛ በቋንቋችን የምንጠራውን ሃሳብ ለመግለጽ የዋለው ቃል *<u>ሰይኔሶ (aineo)</u>* ነው፡፡ ትርጉሙም መናገር ወይም መተረክ የሚለውን ሃሳብ ይይዛል፡፡ ምስባኩ ለቃሉ ሙሉ ለሙሉ ተገዥ ሲሆን የጌታን ማዳንና ታላቅነቱን ይተርካል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌነትን ባበጀበት መበመር ተጉዘን ልባችንን ስናፈስ በምስባኩ የሚተገበረው የእኛ ስሜት የሚሰን ጉዳይ መሆኑ ቀርቶ ጌታ እንድናደርገው የፈለገው ነገር መተረክ ይሆናል፡፡ ስለዚህም እንደ እምነት አባቶቻችን «አፌን ምስጋና ምላ ሁልጊዜ ክብርህንና ግርማህን እዘምር ዘንድ፡፡-- አፌ ጽድቅህን ሁልጊዜም ማዳንህን ይናገራል (መዝ 71፡ 8 ና 15» እንላለን፡፡

በብሉይ ኪዳን ሰዎች እግዚአብሔርን ያመልኩ የነበረው የሠራውን ነገር እያበታወሰ ነው (1ኛዜና 16:7-36÷ ዳን3:28-29÷ ሉቃ 2:13-14 20÷ ሉቃ 18:43 ÷ ሉቃ 19:37 የሐዋ 3:8-9)፡፡ ልክ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነገረን (እንደ ቃሉ) ምስባኩ ላይ ቆመው ልባችንን ወደ አምላክ እንድናፈስ የሚጠይቁን በሙሉ ባምላክ ሥራ ላይ እንድናተኩር ሊረዱን ይገባል፡፡ ጳውሎስ ለኤፌሶን ስጻፈው መልእክት ወደ ትንተናው ከመግባቱ በፊት አምላክን ማደናነት ሲጅምር የባረከን ይባረክ ይላል፡፡ በደሙ የተደረገውን ቤዛነትም እያደናነቱ ይናገራል፡፡ ስለሆነም በምስባኩ ላይ ቆመው የሚያስተባብሩን መሪዎች ስለ ምህረቱ፡ ስለ ታዳጊነቱ ÷ ስለ መዋጀት ሥራው፡ ስለ አምላክነቱ እንዲሁም ስለ ፈዋሽነቱ አምላክን እንድናሞጋግስ የሚያደርገንን የአምልኮ ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርባቸዋል፡፡

ከቃሉ ያፈነገጠ አምልኮ ግላዊና አካላዊ እንቅስቃሴ ወደ መሆን ዝቅ ይላል፡፡ ቃሉን ማዕከል ያደረገ የምስባክ አገልግሎት የስምትን ልብ አምላክ ወደሚገኝበት ሁኔታ ውስጥ ይወስዳል፡፡ ምዕመናንም እንዲህ ዓይነቱ የአምልኮ አየር አካባቢውን ሲቆጣጠር በአምላካቸው ፊት ይቀልጣሉ፡፡ ማንም ምንም ይበል ቁምነገሬ ላይሉት ሁሰንተናቸውን ለእርሱ ያፈሰሳሉ፡፡ ለቃሉ ተገዥነት በጎላበት የምስባክ አገልግሎት ምዕመናን ለአምላክ መረታታቸውን በሚታይ መንገድ ይገልጣሉ፡፡ ቃሉ በነገስበት ቦታ ጨዋነት አለ፡፡ ያ ጨዋነት ለእእምሮ የሚመች ነገርን በቤተ ክርስቲያን መድረኮች በምእመናን ሕይወት እውን እንዲሆን ያደርጋል፡፡ እንዲህ እንዲሆን ቃሉ ምስባኮቻችንን እንዲቆጣጠር ይህም እውቀት በሁሉ ዘንድ እንዲነኝ ያለሰለሰ ጥረት መደረግ አለበት፡፡

የውይይት ጥያቄዎች

1. እምልኮዎቻችን በእርግጥ ቃሉን ማዕከል ያደረጉ፥ ናቸው? ካልሆኑስ ምን መደረግ አለበት?
2. ምስባኮቻችን ለቃሉ ተገዥ መሆናቸውን የምናረጋግጠው እንዴት ነው?

1.5 በምስባኩ ለመቆም የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ነገሮች

በምስባኩ ለመቆም ሁለት መሠረታዊ ነገሮች ይፈለጋሉ፡፡ የመጀመሪያው ውስጣዊ ንጽህና ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ውጫዊ ንጽህና ነው፡፡ በአገራችን ለውስጣዊ ንጽህና የምንጨነቀውን ያህል ለውጫዊ ንጽህና እምብዛም አይገደንም፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉም በእምልኮአችንና በሕብረት እደራረጎቻችን የሚያስከትሉት ተጽእኖ በቀላሉ የሚገመት አይሆንም፡፡ ስለሆነም ለሁለቱም የሚገባቸውን ትኩረት በመስጠት ሚዛናዊ መሆን

ለምሰባክ አገልግሎታችን ይበጃል። የሚቀድመውንም ለማስቀደም ተገቢውን ርምጃ መውሰድ መልካም ነው። የዚህ ዓለም ስዎች ቶሎ የሚማርካቸው ከውስው ይልቅ የውጭው ነገር ነው። ማራኪ ፈገግታ ፣ ትኩረትን የሚስብ አስባበስ፣ ሰዎችን እንደ ፍላጎታቸው ለመያዝ የሚደረግ ውጫዊ ነገርን ያሟሉ የመድረክ ስዎች በቀላሉ በብዙዎች ፊት ሞገስ ያገኛሉ። ይሁን እንጂ ሁነኛ መንፈሳዊ አገልግሎትን ከመድረክ ማግኘት የምንፈልግ ሁሉ ውጫዊው ነገር የቀደመበትን የመድረክ ሁኔታ በጥንቃቄ ልናየው ይገባናል።

ውጫዊው ነገር አያሰፈልግም ባይባልም ለውሳኔ ቀዳሚ ነው መባሉ ሊያሰደነግጠን ይገባል። ውስጣዊ ንጽሕና ለአገልጋዩና ለጌታ የሚታይ የውስጥ ውበት ነው። ከፈጣሪ ጋር ግርዶሽ የሌለበት ሕብረት መፍጠር ለስሚችልና በውስጡ ጽዱ ለሆነ ስው መጽሐፍ ቅዱስ ፣

«በቅንነት የሚሄድ፣ ጽድቅን የሚያደርግ፣

በልቡ እውነትን የሚናገር»

በአንደበቱ የማይሸነግል... » መዝ (15)፡3 በማለት ይናገራል። ይህንንም ሆነው ለመገኘት የተጠሙ አገልጋዮች እንዲህ ብለው ጸልይዋል።

አቤቱ ረድኤቴ መድኃኒቴም

የአፌ ቃልና የልቤ ሃሳብ

በፊትህ ያማረ ይሁን። መዝ (19)፡14 ይህ አባባል ውስጣዊ ንጽህናን ከልቡ በሚፈልግ አገልጋይ የተጸለየ ጸሎት እውን ያደርግልናል።

ስለሆነም በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ኑሮአችንን እንመራለን ለምንል የመድረክ አገልጋዮች መቅደም ያለበት ውስጣዊው ንጽህና እንደሆነ ግልጽ ሊሆንልን ይገባል። በ1ኛ ጢሞ 3፡1- ለሽምግልና አገልግሎት ከተጠቀሱት መመዘኛዎች መካከል የሚበዙቱ ከውስጣዊ ማንነት ጋር የተያያዙ ናቸው። እነዚህ መመዘኛዎች ከችሎታ ይልቅ ተቀባይነት ያለው መልካም አመል ላይ ያተኩራሉ። ስለሆነም ምስባኩ ላይ ለመቆም የሚፈልግ ማንም በግል ሕይወቱ ፣ በቤተሰባዊ ሕይወቱ፣ በማኅበረሰባዊ ሕይወቱ፣ በቤተክርስቲያናዊ ሕይወቱ ተቀባይነት ሊኖረው የሚገባ መሆኑን ከፍሉ ያስረግጣል። በምስባኩ ላይ የሚቆመው ለው በከፍሉ ከተዘረዘሩት የመንፈሳዊነት መለኪያዎች በአያሌው

ያጓደለ አካሄድ እንዲኖረው አይጠበቅም። ስለሆነም በምስባኩ የሚቆሙ አገልጋዮች ለውስጣዊ ንጽሕና ማረጋገጫ የሚሆኑ ምልክቶች እንደ ትህትና፣ ታማኝነት ፣ ታዛዥነት ቅድስና ወዘተ.. በሕይወታቸው በሚታይ መልኩ ሊኖራቸው ይገባል።

እነዚህን ነገሮች አጓድለው አገልጋዮች መድረክ ላይ ለመውጣት ሲደፍሩ ሕዝቡ በእነርሱ ፋንታ ይሸማቀቃል። ገና መድረክ ላይም ሲቆሙ የማንነታቸው መጥቶ እየጮኸበት የሚመሩት ሕዝብ የሚሉትን ሊያዳምጣቸው የይችገራል። የረከሰ ሕይወት እየኖሩ ቅዱስ መሆናቸውን ማስየት ቢፈልጉ ፣ እንቆጣ መሆናቸው እየታወቀ ሰስ ልግስና ቢሰፍፉ ፣ የሰየላቸው ውሸታሞች ሆነው ስለ ሃቅ ቢናገሩ፣ በብዙ መልኩ ወላዋይ መሆናቸው እየታወቀ ስለጽናት ቢሰብኩ፣ ምእመኑ ስለተዥጎረጎረው ሕይወታቸው ያዝንላቸዋል እንደሸነገሉትም ተገንዝቦ ያዝንባቸዋል። ይህ እንዳይሆን የሚነቀፍ ሕይወት ያላቸውን አገልጋዮች ወደ አደባባይ አገልግሎት ወጥተው ሕዝቡን እንዲያሰናክሉት መፈቀድ የለበትም። ጉድለታቸው እየታወቀ በምስባኩ አገልግሎት ወሳኝ ቦታ እንዲይዙ መፍቀድ በሕዝቡ ስሜት ማሾፍና ባለአደራ አድርጎ የሾመን አምላክ መናቅ እንደሆነ ሊስተዋል ይገባል ። ስለሆነም በሞራላዊ አቋማቸው ጥያቄ ውስጥ ያሉ አማኞች የቱንም ያህል መድረኩ ላይ ቆሞ መተወኑ ይሳካላቸው አምልኮ በሚከናወንበት ሕዝቡ አምላክን በጉጉት በሚጠባበቅበት መድረክ ላይ እንዲቆሙ መፈቀድ የለበትም። መድረኩ ላይ ለመቆም የሚያስፈልገው ሁለተኛው ነገር ውጫዊ ሁኔታን የሚመለከተው ጉዳይ ነው። ውጫዊ ሁኔታ ከግል ንጽሕና ጀምሮ ወቅቱን የሚመጥን አለባበስን እንዲሁም ተገቢውን ቃል በማውጣት ምእመኑን በጊዜው ቃል ለመደገፍ የሚደረግ ጥረትን ይጨምራል። ብዙ ሰዉ በሚያያቸው መድረክ ላይ የሚቆሙ አገልጋዮች የብዙዎችን ትኩረት እንደሚስቡ ሊያጡት አይገባም። በዚህ ወሳኝ ወቅት ከመድረክ ላይ የሚቆሙትን አገልጋዮች ወንዱ፣ ሴቱ ፣ ትንሹ ፣ትልቁ በደንብ ይመለከታቸዋል።

በነጭ ልብስ ላይ ያለች ጥቁር ቁሻሻ ትንሽም ብትሆን ከሩቅ እንደምትታይ ፣ ጉድለታቸው ከቆመበት ሥፍራ የተነሳ ጎልቶ ይታያል። በተለይ የማይገጣጠሙ ልብሶች ስብሰው መጥተው ከሆነ ብዙ አምላኪዎችን

በአደባባይ የሚቀበል የትኛውም አገልጋይ የውለጣዊ ሕይወቱ መገለጫዎች በጥብቅ መታየት አለባቸው። ስለዚህ ግላዊ ሕይወትን፥ ቤተሰባዊ ሕይወትን፥ ከሌሎች ጋር ያለ ግንኙነትን እንዲሁም ማኅበረሰባዊ ሕይወትን ጠጋ ብሎ በመመልከት የምሰባኩን አደራ መለጠት ለቤተ ክርስቲያን እንዲሁም ለሚያገለግሏትም ይበጃል ።

በእንዲህ ዓይነቱ ፈታኝ ጎዳና ተንዘው አደራን የሚቀበሉ አገልጋዮች የአገልግሎት ዘመን ይረዝማል። እነርሱም በብለለት በምሳሌነት ለማደግ ዕድል ያገኛሉ። በአሁን ጊዜ በብዙ ሥፍራ የሚታዩ አገልጋዮች ጠዋት ተሰቅሰ ማታ እንዳሚውርድ ለንደቅ ዓላማ ለጥቂት ጊዜ ታይተው ከመድረኮቻችን ወዲያውኑ ይጠፋሉ። ዛሬ ዛሬ ብልጭ ብለው ድርግም የሚሉ አገልጋዮች በዝተዋል። ለዚህ ደግሞ ዋነኛው ምክንያት ተገቢው ፍተሻ ሳይደረግ አደራ ይለጥና አውነተኛ ማንነታቸው ሲገለጥ «ቤተ ክርስቲያንንም ለማዳን ለአገልጋዩ ጥንቃቄ ለማድረግ በሚል ለበብ ገለል» ሊደረጉ ይስተዋላል። ሞራላዊ አቋማቸው የሚነቀፍ ሆኖ ይህንን ማድረጉ ምንም ለህተትነት የለውም። ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቱን ርምጃ በመደጋገም ግለሰቦችን ከመጉዳት በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ላይ ያልተፈለገ ችግርን ከመደንቀር ይፋዊ አድራን የሚቀበሉ አገልጋዮችን በብዙ ጥንቃቄ መመልመሉ ያዋጣል። ለለሆነም የአደባባይ አደራን ከመለጠት በፊት ቅደመ ፍተሻ ላይ ጠንቃቃ አሠራርን ማጎልበት ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለግለሰቦቹ የሚበጅ ነገርን እንዲለመድ ያደርጋል።

እንዲህ ዓይነቱ ጥንቃቄ ይፋዊ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን አገልጋዮች ሁሉ እይዘነጉትም። ስለሆነም በሚከተሉት ሁኔታዎች ምስባኩ ላይ መቆም ያላበቸውን ሰዎች መለየት አለባቸው። ምስባኩ ላይ የሚቆም ግለበብ በሞራላዊ አቋሙ መነቀፍ የለበትም። ለምሳሌ ምለባኩ ላይ የሚቆም ትዳር ያለው ከሆነ የተመለከረለት ያንድ ሚስት ባል መሆን ይኖርበታል። ላጤ ከሆነ ደግሞ አጠራጣሪ ጸታዊ ግንኙነት ያለው መሆን የለበትም። ብዙዎች ጣታቸውን የሚቀስሩበት የሚነቀፍ ሞራላዊ አቋም ያለውን ሰው ወደ እንደዚህ ዓይነቱ አካባቢ ማምጣት አርሉን ማሳጣት ቤተ ክርስቲያንንም ማለነቀፍ ይሆናልና መጠንቀቁ ይበጃል።

ለለሆነም እነዚህ ከዚህ በታች የተጠቀሱት ባህሪያት በምስባኩ ላይ የሚቆመውን አገልጋይ ለሞራላዊ ጥንካሬው በሚበጅው ባህሪ ተገንብቶ እንደሆነ አና እንዳልሆነ ለማየት ለሰሚያግዙት ራሱን ቢያይባቸው ይረዱታል። ለለሆነም አገልጋዮች <u>በመጀመሪያ እነርሱነታቸውን</u> በተመለከተ ራሳቸውን የሚገዙ ፥ እንደሚገባቸው የሚሠሩ ፥ የማይነቀፉ፥ ልከኞችና በቃልም ሆነ በኑሮ ሌሎቹን ለማስተማር የሚበቁ ቢሆኑ በሚቆሙበት መድረክ ሞገስ ያላቸው ይሆናሉ። መድረክ ላይ ስንቆም የምንታየው እኛ ብቻ እንደሆንን ካለብን እራሳችንን አናታልላለን። አኛና ከአኛ ኋላ ያሉት ቤተሰቦቻችንና ጓደኞቻችን ይታያሉ። እኛ ሁሉንም ለማየት የታደልነውን ያህል ሁሉም ፊታቸው የቆምነውን እኛን ብቻ ሳይሆን ከአኛ በለተኋላ ያለውን አበጥረው ያያሉ።

ለለሆነም የእኛን ብቻ ሳይሆን <u>በሁለተኛ ደረጃ</u> ደግሞ ቤተሰባዊ <u>ሕይወታችንን በተመለከተ</u> ማለተዋል የሞላበት አካሔድ ሊኖረን ይገባል። ወላጆች ከሆንን ልጆቻችን የአኛን አምነት የሚያከብሩ፥ ፈለጋችንን የሚከተሉ ሆነው መታየት አለባቸው። አሊያ ቤታችን ያልሠራውን መድኅኒት ለማዘዝ ምስባኩ ላይ ብንቆም ለሚፈርዱብን ለዎች ራሳችንን አሳልፈን አንሰጣለን። ቤተሰቦቻችን የኛን ሕይወት የሚቀበሉ የውጤታማ መንፈሳዊ አመራራችን የተግባር ማረጋገጫዎች ናቸው። ይህ ካልሆነልን በቤታችን አሸንፎ ያልወጣን አውነት በአደባባይ ለመናገር አቅም አናጣለን። በዚህ አቅጣጫ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ያየናቸው አያሌ ቅዱሳን ተፈትነዋል። ዛሬም ይህ ፈተና አውን ነው። ልጆቻችን የማሳመን ችሎታና በግድ የኛን ፈለግ እንዲከተሉ ማድረግ አንችልም። ይሁንና በቂ ትኩረት ለጥተን ጌታን ጌታቸው አድርገው እንዲኖሩ የበኩላችንን ማዋጣት አለብን። በተጨማሪም በአገልግሎታችን ላይ ጥቁር ጥላ እንዳይወድቅና አኛንም የማገልገል ነጻነት እንዳይነሳን የማያቋርጥ የምልጃ ጸሎት ያለፈልገናል።

ምዕመናንም የመድረክ አገልጋዮች ከጠላት ጋር በሚደረግ ፍልሚያ ግምባር ቀደም ግብ ግብ በመግጠም ላይ እንዳሉ ተገንዝበው ሊማልዱላቸው ይገባል። በመድረክ አገልጋዮች ገንቢ አስተዋጽኦ የታነጸን ሁላችን እነዚህ በመድረክ ላይ ግምባር ቀደም ሚና በመጫወት የሚጠቅሙን አገልጋዮች

ሞራላዊ ብቃት እንዲያገኙ እንዲሁም ከጥቃት እንዲድኑ የጸሎት ሽፋን ልንሰጣቸው ይገባል።

ምስባክ ላይ የሚቆም ማንም ቢሆን የሚታየው ግላዊና ቤተሰባዊ ሕይወቱ ብቻ ላይሆን በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ከሌሎች ጋር ያለው ግንኙነቱም በተመለከተ መታየት አለበት። በምስባክ ላይ ቆሞ እገልግሎትን መፈጸም እንዱ የግንኙነት ገጽታ በመሆኑ ግንኙነት ውጤታማ እንዲሆን ሁነኛ ዝግጅት አስፈላጊ ነው። ሞገድ በበዛበት ግንኙነት የሚታወቅ አገልጋይ ነቀፌታ ስለወደቀበት በድፍረት ቆሞ ለማገልገል አቅም አያገኝም። ስለሆነም ድፍረትን ከሚነጥቅ ነቀፌታ የወደቀበት ግንኙነት ለመጠበቅ የመድረክ አገልጋይ በዚህ መስመር ብስለት የተሞላበት ርምጃ መውሰድ ይኖርበታል። ሌሎቹም በተሳለ አንደበታቸው እርሱን ከመቆራረጣቸው በፊት ሰውጤታማ ግንኙነት የበኩላቸውን በማዋጣት ሊረዱት ይገባል። እርሱም ቢሆን ከሌሎች ጋር ባለው ግንኙነት የሚያሳጣውን ድካሙ እንዲቀነስ፥ ባህሪውም እንዲገራ ራሱን ማስናዳት አለበት። ስለሆነም በጎደለው ነገር ከሌሎች ጋር ግጭትን በመፍጠር የማይጨቃጨቅ መሆን አለበት። እንደውም ለሌሎች የሚገደው እንግዳ ተቀባይ መሆን ይኖርበታል።

በተጨማሪም ገር ሆኖ ሌሎችን በየዋህነት መሸከምን ለማጎልበት ጥረት ማድረግ አለበት። ወደ ንትርክ የሚመራ ክርክርን ሆን ብሎ መሸሸን ባህሉ ማድረግ ይገባዋል። እያንዳንዱን ግንኙነት «ምን ያስገኝልኛል?» ከማለት ይልቅ «ከኔ ምን ይጠበቃል? እኔስ ደግሞ ምን አስጣለሁ?» ብሎ መለናዳትን የየዕለት የጉዞው ፍልስፍና ማድረግን መማር አለበት። እንዲህ ሊሆን በነውረኛ ረብ የማይከሰስ ገንዘብን በመውደድ የማይኮነን እገልግሎትን እውን ያደርጋል። ያኔ ሌሎች እርሱን መጣልን እንጂ መጣብን አይሰትም። በምስባክ መገኘቱ ደስታቸው እንጂ ሐዘናቸው ወይም ፈተናቸው አይሆንም። ስለዚህ ግኑኙነት ከምስባክ ጋር ያለውን ትስስር አይተን በዚህም አቅጣጫ መድረክ ላይ እንዲቆም ስለምንፈቅድለት ሰው በጥልቀት ማሰብ አለብን።

ምስባክ ላይ የምናቆመው ሰው ሌላው እንድናይበት የሚያስፈልገው ነገር ከሃይማኖት ቤተሰቦች ውጭ ያሉ የጎበረቱበት ክፍሎች የሚሰጡትን ምስክርነት ነው። ስለዚህም ውጭ ባሉት ዘንድ ተቀባይነት አለው ወይ? የሚለውን ጥያቄ እምንታዊ በሆነ ገጽታው መመልከት ይጀምናል። ስለሆነም

ጥጋብከው የሚመጡ እንግዶቻችን የማይቀበሉት በብዙ መልኩ የሚኮንኑት ለው በምስባክቻችን ላይ እውራ የመድረክ አቀንቃኝ ሆኖ ሲያዩ እንዳይደናገጡ እይታችን ሰፋ ማለት አለበት። መድረኩ ላይ የሚቆመው ማን ነው ብለን ስንልም በጎበረሰቡ ዘንድ መልካም ምስክርነት ያለው መሆን እንዳለበት ልንገነዘብ አለብን።

፬። የመድረክ አገልጋይን እንቅስቃሴ ስንፈትሽ ግላዊውንና ቤተሰባዊውን ብቻ ሳይሆን በአራተኛ ደረጃ በማያምነው ጎብረሰብ ያለውን ውሎ የፈተሸ መሆን ይኖርበታል። ይህንን ማድረግ በብዙ መልኩ ያስችግራል። ምክንያቱም አገልጋዩን ከበስኋላው በሚያውቁትና አብረው በሚውሉ ሰዎች ማስጠናትን ይጠይቃልና። በተጨማሪም በምስባኩ ላይ ቆሞ እንዲያገለግል የሚፈልጉ ሁሉ በጥንቃቄ እንዲከታተሉት ማድረግንም ይጨምራልና። ይህን እንጂ ምክረን ሊያቅተን እንተወው እንጂ የመድረክ አገልጋይ ውጫዊ ግንኙነትን ሰንዳሰስ ወደ መድረኩ ማምጣት አይበጀንም። ምክንያቱም በክርስቶስ ቤተክርስቲያን ነቀፋን በመሠንዘር ቀን ከሌት የሚጥሩ ከሳሾች እድብተው የሚጠበቁት ሁኔታ እንዲህ ዓይነቱን ክፍተት ነው። የመድረክ አገልጋዩን ጥቂት ጉድለት በማጉላት ለማሳጣት የፈጠጠው ዓይን ጥብቅ ክትትል የሚያደርገው በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ጎድለው የተገኙ ሰዎችን ለማደን ነው። ስለዚህ የማያምኑ ሰዎች የመድረክ አገልጋዩን ነቀፌታ መነሻ በማድረግ ለመጥለፍ ያዘጋጁት ወጥመድ እንዲሰበር የመድረክ አገልጋይ መልካም ምስክርነቱን የጠበቀ ሊሆን ይገባዋል።

ለመሪነት ተስፋ የሚጣልበት ማንኛውም ግለሰብ በግላዊ የእድገት ጉዞው ነገሮችን አብላልቶ ከሕይወቱ ጋር ለማዋሐድ እንዲችል የግል የማደጊያ ጊዜ ልንሰጠው ይገባል። ፈተናችን ሃሳብን ማቀናጀትና በእደባባይ መቅረብ የማይፈራ ማንነት ያለውን ማንንም ቢሆን በቶሎ ያልጠበቀውን መድረክ ማስታቀፍ ነው። በእነጋገሩ እዋቂና ጥበበኛ የመሰለን ሰው በሕይወት ውጣ ውረድ ተፈትሾ ሳናይ ቶሎ ወደ እደባባይ ማውጣት ግለሰቡንም ቤተ ክርስቲያንንም አደጋ ውስጥ መጨመር ነው። ስለሆነም በእኛ መለኪያ በእጭር ጊዜ እደገ ብለን የምንለውን ለው ልንጠነቀቅለት ይገባል። ምክንያቱም ለራሱ ከማይገምተው ኃላፊነት ላይ በፍጥነት ስናመጣው ለራሱ የተሳሳተ ግምት በመስጠት ወዳልሆነ ድምዳሜ ሊደርስ ይችላል። ስለሆነም

ቁልፍ የአመራር ቦታ ላይ አንዲመጣ አንዲህ ዓይነቱን ግለሰብ መገፋፋት አንደማይበጅ ተገንዝበን መታቀብ አለብን ::

በጌታ ያልቆየ ግለሰብ ከቆይታው ጋር የማይመጣጠን ታላቅ ኃላፊነት ስንለጠው በትዕቢት ተሞልቶ አንዳይስናከል ወደ መድረክ ከመውጣቱ በፊት በቂ ጊዜ ሊስጠው ይገባል። ምክንያቱም መቻከል የበዛበት ንብረውና በፍጥነት የደረሰበት ቁልፍ የመድረክ ቦታ ስለማንነቱ የበለወ በትዕቢት እንዲያስብ ስለሚገፋፋው አዲስ አማኝ የቱንም ያህል የተዋጣለት ቢሆን ወደ አንደዚህ ዓይነቱ ከፍተኛ የኃላፊነት ሥፍራን በተቻኮለ ሁኔታ ልናመጣው አይገባንም። ይልቁንም ጊዜ ወስዶ ለታማኝ አገልጋይ የሚወቅመ ባህሪያትን እንዲጎነባ ዕድል ልንፈጥርለት ይገባል። ይህንን ማድረግ ለግለሰቡም ለቤተክርስቲያንም ጠቃሚ ነው።

ሲ ምስባኩ ላይ መቆም ያለባቸው በመንፈሳዊ ስጦታቸው የተመለከረላቸው መሆን አለባቸው

በምስባኩ መቆም ያለበት በመጀመሪያ በንጽህናው የተመለከረለት ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ስጦታው እንዳለው ያረጋገወ ሌሎችም ያረጋገጡለት ሰው መሆን አለበት። ልምምድ ለአማኞች መብለልና ለኃላፊነት መብቃት አስተዋጽኦው ቀላል ባይሆንም መንፈሳዊ አገልግሎት በኩረጃ ወይም በልምምድ ብዛት አይከናወንም። ሰው በልምምድ ትንቢት አንደማይናገር ሁሉ በልምምድም የመድረክ አገልጋይ አይሆንም። አዚህ መባል የተፈለገወ ልምምድ ጠቃሚ አይደለም ሳይሆን ልምምድ የስጦታ ምንጭ አይደለም። ልምምድ ስጦታን ያሳለብታል። ይሁን አንጂ ባለስጦታ አያደርግም።

ብዙ ጊዜ «በመገለጥ ይመጣሉ» ሰለሚባሉ ነገሮች ያለን አመለካከት ቅጽበታዊና ተአምራዊ ነው። ተአምራዊ ብለን የተቀበልናቸውም የሰው ጥልቀት ያላው አሳቤ ሳይገባባቸው ድንገት በመሆናቸው ነው። ጊዜ ፈጅተው በአገልጋይ ሕይወት የሚፈጸሙትን ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ግን መንፈሳዊ ስጦታ ቢሆኑም እንኳን በልምምድ አንደሚደረስባቸው አናስባለን። ጊዜ ከሚወስዱ መንፈሳዊ አገልግሎቶች መሐል ዝማሬና ሰብኮት ይገኙበታል። አገልግሎቱ ሲሰጠን ቅደም ተከተል ጠብቀን ሲያስፈልግም ማስታወሻ ይዘን መልእክት እናስተላልፋለን። ያንን አደራረግ ተአምራዊ ብለን መጥራት

አንፈልግም። የተዋበ ድምጽ የለው ሥራት አይደለም። ነገር ለለው በሚገባ መግለጽ በምርጫና በልምምድ አይገኝም የጌታን ረድኤት ይጠይቃል። ጊዜ ወስደን የምናስተላልፈው መንፈሳዊ አገልግሎት በልምምድና በጥረት ብቻ እንደሚገኙ ብቻ ማሰብ ስህተት ነው። ለእነርሱም የጌታ ረድኤት አንደሚያስፈልግ አንረዳ። በመድረክ ቆመው ጌታ የሚናገረኝ አናገራለሁ ልሚሉን ብቻ የጌታ ሌሎችን ግን የፍጡር ማድረግ ይቅርብን።

ያለ ዝግጅት በቅጽበት የሚመጡትን መለኮታዊ ሰንላቸው አንዳንድ የመድረክ አገልግሎቶችን ግን ለአዘጋሚ ልምምድ አንሰጣቸዋለን። ይህም የመድረክ አገልግሎቶችን ትክክለኛ ተፈጥሮአቸውን መካድ፥ ምንጫቸውንም ማራከስ ለለሆነ በውል ሊጤን ይገባል። የሁለቱም ምንጭ አምላክ ከሆነ ቅጽበታዊም ሆኑ አዘጋሚ ስጦታዎችን በማበላለጥ ማየት የለብንም። ቀደም ብለን እንደተነጋገርን በልምምድ መገለጥ አንደማይመጣ በልምምድ ብዛት የመድረክ አገልጋይ አይኮንም። ጊዜ ለብስለታችን የሚያዋጣው ነገር ቢኖርም ጊዜ ግን የስጦታ ምንጭ አይደለም።

ሰለሆነም በምስባኩ ላይ ለለሚቆሙ ሰዎች ስናስብ ስጦታው ያላቸው መሆን ያለባቸው መሆኑ ለድርድር አይቀርብም። ስጦታው የሌለው መድረክ ላይ መቆም የስበትም። ያለው ደግሞ መድረኩን መነፈግ አይኖርበትም። ያለውን ትቶ የሌለውን ማሰማራት ከመስመር ለወጣ ሰይጣናዊ አሠራር ራስን መስጠት ነው። በአካል ውስጥ ያሉ ብልቶቻችንን አገልግሎትና የሥራ አፈጻጸም በተመለከተ ስናስብ ሁሳችንም ግልጽ የሚሆንልን ነገር አንዱ አንዱን ተክቶ ሥራውን መፈጸም አለመቻሉን ነው። አንዱ ብልት ሌላውን ሆኖ ሥራ ማከናውን አንደማይሆንለት ያለብዙ መግለጫ ይገባናል። ልክ እንዲሁ የመድረክ ስጦታ የሌለው ግለሰብ በመድረክ ላይ ይላከለታል ብሎ ማሰብም ሞኝነት ነው። ይሁን አንጂ በመድረኮቻችን ጸጋው የሌላቸው ሰዎች ቆመው አነርሱ ያለ ኃፍረት በሚፈጽሙት ስህተት ጉባኤው ትርምስምስ ሲል ማየት ብዙዎቻችንን አያሳቅቀንም። አንደውም ደግመን ደጋግመን በመጋበዝ ያንኑ ጉድለታቸውን በአደባባይ አንዲደጋግሙ ዕድል አንሰጣቸዋለን።

ከአውቀት ማነስ የተነሳ በምንፈጥረው ስህተት እንዳንቀጥል አምላክ ትዕግሰቱንና ርህራሄውን ለአኛ በማብዛት ተምረን አውነትን አንድረዳና

እንድንታረም ዕድል ይሰጠናል። ዳሩ ግን ሆን ብለን በቸልተኝነት ለምንፈጽመው ስህተት ርህራሄውና ትዕግስቱ ሳይሆን የቁጣው በትር ያገኘ ናል። በተግሳጹም ያስደነግጠናል። በአካላችን ያሉ ብልቶቻችን ምን እንደሚሰሯቸው ምን እንደሚይዙላቸው መረዳት የጠለቀ ትንተናን የሚጠይቅ አለመሆኑ ለብዙዎቻችን ግልጽ ነው። ልክ እንዲሁ ማን መስበክ፥ ማን መምራት፥ ማን ደግሞ መዘመር እንዳለበት በግልጽ የምናውቅ በአመራር ላይ የተቀመጥን ጥቂቶች አይደለንም። ዳሩ ግን ነገሮች ሊገላበጡ አይተን ነገሩን በዝምታ የምናልፈበት ጊዜ ጥቂት አይደለም። እንዲህ ዓይነቱ ገለልተኝነት ሳይጎዳን የሚተወን እንዳይመስለን። ለምሳሌ ዓይን እንዲጎርስ እጅ ግድ ቢለው፥ ምላስም እንዲራመድ በብልቶች ቢገደድ፥ እነዚህ ብልቶቻችን ምን እንደሚገጥማቸው በቀላሉ ይገባናል። ዳሩ ግን ያለቦታቸው ተመድበው ምስባኮቻችንን ስለሚያጣብቡና ስለሚያተራምሱን አገልጋዮች ግን ያን ያህል ሊጨንቀን አይሰተዋልም። ይህ ለምን ይሆን?

እያንዳንዱ ብልት በአካል ውስጥ የራሱ ድርሻ እና ስጦታ አለው። በዚያም ቢሰማራ ውጤታማ ይሆናል። ልክ እንዲሁ በምስባኩ ላይ ሆነው ምእመናን እውነተኛውን የመንፈስ ነጻነት እንዲለማመዱ ዕድሉን ብንፈጥር ውጤት ያለው የምእመኑ አገልግሎት እውን ይሆናል። ይሁን እንጂ ምስባኩ ያልጠራቸውንና ሊያስተናግዳቸው ያልፈቀደላቸውን ሰዎች ስንት ጊዜ አስተናገድን? ለመሆኑስ በመድረክቻችን እንዲያሸፉበት የምንፈቅደው እስከ መቼ ነው? ይህ ዓይነቱ ተደጋጋሚ ጥፋት መቼ ይቆም ይሆን? በእውነት ወረፋ ጠብቀው በሚስተናገዱ የምስባክ ፕሮግራሞቻችን የሚቆሙት በስጦታቸው ተለይተው ወይስ ያለ ስጦታቸው እንዲቆሙ በሚፈልጉ ጓደኞቻቸው ድጋፍ? ለምእመኑ ወቅታዊ ፍላጎት ደንታቢስ የሆኑ መሪዎች ባሉበት አጥቢያ የምዕመኑ ፍላጎት ሳይሆን የአነርሱ ምርጫ ይከበራል።

ዛሬ መድረኮች «ምዕመኑ እንደ እግዚአብሔር ቃል ምን ያስፈልገዋል?» የሚለውን ጥያቄ ከመመለስ ይልቅ ላልታወቁ አገልጋዮች የማስተዋወቂያ በር መክፈቻ መሆናቸው ያስፈራል። መድረኩ ላይ ያለ ስጦታችን ለመቆም መዳፈር ነውር ነው። ስጦታው እንዳለን ርግጠኛ ከሆንን ዕድሉን ልንነፈግ አይገባም። በአካል ውስጥ ያሉ ብልቶች ሥራ እንዲፈቱ

ብናስገድዳቸው እየሰለሉ ሄደው ይሞታሉ። በስጦታቸው መድረክ የሚፈልጋቸውን ሰዎች መጋረድ የሚያስከፍለን ዋጋ አለው። ስጦታው የሌላቸውን ለማሠማራት መምረጣችን ደግሞ የበለጠ ያስቀጣናል። ተራራን በማንኪያ ሜዳ ለማድረግ ብንፈልግ እንደሞኝ እንቆጠራለን። እርሻን በምስማር ለማረስ ብንፈልግ ይሳቅብናል። ልክ እንዲሁ ያለ ስጦታው ሰውን ወደ መድረክ ማምጣት የቢያኑ ያህል ሊያሳፍረን ፥ ሊያስደነግጠን የሚገባ ጉዳይ መሆን አለበት። ስለሆነም መድረኩ ላይ የሚቆሙትን ስጦታቸውንና ንጽህናቸውን በመመዘኛነት እናሰማራ።

የውይይት ጥያቄዎች

1. ለመሆኑ በእኛ አይታ መድረኩ ላይ የሚቆሙት የሚገባቸው ናቸውን? ካልሆኑስ ለምን?
2. በመድረኩ ላይ መቆም ያለባቸው አገልጋዮች ሊያሟሉት የሚገባቸው ባህሪያት ምን ምን ናቸው?

1.7. ምስባኩ እንዲዋብ

ብዙዎቻችን የምንናፍበት ሥፍራ የሚታይ ውበት እንዲላበስ የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን። ቤተ መንግስት አንድን ሃገር ለመምራት ሕጋዊ ውክልና የተሰጠው አካል የሚጠቀምበት መኖሪያ ነው። ለዚህ መኖሪያ ሃገሪቱን የሚመራው መንግስት የተሻለውን በሙሉ ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል። ዓለም የፋክክር አምባ ስለሆነች አንዳንዱም ሌላው እየተራበ እንኳን ቤተ መንግሥት በተለየ መንገድ ይዋባል። አለው የሚባል ግለሰብ ቤቱን ንብረቱን የሚመጥን ውበት የተላበሰ እንዲሆን ለማድረግ ይጥራል። አምላካችን ከሁሉ እንደሚልቅ ለማን ይለወራል? እኛም ከማንም፥ ከምንም አብልጠን እንደምንወደው አንሸሽግም። ይሁን እንጂ ለቤቱ ውበት የምናደርገው ትጋት እምብዛም ሲሆን ይታያል።

ቤተ ክርስቲያን የሚለዉ አገላለጽ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቀጥታ የሚመለከተው ሰውን እንጂ ሕንጻውን አይደለም የሚለውን አዲስ ኪዳናዊ ትንተና ብዙዎች ይቀበሉታል። ይሁን እንጂ ሕንጻውን አምላክን ከመውደድ የተነሳ ማስዋብ ከመንፈሳዊነት ማፈንገጥ ሆኖ ሊታይ አይገባም። የምስባኩን

አካባቢም በቸልታ መመልከት አግባብ አይሆንም። ቢሆንልንና ቢላካልን ውበቱ ከማንኛችንም ላሉን የተሻለ ቢሆን ምን ይከፋል? ግና ለምች አምላክን ትተው ሕንጻን ለማምለክ ካዘነበሱ በኋላ ትኩረታችን ይባባል በሚል ስጋት ለሕንጻው ውበት÷ ለምስባኩ አከባቢም ያለን ጥንቃቄ አምብዛም ነው። ይህ ግን ሚዛን የጎደለው አደራረግ እንደሆነ አንገነዘባለን። ለምች ቦታውን እንዳያመልኩ ተገቢውን ትምህርትና ምክር ከለገስናቸው የምስባኩ መዋብ ወጥመድ አይሆንባቸውም።

በሠርግ ቀን ለጠራን ለው ክብር ስንል ያለንን ጽዱ ልብስ ለብሰን ለመሔድ ተገቢ ዝግጅትና ጥንቃቄ እናደርጋለን። ልክ እንዲሁ አምላካችንን ለማስደሰት ባለን ልባዊ እንቅስቃሴ ምስባኩን ብንችልም የጸሎት ቤቱን ማስዋብ መልካም ነው። ለመሆኑ የስንት ኃላፊዎች ቢሮ ነው ከሚገባው በላይ ሲያሸበርቅ የምናየው? ለለዎቹም ባይሆን ለተቀመጡበት ወንበር ውክልና ስንል ሊሟሉ ስለሚገባቸው ነገሮች አብዝተን እንጠነቀቃለን። የአምላክ ስመ የሚጠራበት እሱ ክፍ ከፍ ይልበታል ብሰን የምናስበውን ሥፍራ ብናስጌጠው ምን አለበት? አኛ «መንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት» አማኞች ሁሉ የአምላክ ቤተ መቅደሶች ናቸው ከሚለው ትምህርታችን የተነሳ መድረኮቻችንን ለማስጌጥ የጎላ ትኩረት አንለጥም። ይሁን እንጂ ተጋቢዎች መድረኩ ዙሪያ ይመጣሉ በተባለ ቀን ለእነርሱ ክብር ለደስታቸውም ብዙ ዋጋ ከፍለን መድረክ እናስውባለን። ግና ለአምላካችንም ይህንን ዓይነቱን ያማረና የተዋበ ነገር መስጠት አይሆንልንም ወይም ሆን ብለን ስናደርገው አንታይም።

መድረክ ወይም ስመ እግዚአብሔር የሚጠራበት ሥፍራ አንዲዋብ የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ነው። ሊዘህም ነው ያን የሚያስጌጡ ሰዎች እርሱ በሚጠራበት ሥፍራ ላይ እንዲሰሩ ለቤቱ ሥራ ለዎችን የስጠው (ዘጸ 35፡30) ታዲያ እኛ ምስባኩን ማስዋብ በቸልታ የምናየው ለምን ይሆን? እግዚአብሔር በባስልኤልና በጓደኞቹ የማደሪያውን ድንኳን እንዲያስጌጡ የጥበብ መንፈስ መመላቱ ለእኛ ምን ይናገረናል? (ዘጸ 35፡30-35) በእኔ አምነት በቤተክርስቲያን ያሉ መድረኮችን እንደ አንዳንድ ቤተክርስቲያናት በተለየ መንገድ ባንጣበቅባቸውም እንኳን ጽዳትና ትኩረት የጎደላቸውን መድረኮች ታቅፎ ደንታቢስ መሆን ተገቢ አይደለም። ታለቦበት ስጌታችን የማለጥን

የተዋበ ነገር ጌታችን ይፈለጋልና እናስብበት። ለለሆነም እኛ የወንጌል አማኞች ጊዜ ለጥተን ማስብና ለዚህም ተገቢውን ርምጃ መወለድ ይኖርብናል።

በሁለተኛ ደረጃ ለለው በምንለጠው ጉዳይ ላይ ብዙ ተጠንቅቀን ደስ የሚለኝበትን ነገር ለማድረግ ከተጋን ለእምላክ ነው የጌታ ነው ለምንለው ነገር የበለጠ ልናደርግ አይገባንምን? ከእምነት አባቶቻችንስ የምንማረው ይህንኑ አይደለምን? የእግዚአብሔር ባሪያ ዳዊት ለመቅደሱ መዋብ ካለው ቅናት በመነሳት አንድ ለትውልድ ሁሉ የሚጠቀስ መልካም ነገር አድርጓል። ይህንንም በብሉይ ኪዳን በ1ኛ ዜና 29 ላይ እናነባለን።

> «ሕንጻው ግን ለእግዚአብሔር ለአምላክ ነው እንጂ ለሰው አይደለምና ሥራው ታላቅ ነው። እኔም እንደ ጉልበቴ መጠን ሁሉ ለወርቅ ዕቃ ወርቁን ÷ ለብሩ ዕቃ ብሩን ÷ ለናሱም ዕቃ ናሱን ÷ ለብረቱም ዕቃ ብረቱን÷ ለእንጨቱም ዕቃ እንጨቱን ...——— አዘጋጅቻለሁ (1ዜና 29፡2-3)።

«የእምላኬን ቤት ስለወደድሁ» ቁ 3 በማለትም ዳዊት በዚህ ሥፍራ እምላክና ሕዝቡ ስለሚገናኝበት ቦታ የወሰደውን ማስተዋል የተሞላበት ርምጃ ይናገራል። በአዲስ ኪዳን ለቦታ የተጋነነ ትኩረት ባይሰጥም እንኳን÷ ሁላችን በጋራ የምንገናኝበት ቦታ የደስ ደስ ያሰው እንዲሆን ለማድረግ ተገቢውን ርምጃ መውሰድ መልካም ነው። ችሎታውና አቅሙ እያለን የጸሎት ቤታችንን በሥለይም የምስባኩን አካባቢ በቸልታ ተራ ማድረግ አይገባም። ስለሆነም የቻልነውን ዋጋ በመክፈል አከባቢውን ጽዱና ዓይነ ግቡ ብናደርገው አይከፋም። ሰግላዊ ቤታችን ጽዳትና ውበት የምንጠነቀቀውን ያህል አምላካችንን ቢጋራ እናመልክበታሰን ለምንለው ሥፍራ የበሰለ ልናደርግ አይገባምን? ምስባኩን በተቻለ መጠን ማራኪ ማድረግና ማስዋብ ለምንም እንደማይጠቅም ከንቱ ነገር መቆጠር የለበትም። ስለዚህ ለምስባኩ ጽዳትና ዉበት ይጠቅማሉ የሚባሉ ልናደርጋቸው የምንችላቸውን ነገሮች በመሉ ማድረግ መልካም ነውና ቸል አንበለው።

1. ምስባክን ማስዋብ መንፈሳዊ ትኩረትን ያዛባልና መደረግ የለበትም ስሚሉን ምን መልስ አለን?
2. ምስባክ ማስዋብ አለብን ብለን የምንናገረው ለምንድነው?

1.8 ምስባኩ እንዲጠበቅ

ቦታን በተሰየ መንገድ የተቀደሰ አድርጎ ማለብ ክአዲስኪዳናዊ ግንዛቤ ይርቃል። ይሁን እንጂ ብዙ ዋጋ ከፍለን ካጸዳነው ሳሎናችን ያነሰ ትኩረት ለምስባኩ ማድረግ ልክ አይመለልም። ስለሆነም የማንኛችንንም ቤት ጽዳት እንደምንጠብቅ ልክ እንዲሁ ምስባኩን በጥንቃቄ መያዝ አለብን። ለዚህ የሚገደውና በየጊዜው አስፈላጊውን ነገር የሚያሟላ ክፍልም መሾም ይገባናል። በሥራቸው ምስባኩ ላይ ለሚከናወን ነገር ትኩረት የሚሰጡ ክፍሎችን ሆን ብሎ ማደረጃት በየእሁዱ ክምናያቸው አላስፈላጊ ነገሮች አንድንጠበቅ ያግዛል። ትናንት ማን ተጠቅሞበት ነበር? ለዛሬ አኮ አልተዘጋጀም! የሚባሉ አሮሮ የሞላባቸው ንግግሮች ምስባኩን የሚጠብቁ አለመኖራቸውን የሚያስገነዝቡ አባባሎች ናቸው።

ምስባኩ እካባቢ ላሉ አበቦች እንዲሁም ከመናገሪያ መሣሪያው ጋር የተያያዙ ነገሮች በሙሉ ለምስባኩ ከምንውስደው ጥንቃቄ ጋር ይያያዛሉ። አለቀድሞ ኃላፊነት የተሰጠው፥ በቋሚ ባለቤትነት የሚታወቅ ወገን ስላልተለየመ አንዳንድ ቦታ የመናገሪያ መሣሪያ ችግር ሲኖር ትርምስ ሲፈጠር ይታያል። አንዳንድ ጊዜ እንግዶች አንኳን ሳይቀሩ በጉዳዩ እንዲገቡበት ልመና ይቀርባል። እንዲህ ዓይነቱ የአደባባይ ትርምስ ያሳፍራል፥ ገበናን ደጅ እንዲወጣ ያደርጋል። የተዝረከረከ አደረጃጀት እንዳለንም ስለሚናገር ምስባኩን ከየአቅጣጫው የሚጠብቁ መኖራቸው አግባብ ነው። የሰለጠነ ባለሙያ በሌለበት ቦታ የድምጽ ማጉያን ከመጠቀም ሰጊዜው ማዘግየቱ ይመረጣል። ስመጠቀም ከፈለግንና በዚህ አቅጣጫ ቁርጥ ውሳኔ ካደረግን ለምኑን በአጭር ጊዜ ከፍያ የሙያ ጥበባቸውን እንዲያጋሩንና ሰውም አለልጥነው እንዲሰጡን ልናስማራቸው ይገባናል። ያኔ በሁሉም

ይሆናል።

የውይይት ጥያቄዎች

1. ምስባክ በአናንቱ አካባቢ በቂ ትኩረት ተሰጥቶታል ትላላችሁ? እንዴት?
2. የምስባኩ ሥፍራ ራሱን የቻለ ባለ አደራ ያስፈልገዋል ብለን አናምናለን? ለምን?

ክፍል ሁለት ትኩረት የሚሹ የመድረክ አገልግሎቶቻችን

ቅዱሳን በሚሰበሰቡበት ቦታ ይብዛም ይነስም ቅደም ተከተል ይኑረው አይኑረውም የሚክናወን ድርጊት አለ። ዱሮ ዱሮ የመድረክ ድርጊቶች በነሲብ መሆናቸው ማንንም አይጣላም ነበር። ያኔ በሁሉም የነገሰው ቅንነት ነበርና። እንደውም ድሮ ድሮ ገና ወደ ጉባኤ የመጣ ግለሰብ ማንነቱ እንኳን ሳይታወቅ «ቃል እንዲያካፍል» ይጋበዝ እንደ ነበር ስናስብ በትዝታ ፈገግ እንላለን። ከየዋህነትና ከቅንነት የተነሳ ይደረግ ስለ ነበር ዘመኑ ያስ ብዙ ጉዳት ታስፈ። አሁን አሁን ግን በአግዚአብሔር ስም ተሰብስበን አንዳንድ ጊዜ በአንዳንድ ምስባክች ጸጋን የሚሰጥ ሳይሆን ጸጋን የሚነጥቅ ነገር ሲከናወን እንመለከታለን። አንደውም አንዳንድ ሥፍራ መንፈሳዊው ነገር ክርዓተ-አልበኝነት እየነገሰበት መጥቶ ከማነጽ ሥራው ይልቅ የማፍረሱ፥ ግራ የማጋባቱ እንዲሁም የመከፋፈሉ ነገር እያየለ በመምጣቱ ጉዳዩ አነጋጋሪ ሆኖአል። እግዚአብሔርን የሚፈሩትም ለምኞ ምን ቢሆን ይሻላል? እያሉ መመካከሩን ቀጥለዋል። አንዳንዶችም ብጤ ለይተው በጎራ ተደራጅተው መቆራቆሱን ተያይዘውታል። ግን በእንዲህ ዓይነቱ ጊዜ ቃሉ ምን ይላል? በተቀደሰው መድረክ ላይ የሚከናወን አገልግሎት ምን ዓይነት መልክ ቢኖረው ይሻለል? የሚሉት ጥያቄዎች መመለስ ይኖርባቸዋል።

ሐኪም ቤት ለንሄድ ሐኪሞቹ የታመምነውን እንደሚነግሩን ለዚያም አለፈላጊው መደኃኒት እንደሚታዘዝልን ይህም ጽሑፍ ጤና ባጣንበት አካባቢ አተኩሮ የበኩሉን መፍትሔ ለመስጠት መከራ ያደርጋል። ሐኪሞች

ስለጤናችን የለፋና የተበራራ መግለጫ እንደማይለጡን ሁሉ ይህም ጽሑፍ ክኒዜ ጥበትና ቅደሚያ ሊለጠው ከሚገባ ነገር አኳያ ሊያተኩር የሚፈልገው መታረም ያለባቸው ጉዳዮቻችን ላይ ነው። ይህ ማለት ግን «በምስባኩቻችን ላይ ምንም መልካም ነገር የለም» ማለት እንዳልሆነ አንባቢው ያስተውል። በበሽታችን ላይ ማተኮራችን ጤናችን ጨምሮ ኃይል እንዲበዛልን ነው። ስለሆነም የምናነሳቸው፥ ትኩረት ይሰጣቸው የምንላቸው ጉዳዮች በሙሉ ስህተትን ስማደን ፈልገን የምንላቸው ሳይሆኑ ይልቁንም ለጥንካሬ የሚያበቁን የመንደርደሪያ መንገዶቻችን ናችው። በዚህም ዕይታ መድረክቻችንን እንቃኛ ለን።

2.1 የመድረክ ትርጉምና ምንነት

መድረክ እምላክ ለሕዝቡ ፈቃዱን የሚገልጥበት አርሰ ብቻ እንዲታይበት ወኪሎቹን የሚልክስት የተቀደሰ ሥፍራ ነው። በዚህ ሥፍራ የሚቆመ ሁሉ የእርስ ወኪሎች እንጂ ምትኮች አይደሉም። የሚበዙት ለዎች ወደ ጸሎት ቤት ሊመጡ ምኞታቸው የዛሬ ሁለት ሺ ዓመት ፊሊጶስ የተጠየቀውን ዓይነት ነው ፦«ጌታ ሆይ ኢየሱስን ልናይ እንወዳለን» (ዮሐ 12:21)። ዛሬም ብዙዎች ይህንን ይጠማሉ። ጌታን ሊያዩ ብቻ ለዎች መፍትሔ ያገኛሉ። ስለሆነም መድረክ ለዎችንና ጌታን የምናገናኝበት በአምላክ የተመረጠ ቦታ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። የትኛውንም ያህል በንግግራችን የተሳካልን እንሁን ምንጩ እኛው ብቻ ሆነን ÷ እኛው ከታየንበት ጉዳዩ የፍጡር ተውኔት ይሆናል። ታዲያ በማብቂያው የስው ነገር የለው ብቻ ሆኖ ይቀራል። ይህ ኪሳራ እንዳይገጥመን እነ ጳውሎስ ለመድረክ የነበራቸውን መረዳት ገንዘባችን እናድርግ።

እነ ጳውሎስ በቆሙበት መድረክ ንግግር ሊያድርጉ ለዎች ያዩ የነበረው እነርሱን ሳይሆን የተሰቀለውን ክርስቶስን ነበር (ገላ3፡1)። በዚያ ሥፍራ ከእነርሱነታቸው ይልቅ ትልቁን ማንነት ለማሳየት ችለው ነበር። ራሳቸውን ሳይሆን የሳካቸውን ለመግለጥ ተግተው ነበር። ለዎች እነርሱን ሊያዩ ጌታን እንዳዩ ይቆጥሩ ነበር። የመናገሪያው መድረክ ላይ ማን መነሳት እና ከፍ ከፍ ማለት እንዳለበት ለለሚያውቁ የቆሙበትን ሥፍራ ሁሉ

የአምላክን ክብር የሚተርኩበት ሥፍራ አደረጉት። ተከሰው በቀረቡበት የወንጀል ችሎት እንኳን ማን መጉላት እንዳለበት ለአፍታም ቢሆን አልጠፋቸውም።

ጌታ ኢየሱስ በእንዲህ ዓይነት መረዳት ባሪያዎቹ ሁሉ እንዲጓዙ ይፈልጋል። ይሁን እንጂ አርሱ እንኳን ባገለገለበት ዘመን ይህ ግንዛቤ በወቅቱ የመንፈሳዊ ነገር አቀንቃኝ ነን ብለው ከሚሉት «መንፈሳዊ ቡድኖች» አገልግሎት እንኳን አልታየም። ጌታ በምድር በተመላለሰባቸው ጊዚያት ልቡን ከለበሩት ነገሮች አንዱ ለመድረክ÷ የአምላክ ስም ለሚጠራበት ቤትና አገልግሎት አገልጋዮች ደንታቢስ መሆናቸው ነበር። በዚህ መንገድ ከሚኮነኑት ቡድኖች ፈሪሳውያን ግንባር ቀደም ሆነው ይጠቀሳሉ። እነዚህ መንፈሳዊ እንደሆኑ የሚለፍፉ ቡድኖች ካሳዩት ቸልተኝነት የተነሳ የመድረክ ምንነትና የአገልግሎት ትርጉም ተዛብቶ ነበር። ስለሆነም ጌታን በቁጣ አንቀሳቀሰው አንዲህም አለ «ቤቴ ለአህዛብ ሁሉ የጸሎት ቤት ትባላለች» (ማር 11:17) ። ቤቱን ጸሎት ቤት አንዳይሆን ስማድረግ የተነሱትን በሙሉ በጅራፍ አባረራቸው።

ዛሬ ዛሬ ደግሞ ተክብሮ የመኖርን ጥበብ ብዙዎቻችን ስላዳበርን የለው ቤት በሃላፊነት አንድንጠብቅ ቢስጠን አደራው ይከብድብናል። ከተሰጠን ኃላፊነት እኳያ አደራውንም የሚመጥን ትኩረት አናደርጋለን። አርግጥ ነው በአደራ ለተሰጠን ቤት ጥንቃቄ ማድረግን አብዛኞቻችን አናውቃስን። ስለሆነም የባስንብረቱን መመሪያና ትዕዛዝ ያገናዘበ ርምጃን በመውሰድ ቤቱን አንጠቀማለን። ታዲያ ወደ አምላካችን ቤት ስንመጣ ይህንን ዋና ነገር ስማሰብ ለምን ተሳነን? በቤቱ የሚጋብዘን ጌታ ነው። በቤቱ ደግሞ ከፍ ከፍ ሊልና ሊልቅ የሚገባው ጌታ ራሱ ነው። አርሱን ማዕከል ያላደረገ ነገር ምስባኩ ላይ ለማድረግ ለምን አንፈተናለን? የቤተ ክርስቲያን ቦታው በእንግድነት የተሰጠን ነው። ይሁን እንጂ ሙሉ ስሙሉ በባለቤትነት የምንቆጣጠረው ለምን ይመስለናል? ወኪልነታችን ረስተን ምትክ መሆን ለምን ይቃጣናል? እንዲህ ዓይነቱ አባባል አንዳንዶችን ግር ያለኛል። ምክንያቱም ወደ ጸሎት ቤት ስንሄድ ጌታ አስተናጋጃችንና ጋባፖችን እንደሆነ በጥልቀት እንገነዘብምና። ሕገሙ ባለበት ጌታ አለ። ጌታ እንዳስ ከገባን አርሱን አያስብን ከአርሱ

በሚመጣ መመሪያ ሁሉን ማድረግ አለብን:: ታሪካቸውን ከላይ ያነሳነው ለዎች በጅራፍ የተገረፉት ለዎች ይህ ጥበብ ጎድሎአቸው ነው:: «ቤቴ ለአህዛብ ሁሉ የጸሎት ቤት ትባላለች» (ማር 11:17) ተብሎ እንደ ተጻፈ ቤቱን እንደ ባለቤቱ አልያዙለትምና :: ስዚህ ነው÷እኛም ቤቱ የእኛና የእኛ ብቻ እንደሆነ ማለብ የለብንም ነው የምንለው::

የውይይት ጥያቄዎች

1. ባለንበት ሥፍራ በእርግጥ መድረክ የሚገባውን ክብር ተሰጥቶታል?
2. አናንተ ለመድረክ ፍቺ ስጡ ብትባሉ መድረክ ማለት ምን ማለት ነው?
3. ጌታ ዛሬም እንደ ብሉይ ኪዳን ዘመን ስለ ሥፍራ ይገደዋል ትላላችሁ? እንዴት?

2.2 የመድረክ ክብር

በጌታ ቤት መድረክ የማንም እይደለም የጌታ ነው:: ዛሬ ጌታ በአካል በመካከላችን ቢገኝ በምንለማው መልኩም ቢናገረን እንደ ሙሴ ዓይነት ድምጹን ያሰማን ነበር:: « ሙሴ ሙሴ...ይህች የቆምህባት ምድር የተቀደለች ስለሆነች.. እውልቅ» ዘጸ 3:4 እንባል ነበር:: መድረክ የተከበረ የሆነው ከቦታው ለየት ማለትና ድርጊት ፈጻሚው ለብዙዎች የሚታይበት ቦታ በመሆኑ እንዳልሆነ ለብዙዎቻችን ይገባናል:: ይሁን እንጂ ባለቤቱ ማን እንደሆነ አብዛኛውን ጊዜ አንረሳለን:: ሙሴ የቆመበትን ያንን ቦታ ልዩ ያደረገው የተለየ አካባቢ መሆኑ አይመስለንም:: ይልቁንም በበግ እረኝነት እንቅስቃሴው እልፎ አልፎም ቢሆን የሚያውቀው ቦታ ሳይሆን አይቀርም:: ይሁን እንጂ ይህንን የተለየ ጥሪ በለማበት ቀን ቦታውን ልዩ ያደረገው አምላክ በተለየ መንገድ በሥፍራው መገኘቱ ነበር:: እግዚእብሔር ሙሴን ሲጠራው እንዲገነዘብለት የፈለገው ነገር አካባቢውን ለየት ባለ ሁኔታ የሚቆጣጠር ማንነት እንዳለ እውቆ ላአከባቢው ንቁ አንዲሆን ነበረ:: ያ ጊዜ የተለየ ክብር፣

ዕይልና ሥልጣን ባለቤት ክሆነው ከተቀደለውና ከተፈራው አምላክ ጋር የሚገናኝበት ጊዜ ስለሆነ ጥንቃቄ የሚያሻው የተከበረ ጊዜ ነው::

እኛም ብንሆን ክተከበረ ሰው ጋር ስንነጋገር በየአቅጣጫው ጥንቃቄ የተሞላበት ነገር እናደርጋለን:: ለምንለብለውም ሆነ ለምንናገረው ነገር የተለየ ትኩረት እንለጣለን:: በሙሴና በያህዌ መሐል የተደረገው ውይይት ለእኛ የሚተውልን ቁም ነገር ከችኩልነት ወይም ከጥድፊያ የጸዳ ንጹሕ ፍርሃት በውስጣችን እንዲኖር የበኩላችንን ጥረት ማድረግ ያለብን መሆኑን ነው:: መድረክ ክቡር የሆነው ባለቤቱ ፍጡር ሳይሆን ፈጣሪ በመሆኑ ነው:: እግዚአብሔር ወደ እርሱ በሚቀርቡና ሌሎችን ወደ እርሱ በሚያቀርቡ ለዎች ስለሚቀደስ ባሪያዎቹ እርሱ የመረጠውን ቅዱስ ስፍራ በቸልታ እንዲመለከቴት እይፈልግም:: ናዳብና አብዩድ አምላክ በቅድስና እና በፍርሃት እንደሚቀረብ ዘነጉ:: ስለሆነም ጥንቃቄ በጎደለው መንገድ ወደ አምላክ ስለመጡ ብዙዎቻችን ያጋጠማቸውን እስደንጋጭ ዕጣ አንረሳውም (ዘሌ 10:1-10):: በድፍረትና «እችለዋለሁ÷የረጅም ጊዜ ተሞክሮ አለኝ» በሚል ትምክህት የሚከናወን ማንኛውም ድርጊት የአምላክን መድረክ እንደመዳፈር ወይም እንደ ማቃለል ይቆጠራል:: ይህ ደግሞ ያ መድረክ የሚሠራበትን መሠረታዊ መርሆ ከመዘንጋት ይመነጫል:: በመረጃ ዘመን እየኖርን የመረጃን ጠቀሜታ ባንክድ እንሞኛለን:: ይሁን እንጂ ከመረጃ የላቀ ሥፍራን የያዘ መገለጥ የሚባል እውራ ክስተት በመንፈሳዊ ርምጃ ውስጥ እንዳለ መረሳት የለበትም::

ስለሆነም በመድረክ ላይ ለሚሆነው ለየትኛውም ነገር ከመረጃ ይልቅ ለመገለጥ ቅድሚያ አለ:: ከብልሃት ይልቅ ምሪት ይከበራል:: ስለሆነም በችሎታችን ከመታመን በችሮታው ለመደገፍ ንጹሕ ፍርሃት ቢኖረን ለመድረኩ አክብሮት ሰጠን ማለት ነው:: ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቱ ግንዛቤ በሁሉ ዘንድ አይገኝም:: በጸሎት ቤት ያሉ መድረኮችን በቁጥጥር ሥር ያደረጉ ግለሰቦች መድረክን ለአምላክ ክብር ከመጠቀም ይልቅ የራሳቸውን ግለሰባዊ ዝና ለማጎልበት የነጠላ ተውኔት ማሳያ ሲያደርጉት ይስተዋላል:: ስለሆነም በቃልም ሆነ በድርጊት ለሚያከናውኑት ነገር ንጽሕና ለበስ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ አይስተዋልም::

ምላስ አጥንት የላትም ግና አጥንት ትሰብራለች እንዲሉ አንዳንዶች ከመድረክ የአያሴ ቅዱሳንን ልብ የሚለብር ድፍረት የሞላበት ንግግር

ሲያደርጉ ይስተዋላል። ይህም ለመድረክ ባላቸው እናሳ ግንዛቤ የመነጨ ነው። መድረክ የተሸለሪ የእምላክ ቦታ ነው። ስለሆነም የጌታ መልእክተኛ ሆነን መልእክት ልናቀርብ በቆምንበት ሥፍራ ሁሉ ትህትናን መጫማት ይናርብናል። በተጨማሪም በዚያ ሥፍራ እምላክ እዳማጭና ተመልካች ሆኖ ቢመጣ ሲለማቸውና ሲያያቸው የሚገቡ ነገሮችን ለማድረግ የተለናዱ ለምች መሆን አለብን። በእርግጥ ጌታ እንደዚሁ ሆኖ ልጆቹ ባሉበት ሥፍራ አለና በሁሉም በኩል ንቁና ጠንቃቃ መሆን ይናርብናል።

ሁልጊዜ በዚህ መንፈስ ለቦታው ትኩረት ካልለጠን ፈቃዳችንን እንጂ ፈቃዱን ለማድረግ አንተጋም። በንጹህ ፍርሃት ውስጥ ተገኝተን ለእኛም ሆነ ለሌሎች የምንጠቅም ጦልካም ነገር የምናፈስስ ለምች እንድንሆን ለመድረክ ጌታ የለጠውን ክቡር ፍቺ እንድንገነዘብ ያስፈልጋል። በዚህ ግንዛቤም እገልግሎታችንን በንጹሕ ፍርሃት ማከናወን እንዲቻለን ሕዝቡ እኛን ለመለማት በጉጉት በሚጠባበቅበት መድረክ ላይ በቅዱስ ፍርሃት መቆም አለብን። የእዲስ ኪዳን እማኞች ይኸኛው ቦታ ከዚህኛው ቦታ ለየት ባለ ሁኔታ የተቀደለ ነው ለሚለው መደምደሚያ እምብዛም እይጨነቁም። ይሁን እንጂ አምላክ በሕዝቡ መሐል እንዳለ እርሱን ሲጠሩት እንደሚመልስ ግን አጥብቀው ያምናሉ። ስለሆነም እርሱን ጠርተን ስለ እርሱ ለመናገር በቆምንበት ሁኔታ ውስጥ መንፈሳዊ ለዛ ሊርቀንና ደንታቢስነት ልንሆን እይገባም።

የውይይት ጥያቄዎች

1. ስለ መድረክ ክቡርነት በብሉይ ኪዳንና በእዲስ ኪዳን ያለውን ትርጓሜ አስረዱ
2. ቦታ በእዲስ ኪዳን ያን ያህል ሥፍራ እልተሰጠውም የሚለውን መደምደሚያ እንዴት ታዩታላችሁ?

2.3 ፕሮግራም መሪዎችና መድረክቻችን

የፕሮግራም መሪዎች ማለት ፕሮግራሙ በሚካሔድበት ዕለት የሚከናወኑ ድርጊቶችን በሙሉ ቅደም ተከተልና ውበት እንዲኖራቸው

የሚያደርጉ የስነ ሥርዓት ፓሊሶች ናቸው። ነገሮች በታቀደላቸው መለመር ለእዳማጮችና ለተመልካቾች ጸጋንና የአምላክን ሪድኤትን ይዘው እንዲፈሱ የጸጋው ምንጭ የሚፈለበትን ቦይ አስተካካይ ናቸው። ስለሆነም የሚዘመረው መዝሙር ÷ እዝማቾች ÷ የሙዚቃው ቅንብር በህብር እንዲፈሱ የመሪዎች አስተዋጽኦ የጎላ ነው። የሚመሩትን ህዝቡን ብቻ ሳይሆን በመዝሙሮችና በሙዚቃው ቅንብር ላይ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። ምክንያቱም የአምልኮ ጊዜ ላይ የሚከናወንን መንፈሳዊ ፕሮግራም መምራት ዜማውንና ቃላቶችን በተገቢው መንገድ ማጣመርን ይጠይቃልና። በእንቅስቃሴያቸውም ሁሉን አስተሳስረው ለምዕመናን መታነጽ ለአምላክ እክብሮት የሚያመጣ ፕሮግራም በእነርሱ አማካኝነት እንዲከናወን የበኩላቻውን ጥረት ያደርጋሉ።

አነቃቂ መሪዎች ባሉበት ሥፍራ ከእነርሱ እልፎ ወደ ጉባኤው የሚፈስስ ባርኮት እንዲዘንብ መሣሪያ ሆነው ያገለግላሉ። ለሕዝቡም ባላቸው እክብሮት ሕዝቡን ካለበት እሉታዊና የሚደብት ሁኔታ ያወጡታል። የአምላኪውን ሕዝብ ልቦና ያክበደ÷ ሐዘኑን ያበዛ ÷ ደለታውን ደግሞ የቀነለ ውስብስብ ችግሩ ተወግዶ ከእምላክ ጋር ትክክለኛ መንፈሳዊ ግንኙነት እንዲያደርግ ያግዙታል። አምላኪው ችግሮቹን ተሸክሞ ያየኖል ወይ? በሚል የውስጥ ጩኸት ውስጥ ሲሆን መንጥቆ የሚያወጣው እጅ እንዲታየው የእምልኮ መሪዎች ድርሻ ትልቅ ነው። የተሳካለቸው መሪዎች ለምችን ካሉበትና ከተጫናቸው ሁኔታ ወጥተው በተስተካከለ መንፈሳዊ አቋም ውስጥ እንዲገኙ የበኩላቸውን ያዋጣሉ። ምዕመኑን የሚያከብሩ ትህትና የተጫሙ አያሌ መሪዎች ያሉንን ያህል ምዕመናን ከማንገጠጥ እንስቶ ተራ ስድብና ዘለፋን በፑልፒት ላይ መፈጸም የማይለቀጥጣቸው መሪዎች ደግሞ ሞልተውናል። በአሁኑ ጊዜም እንዲህ ዓይነት ደፋሮች እየበዙ ስለመጡ ለእርማት እንዲሆን ተደጋግመው መድረኮቻችን ላይ ከሚፈጸሙ ጥፋቶች ጥቂቶችን ብቻ እንስተን እንነጋገራለን።

«ስድብ» (ምሳሌ 13:2-3 15:2-4)

የፐሮግራም መሪዎች የሚመሩዋቸው ሰዎች እነርሱ እንዲሚፈልጉት ላይሆኑላቸው ሲቀር የምእመኑን ስነ ልቡና የሚነኩ አያሌ ቃላትን ይጠቀማሉ። ከብስጭታቸውም የተነሳ የተሳደቡ የማይመስላቸው ብዙዎች ናቸው። ምግብ አልበላችሁም እንዴ? የእነ እገሌ ድምጽ ከእናንተ ይበልጣል። ልታመልኩ አልመጣችሁም እንዴ? ምን ትፈላለችሁ? ከእኔ ጋር ጌታን ማክበር የምትፈልጉ ቁሙ። ሌሎቻችሁ አትቁሙ። እንዳንዶቻችን እንዲህና እንዲህ ሰናደርግ ምንም አይመለሰን፣ እዚህ ግን እንፈላለን። የሚዘመረው መዝሙር እንደምንፈልገው ሳይሆን በታሳቅ ድምጽ እቁሙ !! እቁሙ!! እንላለን። አንዳንዴማ ደፋሮቹ እንዲህ ሲሉ ይሰማል «እንኳን ጌታን ኔኔን እንኳን ደስ አላሰኘኝም» እንላለን።

ከላይ የገለጽናቸው ጥቂቶቹ አባባሎች ስድቦችን የሚነሰጠባቸው መንገዶች ናቸው። ግማሹን በጥያቄ፥ ግማሹን በኃይለ ቃል እጅበን አያሌ ነገሮች ከመድረክ ስንወረውር የምእመኑ ትኩረት ወደ ሌላ ይዞራል። ምን ላደርግ መጣሁኝ? ዛሬ ደግሞ ፕሮግራም የሚመራው እገሌ ነው። እሱ ሲሆን ባልመጣ ይሻለኛል እስኪባሉ ድረስ ሰዎችን የሚዳፈሩ ጥቂቶች እይደሉም። ይህ እንዲወገድ በእንደበታቸው የሚቸገሩ መሪዎች ምላላቸውን ለእክብሮትና ምእመኑን በቃል ለሚደግፉበት ሁኔታ ሊያለለጥኑት ይገባቸዋል። በእግዚአብሔር ፊትና በተከበረ ሕዝቡም መካከል እንደቆሙ ለእፍታም እንኳን ሊዘነጉ እይገባም። በአንደበታቸው የሚቸገሩ ለሆች ቃላቸው ጥቂት ቢሆን ይመከራል።

መከፋፈል (ምሳሌ 10:19)

ሕዝቡን ወደ መንፈስ እንድነትና ትኩረትን በእምላክ ላይ ብቻ የማድረግ ሁኔታ ላይ ማምጣት የሁነኛ መሪዎች ዓይነተኛ ተልእኮ ነው። ይሁን እንጂ እንዳንድ መሪዎች ምዕመኑን በቦታ፥ በጾታ፥ በእድሜ ይከፋፍሉና አንዱ ይበልጣል ሌላው ያንሳል ሲሉ የሰውን ስነ ልቦና ይጎዳሉ። ያልተፈለገ ፉክክርም ለለሚጋብዙ ጉዳዩ እምልኮ መሆኑ ይቀርና ወደ ልምምድ ይቀየራል። ያኔ ሰው በእምላክ ፊት መሆኑን የሚያስረሳ ሁኔታ

ይፈጠራል። እንዲህ እንዳይሆን በመድረኩ የቆሙ መሪዎች ጠንቃቃ መሆን አለባቸው። መሪዎች መክፋፈልን ከሚጋብዙበት መንገድ አንዱ ደግሞ ሳይሰናዱ መጥተው ከምእመኑ በሚመጣ ምርጫ መዝሙር ማስዘመር ሲፈልጉ ነው።

በዚያ ጊዜ ለእነርሱ የሚመቻቸውን ወይም ደግሞ የሚያወቁትን እስኪያገኙ ምእመኑን የሚያዳርሱ መሪዎች አያሌ ናቸው። በዚህ ጊዜ ምርጫው የተመረጠሰት የተከበረ ያልተመረጠሰት የተተወ እንደሆነ ስሰሚሰማው የሚያሳድረው ስነ ልቡናዊ ተጸእኖ ቀላል አይደለም። በአንድ ወቅት የሚፈልገውን መዝሙር ስማግኘት ሰምርጫ ወደ ላይ የተሰቀሉ እጆችን አንተ፥እንቺ፥ እዚያ ማዶ፥ እዚያ ጋ፥ እርስዎ እማማ ወዘተ እያለ ሊያዳርስ ምርጫቸው የተተወባቸው እናት በብሽቀት መሪውን «እከካም» ብሰው ለመሳደብ እንደተነፋፉ እናስታውሳለን። ስለሆነም በርካታ ሰው ባሰበት ስፍራ ምርጫን ምን እመጣው? ከሆነ ደግሞስ የተመረጠወን የመጀመሪያውን ለምን አይወስድም? ስማዘመር እይመችም ካልንስ ምረው ለምን እንላለን? የማይሠራ እንደሆነ ከገባን ለምንስ እንጠቀምበታለን? ጉድስት ገዝፎ እንዳይታይና ትኩረት ከእምልኮ እንዳይዛባ በተቻለ መጠን መሪ ከፋፋይ ከመሆን እንዲጸዳ አስተዋይ ሲሆን ይገባዋል።

ተአማኒነት የሚያጓድሉ ነገሮችን መፈጸም (ምሳሌ 17:20 27)

እንዳንድ ጊዜ መሪዎች የሚያደርጉትን ሕዝቡ እንደሚከታተለው ይረሳሉ። ለእነርሱ ቀላልና የተለመደው ነገር ለእንዳንዶች ትኩረት የሚሰጡት ጉዳይ ነው። ለምሳሌ እንገቶቻችንን ዝቅ አድርገን እንጸልይ ይሉና በጸሎት መንፈስ አያለን ይህችን አዝማች እንዘምር ብለው ነገርየው ሲሞቅ ጸሎቱ ይረሳል። ከዚያ በእለቱ ወደታሰበው ሌላ መዝሙር በቀላሉ ይሻገሩና ያሉትን ያለመፈጸማቸው አይታወቃቸውም። በእዚህ ጊዜ ያሉትን እለማድረጋቸውን የሰማ ደግሞም ያየ መጠየቅ የሚወድ እእምሮ ይቸገራል። ሊመሩት በቆሙበት መድረክ ተመ፯ውን ያደናግሩታል። በዚህ ጊዜ መሪ ወይስ አደናጋሪ የሚል ጥያቄን እንዲጠይቅ ይገፋታል። ሌላ ጊዜ ማንም ሳያስገድዳቸው ይህችን እዝማች 3 ጊዜ ዘምረን እናበቃለን ብለው ሰጠኜም

አይመልሳቸው። በዚህም ድርጊታቸው ሁኔታዎችን በጽሞና መከታተል ሰሚከድ ለው ያልተፈሰገ ሥራ ይሰጡታል። ጌታን ሊያመልክ በመጣበት ቦታ የትዝብት መድረክ ይከፍቱሰታል። መሪዎች እንዲህ ያለውን ጥንቃቄ የጎደለው አደራረግ ቢያስወግዱ ሰአጻማጭም ሰተመልካች የሚበጅ ነገር ተከናውኖ አምልኮውም ይሳካል። አሰበሰዚያ ከአምላኪው ዘፊሱን ሳይወድ በግድ ወደ ታዛቢነትና ገምጋሚነት ሥራ ውስጥ ይገባል። ይህ ደግሞ ትልቅ ጉዳት ነው። ማስተዋል ከጎደሰው አደራረግ የተነሳ ሰምን ሰዎችን አናጣሰን? ሰምንስ ሰዎችን ወዳልተፈሰገ መስመር እንነዳሰን?

የሚያሰለች ድርጊት መፈጸም (ምሳሌ 30:33)

አምልኮን አታካች ከማድረግ የከፋ ድርጊት በሰንበት ቀን አይኖርም። አያሌ ሰዎች ወደ ጸሎት ቤት የሚመጡት በጉጉት ነው። ያንን ጉጉታቸውን ከሚቀንሱ ድርጊቶች መካከል አዝማቾችን በሚያሰለች መንገድ እየደጋገሙ ሰዉ አስኪደክመው መዘመር ነው። ሰዉ መሰሳቸቱን ለመግሰጽ የተሰያዩ ድርጊቶች ይፈጽማል። ቆሞ ከሆነ ይቀመጣል። ቁጭ ብሎም ከሆነ ያዛጋል፣ ወይም ሰዓቱን አሥሬ ያያል። እኛ ግን እንደ መሪ ሕዝቡን ስሰማናነብ ወይም በድርጊት ምሳሹ በለምንቆጣ ሕዝቡ የሚሰሳችበትን ነገር በማድረግ ሰመበቀል አንሞክራሰን። አንዳንዴ ሕዝቡ በግድ አንዲያጨበጭብ ሌላ ጊዜ «አንድ ሰው አንዳይቀመጥ» በሚል ማለጠንቀቂያ ፈቃዳችንን አንዲፈጽም አናስገድዳሰን። እንቀመጥ፥ አንነሳ የሚለው ተደጋጋሚ ትአዛዝ አምልኮ ለመምራት በተሰማራንበት ቦታ አዘውትሮ የሚያጋጥም ጉዳይ ነው። በዚህ የምናታከተው ሕዝብ ልክ የሰውም። ከሚያሰለቹ ድርጊቶች የሚደመረው ሌላው ነገር መፈክር መሰል ነገሮች ምአመኑ አብሮን እንዲል የምንለጠው ትዕዛዝ ነው። እኛ በምንፈልገው የድምጽ መጠን ማሰት ካቃተውማ የት ሊገባ?

አንድን ነገር ሰሰውጥ ያህል መደጋገም ነውር ባይሆንም እንግዶቻችን እስኪደናገሩ፥ ነባር ምዕመናን ምን ነካን አስኪሱ ድረስ መሪዎች እኔ የምለውን ያለ ማቋረጥ በሉ ማሰታቸው አለልቹ ነው። ይህ ደግሞ መወገድ ካለባቸው ድርጊቶች አንዱና ዋናው ነው። ሰዎችን ወደ አውነተኛ አምልኮ

የምንወለዳቸው በተሰየ የመንፈሰ ቅዱስ ረድኤት አንጂ አንደ ምትሃት ቃሳትን ዙሮ ጎሳ አንዲደጋግሙ በማስገደድ አይደሰም። አንዲህ አይነቱ ግዳጅ ሲበዛ ምዕመናን ይታከታሱ። አንዳናታክታቸው የሚጸየቋቸውን ነገሮች ማወቅ አስብን። ሰምሳሌ በቅርቡ በአንድ የአምልኮ ሥፍራ ሳይ መሪው ሰዎችን ደጋግሞ አንድን ቃል ደጋግመው እንዲሉ ሲጠይቅ ሕዝቡ ዝም በማሰት ተቃውሞውን ገሰጸ። ብዚህ ጊዜ ብስጭት ሞገባው መሪ «የአባቴን ወይም የእናቴን ስም የጠራሁ መሰሳችሁ ወይ?» የሚል ቁጣ የተቀሳቀሰበት ዘሰፋ ተናገረ። ምአመኑ አንዲሰሰቸን የሚያደርጉ፥ የሚያሰሰቹ ወይም የሚያታክቱ ድርጊቶች መፈጸም የሰብንም። ጠንካራ የተግሳጽ ቃሳት አንዲሁም የአነርሱን ስሜት ያሳገናዘበ ዘሰፋ የሚያሰለች ድርጊትን ከምንፈጽበት ሁኔታ ስለሚደመር ጠንቃቆች መሆን አስብን።

ምክትል ሰባኪነት (ገላ 5:22-23)

አንዳንዴ መሪዎች ሰባኪው የሚያጠግብ ነገር የተናገረ ካልመሰሰቸው የጎደሰውን ለመመሳት ይፈተናሱ። ወይም ደግሞ ሕዝቡ አይረዳውም ብሰው የሚሉትን አውነት ሰባኪው አንዳካፈሰ ከገመቱ ለሕዝቡ የመከሰስ አዝማሚያ ያሳያሱ። በተጨማሪም ሰሞኑን በውሰጣቸው ሊያውጠነጥኑት ከነበረው ጉዳይ ጋር በቀጥታ ግንኙነት አንዳለው ከተገነዘቡ ነገር ሁሱ በሁሰት ይጸናል ብሰው ያልተነካ የመሰሳቸውን ከፍል ለመጨመር ጥረት ያደርጋሱ። በሌላ ጊዜ ብዙ መናገር ልማድ የሆነባቸው መሪዎች ካሱ መቁረጫ የሌሰው ንግግር ያበዛሱ። አንደ ሰባኪው ያሰ ጊዜ ለሰማያገኙ በዕሰቱ አሰኝ የሚሱትን መልካም ነገር ተንፍሰው የመውረድ ፈተና ይደቀንባቸዋል። ከሳይ የጠቀስነው ጥቅስ ለሰምክትል ሰባኪነት ምን ይል ይሆን? ሰሚሱ አዚህ ጋ ማንሳት የፈለግነው ከመንፈሰ ፍሬዎች አንዱ የሆነውን «ራስን መግዛት» የሚሰውንና «ትአግስትን» ነው። ራሱን የሚገዛ መሪ ምክትል ሰባኪነት አይቃጣውም። ትአግስተኛም ጉድሰትን በጸጋ ያሳልፋል።

ራሳቸውን የማይገዙና መታገስ የሚያቅታቸው መሪዎች ሰምክትል ሰባኪነታቸው የሚሱት አያጠም። በአነርሱ አይታ በወረፋ የምትደርሳቸውን ጊዜ ጠቃሚ በሆነ ሁኔታ ጥቅም ሳይ ሰማዋል ጊዜውን እንደሰሩበት ያስባሱ።

ይሁን እንጂ ለእነርሱ የተሰጣቸው ቦታ የጎደለውን መሙላት ላይሆን የተሰናዳውን ማዕድ ማሳለፍ ነው። ከጨነቀው ሊጨንቀው የሚገባው ባለቤቱን ብቻ ሊሆን እንደሚገባ መረዳት አለባቸው። ከሁሉም የጎደለውን ለመሙላት ሲሞክሩ ወደ ባሻ ጠቅልሌነት እንዳያዘግሙ መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል። ስለሆነም መሪ መሪ እንጂ የየትኛው የፕሮግራም ዓይነት ምክትል እይደለም። መሪው ከምንም በላይ ፕሮግራሙ ስርዓት ጠብቆ እንዲፈሰስ ትኩረት ማድረግ አለበት። ወደ ምክትል ለባኪነት ራሱን ከቀየረ የፕሮግራሙን ውበት ይቀነሳል። ከመሪነት ወደ አደናጋሪነትም ዝቅ ይላል ማለት ነው።

ውትወታ

ብዙ ጊዜ ውትወታ ራሱን የሚገልጠው እንደ አሁድ ባሉ አብዛኛው ምዕመን በሚካፈላቸው መድረኮች ላይ እይደለም። አሁድ ከፕሮገራም በፊት ወይም ደግሞ ብዙሃኑ ሰመጻለይ በተሰበሰበት ቦታ ላይ እመራር እንዲሰጡ ኃላፊነት በተሰጣቸው መሪዎች እደራረግ ነው። መቼም ይህንን ምስባክ ላይ ከሚከናወነው ለይተን የምናይ አይመበለኝም። በቅርብ ጊዜ ከግማሽ ምዕተ እመት በላይ በቤተክርስቲያን ከቆየ አንድ አባቱ ጋር ስንጨዋወት ስለ እንደነዚህ ዓይነት መሪዎች አዝኖ እንዲህ አለኝ

> « በጉባኤ ጸሎትን በተመለከተ የማይገባኝ ሁሉም በየፊናው እንዲጸልይ መደረጉ ነው። የግል ጸሎት ከሆነ በቤቱ ወይም በቢሮው መሆን ነበረበት። በአንድ ክፍል ውስጥ ያለው ሕዝብ ለጥቂት ደቂቃ ጸልይ ይባላል። ሁሉም ለመጸለይ ሲንበረከክ ወይም ዓይኑን ሲጨፍን መረው ስብከት ይጀምራል (መውትወት ብሎው እመርባለሁ)። እርሱን ልስማው ወይስ ልጸልይ። እርሱ እየወተወተ ከአምላኬ ጋር መነጋገር አልችልም። አንድ የጸሎት ሃሳብ ሰጥቶኝ ዝም ቢል ጥሩ ነበር። ካንድ ሃሳብ ወደ ሌላ ሃሳብ እየዜደ ውትወታውን ይቀጥላል። በጸሎት ላይም እያሰን እንጸልይ ወንኖች እንጸልይ ይላል»[3]

ምእመናን እየጸለዩ ላለ እንጸልይ ወንኖች እንጸልይ እያሉ መወትወት ምን ማለት ነው? በዚህ ጉዳይ ላይ እስቲ ልባችንን እስተባብረን ዘአንድ ልብ

[3] Million Belete Informal Talk with the MK college staff : Addis Ababa Meserete Kristos College, June 2,2004.

እንጸልይ ብሎ መናገር የጠራ ነገር ነው። ግና እየጸለየ ላለ ለው ደጋግሞ እንጸልይ!! እንጸልይ!!! ማለት ምን ማለት ይሆን? ከላይ የተገለጸውን ዓይነት ምዕመናንን ግራ የሚያጋባ ድርጊት አብዛኛውን ጊዜ የሚታየው የጉባኤ ጸሎት ለመምራት ዘምስባኩ ላይ በሚቆሙ መሪዎች ነው። በየትኛውም ስያሜ መድረኩ ላይ ይቁመ መሪዎች ከአምላክ ለምዕመናን የሚፈለውን ዘረኩት ለማስተላለፍ ምቹ ሁኔታን መፍጠር እንጂ ማደናገርና የሕብረቱን ጊዜ የጭንቅ ማድረግ የለባቸውም።

ምእመናን ራሳቸውንና ሌላውን እየታዘቡ ጊዜያቸው በከንቱ እንደባከነባቸው ቆጥረው እንዲበሳጩ ፕሮግራም መሪዎች ምክንያት መሆን የለባቸውም። አንዳንዱም በተፈጠረው የማይገባ ነገር «የማይገባ ፍርድ ፈረድኩ ወይስ በእውነት ጸለይኩ?» እያሉ በበደለኝነት በሜት እንዲሰቃዩ ማድረግ የለብንም። እንደ ፕሮግራም መሪ በተቻለን መጠን ለእንዲህ ዓይነቱ ችግር መነሻ መሆን የለብንም። እስተዋይ" ጠንቃቃ ሆነን የጌታን ድምጽ እየሰማን ሕዝቡን ለመምራት ራሳችንን መስጠት ይኖርብናል። *ስለሆነም መሪ የምንሄድበትን መንገድ ሊያሳየን ፊት ፊት የሚሄድ አንጂ አደናጋሪ መሆን የለበትም። ለመሆኑ ዛሬ በጸሎት ቤቶቻችን የሞላው መሪ ወይስ አደናጋሪ?*

የውይይት ጥያቄዎች

1. በአናንተ አጥቢያ ያሉት መሪዎች ምን ዓይነት ናቸው? ከላይ የተገለጹትን ዓይነት መሪዎች በጸሎት ቤት እንዳናይ ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?
2. ስለመሪዎች የቀረበው ጉድለት ተጋንኗል ይልቁን በምልዓት አልተገለጸም ትላላችሁ? እንዴት?
3. እዘውትረው የሚታዩ የመሪዎች ድካም ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝሩና ተወያዩባቸው።
4. መሪ የተሳካላት እንዲሆን ምን መደረግ አለበት?

2.4 ዘማሪያንና መድረኮቻችን

አምላክ ረድኤቱን ለሕዝቡ ከሚልክበት መንገድ አንዱ ዝማሬ ነው። መዝሙር ዜማዊ መልእክት ነው። ዜማዊ ምስጋና ነው። ዜማዊ ጸሎት ነው። ዘማሪያን ደግሞ አምላክ ከፍ ከፍ አንዲል ሕዝቡ ልቡን ወደ ፈጣሪው እንዲያነሳ የሚላኩ የአምላክ መሣሪያዎች ናቸው። የእግዚአብሔር ቃል አዋጅ በዜማ ሲተላለፍ የብዙዎችን ትኩረት ይስባል። አንደውም አያሌ ግለሰቦች መደበኛ በሆነ መንገድ ቃሉን ከምስባክ ከመስማታቸው በፊት መልእክት የሚደርሳቸው በመዝሙር ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ዜማ ብዙ ሰው ቃሉን ሊገነዘብ በሚችል ሁኔታ ለመተረክ የሚያስችል ሶድልን የሚሰጥ ስኬታማ መንገድ ነው።

ዝማሬ ቃሉ በልባችን በቀላሉ እንዲለርጽ የሚያደርግ ለአምላካችንም የተጨበጠ ምላሽ እንድንሰጥ የሚያግዝ አገልግሎት ነው። አማኝን በትክክለኛ ግንዛቤ ለመቅረጽ ከምናቀርበው የእግዚአብሔር ቃል ትምህርት ባላነስ መንገድ ዝማሬ ሰነ መለኮታዊ አመለካከትን ለመቅረጽ የሚጫወተው ሚና በቀላሉ አይገመትም። ዜማ ወደ ሕይወታችን የሚጠልቅ ምግብ የምንቀበልበት መንገድም ጭምር ነው። ዘማሪያን በሚያስታላልፉት መልእክት ልዩ ልዩ ሚና ይኖራቸዋል።

ዘማሪያን እንደ ነቢይ ሊመጣ ያለውን የሚያመለክት መልእክት በማስተላለፍ ሰዎችን ያዘጋጃሉ። በዘመነ ኮሚኒዝም የተዘመሩ መዝሙሮች መልእክታቸው ይህንን የሚናገር ነበር። ለሕብረተሰቡ የድፍረት ንግግር ነቢያዊ ምላሽ የሚሰጡ መዝሙሮች እንደነበሩን እናስታውሳለን። ከሁሉም በላይ አብዮቱ እያለ ሲደነፋና ከእምነቱ ውጭ ሌላውን ያስጨንቁ ለነበሩ ከፍሎች ተግባራዊ ምላሽ ለመስጠት የተዘመረው አንድ መዝሙር እንዲህ የሚል ነበር።

ኢየሱስ ነው ከሁሉም በላይ /2/
አቻ የሌለው በምድር በሰማይ።

እውነት ነው ይህ መዝሙር በማንኛውም ጊዜ እውነት ነው። ውበቱ የጎላው ግን የሚበልጥ አሰን ብለው ከፉዎች ይደነፉ በነበረ ሰዓት የተሰጠ

ልባዊ ምላሽ ሰለነበር ጭምር ነው። ጉዳዩ ጠብያለሽ በዳቦ አልነበረም ግን ንጽሕና የተላበሰ የቅንነት ነቢያዊ ምላሽ ነበር። ወገኖች!! ከፋት አይሉ ነገር ተመሳቅሎ ግራ የሚያጋቡ ነገሮች በዝተው ሰነበረበት ዘመን ዘማሪያንና ዝማሬዎቻቸው ሕዝቡን ለጽናት የሚያበቃ ምርኩዝ የሚያቀብሉ ነበሩ። ለምሳሌ ድሉ የሶሻሊዝም ነው። ድሉ የእኛ ነው፥ እያሉ እሿፊዎች በከበቡን ሰዓት በሚዲያውም «የእኛ ነው ድሉ ድሉ/2/ በርቱና ታገሉ» በማለት ይሰፈፍ በነበረበት ጊዜ በተጨማሪም ተስፋ የሰም በተባለበት፥ ነገር ሰከበደበት ሰዓት «ድሉ የጌታችን ነው» የሚል ዜማ ተዚሟል። በዚያ ጊዜ የሚዜሙ ዜማዎች በሙሉ አማኙን በእምነት የሚሞሉ ፥ በብርታትና በጽናት ለእምነቱ እንዲቆም የሚያደፋፍሩ ነበሩ። ለምሳሌም ያህል የሚከተለውን ዜማ ይመልከቱ

ድሉ የጌታችን ነው ድሉ የአምላካችን /2/
ጠላትን ረገጠ አርነት አወጀ
ለኛ ለልጆቹ ማረፊያ አዘጋጀ
የጠላት ማሽኳኳት ድንፋታ
የሰልፍ የጦር ብዛት ጋጋታ
ለኃይሉ የሱሰ ምኑ ነው
ሁሉም በእጁ ነው።

ለመሆኑ ይህ ሁሉ ግፍ ሊፈጸም አምላክ አለ? የሚል ጥያቄ በተጠየቀበት ሰዓት አዎን አለ። እንዲሁም ነገሮች በሙሉ በእጁ ናቸው ብሎ ማዜም ታላቅ እምነትን ይጠይቃል። መዝሙር የሕይወት መስዋዕትነት የሚያስከፍል ከጠላት ጋር ፊት ለፊት እንድንፋለም የሚያግዝ ረድኤት የተቀበልነበት ዛሬም ቢሆን የምንቀበልበት መንገድ ነው።

ወቅቱን ያነናዘቡ ምእመኑን የሚያነቃቁ እንዲሁም የሚያደፋፍሩ አያሉ ዜማዎች ሕዝቡን ከጌታ ጋር እንዲጣበቅ አግዘዋል። በተጨማሪ የማያምነውን ጠርተዋል። ይህንን በአምንታዊ መልኩ ያስተናገዱ የምሥራቹን ቃል ተቀብለው ድነዋል። ምዕመናን ከኦጢዓት ጋር ፊት ለፊት እንዲጋፈጡና የሚከፈለውን ዋጋ እንዲከፍሉ የሚያነሳሱ ዜማዎች ተዚመው ብዙ አማኞች የልብ ድፍረት ሆናላቸዋል። ወዳጄ ደረጀ ከበደ

ሞት ላይቀር ዞሮ ዞሮ

ማለፍ ጀግነነት ነው ጌታን አለክብሮ
በዘፈን በዝሙት በተልከለከሰ
በብልጭልጭ ዓለም ጎሞት ከፈሰሰ
ያ ነው የሚያሳዝን አልባሌ አሟሟት
አለዚያ ድንቅ ነው ሰጌታ መለዋት/2/

በማለት የፍርሃትን ጥቁር ደመና የሚገፍ ድንቅ ዜማ አዜመ። በዚያም ብዙዎቻችን ላመንነው እውነት እንድንቆም አቅም ሆነን። ለምሳሌ ያህል ትዝ የሚሉን ጥቂቶች አነሳን እንጂ የመዝሙር ነቢያዊ አገልግሎት በዚህ የተወሰነ አልነበረም። ወዳጀ መጋቢ ተስፋየ ጋቢሶም

እምቢ አሻፈረኝ ለምበሰ አልሰግድም
ለሰው እጅ ሥራ አልንበረከክም
ከናቡከደነጾር የቁጣ ነበልባል
የማመልከው ጌታዬ በርግጥ ያድነኛል

በማለት ሲዘምር የጊዜው የዜማው መልእክት አዳማጮችን ለእውነተኛው የእምነት ተጋድሎ ያነሳሳ በጽናት ለተቀበሉት እውነት በመቆም ሕይወት እንዲመሩ ብርሃንን የለገሰ ነበር። የዕብራውያን ጸሐፊ እንዳለው « ስለ ጌዲዮንና ስለባርቅ እንዳልተርከ ጊዜ ያጥርብኛልና» (ዕብ 11:33) አያሌ መዘምራን እንደ ነቢይ ፥ ምስክርና አዋጅ ነጋሪ ድንቅ መልእክትን በማቅረብ ፊት ፊት እንደመሩን ማን እሌ ይላል? ማንበ ይህ አልሆነም ብሎ ለመናገር እቅም ያገኛል? በእገልግሎታቸው ተምረናል ፥ ተመክረናል ፥ ተጽናንተናል ፥ ታንጸናል እንዲሁም በደከምን ጊዜ ብርታትን ፥ በላትን ጊዜ እርማትን ፥ በጨለመብን ጊዜ ምሪትን ተቀብለንበታል።

በእሁኑ ጊዜ ደግም ምድራችን የፈለለው ዜማ እያሌ ወጣቶች በጌታ ቤት ተተክለው እንዲቆዩ ያደረገ የጌታ እጅ ነው። ከአንድ የእገልግሎት ስፍራ ወጥተን ግላዊ ጭውውት ስናደርግ ወንድሜ ጥሩለው ሽበሽና ባለቤቱ አዜብ በዘመናችን ስላለው የዝማሬ እገልግሎት እንዲህ አሉ« በደጅ ያለው ዘፈን ለሚትን የሚመስጥ፥ ትኩረትን የሚለብ ኃይል አበጅቶ ሲመጣ እግዚአብሔር አያሌ ዘማሪዎችን ባይለጠን ብዙ ወጣቶችን በጸሎት ቤት ማየታችንን

እንጠራጠራለን አለ።»[4] እውነት ነው ዘማሪን ብቻ ሳይሆን በልዩ ልዩ ተሰጥኦቸው የሚማርኩንን በርካታ መዘምራንን ጌታ ሰጥቶናል። ስለእነርሱም ልንባርከው ይገባናል።

ለዘዝማሬ እና ዘማሪያን መልካም እገልግሎት ስንቱ ተብሎ ይዘለቃል? ይሁን እንጂ ሁሉም ዘማሪዎችና ዘማሪያን ባሬ በምዕመናን ሕይወት ላይ ከላይ የገለጽነውን ዓይነት ጠቀሜታ አላቸው ብሎ ማሰብ አይቻልም። ስለሆነም ሊታረሙ ይገባል የምንለውን አሰታዊ ገጽታዎች በተለይም ከምለባከ አገልግሎት ጋር በቀጥታ የሚገናኘውን አንሱተን እንነጋገራለን። ወቀላው ለእርማት እንጂ ለማላጣት አይደሰም። ተግላጹ ለውበት እንጂ ለውርደት እንዲናገር አንሻም።

ዘማሪያን ከላይ የገለጽነው ድንቅ ተልእኮአቸውን አንዳንድ ጊዜ ይዘነጉትና ለምችን ለማስደሰት ሲደክሙ ላምላክ ክብርን ከሚያመጣ ዘማሪነት ሰለው ደስታ የሚያዜሙ አዝማሪ ወደ መሆን ዝቅ ይላሉ። በዝማሬ በኩል ያለውን ጥንካሬና ድካም መተንተን የዚህ ጽሁፍ ትኩረት አይደለም። ከመድረክ ጋር በሚገናኝ ገጽታው ብቻ በዚህ ክፍለ ጊዜ ልናነሳው እንገደዳለን። በመድረኮቻችን ብቅ ቢሉ የምንመርጣቸው ዘማሪዎች እንደ ቃሉ የሆኑ፥ በቃሉ የተገሩ ፥ቃሉን የሚያንጸባርቁና ጌታን የሚተርኩ ቢሆኑ ነው። ይመድረኩ ላይ ሥፍራን የምንለጣቸው መዘምራን ወደ እምላክ የሚያስጠጉን ምሳሪያዎች መሆናቸው የሚመረጥ ነው። ዘማሪያን ተዋንያን ሳይሆኑ የእምላክ መልእክተኞች ሆነው የተቀበሉትን ሲያቀብሉን እንታነጻለን። ከዚያ ያፈነገጠ ሥራን ለመሥራት ሲደክሙ ግን አነርሱ ሞተው እኛንም ወደ ሞት ምንደር የሚጎትቱ የሞት ሙሾ ደርጻሪዎች ይሆናሉ። ይህ እንዳይሆን ግን ያሚከተሉት ከመድረክ ጋር የተያያዙ ድካሞች እንዲወገዱ እንጠቁማለን።

ለህብር ያለመጠንቀቅ (ፊሊጵስዩስ 2:2)

ብዙ ጊዜ ለባኪው በልብህ የመጣውን እካፍለን እንደሚባል ዘማሪውም ጌታ ያሳለበህን ይባላል። ታዲያ ለሚዎቹ ያሉበትን ሁኔታ ጀሳገናዘበ እንዲሁም ከዕለቱ መልእክት ጋር ያልተቀናጀ መዝሙርን ማዜም

[4] Tirusewe Shebeshi Interview August 20, 2004

በአብዛኛው ዘማሪ ላይ የሚታይ ጉድለት ነው። ዘማሪያን በተለይም ሶሎ የሚለጠት መልእክትን ካዳመጡ በኋላ ያንን ተከትሎ የሚፈሰ መዝሙር ማዜም መልእክቱን ለማጽናት እንደሚበጅ መረዳት ይኖርባቸዋል። ሰባኪው ስለ ንሰሃ ሰብኮ ዘማሪያን በእነርሱ ጊዜ ሕዝቡን ወደ ምስጋና መጎተት ያልተገባ ድርጊት ነው። ተቃራኒ ነገር ለመፈጸም የሚቻለው ሰባኪው ያልተሳከ እንደሆነ አርግጠኛ የሚሆኑበት ምሪት ያገኙ እንደሆነ ብቻ ነው።

መድረኩ ላይ እነርሱና ሰባኪው የተጣላ መልእክት አስተላልፈው ምእመኑንም ግማሽ ለዘማሪው ግማሽ ለሰባኪው ሆኖ እንዲሄድ መገፋፋት አግባብ አይሆንም። ሶሎ ዘማሪዎች ይህ ኃላፊነት እለባቸው የሚባለው መልእክት ከሰሙ በኋላ ከመልእክቱ ጋር የሚቀናጅ መዝሙር ለመዘመር ዕድል ስላላቸው ነው። አርግጥ ነው ዘማሪዎችም ጌታ የሰጣቸው የራሳቸው የጊዜው መልእክት ሲኖራቸው ይችላል። ግና በአንድ አሁድ ወይም በአንድ ከፍለ ጊዜ ሁለት የሚጣሉ ወይም የሚቃረኑ መልእክቶችን ከመስማት አንድ ጠንካራ መልእክት ለማስተላለፍ ከሰባኪውና ፕሮግራሙን ከሚያቀናጁ ሰዎች ጋር መመካር ጥሩ ነው።

ለመመካከር የተፈጠረውን ዕድል አግኝተው የማይጠቀሙበት ይልቁንም የራሳቸውን ብቻ ብለው የሚሄዱ ዘማሪያን እያየን መጥተናልና ይህ አንድነትንና ሕብርን የሚያናጋ እካሄድ ይታረም ነው የምንለው። መዘምራን በዜማ ቃሉን ማስተላለፋቸው እንደ ተጠቀበ ሆኖ ከተሰጣቸው ተልእኮ መካከል ሕዝቡን ለቃሉ ማዘጋጀት ና ቃሉ ከተሰበከ በኋላም ቃሉን ማጽናት አንዱ እንደሆነ ሊጠፋቸው አይገባም። ከዚህ መለመር ሲያፈነግጡ በልብ የተዛራ ቃልን ለመንጠቅ የምዕመኑን ትኩረት ለማዛባት ሞከረዋልና አይበጁንም። ከማስተዋል መንገድ እየራቁ በመዜዳቸው ተልእኮአቸው ከግንባታ ይልቅ እፍራሽ ይሆናል። ይህ አንዳይሆን ግን በተለይ ሶሎ የሚዘምሩ ሰዎች ለሚያመልኩበት አውድ ተገቢ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል። ፕሮግራም የምናቀናጅም ሰዎች በዚህ መንገድ አነርሱን መደገፍ ይኖርብናል። ብንችልም የዕለቱ የመልእክት ከፍል ምን እንደሆነ ቀደም አድርገን ብንነግራቸው ወይም ከዕለቱ መልእክት አቅራቢ ጋር ብናገናኛቸው በሀብር እንዲፈሉ እንረዳቸዋለን።

አርግጥ ነው የእምልኮ ፕሮግራም ቅድሚያው ለአምላክ ነው። ዘማሪዎችም በዜማ ሲያመሰግኑ በልባቸው ያለውን አድናቆት የሚያቀርቡት ለአምላክ ነው። ይሁን እንጂ ሊያዳምጧቸው ለተሰበሰቡም ለምኞ በዜማ መልእክት ይተላለፋል። መልእክቱን ያጸናሉ ስንል አድራሻው ሰባኪው ብቻ እንደሆነ ካሰብን እንቸገራለን። በቃሉ በዋነኛነት እግዚአብሔር ይናገራል ቀሚለው ግንዛቤ የወንጌል አማኞች ሁሉ ነው የሚለውን ከተቀበልን ቃሉን ያጸናሉ ስንል ለሰባኪው ቲፎዞ ይሆናሉ ማለት አይደለም። ይልቁንም በእለቱ ከአምላክ ለሕዝቡ የተላከው ቃል በምእመኑ ውስጥ እንዲሰርጽ የበኩላቸውን ያዋጣሉ ማለታችን ነው። የዕለቱ አምልኮ መካከለኛ ቃሉ ስለሆነ÷ እግዚአብሔርም በቃሉ ያነጋገረናል ስለሚባል መዘምራን መልእክታቸውን ከእለቱ ከፍል ጋር ማቀናጀታቸው ሁሉንም ይጠቅማል።

ጊዜን ማባከን (ኤር8፡7)

ድሮ ድሮ ዘማሪያን የተመደበላቸውን ጊዜ ተጠቅመው በዜማ መልእክታቸውን አስተላልፈው ለመልእክተኛው ምቹ ሁኔታ ይፈጥሩ ነበር። ዛሬ ዛሬ ግን አነርሱው ራሳቸው ለፕሮግራሙ የተመደበውን ጊዜ እየጠቀሰሱ ወስደው እንዳሻቸው ማድረግን እየለመዱት መጥተዋል። አንዳንዶቹ ሕዝቡን የግል መዝሙራቸውን ሲያስጠኑ ያሉበትን ሁኔታ ይረሳሉ። እንደውም የዘማሪ ቡድን የሚያስጠኑ አስኪመስላቸው ድረስ ሕዝቡን ይጫኑታል። ሕዝቡም እየተሳተፈ ለሚከናውን ድርጊት ትኩረት ስለሚሰጥ የቃሉ ጊዜ መጥጥ ተደርጎ ይወሰድና ሰባኪው ላይ ብዙ ጊዜ እላስፈላጊ ጫና ይፈጠራል። በዚህ አኳያ ዘማሪያን ስለ ጊዜ አጠቃቀም ተገቢውን ግንዛቤ እንዲያገኙ በመርዳት ወረራ የተፈጸመበትን የሰባኪውንና የዕለቱን ጊዜ ነጻ ማውጣት ይገባል። ዘማሪዎች በታቸውን እንዲያውቁ መደረግ አለበት። ያኔ ጊዜው ከመባከን ይድናል።

ሞራላዊ ችግሮች (1ተሰ 4፡ 3 - 6)

በአሁኑ ጊዜ በአብዛኞች የሚፈለገው ለሜትን የሚከረከር ሲሰማ ደስ ደስ የሚል የሚንቆረቆር ዜማ ማዳመጥ ስለሆነ ችግር እንዳለባቸው እንኳን

እየታወቀ ብዙ ሶሎ ዘማሪዎችን መድረኮቻችን ያስተናግዷቸዋል። «የዘማሪን ዜማውን እንጂ ሕይወቱን አትዩ» እየተባልንም ነው። ምስባኮቻችን ይህንን ፌዝ በመታገስ አቀጠሉ ሞት እይቀሬ ነው። ስለሆነም ዘማሪዎች የሞራል ብቃት እንዲኖራቸው ምስባኮቻችን በባህሪያቸው ለማንቀበላቸው÷ ምላሌነት የጎደለው ሕይወት ላላቸው ክፍት መሆን የለባቸውም። ያንን በማድረግ ሕዝባችንን አተጋቦት ሞራላዊ በሽታ እንታደጋለን። በተጨማሪም ስለሞራላዊ ችግር ስንነጋገር ጎላ ብሎ የሚታየው የዘማሪዎች ችግር ጥቅም የሚያባብላቸው ሆነው እየታዩ መምጣታቸው ነው።

በቅርብ ጊዜ ለሁለት ዘማሪዎች ፕሮግራም ለማስያዝ ከገጠር የመጣ አንድ ሰው ሁለት ሶሎ ዘማሪያን ሲያነጋግር አብሬው ነበርኩኝ። ስአነርሱ ጋር የሚግባባበትን ንግግር ከጨረሰ በኋላ «ብሉ አጅንዳችሁ ላይ በእስክሪብቶ ጻፉልኝ» አለ። ለምን አንዲህ አልክ? ስለው በእሁኑ ጊዜ ዘማሪዎች ፕሮግራም ስታሲዛቸው በእርሳስ ክጻፉ በቀላሉ በላጲስ ያጠፉታል። በተሰይ አማራጩ ግብዣ የመጣው ሞቅ ያለ የፍቅር ስጦታ ክሚሰጥ ቡድን ክሆነ አሰቀልህ አለና አላቀኝ። ከጥቂት ደቂቃ ላቅ በኋላ ልቤ በሃዘን ተመታ።

ብዙዎቻችን እንዲህ ዓይነት ታሪክ ስንሰማ ፈራጅነት ቶሎ ይመጣብናል። ለምን እንደዚህ ሆኑ ብለን አንጠይቅም። ብዙ ዘማሪያን ለሕዝቡ የባርኮት ምክንያት ሆነው ካገለገሉ በኋላ የሚራቡ ÷ የሚታረዙ አንዲሁም ጫማቸውን አንኳን መቀየር የሚላናቸው እንዳሉ ለምቹ ልቤ ተሰበረ። አብዛኞቹ የሚያስቡላቸውን የሚፈልጉት ብዙዎቻችን ስለ አነርሱ መሠረታዊ ፍላጎት ደንታ ቢስ ለሰሆንን ነው። እዘውትረን ከፈለግናቸው በኑሮ ስለ ሚጎድላቸው ነገር ሲገደን ይገባል። በእርግጥ ዘማሪን የሙሉ ጊዜ ዘማሪ አድርጎ መጥራት ያለቸግራል። ሆኖም ግን አያደግን ስንመጣ በአንዳንድ የበለጠጉ አገሮች እንደሚደረገው የዜማ መጋቢ (Music Pastor or Worship leader) ልንጠራና ዘማሪያንን በዚያ መልኩ ልንጠቀምባቸው አንችላለን። በቤተ ክርስቲያናት ለሙሉ ጊዜ የቃሉ አገልጋይ ቀለብ እንደምንሰፍር እብዛኛ ውን ጊዜ በቤተክርስቲያን እካባቢ ለሚያሳልፉና ሥራቸውም በዚያችው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሆኖ ባለን ፍላጎት ሲያግዙን ይችላሉ የሚባሉትን አየሠሩ አንዲያገለግሉን ልንጠራቸው አንችላለን።

በተጨማሪ ልዩ የመዝሙር መሣሪያ ተሰጥኦ ያላቸውና በዚህ መንገድ ባሰለፉ ይጠቅሙናል ለሚባሉ ዘማሪያንን መደገፍ በመሪዎች ክታመነበት ለአንዳንዶች እንደ መፍትሔ ሊያግዛቸው ይችላል። እየዞሩ ለሚያገለግሉና በአንድ አጥቢያ ውስጥ ለሚኖር መንፈሳዊ እገልግሎት ትኩረት ላይሰጡ ብየተጠሩበት የሚሄዱትን በገንዘብ ማገዝ ለቤተ ክርስቲያን የአፈጸጸም ችግር ያስክትልባታል። ምክንያቱም የሚያስተምሩትን÷ የሚጸልዩትን ÷ በተመሳሳይ መልኩ መያዝ አለባትና። በዝማሬ እየዞሩ ለማገልገል ሽክም ያላቸውንና ጸጋቸው የተለየውን ዘማሪያንን በየቤተ እምነቱ ከጎብኚና ከተዘዋዋሪ መንፈላውያን ጋር በማቀናጀት በጸጋቸው እየተጠቀመ እነርሱንም መደገፍ ይቻላል። ሁሉም ይህንን መንገድ ስለማይመርጡት የዝማሬ አገልግሎት እያያገዝ በጥንቃቄ መጤን ያለበት ይመስለኛል።

ብዙ ጊዜውን ጸሎት ቤትና አካባቢው ለሚያሳልፈው ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ቀለብ የመስፈር ግዴታ አለባት ብሎ ማሰብ ያስቸግራል። ይሁን እንጂ ዘማሪውን ሁልጊዜ እየፈለግነው ለፍላጎቶቹ ደንታ ባይኖረን አስቸጋሪ ይሆናል። ስለዚህ ከላይ አንዳልኩት ተገቢው የማጥራትና የማጥለል ሥራ ተስርቶ ለሙሉ ጊዜ እገልጋይ ቀለብ አንደምንሰፍር ለሙሉ ጊዜ ዘማሪ ቀለብ ብንሰፍር ይህ ችግር ይቀረፋል ብየ እምናለሁኝ። በዜማቸው ተባርከን የኛን እርዳታ በሚሹበት ሰዓት ግድ ባይኖረን መጠን እንደምንጥለው ሽንኩራ አደረግናቸው ማለት ነው። ዘማሪያንም በበኩላቸው ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት እንዳልተጠሩ ከባቸው የራሳቸውን ጥረት ጨምረውበት እየሠሩ ጌታን ቢያገለግሉ ለብዙዎች በምሰሌነታቸው ይጠቅማሉ። ክአንዱ ፕሮግራም ሳይጨርሱ ወደ ሌላው በመሮጥ በክፉ ከሚታዩ ሰርተው ራሳቸውን በመደገፍ ፊጋ ያለ እገልግሎት ቢፈጽሙ ይጠቅሙናል።

ብዙ የሶሎ ዘማሪዎች ዛሬ ባለቤት የላቸውም። እንደውም በየት ወጣችሁ? በየት ገባችሁ? የሚላቸውና ፍላጎቶቻቸውን ለመድረስ ጥረት የሚያደርግ የለም። ክዚህ የተነሳ ሲቸገሩ አንዱ በእርሳስ ሌላ ጊዜ በእስክሪቢቶ ጽፉ ብለን ለምን እንወቅላቸዋለን? ችግራቸው አንዲቀረፍ በሚገባን መንገድ ልንረዳቸው ይገባን የለምን? ሁሉንም ዘማሪዎች የሙሉ ጊዜ ዘማሪ አድርጎ ለመጥራት አይቻልም። ምክንያቱም ላምንቱን በሙሉ ዘማሪዎችን የሚይዝ የዝማሬ ፕሮግራም ማደራጀት እይቻልምና። ይሁን እንጂ ዘማሪዎችን ብቻ

ላይሆን በየአጥቢያዎቻችን ሥራ አጥተው በኢኮኖሚ ድቀት የሚማረሩትን በሙሉ ለመደገፍ እንዲቻል ሠርተው የሚኖሩበትን መንገድ ቢጋራ ብንፈልግ ችግሩ ይቃለላል የሚል እምነት አስኝ። እነርሱም ሥራ ሳይኑ እየሠሩ በትርፍ ጊዜአቸው ጌታን ለማገልገል ቢተጉ ጌታ ይባርካቸዋል።

ከዘማሪ ጥሩሰው ጋር ባደረግሁት ውይይት የገባኝ አንድ ነገር አያሌ መዘምራን ነገ እንደሚያስጨንቃቸው ነው። በመድረክ ላይ ቆመው ባርኮታቸውን ሲያፈሱልን ደስ እንዳለን የእነርሱ ደስታ እንዲበዛና የሚያስራቸው ነገር እንዲከለከል እጥቢያ ቤተክርስቲያናት ተገቢውን ርምጃ መውሰድ አለባቸው። በዜማቸው የተባረክን ሁሉ ልንማልድላቸው ይገባል። እነርሱም በለ ችግራቸው ደፍረው ሲነግሩን ይገባቸዋል አላለሁ። ሁሉን ልናውቅላቸው ባለመቻላችን ከሚከፋ ግልጥ ሆነው ራሳቸውን ሲያሳዩን ይገባቸዋል። ለለ ሶሎ ዘማሪዎች የምለው ሌላ ነገር ደግሞ በውጫዊ ዝነጣችሁ የሚጎድላችሁ ለለ ማትመስሉ ብዙዎቻችን ታሳስታላችሁና እናንተ ሶሎ ዘማሪዎች ትክክለኛ ሁኔታችሁን በማላወቅ እርዱን ነው። ነገራችሁን ተረድተን ለጋራ ችግራችን የጋራ መፍትሔ በመፈለግ የእቅማችንን ያህል እንኳን እንድናዋጣ እግዙን። አሲያ ሳንረዳችሁ፥ ሳትረዱን ዘመናችን ይረዝማልና ግልጽ ሁኑ ብየ እግረ መንገዴን ማሳሰብ አፈልጋለሁ።

ተአማኒነትን ማጓደል

ምእመናን «እገሌ ዛሬ መጥቶ ያገለግላቸኋል» ተብለው እገሌ በምለባቸ ላይ ሲጠበቅ የሚቀርበት ጊዜ ብዙ ነው። እርሱን/እነርሱን ስንጠብቅ በእሱ/እነርሱ ወረፋ ባዶ ምለባክ የሚያስታቅፉን ጥቂቶች አይደሉም። ከለቅም በላይ ችግር ገጥሞ ለመቅረት ሲገደዱ የገጠማቸውን ተናግረው ምእመኑ እንዲጸልይላቸው ማድረግ የተገባ ድርጊት ነው። ይሁን እንጂ አጥጋቢ ምክንያታቸውን እንኳን ሳያሳውቁ የሚቀሩ ልክ የላቸውም። እገሌን ፈጽሞ እንጠራም ብለው ሲማረሩ ያየኋቸው የምለባክ ኮሚቴ አበተባባሪዎች ብዙ ናቸው። እንደውም ቁጥራቸው ከእምለት የማያንሱ ከአዲስ አበባም ሆነ ከገጠር አካባቢ ያሉ መሪዎች እገሌ አለደግፎን ቀረ ብለው በምሬት ሲናገሩ ለምቼአለሁኝ።

ባልተጋበዙበትና ባልተለናዱበት ሁኔታ ከመድረክ ወጥተው እንግዲህ ዛሬ ዘማሪዎቹ እኛ ነን ሲለ ምእመኑ የሚለማበት ጉባኤ ብዙ ነው። ይህም የሚሆነው ታማኝነት በሚያንድሉ የለሎ ዘማሪዎች ምክንያት ነው። ሁሉም እንዲህ ያደርጋለ ብሎ ጨዋዎችንና ጠንቃቆችን ጨምሮ መጨፍለቅ የሚገባ አይሆንም። የዚህም ጽሁፍ ትኩረት ንጹሃንን ማሳጣት አይደለም። ንጹሕ ዘማሪያን የውለጥ ጥንካሬና ድፍረት የሚያገኙት ከጸዳ አረማመዳቸው ነው። እንዲህ ዓይነቱም ወቀሳ እነርሱን በቀጥታ ለለማይመለከት ራሳቸውን መኮነን የለባቸውም። ይሁን እንጂ አብረዋቸው በተለለፉት እምነት አነዳዮች ምክንያት ግን መነካታቸው አይቀርም። አብረዋቸው የተለለፉትን ለታማኝነት ማነሳሳት አለባቸውና።

የመዝሙሮች ጥልቀት

ስምንጊዜውም በላይ ሚዳዊ መዝሙሮች እየሰማን ያለንበት ጊዜ ቢኖር አሁን ነው። ይህም የሆነው ዘማሪዎችን አሳደግን የምንባል የቃሉ አገልጋዮች/መጋቢያን መዝሙራቸው ጥልቀት እንዲኖረው የበኩላችንን ለላዋጣን ነው። ለለሆነም በአንድ አቅጣጫ ብቻ ያጋደለ መዝሙርን እንለማለን። ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን በመዝሙራቸው የሚለብኩን ዘማሪ ለባኪያን በዛሬው ጊዜ ማግኘት ብርቅ ነው። የምንፈልገውን የሚሉልን አላጣንም። ነቢያዊ ተልእኮአቸውን የሚወጡ ጠንካራ መዝሙሮች ግን ርቀውናል። ለለሆነም መድረኮቻችን ሕብረ ቀለም በጎደለው አንድ ወጥ የዜማ ቀለም በማስተናገድ ወደ ተራነት ዝቅ ያሉ ይመስላል። ይሁን እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክቶች ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ያቀናጁ መዝሙሮች ስመድረክ ቢፈለ መዝሙር ለሁለንተናዊ እድገት የበኩሉን ያዋጣል።

ለለሆነም ዜማና ግጥሞቹ ሊታለበባቸው የሚገቡ የቤት ሥራዎቻችን ናቸው። የእኛን ሁኔታ እያዩ የሚዘምሩልን ዘማሪዎች እየበዙ የመጡበት ጊዜ እንደዚህ ዘመን የለም። ለለሆነም ከጌታ የሚላኩ የዜማ መልእክተኞች ይልቅ እኛን ለማዝናናት የተለለፉ እዝማሪዎች በዝተዋል። ***ለመሆኑ ዛሬ መድረኮቻችን በብዛት የሚያበተናግዱት ዘማሪ ወይስ አዝማሪ?*** ይህ ቃል ድፍረት የሞላበት ሌላውን ለማሳጣት የተነገረ ቃል አይደለም። ልባዊ ጥያቄ

ነው። «ለጌታ ከብር ነው የምዘምረው፥ አገልግሎቴ አንዳች ጉድለት የሰበትም» የሚሉትን አይመለከታቸውም። ጥያቄ የወደቀበት አገልግሎት የሚያገለግሉትን ግን ይጠይቃል።

የወይይት ጥያቄዎች

1. በዘማሪዎቻችን ላይ የምናየው ጉድለት ሲወገድ የሚችለው እንዴት ነው?
2. የሙሉ ጊዜ ዘማሪን ለመጥራት አብያተክርስቲያናት ትኩረት ያልሰጡት ለምንድንነው?
3. እዚህ ከተጠቀሱት ሌላ ዘማሪያን የሚታይባቸው ገድለቶች ምንድን ናቸው? በዝርዝር ከመዘገባችኋቸው በኋላ ችግሩ እንዴት እንደሚቀረፍ ተወያዩባቸው
4. በአሁኑ ጊዜ የዘማሪዎች ባንድ ተቋቁሟል፤ ከዘፋኞች ባንድ የሚለየው በምንድነው?
5. ዘማሪዎች ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያካትት መዝሙር እንዲያቀርቡ ምን መደረግ አለበት?
6. የዜማ መወራረስ የሚወገደው እንዴት ነው?
7. ቤተ ክርስቲያን ለዘማሪዎች የተሻለ ትኩረት ልትሰጥ የምትችለው እንዴት ነው?

2.5 የቡድን ዘማሪያንና መድረክቻችን

ምስባኩ ከሚያስተናግዳቸው ከፍሎች መካከል የቡድን ዘማሪያን መኖራቸው በሁላችን ዘንድ የታወቀ ነው። የተሰጣቸውን መልእክት በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ ሲያስተላልፉ ሰብዙዎቻችን ባርኮት መሆናቸው የታወቀ ነው። አያንዳንዳቸው የድምጽ ዐታቸውን ጠብቀው በጎብር የተሰጣቸውን መልእክት በዜማ ሲያስተላልፉ ሁላችን ውስጥ የሚቀርልን ድንቅ መልእክት ይተላሰፋል። በብዙ ቁጥር ተቀናጅተው እንደ አንድ ሰው መልእክት ለማስተላለፍ መተሳሰር በራሱ ድንቅ መልእክት ነው። ዘጎብር

ሆነው የዜማ መልእክታቸው በደንብ ከተላላፈ ልፋታቸውና ሰመተሳሰር የነፈሱት ዋጋ በተግባር ይታያል። ከአንድ በላይ ሆኖ በሕብረት የሚሠራን ሥራ የማቀናጀቱ ጉዳይ ምን ያህል አድካሚና የሚያሰፋ እንደሆነ ሰብዙዎቻችን የተሰወረ አይደለም። የቡድን መዘምራን በተዋበ ቅንጅት መልእክታቸው ሰተቀባዩ ሲያደርሱ የቤተ ክርስቲያን አባላት ይነቃቃሉ፥ ይበረታታሉ፥ ይታነጻሉም።

ይሁን እንጂ የቡድን መዘምራኑ በዜማ የሚያስተላልፉትን መልእክት ሰማሰተላለፍ መድረክ ላይ ቆመው መቀናጀት ሲያቅታቸው ሲታይ ለተገልጋዩ ጥሩ አይደለም። ስለሆነም ልምምድ አንሶአቸው በአደባባይ ተዝረክርከው ሲታዩ ሲያመልኩ የታደመ አባላት ያፍራሉ። ስለ አነርበም ይሳቀቃሉ። ይህንን ሰማሰወገድ ተገቢ የዝግጅት ጊዜ በመወሰድ የቡድን መዘምራን ሰመዘመር በሕዝቡና በጌታ ፊት ከመውጣታቸው በፊት ተገቢወን ጥንቃቄ ቢያደርጉ መልካም ነው።

በቅርብ ጊዜ በአንዳንድ አዳዲስ የቡድን መዘምራን እየታየ የመጣው ልምምድ ግርታን እየፈጠረ ነው። የፕሮግራሙ መሪ አሁን ጊዜውን ሰመዘምራንና ሰጌታ መንፈስ አተዋለሁ ብሎ ሰመዘምራኑ ከሰጣቸው በኋላ ከቡድን ዘማሪዎች አንዱ መናገሪያውን ተቀብሎ ሰፋ ያለ ንግግር ያደርጋል። ከዚያም አንጸልይ ይልና ሰፋ ያለ ጊዜ ይወስዳል። ከእነዚህ አዳዲስ መዘምራን መረዎች አንዳንዶቹም መልእክት አለን ይሉና ብስለት ያነበው ከወቅቱ ሁኔታ ጋር የማይሄድ ነገር ሲያስተላልፉም ይታያል። በተጨማሪ ኳየሩ ራሱ ተሰማምዶ የሚዘምራቸው መዝሙራት ሕዝቡ ጋ ደርሰው በኳየሩ የሚጠበቀውን ዓይነት ስሜታዊ ምላሽ ካላስገኙ፥ ሕዝቡ የሰመዳቸው የሶሎ መዝሙሮች ይመረጡ (ይወሰዱና) ሰማድመቂያነት ይውላሉ።

ከዚያም የመዘምራን ቡድኑ ጊዜውን ይቆጣጠርና ሌላ ረዘም ያለ ጊዜ ይወስዳል። ይህን የሚያደርጉት ከቡድኑ የተወከሉት አባላት በመፈራረቅ ነው። እንዲህ በመደረጉ በጊዜ የተደራጀው ፕሮግራም መፋሰስ ይገጥመዋል። እንዳንዱም የቡድን መዘምራን ያደርጉታል ብለን በማንጠብቀው ዓይነት የተራዘመ ጸሎት ውስጥ ያቆዩናል። ይዘምራሉ ተብሎ ግብጥ የተሰጣቸው ጊዜውን ወደ ተራዘመ ጸሎት ሲቀይሩት በአንዳንዶቻችን ዘንድ ግርታ

ይፈጠራል። የሚጨበጥ መልእክት ቢተላለፍ ባልከፋ ግና ጊዜ መፍጀት ብቻ ሲሆን ሰምን? ያለኛል።

ቀደም ባሉት ዓመታት ፕሮግራም መሪው አስጸልዮ፡ አገልግኝ ዘምረን፣ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ለምእመኑ የሚደርሱ መልእክቶች ከተላለፉ በኋላ በቀጥታ ወደ ዝማሬ አግልግሎት እንሄዳለን። ታዲያ በዚያ ጊዜ ከመድረኩ እንጸልይ የሚሰው ይፋዊ ጥሪ በድጋሚ የሚቀርብልን ሰባኪው ሲመጣ ብቻ ነበር። አሁን አሁን ደግሞ ዘማሪያን አስጸልየውን ዝማሬያቸውን ሲቀጥሉ ይስተዋላል። በጸሎት መንፈስ ዝማሬውን እንስማ የሚል ግብግ ተደርጎልን እየሰማን ሳለ መልእክት መጥቷል እንባላለን። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ መልእክት አይመጣም የሚል የጠነከረ ተቃውሞ የለንም። ይሁን እንጂ በዚህ መስመር የተላለፉ መልእክቶችን ሲመዘኑ ቀጥተኛ፣ ግልጽና ምእመኑን የሚያንጹ እንዳልሆኑ ሲነገር ይሰማል። በተግባርም ታይቷል። ስለሆነም የቡድኑ መዘምራን ለጊዜው በተለሰፉበት በዜማ መልእክተኝነታቸው ብቻ ቢለሰፉ ያንጹናል። ከመካከላቸው ወቅታዊ መልእክት የሚቀበሰ የመዘምራን ቡድን አባላት ካሉ ከፕሮግራሙ አስተባባሪ ጋር ጉዳዩን እስተካከለው መልእክታቸውን ቢያስተላልፉ መልካም ይሆናል።

ስለዚህ በዚህ በኩል ያሉ ጉድለቶች ቢስተካከሉ እነርሱም ይጠቀማሉ። እኛም እንታነጻለን። ብዙ ጊዜ በቡድን ዘማሪያን መካከል በልዩ ልዩ ጉዳዮች መበታተን ሲከሰት ቁጥራቸው ያንሳል። በቁጥር ሲያንሱ ለአምላኪው የፈተና እና የጥያቄ ምክንያት ከሚሆኑ እገልግሎት ባይቀበሉ ይመረጣል። ስተቀበሉም አገልግሎቱን ለመፈጸም እንዳልቻሉ ቀደም ብለው ሊጋበዛቸው አካል ቢያሳውቁ ይበጃል። ቡቦጨማሪም የተመጠነ ቁጥርና ለዕሰቱ ከተመረጠው ክፍል ጋር የሚሄድ መዝሙር ለማስናዳት እንዲቻላቸው ከፕሮግራሙ አስተባባሪዎች ጋር ቅድመ ዝግጅት ቢያደርጉ የምስባኩ አገልግሎት ሀብር ያለው ይሆናል።

አይጉላ እንጂ በአንዳንድ መዘምራን ቡድን ውስጥ ከጎብረቱ ቅንጅት ያፈነገጠ አካላዊ አንቅስቃሴን በማድረግ የሕዝቡን ትኩረት የሚያዛቡ አባላት ይታያሉ። እነዚህን እንቅስቃሴዎችን የሚያሳዩትን ግለሰቦች ሕብረቱ ቢመክራቸውና ከሕብረቱ ጋር አብረው እንዲፈሱ ቢረዳቸው ሕዝቡን

ለማምለክ ያግዛሉ። አለበለዚያ የሚያመልከው ሕዝብ ለምንድነው እንዲህ የሚሆኑት? እያለ በዜማ ከማምለክ ይልቅ ወደ ታዛቢነት ዝቅ ይላል። ስለ ሶሎ ዘማሪዎች ያልናቸው አንዳንዶቹ አውነቶች የቡድን ዘማሪያንንም ስለ ሚመለከቱ በዚህ ወቅት በዚያ ሥፍራ ያነሳናቸውን የሚታረሙ ጉዳዮች ልብ ማለት ይገባል።

2.6 የሙዚቃ ቅንብር

ሙዚቃ ስው እምላኩን ለማክበር የሚጠቀምበት በመሣሪያዎች እማካኝነት የሚተላለፍ መልእክት ነው። በመድረኮቻችን ብቅ ከሚሉት የፕሮግራም ዓይነቶች እንዱ በሙዚቃ የሚተላለፈው መልእክት ነው። ሙዚቃ በልብ ያደረን ደስታ ለመግለጽ የሚያገለግል ተጨባጭ መግለጫ ነው። ባሰን ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን እንድናመስግን በመጽሐፍ ቅዱስ ታዘናል።

«አግዘአብሔርን በመቅደሱ አመስግኑት
በኃይሉ ጠፈር አመስግኑት
በመለከት ድምጽ እመስግኑት
በበገናና በመስንቆ አመስግኑት።
በከበሮና ለዘፈን አመስግኑት
በአውታርና በአምቢልታ አመስግኑት።
ድምጹ መልካም በሆነ ጸናጽል አመስግኑት
አልልታ ባለው ጸናጽል አመስግኑት (መዝ 150:3-5)

ንስሃ በገባው የአባካኙ ልጅ ታሪክ እንደምናየው በዚያ ሕብረተሰብ ባህል ሙዚቃ የተለመደ የደስታ መግለጫ እንደነበረ መረዳት እንችላለን። የጌታ ምሳሌ በጎብረተሰቡ ተጨባጭ ልምድ ላይ የተመሠረተ እንደነበር እንገነዘባለን። ምክንያቱም ጌታ የሚጠቀምባቸው ምሳሌዎች በሙሉ ተጨባጭና ተግባራዊ ነበሩና። ከላይ ባነሳነው የአባካኙ ልጅ ታሪክ ውስጥ የምናየው ሁኔታ እንደሚያስገንዘበን ደስታን ለመግለጽ ሙዚቃ ሥፍራ እንደነበረው ነው። «ወደ ቤት በተቃረበ ጊዜ የሙዚቃና የጭፈራ ድምጽ

ሰማ» (ሉቃ 15:25) ከሚለው እንሳስጽ እንደምንገነዘበው ንስሃ ሰገቡ ኃጢአተኞች አምሳክ በሚገርምና በሚደንቅ መንገድ ፊቱን እንደሚያራበላቸው ነው፤ አዲሰ ኪዳን በብዙ ሥፍራ ይህንን እውነታ ያስገነዝበናል።

ንስሃ ገብቶ ፊቱን ወደ ፈጣሪ ባዘረ ኃጢአተኛ ውሰኔ ሀሳችን ደስ ይለናል። አብዛኞቻችን ጌታ ያደረገልንን እያሰብን በናመሰግን በውስጣችን የደስታ ስሜት ይፈላል። ስሜታችንን በገሐድ ለመግለጽ የሚያግዙን ልዩ ልዩ መንገዶች እንጠቀማለን። በእንዲህ ዓይነቱ የደስታ ጊዜ የሙዚቃ ድርሻ የጎላ እንደሆነ እንገነዘባለን። ሕብረስቡ ባፈራው የሙዚቃ መሣሪያና በተፈጥሮ የተሰጡንን መሳ የአካል ክፍሎቻችንን በመጠቀም ለአምላክ ምስጋና እና ውዳሴ እንድናቀርብ ቃስ ያደፋፍራል። በዘመናዊ ሙዚቃ መሣሪያም ጌታን መባረክና ከፍ ከፍ ማድረግ ምንም ኃጢአትነት የለውም።

ይህን እንጂ ከመጠን ያለፈ የሙዚቃ ጩኸት ሕዝቡን ከማሸበር በቀር የሚፈይደው ነገር የለም። አድማጮች ያለበትን ሁኔታ ያገናዘበ ለዛ ያለው የሙዚቃ ቅንብር ትኩረትን ወደ እምሳክ እንድናደርግ ያግዛል። የሙዚቃው መሣሪያ ድምጽ ከዜማው ጋር ከሚቀናጁት የቃላት ድምጽ ባይበልጥ ይመረጣል። ከመስመር የወጣ አደንቋሪ ጩኸት ግን ሰዎችን ያደናግራል። እንዳንዶቸንም ያሰደነግጣል። ስለሆነም ከመድረክቻችን የሚፈለለው የሙዚቃ ቅኝት ሳለንበት ሁኔታ የሚመች መሆኑን ማረጋገጥ የሙዚቃ መሣሪያ ተጨዋቾቻችን ኃላፊነት ነው። በግድ ለመኝ ለማለት ጆሮን እስኪያስጨንቅ ድረስ የሙዚቃ መሣሪያውን ማስጮህ አግባብ አይደለም። በተሰይ ይህ ቅጥ ያጣ ጩኸት የድምጽ ማጉያ አካባቢ ስሚቀመጡ ምእመናን ትልቅ ፈተና ይሆንባቸዋል። ድንገት የመጡ እንግዶቻችንም «መካሪ የላቸው ይሆን?» እስኪሉን ድረስ ትዝብት ውስጥ እንዳንወድቅ መጠንቀቅ አለብን።

አንዳንዶችንም ያለ ጊዜው የጆሮ ውታፍ እንዲገዙ ማስገደድ የለብንም። ይህ ከላይ ያለውን አባባል የጠቀስኩት ያለምከንያት አይደለም። ቤተክርስቲያኑን የሚወድ ለአያሌ ዓመታት በቤተክርስቲያን የኖረ ወንድሚ ከፍጂ ሰባኪም ሆነ መጠን ከሌለው የሙዚቃ መሣሪያ ድምጽ ራሱን ለመከላከል ያደረገውን እንዲህ ሲል ተናገረ «አብዛኛው ሰው ጩኸት አይፈልግም። እኔም አልወድም። ታማሽ ቁጭ እላለሁ። ድምጽ የማፉንስልኝ

የጆሮ ውታፍም (ear plug) ገዝቻለሁ። እስከመቼ ልቻለው? የኔ ብጤው ሰንት ይሆን?» አብረውን መሆን የሚፈልጉ ሰንት ወገኖቻችን እንዲህ አስመርረን ይሆን? ይሄ ወንድሜ መዘመር ይወዳል። የድምጽ መጠኑን ያገናዘበ የሙዚቃ መሳሪያም ሆነ የተናገረ ድምጽ መሰማት ይሻል። ይህን እንጂ መጠን ሊያልፍ ሌሎቹን እንዳያስጨንቅ የራሱን መፍትሔ ወስዷል። የጆሮ ውታፍ መግዛት የማይችሉ ጆሮቻቸውን በጥጥና በሶፍት የሚደፍኑ ሰንቶች ይሆኑ ይሆን? እባካችሁ ልብ እንበል ሁሉን በአገባብና በስርዓት እናድርገው።

የውይይት ጥያቄዎች

1. ሙዚቃ ለአምልኮ ጠቀሜታው ምን ያህል ነው?
2. «ያለቅጥ የሚጮኽ የሙዚቃ ድምጽ ወጣቶችን ያስደስታል» የሚባለው ምን ያህል እውነት ነው?
3. «ሙዚቃ ቅንብር ለአምልኮ አይጠቅምም» የሚሉ አሰ ምን ያህል ይቀበሉአቸዋል?

2.7 ሰባኪያንና መድረክቻችን

መድረክቻችን የሚያስተናግዷቸው ሰባኪዎች በማንኛውም መልክ ብቃት ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል። ለሚያገለግሉት ሕዝብ መልዕክት ያላቸውና ከአምላክ የተላኩና ይህን በሱልኝ የተባሉ መሆን ይኖርባቸዋል /ሮሜ 10:15/። ሰባኪዎች እንደ ፈሪሳውያን ግብዝ መሆን የለባቸውም። ፈሪሳዊያን ወደ ሕዝቡ ልብ መድረስ ያልቻሉት እነርሱ በጣታቸው የማይነኩትን ሌላው እንዲታዘዘው ግድ በማለታቸው ነበር። ለዚህ ነው ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 23 ብቻ ስምንት ጊዜ ያህል ግብዝ ብሎ የገለፃቸው። እንደ ግብዝ ፈሪሳውያን ሰባኪ በጌታ የማይዘሰፍ በለይጣን የማይከሰስ ሊሆን ይገባዋል።

በማይከሰስ የሕይወት እቋም ውስጥ እንዲገኝ ዘወትር የሚጠነቀቅ እገልጋይ የሰይጣንን ሥራ ያፈርሳል /የሐዋ 19፡ 1-20/። በምዕመናንንም ፊት ቆሞም እውነትን ለመግለጥ የበቃም ይሆናል /1ጢሞ 3:3/። በመድረክ ለመቆም ሊሚሉ የሚገባቸው ነገሮች እሉ። መንፈሳዊ እገልግሎት

መለኮታዊና ሰብአዊ ክስተቶችን በውስጡ ያቀፈ ድርጊት ነው። በእርግጥ የእውነተኛ አገልግሎት ምንጩ ሰማይ ነው። ይሁን እንጂ በምድር ላሉ ሰዎች መልእክቱ እንዲደርስ በለምኞች ሁኔታ መቀረጽ አሰበት። ስለሆነም ለዚህ ነው ደጋግመን መልእክት በለው ቋንቋ የሚተላለፍ የእግዚአብሔር ሃሳብ ነው የምንለው። እግዚአብሔር ሃሳቡን ለሰዎች ለማስተላለፍ ለዋዊ መሣሪያዎች ይጠቀማል። ስለሆነም በባኪ ከእምላክ የተላከውን መልእክት በመድረክ ላይ ቆሞ ለተቀባዮች የሚያደርስ ማስተላለፊያ መሣሪያ ነው። በዚህ መድረክ ላይ ለመቆም ሊሟሉ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች አሉ። ከእነዚህም ለዚህ ርዕስ ተዛማጅ የሆኑትን ጥቂቶችን ጉዳዮች ብቻ በሚመለከተው መልኩ እናነሳለን።

መልእክተኛነትና መንፈሳዊ ብቃት

ከፍጹምነት የደረሰ ሰው ባይኖርም ሰባኪያን ከእነርሱ የሚጠበቁትን መሠረታዊ የአገልጋይነት መታወቂያዎች ሊያጡ አይገባቸውም። ከማንኛውም ከርስቲያን የተለየ ጥንቃቄ በማድረግ በቅድስና ሊመላለስ እንዲሁም በአጠቃላይ ምሳሌነት ያለው ሕይወት ሊኖር ይገባዋል። ሰይጣን ወንድሞችን ይከሳል / ዘካ፡ 3፡1-5 ራእ 12፡10-11/። ምንጊዜም የጸዳ አቋም ይዘን እንደንገኝለት የሚፈልገው እምላክ «እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ» ብሎ ያለማቋረጥ ይጠራናል። ይህ እምላካዊ ትዕዛዝ ዕለታዊ ትኩረታችንን የሚሻ ጉዳይ እንደሆነ ሰብዘ-ዎቻችን ግልጽ መሆን አለበት። ምክንያቱም ለመስበክ በቆምንበት መድረክ ላይ በክፋው ሰተያዙት በርካታ አእምሮዎች የምንናገር ስለሆንን ከክፋው ተጽዕኖ ነጻ የሆነ በክፋው መንግሥት ላይ በሥልጣንና በድፍረት የሚዘምት ማንነት ሊኖረን ይገባል።

የመንፈሳዊ ሕይወት ብቃት አስፈላጊ የሚሆንበት ሌላው ምክንያት የራሳችን አእምሮ እንዳይፈርድብን ነው። ከሕሊና ወቀሳ ነጻ ያልሆነ ሰው በሚሰብክበት ጊዜ በውስጡ ከራሱ አእምሮ ጋር ስለሚሟገት ለሌሎች ሊናገር በሚሰሙት ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ አናሳ ይሆናል። በሰውም በእግዚአብሔርም ፊት ንጹሕ ሕሊና ሊኖረን ግን በድፍረት እንናገራለን። መልእክታችንም ለውጥን የማምጣት ብቃቱ ይጨምራል። የሕሊና መቆሸሸ

ሊያጋጥም ከለውም ሆነ ከጌታ ጋር በቂ ጊዜ ወስዶ ራስን በንስሃና በይቅርታ ማደስ አማራጭ የሌለው አርምጃ ነው።

የሰባኪው ሕይወት የማይከሰስ መሆን አለበት። አገልግሎትን ከላኪው ይቀበሉታል እንጂ እይኮርጁትም። «የመድረክ ላይ ስብከትህን በጥቂት ደቂቃዎች ልትጨርሰው ትችላለህ ኮሮህ ግን ሳምንቱን ሙሉ ይለብካል።» በእርግጥ ስብከት በጥቂት ደቂቃዎች የመድረክ ትዕይንት የሚያበቃ ከመለሰን ትልቁን ስህተት እንፈጽማለን። ምክንያቱም ትልቁ ስብከታችን መጽሐፍም እንደሚል በጨለማው ዓለም ላይ የሚኖረን የብርሃንነት ሕይወት ነውና /ማቴ 5፡16 1ጴጥ2፡9./። እውነተኛ መልዕክተኛ የሚናገረውን የሚኖር ነው። በተጨማሪም የኖረውን የሚሰብክ ወይም ደግሞም የሚሰብከውን የሚኖር መሆን አለበት።

መልእክተኛነትና ጥሪ

ከምንም በላይ መልእክት አቅራቢነት ጥሪን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። ለሰች ነገር ማቀነባበር ስለቻሉ በመናገሪያ ምስባኩ ላይ ጌታን ወክለው መቆም የሚችሉ ይመስላቸዋል። ይሁን እንጂ ይህ ክብቃትና ችሎታ ይልቅ የአንድዬን ጥሪና ችሮታ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ አንዳነበብነው፥ ሁሉ ሐዋርያት እንዳልሆኑ ሁሉ / 1ቆሮ 12፡29/ ሁሉም ወንጌልን ስባኪዎች እይደሉም። ስለሆነም ወንጌልን ለመበበክ የሚጠሩ ሰዎች ብቻ በዚያው መስክ መሰለፍ እለባቸው /ማቴ 4፡18-19/።

ጌታ ኢየሱስ እገልግሎቱን እያዩ ለነገ ይሰናዱ ለነበሩት ደቀ መዛሙርት «ወጣ ብላችሁ ወንጌልን እንዲሰብኩ ሰዎችን አሰባለቡ» ብሎ አላዘዛቸውም። ይልቁንም በማቴ 9፡38 «*የመከሩ ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞችን እንዲልክ ለምኑት*» በማለት ለሰባኪነት ሰዎች መጠራት እንዳለባቸው በቀጥታ እመለከተ። ላይላኩ የሚሰብኩ፥ መልዕክተኞች ወይም ሰባኪዎች ላይሆኑ ራሳቸውን ያሰማሩ ወዶ ዘማቾች ናቸው። ወዶ ዘማቾነት ሊመች ሊቀጥለበት ላይመች ደግሞ ምን ቸገረኝ? በማለት መንጋውን ለእውሬ የሚያሰጥ ሞያተኛነት ነው/ዮሐ 10፡12-13/። ይህንን የሞያተኛነት እንትስቃሴ ጌታ በመንግስቱ ጉዳይ ላይ ሊያሰማራቸው በሚፈልጋቸው ሰዎች

ሕይወት ውስጥ ሊያየው አይሻም። ለዚህ ነው ጳውሎስ በሮሜ 10:15-16 ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ? የሚል ወላኝ ጥያቄ የሚጠይቀው።

ክዚህ ምንባብ እንደምንገነዘበው የምሥራች አብላሪዎች መልዕክት እስይዞ የሚልካቸው ጌታ አላቸው። ይህንን እድርሱልኝ ተብለው እደራ የተሰጣቸው መልእክተኞች መሆን አለባቸው። ስለሆነም ምንባቡ የሚያስረዳን ሰበኪዎች የመልእክት እድራሾች እንጂ አመንጭዎች አለመሆናቸውን ነው። ይህን እድርሱልኝ የሚላቸው ጌታ ትዕዛዝ ያስለፈልጋቸዋልና። አለበለዚያ በፈጠራ የተሰማሩ ወሬኞች ይባላሉ እንጂ መልእክተኞች አይባሉም። ምክንያቱም ወሬኞች ለይጣን ክራሱ ፈጥሮ የሚያወራውን የክፋውን ተልእኮ ለማሳካት የተሰለፉ ሰፍላፊዎች ናቸው። ይህ እንዳይሆን ነበር ጌታ ደቀመዛሙርቱን መልእክት እስይዞ የላካቸው። ምክንያቱም ክርስቶስን ለማወጅ የተሰማራ ማንም በግሉ ከክርስቶስ ጋር የጠበቀና የወሰቀ ግንኙነት ሲኖረው ይገባልና። በግሉ ያጣጣመውን የጌታውን ፍቅር ለሌሎች ያውጃልና።

በምስባኩ ላይ ቆመን የምናውጀው ቃል ፍላጎቶቻንን ለመፈጸም የምንተጋበትና የራሳችንን ገድል በሰፊው የምናስተዋውቅበት መድረክ ላይሆን ይልቁንም እግዚአብሔርን ለማገልገል ራሳችንን ለጌታ ፈቃድና ፍላጎት መጠቀሚያነት የምናቀርብበት የጌታ መላሪያ ነው። ምስባኩ ሰባኪው ጌታ ምን እንደሚፈልግበት ተገንዝቦ ለጌታ ፈቃድ መተላለፊያ እንዲሆን ራሱን በትሕትና ለማቅረብ የሚቆምበት የተቀደሰ ቦታ ነው። ስብከትም ይህንን ለመፈጸም የሚያበቅል የአምላክ መሣሪያ ነው።

ቢላ ለመቁረጥ፣ ልብስ እርቃንን ለመክደን ÷ መነጽርም የዐይን ድካም ለማገዝ እንደሚጠቅሙ ሁሉ በብከትም በጌታ የተፈለገውን ሥራ ለማከናውን የተመረጠ የጌታ መሣሪያ ነው። ስለሆነም ፈጣሪ ፍጡር የሆነውን ሰው በማዘጋጀት መልእክትን በውስጡ አቆይቶ ለሚዎች ቢተናዱ ለዓት ከእርሱ ጋር በመሆን መልእክቱን እንዲያስተላለፍ ይገለግለበታል። ሰባኪው ፈጣሪ በፍጡር ቋንቋ መልእክቱን የሚያስተላልፍበት መሣሪያው ነው። ስለዚህ ሰባኪው እንደ እግዚአብሔር መሣሪያ የተለያዩ ሚናዎች ይኖሩታል። የሚከተሉትን ብቻ ለምሳሌ ያህል እንጠቅሳለን።

ሀ. ሰባኪው እንደ ነቢይ

በመጽሐፍ ቅዱስ ያየናቸው እያሌ ነቢያት መልእክትን ክጌታ ተቀብለው በሳኪው ኃይል መልእክቱን ለተቀባዮቹ በታሳቅ ድፍረትና ኃይል ያስተላልፋሉ። ልክ እንዲሁ ሰባኪው የተቀበለውን መልእክት በእርግጠኝነትና በድፍረት ተሞልቶ በመድረክ ላይ ለለሚዎቹ ሲያውጅ እንደ ነቢያት ራሱን ለእምላክና ለሰዎች ሰጥቷል ማለት ነው። ነቢያት የሎሌነትን መንፈስ በተግባር እያላዩ የላኪውን ድምጽ በክፍተኛ ደረጃ ያስተጋባሉ። እነርሱ በቃሉ የሚሰሰጥ የተውኔት ለዎች ላይሆኑ ለቃሉ ሥልጣን ሙሉ ለሙሉ ራሳቸውን ያስገዙ የቃሉ ሎሌዎች ናቸው። ደስታቸውም ለዎች ለዚህ መልእክት ልባዊ መታዘዝን ሲያሳዩና በመልእክቱ የላኪውን ክብር እይተው ለግደት ሲያደርጉ ማየት ነው።

እዋጅ ነጋሪው ከእርሱ ደካማነት ውስንነት በላይ የሳኪውን /የመልእክቱን ምንጭ / በጉልህ ሁኔታ በማሳየት ላይ ብቻ ያተኩራል። ጉዳዩ ወደ መልእክቱ ባለቤት ብቻ እንዲሆን ለዎችን ያነሳሳል። እዋጅ ነጋሪ የእዋጁ ምንጭ ባለ ሥልጣን ካልታየ እርካታ ስለሌለው እርሱ እንዲታይ የሚከፈለውን ዋጋ ሁሉ ይከፍላል። ይህን የከበረ ዕድል ለእድማጮቹ በመስጠትም ይረካል። ሰባኪው የእግዚአብሔር መሣሪያ እንደመሆኑ የመልእክቱ ባለቤት ሎሌ መሆኑን ደጋግሞ ያስገነዝባል። ይህንንም «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል» በሚለው ተደጋጋሚ ቃሉ ያስረግጣል። ሰባኪው እንደ እግዚአብሔር መሣሪያ የነቢይነት ተልእኮውን የሚወጣው እንደ እዋጅ ነጋሪ ሆኖ ነው። እዋጁንም እንዲህና እንዲህ ተብለሃል እያሰ በመደጋገም ያስተጋባል።

ለ. ሰባኪው እንደ እረኛ

መጋቢው መዳቢ ባልሆነበት ሥፍራ ወቅቱን የጠበቀ የምዕመኑን ፍላጎትና ሁኔታ ያመቻቻል። ሰባኪው እንደ እረኛ መንጋውን ባለበት ሁኔታ ለመድረስ የሚያስችል ምግብ ከመድረክ ያቀርባል። ለእረኛው ሰባኪ በጎች ሁሉ እንድ ዓይነትና በእንድ ደረጃ ላይ ያሉ እይደሉም። ስለሆነም ልዩ ልዩ ሁኔታቸውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የሚፈልጉትን ወቅታዊ እንክብካቤ

ሕይወት ውስጥ ሊያየው አይሻም። ለዚህ ነው ጳውሎስ በሮሜ 10:15-16 ካልተላኩ አንዴት ይሰብካሉ? የሚል ወሳኝ ጥያቄ የሚጠይቀው።

ከዚህ ምንባብ አንደምንገነዘበው የምሥራች አብሳሪዎች መልዕክት አስይዞ የሚልካቸው ጌታ አላቸው። ይህንን አድርሱልኝ ተብለው አደራ የተሰጣቸው መልእክተኞች መሆን አለባቸው። ስለሆነም ምንባቡ የሚያስረዳን ለበኪዎች የመልእክት አድራሾች አንጂ አመንጭዎች አለመሆናቸውን ነው። ይህን አድርሱልኝ የሚላቸው ጌታ ትዕዛዝ ያለለፈልጋቸዋልና። አለበለዚያ በፈጠራ የተሰማሩ ወሬኞች ይባላሉ አንጂ መልእክተኞች አይባሉም። ምክንያቱም ወሬኞች ሰይጣን ከራሉ ፈጥሮ የሚያወራውን የከፋውን ተልእኮ ለማሳካት የተለለፉ ለፍላፊዎች ናቸው። ይህ አንዳይሆን ነበር ጌታ ደቀመዛሙርቱን መልእክት አስይዞ የላካቸው። ምክንያቱም ክርስቶስን ለማወጅ የተሰማራ ማንም በግሉ ከክርስቶስ ጋር የወበቀና የጠለቀ ግንኙነት ሲኖረው ይገባልና። በግሉ ያጣጣመውን የጌታውን ፍቅር ለሌሎች ያውጃልና።

በምስባኩ ላይ ቆመን የምናውጀው ቃል ፍላጎቶቻንን ለመፈጸም የምንተጋበትና የራሳችንን ገድል በሰፊው የምናስተዋውቅበት መድረክ ሳይሆን ይልቁንም አግዚአብሔርን ለማገልገል ራሳችንን ለጌታ ፈቃድና ፍላጎት መጠቀሚያነት የምናቀርብበት የጌታ መሳሪያ ነው። ምስባኩ ሰባኪው ጌታ ምን አንደሚፈልግበት ተገንዝቦ ለጌታ ፈቃድ መተላለፊያ አንዲሆን ራሱን በትሕትና ለማቅረብ የሚቆምበት የተቀደሰ ቦታ ነው። ስብከትም ይህንን ለመፈጸም የሚያስችል የአምላክ መሣሪያ ነው።

ቢላ ለመቁረጥ፣ ልብስ ኣርቃንን ለመከደን ÷ መነጽርም የዐይን ድካም ለማገዝ አንደሚጠቅሙ ሁሉ ስብከትም በጌታ የተፈለገውን ሥራ ለማከናውን የተመረጠ የጌታ መሣሪያ ነው። ስለሆነም ፈጣሪ ፍጡር የሆነውን ለው በማዘጋጀት መልእክትን በውስጡ አቆይቶ ለሚዎች በተሰናዱ ሰዓት ከአርሱ ጋር በመሆን መልእክቱን አንዲያስተላልፍ ይገለግለበታል። ሰባኪው ፈጣሪ በፍጡር ቋንቋ መልእክቱን የሚያስተላልፍበት መሣሪያው ነው። ስለዚህ ሰባኪው እንደ አግዚአብሔር መሣሪያ የተለያዩ ሚናዎች ይኖሩታል። የሚከተሉትን ብቻ ለምሳሌ ያህል አንጠቅሳለን።

ሀ. ሰባኪው እንደ ነቢይ

በመጽሐፍ ቅዱስ ያየናቸው አያሌ ነቢያት መልእክትን ከጌታ ተቀብለው በሳኪው ኃይል መልእክቱን ለተቀባዮቹ በታላቅ ድፍረትና ኃይል ያስተላልፉ። ልክ አንዲሁ ሰባኪው የተቀበለውን መልእክት በአርግጠኝነትና በድፍረት ተሞልቶ በመድረክ ላይ ለሰሚዎቹ ሲያውጅ አንደ ነቢያት ራሱን ለአምላክና ለሰዎች ሰጥቷል ማለት ነው። ነቢያት የሉሌነትን መንፈስ በተግባር አያሳዩ የላኪውን ድምጽ በከፍተኛ ደረጃ ያስተጋባሉ። አነርሱ በቃሉ የሚለለጥኑ የተውኔት ሰዎች ሳይሆኑ ሰቃሉ ሥልጣን ሙሉ ሰሙሉ ራሳቸውን ያስገዙ የቃሉ ሉሌዎች ናቸው። ደስታቸውም ሰዎች ለዚህ መልእክት ልባዊ መታዘዝን ሲያሳዩና በመልእክቱ የላኪውን ክብር አይተው ስግደት ሲያደርጉ ማየት ነው።

አዋጅ ነጋሪው ከአርሱ ደካማነት ውስንነት በላይ የላኪውን /የመልእክቱን ምንጭ / በጉልህ ሁኔታ በማሳየት ላይ ብቻ ያተኩራል። ጉዳዩ ወደ መልእክቱ ባለቤት ብቻ አንዲሆን ሰዎችን ያነሳሳል። አዋጅ ነጋሪ የአዋጁ ምንጭ ባለ ሥልጣን ካልታየ አርካታ ስለሌለው አርሱ አንዲታይ የሚከፈለውን ዋጋ ሁሉ ይከፍላል። ይህን የከበረ ዕድል ለአድማጮቹ በመስጠትም ይረካል። ሰባኪው የአግዚአብሔር መሣሪያ አንደመሆኑ የመልእክቱ ባለቤት ሎሌ መሆኑን ደጋግሞ ያስገነዝባል። ይህንንም «አግዚአብሔር አንዲህ ይላል» በሚለው ተደጋጋሚ ቃሉ ያስረግጣል። ሰባኪው አንደ አግዚአብሔር መሣሪያ የነቢይነት ተልእኮውን የሚወጣው አንደ አዋጅ ነጋሪ ሆኖ ነው። አዋጁንም አንዲህና አንዲህ ተብለሃል አያለ በመደጋገም ያስተጋባል።

ሰ. ሰባኪው እንደ አረኛ

መጋቢው መዳቢ ባልሆነበት ሥፍራ ወቅቱን የጠበቀ የምዕመኑን ፍላጎትና ሁኔታ ያመቻቻል። ሰባኪው አንደ አረኛ መንጋውን ባለበት ሁኔታ ለመድረስ የሚያስችል ምግብ ከመድረክ ያቀርባል። ለአረኛው ሰባኪ በጎች ሁሉ አንድ ዓይነትና በአንድ ደረጃ ላይ ያሉ አይደሉም። ስለሆነም ልዩ ልዩ ሁኔታቸውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የሚፈልጉትን ወቅታዊ እንክብካቤ

ይለግሳቸዋል። እማኞች ያሉበትን ሁኔታ ያገናዘበ በአቅማቸው የሆነ መንፈሳዊ ማዕድን በማዘጋጀት ለወቅቱ ርሃባቸው የሚሆን ማዕድ ያቀርብላቸዋል።

ከደረሰባቸውና ካጋጠማቸው ልዩ ልዩ ችግር የተነሳ የምግብ ፍላጎታቸው ጠፍቶ በድካም ውስጥ ያሉትን ደግሞ ያበረታታል። ሕይወት ትግል በበዛበት ጉዞ ይመስላል። ታዲያ በዚህ የሕይወት ጉዞ ዝለው የተዝለፈለፉትን ደግሞ አይሂችሁ፥ በርቱ ማለት ለእረኛው ሰባኪ ሩቅ አይደለም። «በርቱ! ግድ የላችሁም ጨክኑ!! የቀረን ጥቂት ነው።» በማለት ተስፋቸው እንዲታደስ በማድረግ፥ የእምነት በጎነት እንዲያስቡት ያደርጋል። ደክሞት ለተዝለፈለፈውየእረኛ መልእክት ይሽው ነውና።

ይህች ዓለም በእታሳይነቷ፣ በስባሹ ስጋ በስግብግብነቱ እንዲሁም ሰይጣን በጭካኔው እቁስለው ጤናቢስ ያረጓቸውን እንዲያገግሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ስለሆነም ጤንነት የጎደላቸውን ጤነኛ የሆነ መንፈሳዊ እቋም እንዲኖራቸው እስፈላጊውን ዕገዛ በማድረግ ካሉበት ሁኔታ እንዲወጡ ምርኩዝ ከመድረክ ማቀበል ሰባኪው እንደ እረኛ የሚያከናውነው ጠቃሚ ድርጊት ነው። ወደ ባህር የተጣለ መረብ ዓሳን ጨምሮ ጎትቶ የሚያመጣቸው ነገሮች ዓይነታቸው ብዙ እንደሆነ ሁሉ ወደ ጸሎት ቤት የሚመጡ ሰዎችም ዓይነታቸው እንዲሁ ብዙ ነው። አንዳንዶቹ ከራሣቸው በመነጨ የተሰላቱ ምርጫም ሆነ ስሌሎች በደረሰባቸው ግጭት የተሰበሩ ናቸው። ታዲያ ለባኪው እንደ እረኛ እነዚህ ሰባሮች እንዲጠገኑና ሕይወትን በተሻለ እቅም እንዲጋፈጡ እቅም ይፈጥርሳቸዋል።

ለባኪው እንደ እረኛ ከመድረክ የሚያደርገው ሌሳ ነገር ቢኖር እቅጣጫን በማመሳከት የባዘነውን መለመር ማስያዝና ነገን በተሻለ ብርሃን እንዲያዩ መደገፍ ነው። በተጨማሪም ለባኪው እንደ እረኛ ሁነኛውን መንፈሳዊ የህይወት መርሕ በተግባር ያመሳክታል። በዕለት ተዕለት የምሳሌነት ሕይወቱ ፊት ፊት እየሔደ በተግባር ሲመራው የቆየውን ሕዝብ ከመድረክ በሚያቀርባቸው መልእክቶቹ፥ የእተረጓጎም ጥበቡና ጨዋ እቀራረቡ ምሳሌነትን ከመድረክ በተግባር ያሳያል። በተጨማሪም ከእጥቂ በመከሳከል ከለላን በመስጠት በመንከባከብ ወደ እነርሱ በጭካኔ የሚገስግለውን ጥቃት ፈፃሚ ኃይል እንዲመክቱ ያዘጋጃቸዋል /ኤፌ. 6:18/ እንደ እረኛ እርሱ

የሚጠብቀውና የሚመራው መንጋ ለበላተኛ የተጋለጠ መሆኑን እጥብቆ ይረዳል። ስለሆነም ከበላተኛ ለማስጣል ተገቢውን ትጥቅ ከመድረክ ያቀብላቸዋል። በሚጠብቃቸው የጸጋ ቃል እንዲሞሉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ከመድረክም ይህንን ደጋግሞ ያደርጋል። በዚህም እንደ እረኛ ተልእኮውን ይወጣል።

ሐ. ሰባኪው እንደ ምስክር

ሰባኪው ጌታ በሕይወቱ ለሠራው ሥራ ምስክር ነው። እንደ ምስክርም ለአምላኩ መሣሪያ ሆኖ ሲያገለግል እውን የሚሆነው ነገር በሕይወቱ ያሰፉ እውነቶችን በተግባር ለማረጋገጥ መቆሙን ነው። ሰባኪው በተቀደለው ምስባክ የቆመው እፈታሪክ ለማነብነብ፣ የሰማ በለው ታሪክ ለማቅረብ አይደለም። እንደውም ይህ ድርጊት (ማለትም ስብከቱ) ለባኪው ስለሚናገረው እውነት ሕያውና ተጫባጭ ምስክር እለኝ ለማለት የሚያስችለው እርሱ ራሱ በግሉ ያጣጣመውን መንፈሳዊ መዳሰስ የሚያስረግጥበት ሁኔታ ነው። የሚያውጀው እውነት በሕይወቱ ትርጉም ያለውና ታሳቅ ሥፍራ የሚለጠው ቁም ነገር መሆኑን ይመስክራል። ይህንና ያንን ጌታ ሲሠራ እኔ እይቻለሁለማለት የሚችልበት ጭብጥ እያቀረበ ሁኔታዎችን ሲተርክ የዓይን ምስክርነቱ ወደ እድማጮቹ ጆሮ ይፈሳል። የሚያውጀው እውነት እርሱ ራሱ የተነካበትና በእርሱ ሕይወት ትርጉም ያገኘ መሆኑን በድፍረት ይናገራል።(1ኛ ዮሐ1:1-3) ይመለከታል።

ደጋግሞ እኔ ምስክር ነኝ ይላል። መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ያለምንም ማወላወል መሰከረ። ዓይኖቹ ሰማያት ተከፍተው ሲከናወን ያዩትን እውነት መካድ አይችሉምና። ሰባኪው ምንም ሳይደርሰው የሌላውን መልእክት እንደሚቀበል የቴፕ ሪከርደር የተቀበለውን እያስተጋባም። ለራሱ ምንም ሳይቀርለት እንደ ገደል ማሚቶ የሌላውን መልእክት ዝም ብሎ ካስተጋባ ከሁሉ ይልቅ ቃሚያሳዝን ምስኪን ለው ነው። ሰባኪ በውስጡ ለምስክርነት ምንም ሳይቀርለት ከመድረክ ላይ የሚቆም እገልጋይ ስትሸክም እየዋለች የተጫነችውን እንደማትበሳ አህያ ወይም ክትልቅ ማዕድ ዙሪያ ተቀምጦ ለመብላት እንደሚቋምጥ ግን ዕድሉን እንዳላገኘ ግለሰብ ነው። ስለሆነም ሰባኪ ከእንደዚህ ዓይነቱ አላዛኝ ክስተት ውስጥ ራሱን እንዳያገኝ

ለምስክር እንዲቀርለት ክቴታው ያየው ወይም ደግሞ የለማው ነገር ሊኖረው ያስፈልገዋል። [5]

መ. የሰባኪው ልዩ ልዩ የመድረክ ላይ ገጽታዎች

በስብከት ላይ እያለን ከሚሆኑት ብዙ ነገሮች ዋናውና የሁላችንም ትኩረት ሊሰብ የሚገባው በአኖና በምናገለግላቸው ሰዎች መካከል ያለው በፍቅር የመሳሳብ ድርጊት ነው። የሚሰሙን ሰዎች ጌታ በእኛ በመጠቀም የሚተውላቸውን መልካም ነገር በጉጉት የሚጠብቁትን ያህል ለእኛ የፍቅር እንክብካቤ ለመለጠት የሠራ አካላቸውን ይጠቀማሉ። ፈገግታ ይመግቡናል፥ በዓይኖቻቸው ልዩ ልዩ ምልክቶች ያሳዩናል። የመስበክ ሂደት በእግዚአብሔርና በሕዝቡ የፍቅር እንክብካቤ የምናገኝበት ወሳኝ ወቅት ነው። እኛም ምዕመናን ያሉበትን ሁኔታ በመንፈስ ተረድተን እንደየሁኔታቸው የሚያስፈልጋቸውን ማእድ ስናለናዳና የፍቅርና የርህራሄ እንክብካቤም ስንለጣቸው ፍቅር በቃል በማይገለጽ ሁኔታ ከእኛ ወደ እነርሱ ይፈስሳል።

በመስበክ ሂደት ውስጥ ከእኛ አቅም በላይ የሆነ መልእክት ተሸክመን እንደምንጓዝ ግልጽ ሊሆንልን ይገባል። እግዚአብሔር በተለየ መንገድ እንዳለፈ ሲታወቀን መንፈሳችንን መጠበቅ አለብን። አድማጮቻችን ውስን ከሆነው ከእኛ ማንነት ውጭ የሆነ ነገር ሊያገኛቸው የሚያደርጉን ቅጡ ይጠፋቸዋል። ያኔ በመስበክ ሂደት ውስጥ ክብርን ክብር ሊሚገባው እንድናመጣ ልዩ ንቃት ያስፈልገናል። ብልሃታችንና ትጋታችን ይህን እንዳመጣው የሚመስል ምልክት ለአዳማጮቻችን እንዳንልክ መጠንቀቅ ይኖርብናል። አም የጌታ ልዩ መገኘት የኛም የአድማጮቻችንም ደስታ ነው። እንደ ተገራ በቅሎ ጌታ ሊወስደን ወዳሰበው ብቻ ለመሔድ መንፈሱን እያደመጥን መጓዝ እንጂ ክብሩን መሻማት የለብንም።

እስካአሁን በመድረክ ላይ እንደ ሰባኪያን ለንቆም ልናስተውል የሚገባንን አውነቶች በተመለከተ አምንታዊ ገጽታቸውን በመጠኑ አይተናል። በተጨማሪም እንደ ሰባኪ በመድረክ ላይ ብንፈጽማቸው የሚጠቅሙንን

[5] Hailu Cherenet Hiyaw Kibibil Addis Ababa: Commercial Printing Press, 2003.

ጉዳዮች በጥቂቱ ለመንካት ተሞክሯል። ይሁን እንጂ የዚህ ጽሁፍ ቀዳሚ ትኩረት በመድረካችን የሚፈጸሙ አርማት የሚያሻቸውን ጉዳዮች አውጥተን መፍትሔ ማበጀት ስለሆነ ሊታረሙ የሚገባቸውን ጥቂት ጉዳዮች በሚከተለው መልኩ አንስተን እንነጋገራለን።

የመድረክ ዕብሪት (ቲቶ 2:8 2ኛጴጥ 2:12)

ቃላት አብዛኛውን ጊዜ የሞትና የሕይወትን ጉዳይ ይወስናሉ። በቅርቡ አያየን የመጣነው አንደ ባህል አየተወለደው ያለው ነገር ምእመናንን ክመድረክ ማዋረድ ነው። ይህም ድካም በአብዛኛው የሚታየው ሕዝቡ ክሚያክብራቸውና ከሚቀበላቸው ወገኖች አገልግሎት መሆኑ ያስፈራል። ጌታ በዘመናችን ያለነሳልን (አንደ አንዳንዶች አገላለጽ ለወቅቱ የቀባልን) «የዚህ ትውልድ ተስፋዎች ናቸው» ክሚባሉ ታዋቂ ሰዎች የሚለማው የዕብሪት ቃል ያስደነግጣል።

ለምሳሌ ለመጥቀስ ያህል

«አሜን በል አባክህ !! አሜን ብለህም በሆነልህ!!
አሜን በይ እባክሽ !! አሜን ብለሽም በሆነልሽ»

ብሎ በንጹሕ ልቦና ሲያመልክ የመጣውን ሕዝብ መጻፈር የተገባ አይመስለንም። የአግዚአብሔር ሕዝብ የተከበረ ሕዝብ ነው። ቀደም ብለን ባነሳነው የሆስፒታሉ ምሳሌ በሆስፒታል ዋናው በሽተኛው እንደሆነ ሁሉ በጸሎት ቤትም ዋናው ሕዝቡ ነው። ዓላማ ጌታን ለመስማት የሚመጣ ሕዝብ ባይኖር ለባኪ ÷ ዘማሪና መሪ የሚባሉ ነገሮች ትርጉም የላቸውም። ስለዚህ ከሕዝቡ የተነሳ እዚያ መቆማችንን ተረድተን እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ የተሰጠንን ጸጋ አንኳን ስለ እናንተ ነው እያልን የሕዝቡን ክቡር ሥፍራ በአገልግሎታችን ለማጉላት መትጋት ይኖርብናል «ለእናንተ ጥቅም ሊባል ስለ ተሰጠኝ የአግዚአብሔር ጸጋ መጋቢነት በእርግጥ ሰምታችኋል» (ኤፌ 3:2 አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

በየትኛውም ጊዜ የተሳካላቸው አገልጋዮች ብንሆንና የተለየ ጸጋ ቢሰጠን ሕዝቡን ለማነጽ ነው። አግዚአብሔር አባታችን ለሕዝቡ ሊል ያሰጠንን ጸጋ የራሳችንን ገድል መተረኪያ ስናደርገው አርሱ ያዝናል።

ሕዝበ[illegible] ይሰብከራል። ብዙ ሰው ጌሮሳታችን የሚረዳልን ቃላችንን በመስማት ነው። ይሁን እንጂ ቃላችን የድፍረት ሲሆን ይጎዳል። ቃላችን የልባችንንም ሁኔታ ገላጭ እንደሆነ እንዘንጋ። ስለዚህ በመድረክ አስታዋቂ ተጽእኖ የሚያመጡ ቃላትን እንጠቀም። እኛ ስሕዝቡ በተሰየ መንገድ አሳቢዎች እንደሆን አይምሰሰን። ምክንያቱም መንጋው የእግዚአብሔር እንደሆነ ለእፍታም እንኳን ሊጠፋን እይገባም።

በሌላ እቅጣጫ የመድረክ እብረት የሚታየው እንደተሳካልን በመሰሰን ጊዜ አና ያንን የሚያስረግጡ ፍንጮች ስናይ ነው። በመድረክ ከሚቆም ስባኪ አንደበት የሚፈስሱ ቃላት በሰው ስሜት ላይ የሚፈጥሩት ሁኔታ እንዲህ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ስምች የሚቀበሉንና ያንን በምልክት የሚያሳዩን ከሆነ አዚያው መድረኩ ላይ ማበጥ እንጀምራለን። ሲሳካልን በቃ አኔ እኮ እደረግሁት ማስት ይቃጣናል። በዚህን ጊዜ የልባችንን ንጽህና የሚነጥቅ አብረት ይገባብናል።

መልካም ሥራቸውን ለሰዎች ኤግዚቢሽን በማቅረብ ክሰዎች ሙገሳ የፈለጉትን ፈረሳውያን እይነት ሆነን መታየቱ እይክበደንም። በዚህም ለመንፈሳውያን ሃፍረትን፥ ለእምላካችን ሃዘንን ፥ ለራሳችን ደግሞ ውርደት እናተርፋለን። ስኬት ትዕቢትን ጎትቶ ውድቀትና መሳቅ የሚዳረስ ክፉ መልእክት (ነንሮች) ሉሴልፎ እንዳይሰጠን ሲሳካልን እንፍራ እንዲሁም ትሁት እንሁን። በመንቀጥቀጥና በመደነቅ ክብሩን ክብር ለሚገባው ጌታ ማምጣት የምንችልበት አቅም እንዲፈጠርልን ጉዳዩን ለፈጣሪያችን ያለማቋረጥ በጸሎት እናቅርብ። ብዙ ወገኖችም በጸሎት ሽፋን እንዲሰጡን ድጋፋቸውን እንጠይቅ። ክመድረክ ዕብጠት እንድንድንም ያለማቋረጥ እንጸልይ።

ትወና (1ኛ ቆሮ 5:2 :8)

ቀደም ብሰን ያነሳነው የመድረክቻችን ፈተና እግዚአብሔር የሠራውን የአኛ እድርጎ ለመውሰድ የሚገፋፋንን ውስጣዊ ዝንባሌ በሚመስከት የሚገጥመንን ነው። ቀጥለን የምንናሳው የስባኪ ሌላው ጉድለት ስባኪው

የቃሉ አገልጋይ መሆኑን ረስቶት ራሱን እርቲስት ወይም ተዋናይ እድርጎ ማቅረቡ ነው። ተዋናይ ንጉስ ላይሆን መሆን ይችላል። ድሃም ላይሆን ድህነቱን ያውቅበታል። እዋቂም ሳይሆን እንደ አዋቂ መሆን አይጠፋውም። ስለሆነም የወከለውን ገጸ ባህሪ ሆኖ መልእክቱን ስተመልካች ያቀርባል። ይህን በማድረጉ ተዋናይ ሊወቀስ አይገባውም። ይልቁንም ወክሎ የተጫወተውን ባህሪ መሆን በመቻሉ በብዙዎች ይሞገሳል። ለባኪ ግን ከተዋናይ ይሰያል። ምክንያቱም የኖረውን ስመናገር መትጋት ስስሚጠበቅበት ነው። በመጀመሪያ ቃሉ እሱን ሊስውጥና በቃሉ ሥልጣንና ቁጥጥር ሥር መሆኑን ማረጋገጥና አውን ማድረግ አለበት። ያኔ በሕይወቱ ያጣጣመውን ማቅረብ ቀላል ይሆንስታል። አስበስዚያ ነገራችን ወደ ታይታ ይወርድብናል። ከቃሉ አዋጅ ነጋሪነት ይልቅ ወደ ተዋናይነት ዝቅ ያሉ ስንቶች ይሆኑ? ይህንን ስንል ያጋነንን የሚመስሳቸው ብዙዎች ናቸው።

ዛሬ ዛሬ አሳፋሪና የሚያስደነግጥ የርኩስት ሕይወት እየኖሩ ስለ ቅድስና የሚስበኩን ብዙዎች ናቸው። እምነት አጉዳይ ሆነው ስለ ታማኝነት የሚናገሩ ጥቂቶች አይደሉም። እንደውም ይህንን ሳስብ በዳንኩ ዘመን አዘውትሬ የምሰማው የተሰመደ የስባኪዎች ምሳሌ ትዝ ይለኛል። ለአናንተም ባጭሩ አንዲህ ሳቅርበው

« በአንድ ወቅት በቤቱ ችግር ያስበት ስባኪ በመልአክቱ መሐል ላይቸግረው ስስባልና ሚስት ግንኙነት እያነሳ መናገር ጀመረ። ሚስት ብታጠፋ ባል አንዱት መታህስ አንዳስበት ባል ቢያጠፋ ሚስት እንዱት መቻል አንዳስበት መናገር ቀጠለ። በተስይ በትዳር ጓደኛሞች መካከል ሊኖር ስለሚገባ ፍቅርና መተሳሰብ አንስቶ ሲተነትን ሚስት በቦታው ቆሞ የሚናገረው ባሏ ነው ወይስ በሉ ምስል የተሳከ መልአክ እስከትል ንግግሩ አስደናቂ ነበር። ስዚያማ ሚስት ባሏ መሆኑን ስታጣራ በሚቀጥለው ቀን የኔ እና የባሌ መኖሪያ እዚህ ነው ብላ አረፈችው። ለምን ቢሏት ባሌ የሰሞኑን ዓይነት አስደናቂ ነገር የሚናገረው እዚህች ቦታ ላይ ብቻ ነው አስች።»

ነገሩ በአርግጥ ሆኖ እንደሆነ አላውቅም። ግና በአባባሉ የጠሰቀ እውነት አሰ። ስባኪ የሚናገረውን ሁሉ የሚሆን ፍጹም ሰው መሆን አስበት ስማለት ባንደፍርም በሚበዛ ነገር መነቀፍ የስበትም። አማኞች ከጎሊና ያስፈ ዳኛና ፈጣሪ እስን። ያንንም ፈጣሪ በመፍራት ሊንኖር ይገባናል። ይሁን አንጂ

ማንኛውም ለሕሊናው የሚኖር መልካም ለው በሚያሸንፋቸው ሞራላዊ ጉዳዮች ላይ ወድቀን መገመት አይገባንም። ያልሆነውን ሆኖ መናገሩም ታማኝነታችንን እጅግ ይጎዳል። ስለሆነም በመድረክ ያልሆነውን ሆነን መታየት ዞሮ ዞሮ የሚጎዳው እኛኑ ስለሆነ ጠንቃቃ መሆን አለብን።

መሸቃቀጥ (ኤር 23:16-32 2ኛቆሮ 2:17 4:2)

በመድረክ ላይ የሚቆመው የቃሉ አዋጅ ነጋሪ ሌላው ድካም ለለዎች የሚያስፈልጋቸውን ሳይሆን የሚፈልጉትን መናገር ነው። ብዙ ጊዜ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር ያዘነባቸው የቃሉ መልእክተኞች ጌታ ካለው ይልቅ የለዎችን የልብ ፍላጎት በማጥናት ለእነርሱ የሚስማማውን ብቻ ለማለት በመቁረጣቸው ነበር (1ኛ ነገ 22:8-39)። እርግጥ ነው ለዎች ካሉበት ሁኔታ ጋር የሚዛመድ መልእክት ማቅረብ ይጠበቅብናል። ይህ ሲባል ግን የሳተውን የሚመልስ ተግሳጽ ÷ የተሰበረን ልብ የሚጠግን ማጽናኛ÷ እቅጣጫ ለጠፋበት ምሪት፣ ጥበብ ለጎደለው ብርሃንን ተባለ እንጂ ለዎች የሚፈልጉትን ሁሉ ለማሟላት የሚሆንን ሁኔታ እንፍጠር እልተባልንም። ለባኪን የሚሞግተው የዚህ ዘመን ሁኔታ ለዎችን ሙሉ ለሙሉ በማስደሰት ላይ የተመረኮዘ እካሔድንና አደራረግን መምረጥ ነው።

አንዲህ ዓይነቱ አገልጋይ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ለማለት አቅም የለውም። ምክንያቱም አሉን የሚነዳው ለዎች ምን ይፈልጋሉ? የሚለው የሸቀጥ ነጋዴ እስተሰሳብ ነው። በብሉይ ኪዳን ከነበሩት አገልጋዮች መካከል ሴዴቅያስ የሚባለው ለው እንዲህ ዓይነቱ መንፈስ የተጠናወተው ነበር። እሱ ራሱ ብቻ አይደለም አብረውት የተሰለፉትን በሙሉ አግዚአብሔር እንዲህ ይላል ብለው ያልተባሉትን እንዲናገሩ አስተባበረ። ከዚያማ ንጉሡ የሚፈልገውን በአንድ ድምጽ ሆነው እንዲናገሩለት እደረገ። የእግዚአብሔር ለው መጥቶ እውነተኛ መልእክት ሲያቀርብ ከሸቃጩ ሴዲቅያስ ፍጹም የተለየ ስለነበር « ሴዴቅያስ ወጥቶ ሚክያስን በጥፊ መታውና ÷ ለመሆኑ የእግዚአብሔር መንፈስ ከእኔ ስየት በኩል ዐልፎ ነው አንተን መጥቶ ያናገረህ?»/1ነገ 22:24/ አለ። ከዚህ ታሪክ አንደምንገነዘበው ሸቃጭነት ሊያይል እውነተኛ የቃሉ አገልጋዮችን በጥፊ እስከመማታት ያደርሳል። ዛሬም

የሴዴቅያስ መንፈስ የሚሠራባቸው ሸቃጮች በየመድረኩና በቤት ለቤት ፕሮግራሞች ልክ የላቸውም። ለዎች ምን ይፈልጋሉ? ብሎ በዚያ መልክ ብቻ የተቀረጸ እገልግሎት እደጋ አለው።

በሸቃጭ ኑሮና መንገድ ላይ ከእግዚአብሔር መልእክተኛነት ይልቅ ለዎች ምን ይፈልጋሉ የሚለገው የሸቀጥ ንግድ አበተሳሰብ ያይላል። ከእውነተኛ የቃሉ አገልግሎት ይልቅ ለመሸቃቀጥ ለፊ ትኩረትን የሚሰጥ አገልጋይ መለበዘን የሕይወት ዘመን ጥሪው አድርጎ መቀበል አይኖርበትም። ከመሸቀጥ የጸዳ እውነተኛ የቃሉ አገልጋይ ምእመናን የሚፈልጉትን ብቻ ሳይሆን የሚያስፈልጋቸውን ለማቅረብ ይተጋል።

ከሸቃጭነት ጋር በቀጥታ ባይገናኝም በዘመናችን ሸቃጭነትን እያበራከተው የመጣው ነገር በእሁኑ ጊዜ አገልጋዮችን ለመደገፍ የሚለጠው የፍቅር ለጥታ ነው። ዳጎስ ያለ ስጦታን በመስጠት የሚንክባከቡንና በብዙ የሚጠነቀቁልንን ክፍሎች የሚያስደስት ነገር ብቻ ለመናገር እንፈተናለን። እንዳንዶች በዚህ የሸቀጥ እንቅስቃሴ እንዲካሉ ወፈር ያለ የፍቅር ለጥታ የሚለጠ እጥቢያዎችን ማሳደዱን ተያይዘውታል። ወደማናውቀው አዲስ አካባቢ የመሔድ ጉጉት የሁሳችንም ፈተና ነው። እነዚህኞቹ ማንኛውንም ቀደም ብሎ የተያዘ ፕሮግራም ሠርዘው በምትኩ እንዲሰናዱ ሳይነግሩ ጥፍት የሚሉ ጥቂቶች አይደሉም። በምክክር ፕሮግራም ማጠፍ ኃጢአትነት የለውም። በዛሬ ዘመን ያስን ብዙ አገልጋዮች ከመርካቶ ቶሮንቶ÷ ከወሳይታ ይልቅ እትሳንታ÷ ከጎንደር ይልቅ ሃንኡቨር ስሚደረግልን ጥሪ የቅደሚያ ምላሽ እንሰጣለን። ድሮስ ከሸቃጭ ሌላ ምን ሲጠበቅ? ጌታ የሚፈልገኝ የት ነው? ብለን መጠየቅን በዚህ ወቅት ብዙዎቻችን እቁመናል። ዛሬ ተሳክቶልን በዚህ የማንወቀስ ካለን እስየው። በመሸቀጥ ፈተና ውለጥ እንዳንወድቅ ግን ይህንን ተፋላሚ ሁኔታ ከወዲሁ ተገንዝበን ተገቢውን ርምጃ ልንወስድ ይገባናል። ከላይ ያነሳነው የመድረክ ማማረጥ ፈተና በመድረክ ላይ ከሚሸቃቀጥ ጋር በለያፉ ይገናኛል። ደግሞም ያልተገባ ድርጊትን በማመለከት ምላሌነት አለው። ሁሉም መድረኮች ትኩረት እይነፈጋቸው። በሁሉም ቦታ ጌታ አለ። መድረክ የማማረጥ ፈተናን እለማለፍ ለለመድረክ ካለን የተዛባ ግንዛቤ ይመነጫል።

መርዶ ነጋሪነት – ጨካኝነት (ዘኁ 13:31-33 የሐዋ 20:29፤ ሕዝ 34:5-9)

መልካም ነገር ክመናገር ይልቅ ሁልጊዜ በስው ጉድለትና ስበራነት ላይ ያነባጠረ መልእክት የሚያቀርቡ ግለስቦችን ይመለክታል። ስውን በደለኛ የሚያደርግ መቋጫ የሌለው ዘለፋን ለታዳሚ ማጥገብ የለመዱ ስባኪያን መድረክቻችን በብዛት ያስተናግዳሉ። እነዚህ እገልጋዮች እቅምን የሚነካ ላይሆን የውስጥ ጥንካሬን የሚነጥቅ ንግግር በመናገር ይታወቃሉ። ጳውሎስ ኤፌሶንን ለቆ ሊሄድ ሊል ካቀረበው የሽኝት መልእክት እንደምንገነዘበው እስ ከለቀቀ በኋላ «ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች እንደሚነሱ እኔ እውቃለሁ..» (ሐዋ20:29) ሊል ለማለት የፈለገው ነገር መንጋውን ለራላቸው ፍላጎት የሚያለልፉ ወይም ክፋ÷ ክፉ ነገር እየተናገሩት ሊበታተን በፈጠሩት ቡድን የሚረክ ማለቱ እንደሆነ ይታመናል። እንደ እነዚህ ዓይነት ስባኪያን ሕዝቡ ሊከፋፈልና ሊበላላ ደስ ይላቸዋል። የሚደግፉቸውም ለለማያጠ እንደቀናቸው ያስባሉ። እነዚህ በመንጋው ስቃይ የሚደሰቱ ናቸው። ለለሆነም የጌታ ባሪያ ቀደም ብሎ እንደ እነዚህ ዓይነት ለምች እንደሚመጡ እስጠነቀቀ። ለዚህ ነው ጳውሎስ በዚያ ለነበሩ መሪዎችም ለመንጋውና ለራላችሁ ተጠንቀቁ ሊል ማሳሳቢያ የሰጠው። እንዲህ ዓይነት ክፉ ነገር በመናገር መንጋን የሚከፋፍሉ ዛሬም አሉ።

በብሉይ ኪዳን በአንድ ወቅት ምድራቱን እንዲስልሉ ሙሉ ከላካቸው ለምችም መሐል የሚበዙቱ በዚህ መስመር የተለለፉ ነበሩ። መልእክት ነበራቸው ግና ሕዝቡን የሚያንኳስስና የሚከፋፍል ነበር። ባቀረቡት ሪፓርት ሕዝቡን አሸበሩ። ያዘኑለትና የራሩለት መሆኑን አበታወቀው የጌታ ዓላማ ተቃራኒ በሆነ መንገድ ሊመሩት አነሳስት። ለሕዝቡም የተናገሩት መልእክት ሃሳብ ይዘት ሊፈተሽ በላተኛዋ ምድር ላትውጣችሁ መላ ፈልጉ የሚል ነበር (ዘኁ13:31-33)። በለሙት መልእክት ተቀባዮቹ ክእምላክ ዕርዳታ ይልቅ የራላቸውን ድክም እንዲሁም የጠላቶቻቸውን ጭከኔ በማስብ እንዲሸበሩ እደረጉ። ለሕዝቡም ደጋግመው እንተ አቅመቢስ ነህ÷ ዕጣ ፈንታህም ሞት ነው የሚል ነበር። በዚህ ጊዜ ሕዝቡ የኋሊት ለመሔድ ተፈተነ።

ከለሙት እስደንጋጭ መልእክት የተነሳ ምነው ክርስቲያን ባልሆንኩኝ የሚሉ ዛሬም ቢሆን ጥቂት አይደሉም። የአማኙን እለመብቃት የሚነግሩት አንዳንድ ጉድለቶቹን ያለቅጥ በመለጠጥ የሚያሰደንግጡት÷ ይህንና ይህንን ካለደረግህ ወየውልህ÷ የሚሉት ዛሬም ብዙ ናቸው። ተስፋ የለህም÷ በዚህና በዚያ ተከበሃል÷ ምንም ይውጥሃል የሚያስደንግጡ ትክረትን ከአግዚአብሔር ይልቅ ውድራላቸው የሚያመጡ ጥቂት የማይባሉ ለባኪያን ናቸው። መፍትሔውም እነርሱ ያመነጩትን ቀመር ቢከተል እንደሆነ ያስገነዝባሉ። እነዚህ መርዶ ነጋሪዎችና ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች በመባል ይታወቃሉ። የመርዶ ነገሪ ስበኪዎች ሌላው ገጽታ ጭካኔያቸው ነው።

የእንዳንድ ስባኪያን ጭካኔና - መርዶ ነጋሪነት የሚገለጥበት ሁለተኛው መንገድ መድረክን ከሚያገኙት ጥቅም እኳያ ማየታቸው ነው። እያንዳንዱ ንግግራቸው እነርሱ በሚያገኙት ጥቅም ዙሪያ የሚሽከረከር ነው። ምክንያቱም ግባቸው መንጋውን ማብላት ላይሆን መንጋውን መብላት ነውና። በብሉይ ኪዳን እንዲህ ዓይነቶቹን ለምች እግዚአብሔር ርህራሄ የጎደላቸው በህዝቤ ለቃይ የሚደስቱ አውሬዎች ብሎ በተደጋጋሚ ሲጠራቸው እናያለን (ሕዝ 34:5-12)። መንጋውን ማለማራትና እስፈላጊውን የእረኝነት እንክብካቤ መስጠት ሊኖርባቸው ይህንን ቸል ብለው ነበር። ዛሬም ቢሆን መድረክን እነርሱ ለሚያገኙት ጥቅም ብቻ ለማዋል የሚፈተኑ ብዙ ራስ ወዳድ ስባኪያን አሉ። እንደ እነዚህ ዓይነት ስባኪያን ጨካኞች ይባላሉ። መሪዎቹንም ይህንን የመለለ ጭከና የተሞለ ሆዳሞች መጥተው በእንከባከብላቸው ፈሊጥ ሕዝቡን እንዳይሸነግሉ መጠንቀቅ አለባቸው።

ታዳሚን ያለማቋረጥ በመኮነን ደስታ የሚያገኙ ወይም በለራላቸው ብቻ በማስብ የራላትው ነገር ብቻ የሚያደርጉ ለምች ከስብዕና ተራ ወጥተዋል። ለለሆነም የቃሉ አገልጋዮች የሆንን ማንኛችንም ከእንዲህ ዓይነቱ ጉድለት ነጻ ለመሆን መትጋት አለብን።

የአንዳንድ ስባኪያን መረዶ ነጋሪነት- ጭካኔ ራሱን የሚገልጠበት ሦስተኛው መንገድ ሌሎችን በእደባባይ በማሳጣት ነው። በዘለፋ የተካኑ ስባኪያን የለሚሎቻቸውን ሁኔታ ያሳገናዘበ እስደንጋጭ ነገር ያለማቋረጥ

ለመናገር ይደፍራሉ። ጉዳዩ በማይመለከታቸው አዳዲስ አማኞች፥ ተጋባዥ አንግዶች፥ አንዲሁም ስለ ወንጌል ለመስማት ዕድሉን ለመጀመሪያ ጊዜ ባገኙ አዳማጮች ፊት የማይባሉ እያሉ ነገሮች ያፈስሳሉ። በተለይ ሽማግሌዎችን ፥ የሙሉጊዜ አገልጋዮችን፥ ዘማሪዎችን ደካማ ጎን አያነሉ ያብጠለጥላሉ። አንዲህ ዓይነቱ ዘለፋ የራሱን ጊዜና ቦታ ጠብቆ ቢከናወን ያንጸል ። ይሁን እንጂ ጉዳዩ በቀጥታ የማይመለከታቸው በርካታ ሰዎች ባሉበት ቦታ ይህንን አንስቶ መናገር አግባብ አይሆንም። እንደውም ምስባኩ በተለይ የሰንበቱ ሁሉን አቃፊ አንዲሆን ቀደም ብሎ በጥልቀት ሲታሰብበት ይገባል። ስለሆነም ስባኪ የሚለውን ሲያጣ ከምሥራች ቃል አብሣሪነት ወደ መርዶ ነጋሪነት ዝቅ ይላል። አንዲህ አንዳንሆን ጠንቀቅ ማለቱ ያዋጣናል።

ከላይ በጠቀስነው ሦስት ዓይነት ጉድለቶች ውስጥ ለሚገኙ የቃሉ መልእክቶ እግዚአብሔር በተደጋጋሚ ያደረገው ጥሪ ነቢይነትን ከክህነት ጋር አቀናጅተው እንዲይዙት ማላሰብ ነው። ነቢያት ፍርድን በተናገሩበት ቅጽበት ለምልሶች የሚመጣውን ተስፋ ጭምር አብረው ይናገሩ ነበር። የክህነት አገልግሎት በለውና በአምላክ መሐል ለበጎ መቆም እንደሆነ ስብዙዎቻችን ግልጽ ነው። ስለሆነም ካህናትና የጌታ ልብ ያለቸው አረኞች የደከመውን እንዲያበረቱ፣ የባዘነውን አንዲፈልጉ፣ የቆሰለውን አንዲፈውሱ፣ የጠገበውን ከተራበው እንዲለዩ አሳስበ። ያኔ ማ ምን እንደሚፈልግ ይለያሉ። ለማን መርዶ ለማን የምሥራች እንደሚያሻ ይገነዘባሉ።

ዘጋቢነት (1ኛ ጢሞ1:5. 4:2.:7: 2ኛ ጢሞ 2:17)

በጥንቲቱ ቤተ ክርስቲያን የትውልዶችን ታሪክ በመተረክ ተረታ ተረት ላይ ጊዜያቸውን የሚያባክኑ የመድረክ አገልጋዮች ነበሩ። ጳውሎስ የአግዚአብሔር አገልጋዮች የሆኑትን ጢሞቲዎስንና ቲቶን ለአግዚአብሔር ክብርን ከማያመጣ አርባናቢስ ልፍለፋ እንዲርቁ ደጋግሞ ያሳስባቸዋል። ከቁም ነገር ይልቅ ተራ ወሬ ላይ የሚያነጣጥሩ የመድረክ አገልጋዮች ጌታን ለመምሰል የሚሆነውን ጥበብ አይለግሱንም። ይልቁንም ሕይወታችንን የሚበርዝ ክፉ ዘር በአማኞች መሐል ይዘራሉ። የቱ ለበለሰ የቱ ደግሞ ለሁሉም እንደሚሆን ስለማያውቁ ሕዝቡን ውዝግብ ውስጥ የሚከት ጥንቃቄ

የጎደለው ንግግር ይናገራሉ። ታዲያ ዛሬ ዛሬም ምስባኮቻችን በእንደእነዚህ ዓይነቶቹ ግለሰቦች እየተጨናነቁ ስናይ ለቤቱ የሚገደን በሙሉ ምስባኩን ከዚህ ተጽእኖ እንዲላቀቅ ተገቢውን ርምጃ ለመውሰድ ምን መደረግ አለበት የሚለውን ጥያቄ ወይቀን አስተማማኝ ምላሽ ማግኘት አለብን።

ስብከት በቃሉ ውስጥ ያገኘነውን ብርሃን አግዚአብሔር እንዲህ ይላል ብሎ ከጌታ የተሰጠን መልእክት ማቅረብ ነው። ይሁን እንጂ ለዘጋቢያን ስብከት ማለት በሳምንቱ ምን እንደተደረገ፥ ማ ምን እንዳለ፥ ተረታ ተረቱን በአደባባይ መናገር ነው። እንደውም ንግግራቸው እንዲሞቅላቸው በአደባባይ እንዲያካፍሉት ያልተፈቀደውን የጓዳን ምስጢር በድፍረት ገሐድ ያደርጋሉ። የምስጢሩ ባለቤቶችን አስፈቅዶ ለትምህርት የሚሆነውን ለሕዝቡ መግለጥ እግባብ ቢሆንም፥ ያለ ፈቃድ የብዙዎችን ምስጢር እደባባይ ማባከን ግን የተገባ አለመሆኑን አይገነዘቡም። ስለሆነም ለጥቂቶች ብቻ እንዲጠበቅ የሚፈለግ ምስጢር በዘጋቢያን ስባኪዎች እደባባይ መውጣቱ እየተለመደ የመጣ ጉዳይ ሆኖአል። መድረኮቻችንን ዘጋቢያን አጣበውታል ቢባል ማጋነን አይሆንም።

አንዲህ ባለ መንገድ ምስባኩ ከተልእኮው ዝቅ ያለ ነገር ሲሠራ ጌታን በቅንነት በንጽሕና እናገለግላለን የምንል ሁሉ እንደ ቃሉ የሆነ ነገር በምስባኩ እንዲለመድ ዋጋ መከፈል አለብን። ስለሆነም አንዲተላለፍ የምንፈልገው በተከታታይ ርዕስ የተቀረጸ መልእክት ከሌለን ለሪፓርት እቅራቢዎች ምስባኩን ከመልቀቅ ሕዝቡን ለጽሞና በአምላክ ፊት መጥራት የተሻለ ነው። ስለሆነም ከመድረኮቻችን የዘጋቢያን መቀረጫ የሌለው ወሬ እንዲገታ፥ ምስባኩ ላይ ማን መቆም እንዳለበት በትክክል መወሰን አለበት። አሉባልተኛ ዘጋቢያን በመድረኩ የነሰነሱትን መርዝ ከሕዝቡ ለማውጣት ሌላ የቤት ሥራ ከመቀበልና በዚህ አላስፈላጊ ድካም ውስጥ ከመግባት ቀድሞውኑ በምስባኩ እንዳይቆሙ ጥሩ ዘብ ማቆም ይገባናል። እስከለዚያ በእነርሱ የለሰጠነው መንፈስ ገሸር ይሆንና ቤቶ ክርስቲያን በወሬኞች ትሞላለች። ስለዚህ ጠንቀቅ ማለቱ ይበጃል።

ተሳዳቢነት (ይሁዳ ፡8-10)

ዛሬ ዛሬ የቃሉ አዋጅ ነጋሪ ከመሆን ይልቅ ሰብዙዎች መድረክ ላይ ወጥቶ መሳደብ ቀላል አየሆነ መጥቷል። ሕዝቡ ጌታ ምን ይለኛል? በሚል ፍርሃት በጥሞና መጥቶ፥ ስድብና ዘለፋ ጠግቦ የሚሄድበት ሁኔታ ጥቂት አይደለም። ለምሳሌ እስቲ የሚከተለውን እባባል እንይ

አሜን በል እባክህ!! አሜን ስል!!!

ደነዝ ሁሉ!! እትፍዘዝ!!! ፈዛዛ ሁሉ!!

ነቅነቅ ያለ አሜን!! እረ እባክህ!!

ነቅነቅ ያለ አሜን እምጣ እባክህ ወዘተ.. የመሳሰሉት አባባሎች መድረክ ላይ የሚስተዋሉ ጉዳዮች ከሆኑ ዋል አደር ብለዋል። የሰውን ጤነኛ ስሜት ያላገናዘበ ስድንጋይና ለዛፍ የምንናገር እስኪመስለን ድረስ ሊስሙን የተስለሰቡ ስዎችን ማዋረድ የእዳባባይ ጉዳይ ሆኖአል። ይህ ብዙዎችን የሚስቀጥጥ ሳይሆን የሚያስቃቸው ክስተት መሆኑ ደግሞ ይገርማል። ቢሳቅላቸው ከልብ የተወደዱ መስሎአቸው አባባሎችን በየቀኑ መፈብረክ እየለመዱ የመጡ ደግሞ ብዙዎች ናቸው።

የተወቀስበት መድረክ ሌላ ሆኖ ሳለ በየመድረኩ ምላሽ ለመስጠት የደፈሩ እዚህ መጥቀስ የማልፈልገውን ተራ ስድብ በመድረክ ላይ ለመናገር ያልፈሩ አንድ ስባኪ በቅርቡ ስምቼአለሁኝ። ሊያነጋግራቸው ስሚፈልግ ሁሉ በዚያ መድረክ አድራሻቸውን ሰለ ሰጡ ላነጋግራቸውና በማስተምርበት መንፈሳዊ ኮሌጅ ልጋብዛቸው ፈቃዴ ነበረ። ይሁን እንጂ ያነጋገራቸው ወዳጀ ብዙ ስው አነጋግሮአቸው ስለደከማቸው እንድተዋቸው ተማጸነኝና ተውኩት። የታወቁት ግለሰብ መድረክ ላይ እንዲህ ደፍረው ከግለሰቦች ጋር ከተጨቃጨቁ በዕሰቱ ጌታ ምን ይለኛል? ብሎ ለመጣው ሕዝብ አላዘኑለትም ማለት ነው። እርግጠኛ ነኝ ይህ ዘለፋ ያየለበት፥ ሙግት የበዛበት መልእክት የተላለፈ ዕለት ብዙ ምእመናን ይህንን ስዎቹ የሚለሙበት ሌላ መድረክ የለምን? ሳይሉ የሚቀሩ እይመስለኝም። ግና ምን ምርጫ አላቸው? ዝም ብሎ ከማደመጥ በለተቀር። ሰብኩት የእንድ እቅጣጫ ግንኙነት ነውና።

ወገኖች በመድረኩ ላይ የጌታ ወኪል እንጂ የራሳችን ጠበቃ አለመሆናችን ገሐድ ሊሆንልን ይገባል። የሚያዋርዱን ጨካኞች እንኳን

የሚያዋርደንና አገልግሎታችንን የሚያንኳስስ ነገር ቢያደርጉ እንኳን ይህንን በፈጸመበት ጉባኤ ዕድሉን ጠይቆ መናገር ወይም ሌሎች በሪፓርት መልክ ምላሽ እንዲሰጡ መጋበዝ ጨዋነት ይመስለኛል። ጌታ እንዲያስተምረን እንጸልይ ብለን ከምእመኑ ጋር ከጸለይን በኋላ መድረኩን እኛው ብቻ ብንጠቀልለው ከመንፈስ ቅዱስ ተልከን የምንሰጠውን ነገር እናጓድላለን። ከጌታ ጋር ቆይተው መልእክት ካገኙ በኋላ መልእክቱን እንዴት ማስተላለፍ እንዳለባቸው ባለማወቅና በባህሪ የሚቸገሩ እንዳሉ ቢታመንም ተራ ተሳዳቢነት ግን የችግሩን ውስብስነት ሊያሳየን ይገባል።

በምንም መልኩ የቤተ ክርስቲያን መድረኮች ለሰድብ መዋል የለባቸውም። አንዳንዶች እገሌ እንዲሁ በአፋ ይናገራል እንጂ በሆዱ ምንም የለም ይላሉ። ግን ይህ እውነት አይደለም። በዚህ አካባ የተስተካከለ እቋም እንድንይዝ የሚያግዘንን ብርሃን የሚሰጥ አንድ ምሳሌን ከአንድ ጋዜጣ አነበብኩና ለእርምት ሆነኝ። እኔ እኮ እፌ ነው እንጂ በሆዴ ምንም የሰ በማሰት ብዙዎቻችን እንናገራለን። ሰለ ሌሎቹም ተናጋሪና ተሳዳቢ ስዎች ይህንኑ እንላለን። ይሁን እንጂ ይህ እውነት እንዳልሆነ በቅርቡ ያነበብኩት ጋዜጣ ጥሩ ምክር በሚከተለው መልኩ ይሰጣል፡

> « በአንድ ቤተ ክርስቲያን አባል የሆነች ቤትንሽም በትልቁም ቱግ የምትል ተናጋሪና ተሳዳቢ ሴት ነበረች። አንድ ቀን የቤክርስቲያኗ ቄስ አጠገቧ እያሉ አንዲትን እህት ሙልጭ አድርጋ ትሰድባለች። እንደገና ወደ ቄሱ ዞራ ቄሰዬ ይቅርታ እኔ እንደቡቴ እንጂ ሆዴ ንጹሕ ነው አለች። አንዱ ከተናገርኩ በኋላ፥ እንደገም ብን ይላል። በሆዱ ምንም የለ ትላቸዋለች። ቄሱም ቀበል አድርገው ልጄ ድማሚትም እንደዚሁ ነው። አንዱ ከፈነዳና ካፈራረሰ በኋላ ዝም ነው የሚለው አሏት። ወገኖቼ እንደበት አሳት ነው። አንዱ ስንናገር የምናፈርሰው ብዙ ነውና እንጠንቀቅ»[6]

በአንድም በሌላም መንገድ መድረኩን የሚያላድፉ ነገሮች እንዲገቱ ይገደናል የምንል ሁላችን የበኩላችንን ማዋጣት አለብን። በየጊዜው ዕሁድ እያነሳን ከማብጠልጠል ለለ ዕሁድ በጥልቀት በማስብና ቦታውን ለሚመለከታቸው ሁነኛ ለምች ብቻ ለመልቀቅ መስናዳት አለብን።

---

[6] Gesam Spiritual News Paper No. 8 Addis Ababa: Gesam PLC, April 1996 issue (pp12)

ቀልደኛነት-ፈዘኛነት (አፌ 4:29 :5:4)

ፈገግ የሚያደርጉ ታሪክችን በመጠቀም ቁምነገርን መግለጽ እግብብ ነው። በተለይ ከምንናገርበት ሃሳብ ጋር በቀጥታ የሚገናኝ፥ ሃሳቡንም የሚያጎላ፥ የሚያዝናና እና ደስታን እውን የሚያደርግ ነገር በመጠቀም እውነት መግለጽ መቻል ውብ ነው። ይሁን እንጂ ከመልእክቱ ሃሳብ ጋር የማይገናኝና የመጽሐፍ ቅዱስ እውነትን ለማጉላት የማይጠቅም ተራ ንግግር ትኩረትን ከማዛባት ያለፈ ሥራን አይሠራም። ቀልደኛነትን መጽሐፍ ቅዱስም ምእመኑም እንደማይደግፈው እየታወቀ እንዳንድ ሰባኪያን በመድረክ ላይ ሲቆሙ ኮሜዲያን የመሆን ጥማት ይታይባቸዋል።

እንድ ቦታ እንደሄውልት ተገትሮ ፈገግታ በጎደለው የማይሰብ ቁመና መታየት ባይመከርም እንዲሁ ስሜትን እየከረከሩ ÷ ጉባኤን በአብዛኛው እያሳቁ፥ ነጥብ ሳያስጨብጡ የተሰጠን ጊዜ በከንቱ ማባከን የቃሉ ባለቤት የሆነውን ጌታችንን ያስቆጣል። በተጫማሪም እኛን ኮሜዲያን መሆን የሚቃጣንን ሰባኪያን በሕዝቡ ዘንድ በተሰይም በበሰሉት ያስንቀናል። ስለሆነም እንዲህ ዓይነቱን የማይገባ ነገር ሰባኪዎች በተቀደሰው መድረክ ላይ ሲያደርጉት መድፈር የሰባቸውም። በእንዲህ ዓይነት ችግር ውስጥ ራሳቸውን ደጋግመው የሚያገኙ ካሉ በታቸው በብክት ሳይሆን ኮሜዲያን መሆን ስለሆነ ወደ መደበኛ ኮሜዲያንነት ቢቀየሩ ሳይሸላቸው አይቀርም። ጉዳዩ በመጽሐፉ የተጠቀሰ ሌላ ቀልድ ይመስላል።

በጌታ ቤት፥ ስሙን ጠርተን እንስብክለን ብለን በምንልበት ቦታ የጌታን ወቅታዊ መልእክት ለሕዝብ ለማድረስ መትጋት በመድረክ ከምንላቸው የራሳችን ነገሮች መቅደም አለበት። ስለሆነም ከእኛ የማላቅ ብቃትና ችሎታ ይልቅ የእምላካችንን ምህረትና ይቅርታን ማወጅ ቀዳሚ ትኩረታችን ማድረግ እግብብ ነው። ስንችል በሚያስፈግጉ ምሳሌዎችና ታሪኮችን መልእክትን ማስጨበጥ ስህተትነት የለውም። ይህም የተሰየ ስጦታን ይጠይቃል። ተራ ፌዝ ግን እኛን እንድንናቅ ያደርጋል እንጂ አይጠቅምም። ስለሆነም ሰባኪው የሚነቀፍበትን እርባና የሌለውን ቀልደኛነት የማያንጽ መሆኑን ተገንዝቦ የመድረክ ቀልድ ከሕይወቱ እንዲወገድ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል።

አቤቱታ (ማር 9:33-36 እና ማር 10:35-45)

አቤቱታ ብለን በምናነሰው የሰባኪው አሉታዊ ገጽታ የምናነሳው የሚከተሰውን ነው። ታፍኖ የከረመ፥ በውስጣችን ታጭቆ የሰነበተ ነገርን እንዲህ እንድናደርግ ባልተፈቀደልን መድረክ ላይ ለማድረግ መድፈርን የሚመለከት የሰባኪው ድካም ነው። ለአያሌ ቀናት ሳምንታት እንዲሁም ወራት በናፍቆት ስንጠብቀው የቆየነው መድረክ ስናገኝ ከፊት ለፊታችን የሚደቀን ፈተና ነው። በዚህ ጊዜ እንዲህ ዓይነቱን ነገር ለማድረግ የምንደፍረው ቀዳዳ ሲገኝ፥ ስለ ራስ እኔ ያለኝ እውነት ይሻላል ብለን ስናስብና ለዚያ ይፋዊ ማረጋገጫ የሚሰጠን ሲጠፋ፥ የመድረክ ላይ አቤቱታን እንደመሣሪያ በመጠቀም እኛው ራሳችን ለራሳችን ድጋፍ ለማሰባሰብ ጥረት ስናደርግ ፍረዱኝ የሚል ደምጽ እናሰማለን። ደቀመዛሙርት ለመናገር ዕድሉ በተሰጣቸው ጊዜ ግማሾቹ በዘመድ፥ ግማሾቹ ደግሞ የራሳቸውን እንደበት በመጠቀም ምኞታቸውን ለማስተዋወቅ ደፈሩ። በዘመናችንም እንዲህ ዓይነቱን ዝንባሌ በልዩ ልዩ መልኩ መድረኩ ላይ እናያዋለን። በልዩ ልዩ ቡድኖች ከመድረኩ በስተጀርባ ትግል በሚደረግበት ቤተክርስቲያን ከጓዳ የተረፈው ቅሬታ መድረኩ ላይ አፈትልኮ የሚወጣበት ጊዜ ብዙ ነው። ይህም ምእመኑን ግራ ያጋባዋል። ተወቃሽ ወይም ተሳጪ የሆነውን ክፍል ያበሳጨዋል። ታዳሚውን ደግሞ የት ልድረስ በሚል ድንጋጤ ይሞላዋል። ምክንያቱም አቤቱታን በየጣቢያው በተለያየ መልኩ ሲያሰተናግድ ቆይቶ መጥቶ ጸሎት ቤት ምስባክ ላይ ብቅ ሲልበት «ምነው!!» ያሰኘዋል። ስለዚህ ነው፥ ሌላው ልባችንን በድካም የሞላ አስደንጋጭ የሰባኪው አሉታዊ ገጽታ ማላዘን ነው የምንለው።

እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ሲሉ ቆሞው እኔ እንዲህ አሳሰሁ የሚሉንን ሰባኪ ተብዬዎች ዛሬም መድረክቻችን ያስተናግዳሉ። በመሠረቱ እንደ ሰባኪ በምስባኩ ስንቆም የተሳከን ፖስተኞች እንጂ የራሳችንን እጀንዳ በክርክር ለማሳመን የቆምን ጠበቆች አይደለንም። እንዲህ ዓይነቱን መንፈስ መድረኩ አይፈቅድም። ይሁን እንጂ ከመድረኩ ባህሪ ውጭ በስሰት የተገኘ ችውን ዕድላችንን ለመጠቀም ሕዝቡ ይፍረደኝ፥ ይይልኝ ብለን እሮሮ

ማለማት ላንዳንዶቻችን ቀሎናል። እንደውም ለአንዳንዶቻችን የቃሉን መልእክት ሳይሆን ቅሬታችንን መዘርገፍ የተለመደ ጉዳይ እየሆነብን መምጣቱ አሳዛኝ ከስተት ነው።

እንዲህ ዓይነቱ አሉታዊ ድርጊት አዘውትሮ የሚፈጸም ስህተት እየሆነ መምጣቱ ስለ መድረኮቻችን በጥልቀት እንድናስብ ግድ ሊሰን ይገባል። አቤቱታ መቅረብ ቢኖርበትም ሕዝቡ ቀደም ብሎ ተሰናድቶ በመጣበት ጊዜ እንጂ ድንገትና ወረራ ተፈጽሞበት ሊሆን አይገባም። ባልጠበቀው ነገር ሕዝባችንን ከመድረክ ማስደንገጥ ለምደናልና ይህ የሚታረምበትን መንገድ በጋራ እንፈልግ። ብዙ ጊዜ በዚህ የምንወቀሰው በቤተ ክርስቲያን በልዩ ልዩ የአገልግሎት ክፍሎች ተሰልፈን የምናገለግለው ነንና ለዚህ ችግር መቀረፍ የበኩላችን ለማዋጣት እንትጋ።

አሉባልታ (ሮሜ 16፡18 2ኛ ቆሮ 6፡5-8 ፊሊጵ 3፡17-21)

በቅርብ ጊዜ የተነሱ አንዳንድ ለባኪያን ንግግራቸውን ለመጀመር ለሳምታ ከለጡ በኋላ በቀጥታ ደረሰብኝ ከሚሉት ነገር ይነሳሉ። አንዳንዶቹም ገና ንግግር ሊጀምሩ «ያሳዝናል ወገኖች በቅርብ ጊዜ አንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲህ ሆነ፥ እኔ እንዲህ ብየ ለስዓለጽኩ አንዱ መሪ ተብዬ አገልግሎቴን እንዲህ እና እንዲያ ሊያደርግ ነበር። ነገር ግን ጌታ ታደገኝ።» በማለት ከዕለቱ መልእክታቸው ጋር የማይገናኝ ወይም ለምሳሌነት የማያገለግል ነገር ይናገራሉ። ይህን ብለው በመጀመራቸውም ጉባኤ ውስጥ ካሉ ልዩ ልዩ አመለካከት ካሳቸው ለዎች ጋር ትንንቅ መግጠሙን ሥራዬ ብለው ይያያዙታል። አብዛኞቹ ይህንን የሚያደርጉት እንዲያው መተነኪከስ አመል ሆኖባቸው ነው እንጂ ይህንን ማለታቸው ፋይዳ ኖሮት አይደለም። ከመድረክ አገልግሎት በኋላ ለምን እንዲህ አልከ ሊባሉ ማለታቸው እንኳን ትዝ አይላቸውም።

ከዚህ አኳያ በአንድ ወቅት የገጠመኝን አንድ ተግባራዊ ነገር ላንሳ፥ ነገሩ እንዲህ ነው። ብዙዎቻችን የዕለቱን ለብከት በጉጉት ስንወብቅ ለባኪው መልእክቱን በጀመረ ጥቂት ደቂቃዎች እንዲህ አለ፡-

«አንዳንዶቻችሁ ይህ ስብከት ከምዕመኑ ወቅታዊ ሁኔታ ጋር ይዛመዳል ወይ? ስምን እንዲህ ዓይነቱን ነገር በዚህ ጊዜ ይናገራል? ይህ ወቅቱን ሳያነብ የሚናገር ስባኪ ነው። ሌላም ሌላ እያላችሁ እንደሆነ አገምታለሁ። አንዳንዶቹ ደፋሮች ደግሞ ለመሆኑ አሁን እንዲህ ማለት ይገባል? ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል። ጨምራችሁም ምናልባትም ይህ የስብከት ዘዴ ያልተማረ ትሰኝ ይሆናል።» ካለ በኋላ ወዲያው በቁጣ አሱነቱ ተቀይሮ «እኔ ኑሮ በዘዴ ነው እንጂ ስብከት በዘዴ አላውቅም። ዘዴህን አዚያ ጣለው!!!። ዋናው የሚያስፈልገው ከጌታ የስማሁት ድምጽ ነው» አለ።

በአርግጥ ድምጹን ለምቶ ከሆነ አለየው። ነገር ግን መድረክ ላይ ሆኖ ጉበኤ ውስጥ ካሉ ልዩ ልዩ አመለካከት ካላቸው ለዎች ጋር ንትረከን ምን አመጣው? በአለቱ ከምናካፍለው ነገር ጋር በቀጥታ የማይገናኙ ነገሮችን ለለራሳችንና ለለሌሎች መናገር ግን ከአሉባልታነት አያልፍም። ለአብዛኞቹ ለባኪዎቻችን «ጌታ በድምጽ እንዲህ አለኝ» ማምለጫ ናት።

መድረኮቻችንን ያጨናነቀው ሌላው ነገር በመረጃ ያልተደገፈ ወሬ ነው። በተሳዳቢነት አኖው ኃላፊነቱን ለንወበድ በአሉባልታ ሌሎችን ተተግነን ከቃሉ ይልቅ ወሬን ለማውራት የምንጠቀምበት ለልት ሲሆን ይስተዋላል። እንዲህ ዓይነቱ ከመልእክታችን ጋር ያልተዛመደ ንግግር ሰፍሳፊነት ነው። ለለሆነም ያልሆነውን ሆነ፥ የሆነውን ደግሞ ያለቅጥ ለጥቦ፥ ማጣፊጫ ጨምሮ፥ ባልተለመዱ የአነጋገር ዘይቤዎች ሕዝቡን ማለደንገጥ አይበጅም። አሁን አሁን እያየለ በመምጣቱ በአፋጣኝ እርምት ሊወለድበት ይገባል። ብዙ ጊዜ አሉባልታ ለለባኪዎች ቀላል የሚሆንላቸው አናሳ ዝግጅት ሲኖራቸው እንደሆነ ይታመናል።

ስለሆነም ሳይዘጋጁና የጌታን ፊት ሳይፈልጉ አነርሱኑ የሚያስገምት፥ ለሚውን ምነው እንደዚህ ባይሉ የሚያለኝ ጭንቅ ውስጥ የሚከቱ፥ ከመልእከተኛነት ይልቅ ለአሉባልተኛነት ራሳቸውን ለለጡ የመድረክ ለዎች፥ ምለባኩ ክፍት መሆን የለበትም። በዚህ መስመር ነገራችን መልከ ለማሊያዝ ግዎግማ ጥሩ መሳሪያ ሆኖ ሊያገለግለን ይችላል። ምስባኩም ከእንዲህ ዓይነቱ የአደባባይ አድፍ ይጸዳ ዘንድ በየሳምንቱ የዕለቱ ለብከት ጥሩ ነበር መጥፎ ከማለት ያለፈ ጠበት ያለ ፍተሻን የአጥቢያ ቤተክርስቲያናት ባሕል ማድረግ አለባቸው።

ግነት - ቅጥፈት (ኤፌ 4:25 5:6 ቆላ 2:4 ኤር 23:8- 32 ዘካ 8:16)

በመሠረቱ በተቀደሰው ምስባክ ለመቆም የመጀመሪያውና ዋናው ቅደመ ሁኔታ አውነትን መናገር ነው:: ይሁን እንጂ ቀጣፊዎች መድረኩን ካጣበቡ ቀናት ተቆጠሩ:: በእደባባይ መዋሸት የሚያሳፍር መሆኑ ከቀረ ሰነበተ:: ቀንሶና ጨምሮ መናገር ሕሲናን የሚለቀጥጥ ጉዳይ መሆኑ አቁሟል:: ስለሆነም መድረኮቻችን ኃይል ሲያንሳቸው ይለተዋላል:: እውነት ከራቀው ኑሮ ሕይወትን የሚለውጥ መልካም ነገር ይፈሳል ብሎ ማለብ እንዴት ይቻላል? ግና ብዙዎቻችን እንዲህ ዓይነቱን ነገር በቀላሉ እናያለን:: ሰምሳሌ ከጥቂት ዓመታት በፊት በአዲስ አበባ መሠረተ ክርስቶስ ኮንፍራንሰ ላይ እንዲናገር የተጋበዘው እንድ ተናጋሪ ከመጠን ያለፈ የተጋነነ ነገር ፍርሃትና ድንጋጤ ሳይገባው ይናገር ነበር::

የአዲስ አበባ ስታዲየም ሜዳውን ጨምሮ ጢም ብሎ ቢሞላ አንኳን የሚያስተናግደው 35000 (ሠለሳ አምስት ሺህ) ለው ነው:: ያንን እንኳን ለማስተናገድ ምን ያህል የድምጽ መሣሪያ ችግር እንደነበር እየታወቀ ያ ሰው ደቡብ ሄጀ 200000 (ሁለት መቶ ሺህ) ተሳታፊ ባለበት ሳገለግል ሲል ብዙዎችን እልገረማቸውም:: የቁጥር ለዎች ግን ከዚያ ጉባኤ በሃዘን አንደወጡ አስታውሳለሁኝ:: ለዚህ ለው ወይ ቁጥር ትርጉም የለውም ወይም ደግሞ እንደተመቸው መናገር ለምዶበታል:: ያልተፈወለውን ተፈወለ ማለት ያልተፈታውን ችግር ተፈቷል ማለት ብዙ ምዕመናን አደናግሯል:: ይህንን ለል በእግዚአብሔር መናገርና በተአምራዊ አደራረጉ እንደማያምን ለው እንድናገር አልሻም:: ጌታ ዛሬም ይናገራል:: በተአምራዊ አደራረጉ ከተጠቀሙት መሐል ነኝ:: ግና ቅጥፈት ወይም ግነት ለጌታ አንዳች እንደማይጨምርለት አውቃለሁ::

ለጌታችን ክብርን የምናመጣለት በእውነት አንጂ በውሸት እለመሆኑን ግድ ካለን ግነትና ቅጥፈት ከመድረኩ እንዲወገዱ የበኩሳችንን እናዋጣለን:: ይሁን እንጂ በዚህ መስመር በቅጥፈት ተስፋ ላይ ቆመው ነገሩ ባልሆነ ጊዜ ከጉዳታቸው ያለገገሙ ዛሬም ብዙ ናቸው:: ባዶ ተስፋ ተለጥቷቸው ያንን ሲጠብቁ ነገሩ የተገላቢጦሽ የሆነባቸውን ቤታቸው ይቁጠራቸው:: ይድናሉ ተብለው የሞቱ፥ ይሆንላችኋል ተብለው የተባሉት ያልደረለላቸው እምነት

እንደሌላቸው ተቆጥረው የተኮነኑ ጥቂቶች እይደሉም:: ከዚህ አኳያ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያናት የደረለው ጉዳት በቀላሉ እይገመትም:: ወደ ፊት በዚህ ርዕለ ጉዳይ በጥልቀት የሚያስነብቡን ጽሐፍት ብቅ እንደሚሉ አልጠራጠርም::

የጆሮ ሚዛን የማይመጥን አደንቋሪ ጨኸት

ይኸኛው የሰባኪው ችግር ከለልጣኔ ጋር ይያያዛል:: ድሮ ድሮ ለው በበዛበት ሥፍራ ለበኪያን ቢጮኹ ይታዘንላቸዋል:1 ምክንያቱም በጉጉት ሲያዳምጣቸው ለቆመው ሕዝብ በሹክሹክታ ቢናገሩ የሕዝቡን ፍላጎት አይደርሉምና:: ለሕዝቡ ጆሮ እንዲደርስ የሚፈልጉት መልእክታቸው በሚሰማ ድምጽ እንዲደርስላቸው የቻሉትን ያህል ይጮኻሉ:: እንዲያ ሆኖ መልእክታቸው ለሕዝቡ ሲደርስላቸው ደስታን ይፈጥርላቸዋል:: ዛሬም ይህ ችግር በአያሌ የኢትዮጵያ ገጠሮች በላልተቀረፈ ብዙ ሰባኪዎች እንዲጮኹ ይገደዳሉ:: በዚህ መንገድ መልእክታቸውን ለማድረስ ጉሮሮእቸው የሚሰነጣጠቅ ለበኪያን ብዙ ናቸው:: ጌታ ይድረስላቸውና ትንሽ ይተንፍሉ:: መልእክትን ለእድማጭ ለማድረስ የሚደከም ድካም ይበረታታል::

ድምጽ ማጉያ መሳሪያዎች ከመጡ በኋላ በከተሞች እካባቢ የሰባኪዎች ድካም ተቀንሷል:: ስልጣኔ በጨመረ ቁጥር ድምጽን በማጉላት ረገድ ያለው ችግር በከተሞች አካባበቢ አየተቀረፈ መጥቷል:: ቢዘህ መንገድ በፈጠራ የተሰሉትን ስናመስግን የዚህ ሁሉ ችሎታ ምንጭ የሆነውን እምላክ ከፍ ከፍ እናደርጋለን:: ይሁን እንጂ ሲረዳን የተፈጠርልን ይህ መሣሪያ እደናቃፊ ሲሆን ማየት እንዴት ያስቸግራል? መድረክ እካባቢ ቢሆኑ ይበጃል በምንላቸው ነገሮች ዙሪያ ስንነጋገር ከላይ ቀደም ብዬ ካነሳሁት እባቴ ጋር ብዙ ተባብሰናል:: በዛሬው ጸሎት ቤት የምስባክ አደረጃጀቶች መሻሻል ያለባቸው ብዙ ነገሮች እንዳሉ ሁሰታችንም አሰመርንበት:: እርሱ የኤሌክትሮኒስ ጥበብ ባለሙያም ጭምር ስለሆነ የደምጽ ማጉያ እጠቃቀምን አስመልክቶ የሚተከተለውን ተናገረ:-

> «በተስይ በደምጽ ማጉያ ታግዞ የሚደረገው የሰባኪው ጨኸት እኔና መስሎችን ይረብሻል:: ድምጽ ማጉያ የሚያስፈልገው መልእክተኛው የሚለውን አዳማጭ እንዲሰማው ነው:: ድምጽማጉያው ከሚገባው በላይ ከፍ ሲል ከመጮኹም

በላይ ሰባኪው የሚለው አንዳንዱ ቃላት አይሰማም። ሁለት ዓይነት ማይክሮፎኖች አሉ። ለአንድ ሰው የተሠሩ ክቅርብ ድምጽ የሚቀበሉና (Unidirectional) ከየአቅጣጫው ድምጽ የሚቀበሉ የብዙ ድምጾ ለመሳብ የተሠሩ (Omnidirectional) ናቸው። ሁሉም ከተናጋሪው የተወሰነ ርቀት መሆን አለባቸው። በጣም ቢተርቡ ድምጹ ግልጽ አይሆንም። አንዳንድ ሰባኪዎች የሚሉትን ካልሰሙ የሰበሰ አይመስላቸውም። ድምጹን ከፍ አድርገው ይላሉ። አስኪያፏጭ (Feedback) ድረስ ድምጹን ከፍ ይደረግ ይላሉ። ዘመኑ የጩኸት መሆኑን አያሰሁ። መጮኹን የሚፈልግ ከመቶ በጉቱ ይሆን? በዚህ ጉዳይ የማን ፍላጎት ይፈጸም? የሰባኪው ወይስ ያብዛኛው ምዕመን? ስለዚህ ነገር ብዙ ሃሳብ ጠይቄአለሁ። አብዛኛው ሰው ጩኸት አይፈልግም። እኔም አልወድም። በመቻል ቁጭ እላለሁ። ድምጽ የሚቀንስልኝም የጆሮ ውታፍም (Earplug) ገዝቻለሁ። እስከ መቼ ልቻለው? የኔስ ብጤው ስንቱ ይሆን?»[7]

በማለት በውስጡ የታመቀ ምሬቱን ገልጸልኛል። አሉንና አሉን መለሎች እያለመረርን፥ እንግዶችን እያስደነገጥን፥ ጆሮን በሚለቀጥጥ ድምጽ ለመጠቀም የምንፈልገው ለምንድንነው? ባለሙያዎችስ እንዲህ ዓይነቱ ትርምስ በጸሎት ቤት ሲፈጠር ዝም የምትሉን እስከመቼ ነው? እኛስ ለባኪዎች የሙያው ለዎች ነገሮች አድማጮችን ሳይረብሽ የሚከናወኑበት መንገድ አንዳለ ከነገሩን ለምን አንለማቸውም? ይህ በመልእክታችን ላይ አሉታዊ ተጽእኖን የሚያመጣ ከሆነ ለምን እናስወግደውም? ወገኖች የባለሙያዎቻችንን ምክር ገንዘብ የምናደርግበትን መንገድ ብንፈጥር እንጠቀማለን እንጂ እንጎዳም። ስለዚህም ክድምጽ ማጉያ አኳያ የሚነሱ ችግሮችን ክሙያው ለዎች የሚቀርብልንን ሃሳብ በመተግበር ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት እናድርግ።

አግረ መንገዴን ስለ ማይክሮፎን አጠቃቀም ጥቂት ብየ ባልፍ የሚጠቅም መሰለኝ። ይህንን በንዑስ ርዕስ ስር ባደርገው ጥቅስ ስለማላገኝለት ተያያዥ ክሆነበት ሃሳብ ጋር የሚጠቅም ማሰላቢያ ብለጥበት መልካም መስሎ ታየኝ። አንዳንድ ሰባኪዎች መናገሪያውን «ባልተወለደ አንጀታቸው» አናት አናቱን ሲያሳነት ይስተዋላል። የማይክሮፎን ሽቦዎች በጣም ስስ ክመሆናቸው የተነሳ በቀላሉ ይላቀቃሉ። እነዚህ በቀላሉ የሚረግፉ ሽቦዎች አጥቢያ ቤተ

[7] Million Belete Informal Talk with the MK college staff: Addis Ababa Meserete Kristos College, June 2,2004

ክርስቲያናትን ላልተፈለገ ወጪ ይዳርጋሉ። ስለሆነም ሁሉን በአግባብና በስርዓት ማድረግ ይጠቅማል። ለምሳሌ መሥራት አለመሥራቱን ለማረጋገጥ ትንፋሽን መጠቀም ወይም ደግሞ መክራ የሚሉ ቃላትን መጠቀም ወይም ደግም ለለምታ ለመለጠት መክራ ማድረግ ይበጃል። በየሐዲንበት አብያተ ክርስቲያናትን እንዳናደኽይ መጠንቀቅ ልባምነት ነው።

የውይይት ጥያቄዎች

1. የሰባኪዎች አሉታዊ ገጽታ እንዲወገድ ምን መደረግ አለበት? የአናንተ ቀደም ያለ ልምምድ ከዚህ አኳያ ምን ይመስላል?
2. እዚህ ያልተጠቀሱ የሰባኪው አሉታዊ ገጽታዎች ምን ምን ናቸው?
3. ለሰባኪው አሉታዊ ገጽታ መበራከት የቤተክርስቲያን ድርሻ ምን ያህል ነው ትላላችሁ ?
4. አገልግሎት ከጥቅም ጋር እንዳይያዝ ምን መደረግ አለበት?
5. ጉድለት እየታየ አንዳንድ ለዎችን በተዳጋጋሚ በምስባኩ የምናየው ለምንድነው?
6. ሁነኛ የመድረክ አገልጋዮች እንዲበራከቱ ምን መደረግ አለበት?
7. የድምጽ ማጉያ ጩኸትን አንዳንድ ሰባኪዎች የሚወዱት ለምንድነው?

2.8 መባና መድረኮቻችን

በመድረኮቻችን አስተባባሪነት ከሚስተናገዱ ይፋ ክንውኖች አንዱ መባ ነው። ፕሮግራሙን በሚመራው ለው ማላስቢያ መሠረት አሁን ደግሞ በመስጠት እናመልካለን ይባልና ወደዚያው መባ ወደሚለበለብበት ድርጊት በመቻክል እናመራለን። እንዲህ ዓይነቱ ጥድፊያ ግን በዚህ ጊዜ መታየት እንደሌለበት ማስታወስ አለብን። ምክንያቱም በመስጠት እግዚአብሔርን ማምለክ ያለማቋረጥ ሲያሳስበን የሚገባው ነገር፣ አለን ብለን የምንለው ሁሉ የእርሱ መሆኑን ነው። እንዲህ ዓይነቱን ለለጪው አውቅና የሚሰጥን ድርጊት በጥድፊያ ማከናወን የሚያጎድብን ነገር አለ። በዚህ ጊዜ ከግርግር ይልቅ በጥሞና ሆነን የመልካም ነገራችን ሁሉ ምንጭ የሆነውን ጌታችንን በምንባርክበት መንፈስ ውስጥ መሆን አግባብ ነው። የምንለጠውን የለጠን

እርሱ ነው፡፡ እርሱ ተገርሞና ተደንቆ አዲስም ሆኖበት ከእኛ የሚወስደው ከቶ ምን አለ? ለመሆኑ እሱ የሌለው እኛ ያለን ምንድነው? እርሱ የሁሉም ነገር ምንጭ መሆኑን በማወቅና በመረዳት ነው ጌታ ለሐዋርያቱ ያስተማረውን ጸሎት ስንጸልይ «..ስጠን..» በማለት የምንለምነው፡፡

እሱ የሚያስፈልገንን የሚሰጠን÷ በደላችንን ይቅር የሚለን÷ ከክፉ እንድንጠበቅ ከሰላ የሚሆነን ጌታችን ነው፡፡ የምንሰጠው ደግነቱን ÷ ሰጪነቱን እያሰላሰልን ነው፡፡ ታዲያ በምንሰጥበት ጊዜ ጽሞና ባልተለየው እርጋታ ውስጥ ልንሆን ይገባናል፡፡ መስጠትን ብቻ የሚያነሳሳ ከዚያም ጋር የተያያዘ ነገር ማድረግ ይኖርብናል፡፡ ይሁን እንጂ እንዳንድ ጊዜ መባ እየተስበሰበ ማስታወቂያ እንሰማለን ሊባል መደመጡ የሚገርም ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ንግግር ስመስጠት ለማምለክ የተሰጠውን እናሳ ትኩረት የሚያመለክት እባባል ይመስለናል፡፡ ሆን ተብሎ ባይደረግም ስንሰጥ ትርፍ ነገር እንደምናደርግ ታስቦ «እየሰጠን እንሰማለን» የሚለው እባባል ስህተት መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ጊዜን በአግባቡ ለመጠቀም ከማስብ የመነጨ ብልህነት ይመስላል፡፡ በእኛ ዕይታ ግን ልክ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የስዎችን ትኩረት ወደ ሌላ ነገር ይወስዳልና፡፡ ጌታ ሆይ ስለሰጠኸኝ÷ ከሰጠኸኝ ላንተ መልሼ እስጣለሁ የምንልበትን ትኩረት ይነፍገናልና፡፡

ጊዜን ለመሻማት በአግባቡም ለመጠቀም ብንፈልግ ከዚህ ድርጊት በፊት ብዙ ምርጫዎች እንዳሉን ማሰቡ አይከፋም፡፡ እየሰጠን የሚለው ትርፍ ነገር እያደረግን እንደሆነ ያሳስባል፡፡ መባ በመስጠት በልባችን የሰጠንን ጌታ ስንባርከ የሚከናወነው ድርጊት ከእምልኮ ወጣ ያለ ሁኔታ ነው ብለን ማሰቡን ከየት እመጣነው?፡ ለመድረኮቻችን መንፈሳዊ ለዛን ከሚጨምሩ እኛ ንም ከሚያንጹን መንፈሳዊ ድርጊቶች አንዱ በመስጠት ማምለክ ስለሆነ ሌላ ነገር ጣልቃ እየገባበት ትኩረትን ባያዛባ መልካም ነው፡፡

ሌላው ስዚህ ክፍለ ጊዜ ቢወገድ ይበጃል የሚባለው በምእመኑ በኩል የሚታየው ድርጊት ነው፡፡ የምንሰጠውን የወረቀት ገንዘብ አጫማዶ መያዝ አግባብ አይደለም፡፡ አንዳንድ ጊዜ መባን ሊሰጡ የተሰናዱት ወገኖች በመባው ሊያኖሩት የያዙትን ብር ሳይታወቃቸው ይሁን አውቀውት የሚያጣጥፉት እሉ፡፡ እንደውም የወረቀቱን ገንዘብ ማጨማደድ በስልጠና የተገኘ ያህል ብሩን

የሚያጨማድዱና ሰዲያቆናት ሥራን የሚጨምሩ ሊጋሶች እንዳሉ ከዲያቆናት ጋር አብሬ አሳልፍ በነበረ ጊዜ አስተውያለሁ፡፡ የወረቀት ገንዘቡን አጨማዶ መሰጠቱን ልማድ ከየት እንዳመጣነው አላውቅም፡፡ ግና ገንቢ ልማድ እንዳልሆነ ግን አውቃለሁ፡፡ ስለሆነም የምንሰጠውን በእጃችን ይበን፡ ጌታ ሆይ አንተ የሁሉም ነገር ምንጭ ነህ፡ ከሰጠኸኝ ጥቂቱን ብቻ እለጣለሁ፡ ብለን በጽሞና መስጠትን ብንለምድ እንታነጻለን፡፡

ብሩን ማጨማደድ ብናቆም ደግሞ ለዲያቆናት ድካም እንቀንሳለን፡፡ ስለዚህ ተረጋግተን በመስጠት ማምለክን መልመድ አለብን፡፡ ብዙውን ጊዜ ስቦታው የዝማሬ አገልግሎት ከተከናወነ በኋላ ቢሆን ይበጃል፡፡ ይኸው ቦታ ሕጻናት በመስጠት ማምለክን ከታላላቆቻቸው በማየት እንዲማሩ ዕድልን ይሰጣቸዋል፡፡ አንዳንድ አብያተክርስቲያናት የሕጻናት የአምልኮ ጊዜ እየጀመሩ ለለመጡ በእነርሱ ጊዜ ማድረጉም ሌላ አማራጭ ነው፡፡ ለማንኛውም በግርግር እነርሱ በመስጠት የሚያመልኩበትን ጊዜ እግረ መንገድ ለማሳሰብ ነው፡፡ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ መባ መስብለቢያውን መልእክቱ ካለቀ በኋላ ያደርጉታል፡፡ ይህንን የሚያደርጉት መስጠት ተግባራዊ ምላሽ እንዲሆን በማሰብ ነው፡፡ የባረከንን ለመባረክ በማሰብ፡፡ ሁለቱም ቦታዎች በጥሞና ልንሰጠው የተዘጋጀነውን ከሰጠን መልካም ናቸው፡፡ በማብቂያው መባ የሚሰበሰብበት ቦታ አርፍደው ለሚመጡ ወይም ለመጡ ምእመናን በመስጠት የሚያመልኩበትን እድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ዋናው ቁምነገር የልባችን ትኩረት እንጂ ሰዓቱ አይደለም፡፡ ተጠንቅቀን ሰሁላችን በሚበጅ ሰዓት ላይ ብናደርገው እንታነጻለን፡፡ በተጨማሪም ከመስጠት ጋር የተያየዘ ልባችንን አምላክ ፊት እንድናፈስ የሚያደርግ ዜማ በሰሆሳስ ድምጽ ብንስማ የሁሉም ምንጭ በሆነው ታላቁና የተፈራው አምሰካችን ላይ እንድናተኩር ይረዳናል፡፡

የውይይት ጥያቄዎች

1. መባ እየተሰበሰበ ማስታወቂያ መናገር አግባብ አይደለም በሚለው መደምደሚያ ትስማማላችሁ? ለምን?

2. በመስጠት ማምለክ ስንል ምን ማለታችን ነው?
3. ምእመናን ለመጣ የሚሰጡትን የወረቀት ብር የሚያጨማድዱት ለምንድነው?
4. መጣ እየተሰበሰበ መዘምራ መስማት በተለይም የሶሎ ዝማሬ ትክረትን ያሳጣል የሚባለው ለምንድነው?

2.9 ማስታወቂያዎችና መድረክቻችን

በመድረኩ ወረፋ ወስዶው ከሚስተናገዱ የፕሮግራም ዓይነቶች አንዱ ማስታወቂያ ነው። ይህም በተለያየ መንገድ ሊከናወን ይስተዋላል። ሳምንታዊ ማስታወቂያዎች ቤተክርስቲያን ያለችበትን ወቅታዊ ሁኔታ እንድንገነዘብ የሚያግዘንን መረጃ የምንቀበልበት መንገድ ነው። ይህም ትክክለኛ ቢታውን ወስዶ ሲከናወን ለቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞች ወሰት ይጨምራል። ለምሳሌ አንዳንድ ሥፍራ ማስታወቂያ የመናገሪያው ቢታ መዝምራን ከዘመሩ በኋላ መሆኑ የመንፈሳዊ አገልግሎት ፍሰትን ስለሚተንስ መረዎች ሕዝቡን አዘምረው ጥቂት እርፎታ በሚወስድበት ቢታ ላይ ማስታወቂያው ቢነገር ይበጀል። በማሪዎች ከዘመሩ በኋላ በመሐል ባልቃ የሚገባ ነገር ሳይኖር ስሕጻናት ተጸልዮ ወደ መልእክቱ መሸገር ቢሞክር ማስታወቂያው በትክክለኛ ው ቢታው ላይ ሆነ ማለት ነው። ለሕዝቡ በማስታወቂያ መልክ የሚነገሩ ነገሮችን ማጥለል የሽማግሌዎች ኀላፊነት መሆኑ መረሳት የለበትም። ጉዳዩ አጣዳፊ ሆኖ ነገሩን ስማስተላለፍ ሌላ መንገድ እንደሌለ ካልተረጋገጠ በስተቀር ወደ ፕሮግራም መረዎች ጠጋ እያሉ በጆሮ የሚደረግ የመድረክ ላይ ሽክሸክታ ጸያፍ ነው። ስለሆነም ምዕመኑን የሚያዘናጉና ትኩረቱን የሚያዛቡ ድርጊቶች መድረክ ላይ ባይፈጠሩ ለፕሮግራሙ መሰካት ይበጀል።

በብዙ አካባቢዎች የተለመደው የማስታወቂያ መናገሪያ መንገድ በቃል ለሚናገረው ሰው ኀላፊነት መስጠት ነው። ያ መናገር የሚችል ሰው ያለምንም ማስታወሻ ሊነገሩ የሚገባቸውን ማስታወቂያዎች በቃሉ አነብንቦ ቁሟ ሲል በብዙ ጸሎት ቤቶች ይስተዋላል። እንዲህ ዓይነቱ አደራረግ መልእክቱን ለማስተላለፍ ቀልጣፋ መንገድ ቢሆንም የሚያጎድለው ነገር አለ። እርሱም የማስታወቂያን ታሪካዊነት ይረሳል። በቃል ያለ ይረሳል በጽሁፍ ያለ

ይወረሳል የሚለውን የአበው ብሂል ማምት ውስጥ ያስገባ አይደለም። ስእገልግሎት በየስፍራው ስንዘዋወር ያስተዋልነው አንድ ሌላ ነገር ደግሞ ማስታወቂያዎችን በብዙ ብጥስጣሽ ወረቀት ተናጋሪው መድረክ ላይ ይዞ መቆሙ ነው።

ከላይ ካየነው በቃል የመናገር ባሕል ሻል ያለ ቢሆንም ብጭቅጫቂ ወረቀትን እያሳደዱ የማንበብ ድርጊት ደግሞ የሚያጎድለው ነገር አለ። በአሁኑ ጊዜ ያሉን ጸሎት ቤቶቻችን መጠለያ ናቸው። ታዲያ ንፉስ መድረኩ አካባቢ ነፍሶ በብጥስጣሽ ወረቀት የተጻፉትን የማስታወቂያ ጽሁፎች ሲወስዳቸው እኛ ወረቀቶቹን ለማስደድ የምናሳየው ክትትል እጅግ ያሳፍራል። በመሠረቱ ማስታወቂያ ደስታና ሐዘንን እንዲሁም ልዩ ልዩ ዜናዎችን ያከተተ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ወቅታዊ ታሪክ በመሆኑ በብጥስጣሽ ወረቀት መቅረብ የለበትም። ሣያና ሠላሳ ዓመት ወደ ኋላ ተመልስን ከሰንበት ጋር የተያያዘ አንድ ጥያቄ ለመመለስ ብንፈልግ በብጥሳጣሽ ወረቀት ከሠራነው መልሱን በቀላሉ ለመስጠት እንቸገራለን። በጽሁፍ የሚቀር ነገር ለተተኪ አሳቆየንምና አጥቢያ እሁድ እሁድ ምን ትመስል ነበር ብሎ ከማስታዎሻ ለመቃኘት መነሳት ከንቱ ድካም ይሆናል።

ስለዚህ ይህንን ለማስመገድ የማስታወቂያ መዝገብ ወይም የኩምፒውተር ስነድ ሲናሪን ይገባል። መደበኛ ጉዳዮቻችንን በቤተክርስቲያን የማስታወቂያ ለሌዳ መስጠፍ ከተንዛዛ የማስታወቂያ ንግግር ያድነናል። ማስታወቂያ ተናጋሪውም ደግሞ የተመረጠና የተሳካለት መልእክት አስተላላፊ ሊሆን ይገባዋል። ልክ እንደ ቃሉ የቤተክርስቲያን መልእክት በአግባቡ እንዲደርስ በዚህ ጉዳይ የሚሳካለትን ሰው መመደብ ያዋጣል። በመረዎች መካከል ወር ተራን ለመጠበቅ ታስቦ ስጦታው የሌለውን ግለሰብ በሕዝቡ ፊት ቆሞ እንዲንተባተብ ማድረግና ማሳጣት የተገባ አይደለም። የአደባባይ አገልግሎት ለሁሉ ስላይደለ ይህንን ባለማድረጉ መሪ በጣም ትልቅ ነገር እንደቀረበት መታሰብ የለበትም። ማስታወቂያ እጥር ምጥን ብሎ ትኩረትን እንዲስብ ተደርጎ መሰናዳት አለበት። መድረክ ላይ ቆሞ የተራዘመ ዲስኩር መሆን የለበትም። ስለሆነም ቀደም ብሎ በተወና መልኩ መጻፍና ታርሞም መዘጋጀት ይኖርበታል።

እንዲህ ሲሆን ፕሮግራሞች አርስ በአርስ ተደጋጋፊ ሆነው በመፍሰስ ለአንድ ትልቅ የሰንበት ውበት የበኩላቸውን ያዋጣሉ። በስልጣኔና በብልጥግናው ወደፊት የገፋት አብያተክርስቲያናት ለእያንዳንዱ የፕሮግራም ተሳታፊ ሁሉንም መረጃ በአጅ የመሰጠት ባሕል አሳቸው። ማስታወቂያ ተናጋሪው አስታዋሽ አንጂ ሙሉ ለሙሉ የማስታወቂያ መልእክት አስተላላፊ አይደለም። በሚቀጥለው ጊዜ በዚህ ሰዓት እንዲህና እንዲያ እንደምናደርግ አስታውሱ ይሉል እንጂ እያንዳንዱን የማስታወቂያ ሃሳብ እያነሳ አይናገርም። ድህነት ሲጠፋና በሁሉም አቅጣጫ ሲሞሳልን ይህን ባህል ማዳበሩ ይበጀናል።

እሰክዚያው ግን ዓለም ሁሉ የሚያውቀውን ፕርግራማችን መደጋገም አሰፈላጊ አለመሆኑን ተገንዝበን ጊዜያችንን በአግባቡ እንጠቀምበት። ያለ ቅጥ የተራዘመ ማስታወቂያ የእሁድ ፕሮግራሞቻችን ውበት እንደሚቀንስ እንገንዘብ። የተደራጀና የተቀናጀ የማስታወቂያ ባሕል እንድናዳበር አምላክ ይደግፈን።

የውይይት ጥያቄዎች

1. ማስታወቂያን ለማስተላለፍ የተቀላጠፈውን አማራጭ አሠራር ግለጽ
2. ማስታወቂያን በመዝገብ መያዝ ጠቀሜታው ምንድነው?
3. በመድረክ ላይ የሚታየው ሽክሽክታ እንዲወገድ ምን መደረግ አለበት?
4. ማስታወቂያ በብዥታስላሽ ወረቀት ጽፎ መናገር ሌላውን ስሕተትነቱ እምነ ላይ ነው?

ክፍል 3 የምስባክ (ፑልፒት) ኮሚቴ

3.1. የምስባክ ኮሜቴ

በአብዛኛዎቹ የኢትዮጲያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የቡድን አሠራር የሚበረታታና የጠቀመን መሆኑ አይካድም። ፑልፒታችንንም በኮሚቴ ማስተዳደሩን መርጠን እየተክተልነው ነው። የምስባክ አገልግሎትን በተመለከተ የሚያስተዳድረው ቡድን ስያሜ ከቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን

ቢለያይም በዚህ ርዕስ ጉዳይ የምናነሳው በዕለቱ ስንበት ኃላፊነት ወስዶ ፕሮግራም የሚያደረጀውን ቡድን በሚመለከት ይሆናል። እኔ በማነስግልበት ቤተ ክርስቲያን አንዲህ ዓይነቱን አገልግሎት የሚያቀናጀው ክፍል የምስባክ ኮሚቴ ይባላል። በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የመንፈሳዊ አድገት ኮሚቴ የሚል ስያሜ አለው። በእንዳንዶቹም የአለቱ ስንበት መልእክት አቅረቢዎችን የሚመድብ ክፍል በመባል ይታወቃል። በቡድን ይሁን፥ በክፍል በዚህ ርዕስ ጉዳይ ሥር የምናነሳው አካል ተመሳሳይ ተልእኮ ያለውን አንደሆነ ይታወቅልን። ለሙ ሳይሆን የኛ ትኩረት ሥራው ነውና። አንገዲህ የምስባክ ኮሚቴ ስል በአሁድና በሌሎቹም የአዘበት ቀናት በሚኖሩ ፕርግራሞች በመድረኩ ላይ የሚናገሩ ክፍሎችን ቅደም ተከተል የሚያሲዘውን ክፍል ማለቱ እንደሆነ እንዲታወቅልኝ። አንዱን አማርኛ አየተጠቀምን ልጅ ለማለት ስንፈልግ ግማሾቻችን ማቲ ስንል ግማሾቻችን ደግሞ ኩታራ ወይም አሽከር አንል የለ? አንዲሁ ተናጋሪዎች የሚቆመውበትንም ቦታ በተመለከተ አንዳንዶቻችን የአንግሊዝኛውን ሃሳብ በመውሰድ ፑልፒት ስንል፥ ሌሎቻችን ምስባክ ማለቱን መርጠናል። ሌሎቹ ደግሞ መሠዊያው አንዲህም መድረኩ ማለቱን ይመርጣሉ። ከእነዚህ ልዩ ልዩ አጠራሮች የሚቀለንን በመውሰድ ፑልፒት፥ ምስባክ፥ መሠዊያው፥ መድረክ ብንል ስለ አንድ ነገር እየተናገርን አንደሆነ እገነዘባለሁኝ። ቦታውንም አንዲህ በመለለን መንገድ ልንጠራው ምርጫው የአያንዳንዱ ክፍል ነው። ስለሆነም ቀጥሎ በሚቀርበው ማብራሪያ እኔ የምስባክ ኮሚቴ ስል እናንተ የምትመርጡትን ስያሜ በማስገባት . . . . ኮሚቴ እንደትሉ አደፋፍራችኋለሁኝ። አንዳንዱም የምስባክ ወይም የፑልፒት እያልኩኝ በማፈራረቅ ስጠቀም ያው ስለ አንዱ ኮሚቴ እየተናገርኩኝ ነው።

በኮሚቴ መሥራት ተመራጭ የሆነበት አያሌ ምክንያቶች አሉ። የኮሚቴ ስብጥር ድካሞች እንደተጠበቁ ሆነው ከብዙ ጉድለቱ ጋር ነገርን በኮሚቴ መሥራት በርካታ ጥቅሞች አሉት። የምስባክ ኮሚቴ ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት በአባላቱ መረዳዳት ምእመናን የተሻለ መንፈሳዊ እንክብካቤ የሚያገኙበት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል በሚል እሳቤ ነው። ጤናማ የምስባክ ኮሚቴ አባላት ባሉበት በሁሉም አባላት የአምነትና የሃሳብ (የራአይ) መዋጮ ላይ የተመሠረተ በሳል ሥራ ለመሥራት ያግዛል። ምንጊዜም ኮሚቴ

የሚመረጥበት ዋናው ምክንያት ከአንድ የሰላ ጭንቅላት የብዙኃኑ የተሻለ ነገርን ያስገኛል ከሚለው መረዳት ተነስቶ ነው። ስሀተትን ለመቀነስ ከማገዙ ባሻገር የተጨመቀ በጎ ሃሳብ ለማመንጨት ይረዳል በሚል ግንዛቤም ነው።

በኮሚቴ አንዱ የአንዱ ጠባቂ ሆኖ ያገለግላል። ለአንደኛው አባል ያልታየው ለሌላው ይታየዋልና። ይህንንስ አይተኸዋል/ሽዋል? ለማለት ዕድል ይሰጣል። ስለሆነም እንደ ስጋት መቀነሻ ሆኖ ስለሚያገለግል አንድ ብቻ ከመሆን ከዚያ በላይ ሆኖ መሥራት በብዙዎች ዘንድ ተመራጭነት ኖሮት ጠቀሚታ ላይ ሲውል ይስተዋላል። አንዲህ ዓይነቱ መደጋገፍ ሲኖር ደስታን አብዝቶ ኃዘንን የሚቀንስ ጥሩ ሁኔታ በምአምናን መካከል ይታያል። ምአመናንም በተደራጀ አካል የጊዜውን አንከብካቤ ለማግኘት ይታደላሉ። በተጨማሪም የኃይል ክምችት በጣት ከሚቆጠሩ አንድና ሁለት ስዎች እጅ ወጥቶ ኃላፊነት በተሰጠው ኮሚቴ እጅ ሲሆን ነገሮች ስመስመር የሚወጠብትን ክፍተት ይደፍናል። ምክንያቱም በጥቂቶች እጅ የተያዘው ኃይል ሲዳላደል ኃይል በጋራ ስጋራ ልማትና አድገት ይውላል። ሌላው የኮሚቴ ጠቀሚታ አያንዳንዱ ለክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የሚጠቅመውን መልካም ነገር ሲያካፍል አነኛን መልካም ነገሮች አቀናጅቶ ብርቱ ነገር በአማኞች እንደሰርጽ ያደርጋል።

በብዙ ወንጌላውያን የአጥቢያ ቤተክርስቲያናት የፑልፒት ኮሚቴ ከሙሉ ጊዜ አገልጋዮችና ከትርፍ ጊዜ መሪዎች የተውጣጣ ነው። በአንዳንድ ቦታ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮቹ የበለጠውን ኃላፊነት ሲወስዱ በሌላ ቦታ ደግሞ የሌሎቹ የበላይነት ይንጸባረቃል። ይህንን ያልነው ያለምክንያት አይደለም። በመድረኮቻችን ላይ የማይገባ ትምህርትና ስብከት ሲስተናገድባቸው ያዩ ምዕመናን ሮጠው ሄደው ፓስተሩን «ምነው? እንዲህ ያለ ለባኪ አመጣችሁብን...» ሲጠይቁት የሚሰጠው መልስ «አኔ እኮ ብዙ ሥልጣን የለኝም የእነ አገሌ ቡድን ስለፈለጉት ነው» የሚል ነው። የሙሉ ጊዜ አገልጋዩ ወይም የትርፍ ጊዜው አገልጋይ ይኮነንና ነገሩ ይታለፋል።

የሚያስገርመው ነገር ግን ይህ ሁኔታ በስህተትነት ተተችቶ መልሶ መላልሶ መደጋገሙ ነው። ለዚህ ዋናው ምክንያት ኮሚቴው የሚመራበት ወጥ የሆነ አሠራር አለመኖሩና ሥራዎቹም በተገቢው መንገድ መሠራታቸውን ክትትል አለመደረጉ ነው። እንዲያውም በውሳኔ ደረጃ

የሚተላለፉ የቤተ ክርስቲያን አቋሞች (ውሳኔዎች) ያለምንም ስጋትና ቅሬታ የሚጣስበት ሁኔታ አንዳለ የአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ዶክመንቶች ያስረዳሉ። በቡድን ከሚሠራው የፋክክር ሥራ የተነሳ የቤተ እምነቱ ውሳኔ ለጪ ክፍል የስጣቸው ውሳኔዎች እንኳን ሳይቀር የሚሻሩበት ሁኔታ አናውቃለን። ማንኛውም ኮሚቴ ጠንካራም ደካማም ጎን እንዳለው ሁሉ ይህም ኮሚቴ በዚህ ሁኔታ መፈተኑ በብዙዎች አብያተ ክርስቲያናት የሚስተዋል ክስተት ነው።

የፑልፒት ኮሚቴ እንደ ኮሚቴ የቤተክርስቲያኒቱን መንፈላዊ አቋም ከማንም በተሻለ ሁኔታ የተረዳና ያንንም አቋም ለማጠናከር የሚሠራ መሆን አለበት። በቅርቡ በተግባር አያየን የመጣነው ጉዳይ ግን የዚህ ተቃራኒ ብቻ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ የተቃራኒ ተቃራኒውን ነው። የተሰጠውን አደራ በአግባቡ የሚወጣ ኮሚቴ ሲኖር መልካም ይሆናል። ይሁን እንጂ ኃላፊነት የሚሰማው ክፍል ሲጠፋ መድረክች ለሥርዓተ አልበኝነት አልፈው ይሰጣሉ። በተቀደሰው የቤተ ክርስቲያን መድረክም ከቃሉ ያፈነገጠ ነገር ማየት እንግዳ አይሆንም። ይሕም የሚሆነው አቅም ያጣ የምስባክ ኮሚቴ በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ሲኖር ነው። በዚህ ጉዳይ የሌላውን አብያተ ክርስቲያን ጉዳይ ከምናገር በራሴው ቤተ እምነት ያጋጠመንን ሁኔታ አነሳለሁ። ከሞላ ጎደል የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ብዙ ነገሮቻችን ስለሚመሳስሉ ለትምህርት ይሆነናል።

ከጥቂት ጊዜ በፊት በሁለት የመሠረተ ክርስቶስ አጥቢያዎች የሆነውን ነገር ለምሳሌ እንጠቅሳለን። በአንድ የአሁድ የአምልኮ ክፍለ ጊዜ በሺህ የሚቆጠሩ ምአመናን ፊት ቆሞ ቃሉን ሲያካፍል ከቆየ በኋላ ድንገት መሐል ላይ ስባኪው እንዲህ አለ «በአሁኑ ወቅት የተቀባው እግሬ ነው። የተቀባውን፡ እግሬን ጭኜ ልጸልይላችሁ» በማለት በምዕመናኖቻችን ላይ እንግዳ ተጋባዥ ሲፈነጭ ማየት የብዙዎቻችን ስቃይ ያበዛ ክስተት ነበር።»[8]

የተቸገሩትና በወቅቱ ለችግራቸው መፍትሔ የሚሹ የዋሃን ላይ እግሩን እግራቸው ላይ ጫነ። እንዲህ ዓይነቱ ክስተት አጅግ አስደንጋጭ ነው።

[8] Selamawit Estafanos Interview. Meserete Kristos College Addis Ababa: 6 July, 2004

እንዲህ ዓይነቱ ደፋር ስው በአደባባይ ምስባኮቻችን ላይ እግሩን እንዲጭን ከመፍቀድ ሌላ ምን ይመጣል? መፍቀድ ብቻ ላይሆን ይህንን ያደረገውን ሰው ደጋግሞ መጋበዝ የሰውየውን እንግዳ ትምህርት ግፋበት ማለት አይደለምን? የፑልፒት ኮሚቴው አባላት ይህንን ሊያምኑ ይችሉ ይሆናል፣ ወይም ግድ የላቸውም። ይህ ግን የቤተክርስቲያኒቱ አቋም መሆኑ ሳይረጋገጥ ሁሉም አጥቢያ ውስጥ ያለ የፑልፒት ኮሚቴ እንደመሰለው የሚሄድ ከሆነ ሁኔታው «ያዲስ ኪዳን ዘመነ መሰፍንት» መሆኑ አይደለምን? ሁሉም በመሰለው የሚሄድበትን ዘመን ከዚህ የተሻለ ስም ካለ ቢሰጠሰው ደስ ይለናል።

ትርምስ ያየሰበት በወረፋ ስድብ የጠፈበት የጦርነት አውድማ መፈጠር ምክንያቱ ፑልፒት ኮሚቴው የተስተካከለና ጠንካራ አቋም ሰማስያዝ እቅም ስለሚያንሰው ወይም ሆን ተብሎ እንዲያንሰው ስለሚደረግ አይደለምን?።

የቤተ ክርስቲያን ነገር ግድ የሚላቸው÷ በውስጧም የሚደክሙ÷ ነገሮችን አቅጣጫ ሰማስያዝ ጸጋውና ችሎታው ያላቸውን ሰዎች ቸል ብሎ በስም የጨነኛ ቤተ ክርስቲያን አባል ሆነው በተግባር ግን የተሰየ ተልዕኮ ያላቸውን ሰዎች በመድረኮቻችን ላይ እንዲፈነጩ ሲያደርግ የሚስተዋለው ደካማ አቋም ያለው የፑልፒት ኮሚቴ ነው። በቅርቡ አብሮኝ በኮሌጅ በአገልግሎት ከተጠመደ ወዳጄ ጋር ለስ ፑልፒት ኮሚቴ ሚና ስንጨዋወት ከሁለት ወዳጆቹ ጋር ያደረገውን ጭውውት ሲነግረኝ አባከህ ጽፈህ አምጣልኝ ብዬ ስመንኩት በሃሳቤ ተሰማምቶ ከላይ ያነሳኋቸውንና ሌሎችንም ነጥቦች ጨምሮ ከዚህ በታች ያለውን ጽፎ አመጣልኝ። እኔም በሆነው ነገር እጅግ ስለተነካው ቃል በቃል ከዚህ እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁኝ።

«ከቤተክርስቲያን አፈንግጠው በቤተክርስቲያን ውስጥ
ተልዕኮአቸውን ለማራመድ የሚሠሩትን ያነጋገረ አንድ
ሰው ሌሎች ቤተክርስቲያንን ለማፍለስ፥ ቢችሉ ለማፍረስ፣
የነገሩትን ሲናገር አንዲህ አለ «ከኛ በፊት የወጡ
ተሳስተዋል። ቤተ ክርስቲያንን ፈተ ለፈተ በመቃወማቸው
አወዳደቃቸው ተበላሽ። እኛ የምንከተለው አካሄድ ግን
በውስጥ ሆነን ሰዎችን ወደውጭ ማውጣት
ነው» አለ። ይህንን የለማው ግለሰብም በተራው እንዲህ
አለ «እኔም ቆም ብዬ ስታዘብ በእኛው ቤተ ክርስቲያን
ውስጥ በዕቅዳቸው መሠረት በተሳካ ሁኔታ እንደሚሠሩ
አስተዋልኩ። ለምሳሌ አንድ ዕሁድ ከአዲስ አበባ
አጥቢያዎች ባንዱ ለአምልኮ ሰዓድ የሚሰብከው ሰው
የማውቀው ነበር። ከአገልጋዮችም አንዱን «ይሆን ሰው
ከየት አገኛችሁት» ሰለው «ፓስተራችን እሱ እሱ
ነው» ብሎ በምጸት መለሰልኝ። ይህ ሰባኪ
በአሳልኔት በአንዲት ጤነኛ ቤተ ክርስቲያን ቢመዘገብም
በተግባር ግን የተለዩ አንቅሰቃሴዎች አንቀሳቃሽ
መሆኑን እኔ አወቅ ነበርና ነገርኩት።
አገልጋዩም «በዚህ ቤተ ክርስቲያን በአማካይ በወር
ሁለቴ ይሰብካል እኮ» አለኝ። የኔም ጥያቄ
«የፑልፒት ኮሚቴዎቹ እነማን ናቸው?» የሚል
ነበር። ከላይ ያልኩትን ዓይነት ኮሚቴዎች
እንደሆኑ ካጸናልኝ በኋላ የዕለቱ ሰባኪ ከኮሚቴዎቹ
አባላት መካከል የአንድ ሰው የቅርብ
ወዳጅ እንደሆነ ገልጸልኝ በዚያው ምክንያት ደጋግሞ
እንደሚጋበዝ ተረዳሁ። እኔም መድረኮቻችን
የኮሚቴው ወይም ከኮሚቴው አባላት የጥቂቶች
ሰዎችን ጥማት የሚያረኩ ማንነታቸው ያልተጣራ
መጤዎች ቁጥጥር ውስጥ ያለ መሆኑ በተደጋጋሚ
በማረጋገጤ አዝኜ በመጸለይ ላይ ነኝ[9]።

ይህንን ጽሁፍ የምታነቡስ ወገኖቼ የፑልፒት ኮሚቴዎች የተጣሰባቸውን አደራ እየተወጡ ነው ትላለችሁ? ቆም ብላችሁ አስቲ በሃላፊቻችሁ የየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁን ምስባኮች ስእፍታ ቃኙዋቸው። ምን ይመስላሉ? ሰመሆኑ እናንተን ቅኝታችሁ ምን እንድትሉ ገፋችሁ? (ቀደም ብየ እንደነገርኳችሁ ፑልፒት÷መሰዊያ÷መድረክ÷ምሰባክ ወዘተ.. የቁንም በሉት ግለሰብም ይሁን ቡድን ያደረጃው ለምአምናን የሚቀርበው የቃሉ አገልግሎት ምን ይመሰላል?) ስለምስባኩ ልቅሶ ልቅሶ አሳችሁ? ወይስ የተሳካለት ስበሆነ ምስጋና ምስጋና? የናንተ የቱ ነው? የኔን ና የወዳጄን ልንገራችሁ። ወዳጄ በልብ ስብራት በብዕሩ ያስፈራቸውን ቁም ነገሮች እናንተን ለመጠየቅ ስል ቆም አድርጌው ነበር። በውስጡ የተስማውን ስሜት እስቲ አንብቡለት አብራችሁት ወደሃሳቡ ሥፍራ በሕሊናችሁ ትጓዙ ዘንድ ሃሳቡን ከዚህ በሚከተለው መልኩ አቀርበዋለሁኝ። ወዳጄ ብሶቱን ብዙ ሰው ያውቅልኛል ይላል እንዲህ ሲል፤-

«እኔ ብቻ ሳልሆን በርካታ ሰዎች ይህን እንዳስተዋሉም
እውቃለሁ። የመፍትሄ ያለህ!!! እያሉም በመጮህ ላይ
ያሉ ፡ ተሰፋ ቆርጠውም የተሰዩን አሉ። ኧረ መፍትሄው
ምንድን ነው? የቤተክርስቲያናችን የፑልፒት ኮሚቴዎች
ምዕመኖቻችንን በሰህተት ትምህርት ለሚያጠቁ ልዩ
ተልዕኮ ላላቸው ሰዎች ተገን ሆነዋል። እንደውም ከጥቂት

[9] Wudineh Endaylalu Interview. Meserete Kristos College Addis Ababa: 3 July, 2004

ጊዜ በፊት በአብያተክርስቲያን መድረኮች ላይ ከሚሰብኩት
ስብል የሰማሁትን ልዩ ተልዕኮ ያላቸው ሰዎችን «ጥበብ»
የሚገልጽ አባባል ላካፍላችሁ። ይህ ድርጊት
የተፈጸመው ቤተክርስቲያን አሁን የያዘችውን
ትምህርትና አካሄድ የማይቃወሙ ሁለት ሰዎች አርስ
በርስ ሲተቻቹ ነው። በዚህ የሁለትዮሽ ክርክር
አንደኛው ሌላውን አንዲህ አለው፡- «እገሌ ግድግዳውን
ይገፋል፡ እኔ ግን ግድግዳውን ተደግፌ አገለግላለሁ።»
ግድግዳዋ ቤተክርስቲያን መሆኗ ነው። ብዙዎች ሲገፏት
ሞክረው ያልጣሏት። ተደግፈዋት እንዲገፏት
ግን የፑልፒት ኮሚቴዎች መሳሪያ ሆነዋል። ይህ ስህተት
አብዛኛውን ጊዜ ባለማወቅ ሲፈጸም፡ አንዳንዱም የነርሱ
የሆነ ሰው ፑልፒት ኮሚቴ ውስጥ እንዳለም አስኪታመን ድረስ ሆነ
ተብሎ ይደረጋል። እግዚአብሔርን ሲሰማ ቤተ ክርስቲያኔም
ሰስህተት አሳልፋ አትሰጠኝም ብሎ አምኗት
የመጣውን የእግዚአብሔር መንጋ በጨካኞች ዱላ
በየሳምንቱ ስታስደበድብ የምትታየው ቤተ ክርስቲያን
ምንዳዋ ምን ይሆን? አስከዛሬስ የሚሆነውን እያየን
ሰመንፈስ አንድነት በመወንቀት ወይም «ለሥልጣን
በመገዛት» ሳቢያ እጆቻችንን በአፋችን ላይ ጭነን
የተቀመጥን፡ ነቅተን ግን ያላነቃን ሰዎችስ «ቅድስትና
ንጽህት ሆና እንዲያገኛት ወዶ ለሚገለጠው
ጌታ ምን እንመልስ ይሆን?» እስካሁን የሆነው ሆኖ አልፏል።»[10]

በምለባቸቻችን የሚነናወነውን ነገር ሁላችንም እኩል እናያዋለን ማለት አስቸጋሪ ነው። እይታ ከትኩረት ጋር የሚያያዝ፥ ከዓላማ ጋር የሚቀናጅ ነገር እንደሆነ ከወንጌላት ጸሐፊዎች እንረዳለን። ጌታ ኢየሱስ የሰጠውን ምድራዊ አገልግሎት እስመልከተው ወንጌላትን የጻፋልን አራቱ ወንጌላውያን እንድናየው ያደረጉን የጌታ ገጽታ የተለያየ መልክ አለው። የአነርስ ሁኔታ በቀጥታ እኛ ዛሬ ካለንበት አሁን ከምናነሳው ጋር ይገናኛል ባይባልም ከትኩረት አኳያ ግን መልእክትና አወሳሰዶቹ ሊለያዩ መቻላቸውን ያስረዳናል። ዛሬም ወደ ጸሎት ቤት የምንመጣ ሁላችን የተለያየ ዕይታና ትኩረት አለን።

እንዳንዶቻችን ቤተክርስቲያን ለንሄድ የምንፈልገው ጥቂት ነገር ነው። ያንን ካገኘን እንረካለን። ሌሎቻችን ደግሞ መሪው፥ ዘማሪው፥ ማስታወቂያ ተናጋሪው፥ የሙዚቃው ቅንብር፥ ለባኪው፥ ጸሎት የመራው ብለን ማን ምን እንዳለ ካለው ምን ማለት እንደነበረበት ጭምር

[10] Wudineh Endaylalu Interview. Meserete Kristos College Addis Ababa: 3 July, 2004

እንመለከታለን። የሁላችን ተሰጥኦ ይለያያል። በአካል ውስጥ ያለን የተለያየን ብልቶች ነንና። ብልቶች ከመለመር የወጣ ድርጊት ሲፈጽሙ አካል ይጎዳል።

እንደ ብልቶች የመተያየት መረዳት በሁላችን ዘንድ በጥልቀት ከሠረጸ እንከባበራለን፥ እንተዛዘናለን ደግሞም እንቀባበላለን። ይሁን እንጂ ይህ የብልትነት ግንዛቤ ከራቀ እንጎዳዳለን።

እስቲ በአንክሮ እስተውሉት ÷ እንደ እርሱ በጌታ መልከና ምሳሌ የተፈጠሩትን የአባቱን ልጆች በቅርቡ የተቀባው እግሬ ነውና ዛሬ እግሬን እጭናለሁ የሚል ድፍረት በአካሉ ውስጥ እንደኖው ብልት የሆነው ወንድማችን ከየት ሊያመጣው እንደሚችል እናንተው ገምቱ። እንከንየለሹ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳን እንዲህ ዓይነት የድፍረት ቃል አላወጣም። ይኸኖው መንፈስ ከየት የመጣው ይሆን?

የዚህ ሁሉ ለበቡ አብዛኛውን ጊዜ በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ለመጋቢነት አገልግሎት የተሰጠው ትኩረት አናሳ በመሆኑ እንደሆነ ግልጽ ሊሆንልን ይገባል። መጋቢዎቻችን በአብዛኛው መዳቢዎች እንዲሆኑ ሁኔታዎች አስገድደዋቸዋል። አንድ መጋቢ በሚያገለግልበት አጥቢያ ቢያንስ በወር ሁለት ጊዜ ስብከት የሚያቀርብበት ዕድል መፈጠር ነበረበት። ይሁን እንጂ ከሕዝቡ ጋር በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴው የተቆራኙት መጋቢዎች ተትው በአብዛኛው የኢትዮጵያ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እንግዳ መድረኩን እንዲቆጣጠር ይደረጋል። ስባኪዎቻችን ያለማቋረት ከመድረክ ቢመግቡን ለአነርስና ለትውልድ የሚተርፍ ቅርስ ይተዉልን ነበር። በእንግሊዝኛ ቋንቋ በአድናቆት የምናነባቸው አያሌ መንፈሳዊ መጽሐፍት የተጻፉት መጋቢ ስባኪያን ከመድረክ ሕዝቡን ለመመገብ ባደረጉት ጥረት ነው። መጋቢዎቻችን በቃሉ ላይ በማተኮር እንዲመግቡን ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር ይልቅ በሙሉ ጊዜ ጉዳይ አስፈጻሚነት ላይ እንዲያተኩሩ ገፍተናቸዋል። እነርሱ እንዲህ ቢያደርጉ እንኳን ልንረዳቸው አጠገባቸው ያለን አጋገሮቻቸው በቃሉ ላይ እንዲያተኩሩ ልናደፋፍራቸው ይገባን ነበር። ነገር ግን ይህንን ለማድረግ አልተጋንምና ብዙ ጽሐፍት መጋቢያንና የበለሉ የቃሉ አገልጋዮች አላፈራንም።

ባሬ ያሱን አገልጋዮች አንዳገስገሱበት ዘመን የበለሱ አይደሉም። ኸምላሌ ሃያ ዓመት ቢያገልግሉ ከዚያ ውስጥ አራት ጥሩ ዓመታት ኖረው አነርሱን በአምስት ያባዙ ናቸው። ስለሆነም በምድራችን የቃሉ አገልግሎት የተስጠው አነላ ትኩረት መጋቢዎቻችን እንዲጠነክሩ አላደረጋቸውም። መጋቢዎቹም ስላልጠነከሩ ከመድረክ ለሕዝቡ ተከታታይ ትምህርትና ስብከት የማቅረብ አቅም የላቸውም። ሕዝቡም በየሳምንቱ አዲስ ፊት የማየት የዓመታት ልማድ ስላከበተ ጌታ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ የስጠውን አገልጋዮች ደጋግሞ በመድረክ ሊያያቸው አይፈልግም። ግና ይህ እስከ መቼ ይቀጥላል? ሊሆን ጸባዩን የሚያውቁለት የሚፈልገውን ላይሆን የሚያስፈልገውን የሚረዱለት መጋቢዎቹ ሁኔታውን የሚመጥን ምግብ ቢያሰናዱለት ተገቢ ይሆን ነበር። የልቡን የሚያወቅሱትንና በጸጋ የሚያንጹት መጋቢዎቹ ቢመግቡት በመንፈሱ ይፋፋ ነበር። ዳሩ ግን በቤታቸው እንደሚገባ የመንፈላዊውን አገልግሎት ዕድል መጋቢዎቹ በላሳገኑ በአጥቢያዋ ራዕይ የተቀረጹ ምእመናን ማፍራትም አልታቸለም። እንደውም በምእመናን አመለካከትና ልምምድ የተዥጎረጎረ ነገር ይታያል። የመጋቢውሚና በሚለው ርዕስ በዚህ ጉዳይ በስፋት እንነጋገርበታለን።

ወገኖች ፑልፒት ኮሚቴ (የመንፈላዊ አድገት ኮሚቴ) ጠንካራ ሆኖ ተልእኮውን ሊወጣ የሚችለው እንዴት ነው? ወቅቱን የጠበቀ የአምላክ ሪድኤት የሚፈስበትን ሁኔታ ለማደላደል የፑልፒት ኮሚቴ ሚና ምንድነው? ዓይነተኛ የፑልፒት ኮሚቴ መገንባት የሚቻለው እንዴት ነው? ሚዛኑን የጠበቀ በላል ኮሚቴ እንዴት እውን ሊሆን ይችላል? አነዚህንና አነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎችን በሚቀጥሉት ጥቂት ገጾች ለመዳሰስ እንሞክራለን።

የውይይት ጥያቄዎች

1. ጠንካራ ምስባክ ኮሚቴ እንዲገነባ ምን ማድረግ አለብን?
2. ምስባክ ኮሚቴ ጠንካራ ሆኖ ኃላፊነቱን እንዳይወጣ የሚያግዱት ተፋላሚ ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው?

3. የምስባክ ኮሚቴ ክጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል ይባላል። ይህ አባባል ምን ያህል አውነት ነው። ጥቅሙን በዝርዝር አብራሩ።

3.2 ውጤታማ የምስባክ ኮሚቴ (የመንፈላዊ አድገት ኮሚቴ)

የአንድ አገልግሎት ክፍል ጥንካሬ የሚወሰነው ለአገልግሎት በተሰለፉት አባላት ጤናማነት ነው። ስፖርተኞች የአደባባይ ድል ባለቤት ከመሆናቸው በፊት በግላቸው በሚያደርጉት ዝግጅት ላይ የሚመሠረት የሞራል ጥንካሬ እንደሚገነቡ ሁሉ የምስባክ ኮሚቴ አባላትም ቀደም ብለው በሁሉም አቅጣጫ የተገነቡ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ መፈጠር አለበት። የኮሚቴው አባላት የጠለቀ የአግዚአብሔር ቃል ዕውቀት ያላቸው፥ ምእመኑን የሚያውቁ፥ የቤተክርስቲያኒቱን መሠረታዊ የእምነት አቋም የሚያውቁና ሊተገብሩ የሚችሉ መሆን አለባቸው።

ይህንንም በሥልጠና አግኝተውት በቃል ኪዳን በሕዝቡ ፊት የወሰዱት ኃላፊነት አንዲሆን መደረግ ይኖርበታል። ይህን ማድረግ አጥቢያ ቤተክርስቲያኒቱ ለአገልግሎቱ የስጠችውን ከብደት ከማሳየቱ ባሻገር ከኮሚቴዎቹም አባላት የምትጠብቀውን ታላቅ ኃላፊነት በምን ያህል ውጤታማነትና ጉጉት እንደምትጠብቀው የሚያሳይ ነው። ስለዚህ ኮሚቴ የሚታጩ ሰዎች በጥንቃቄ የተመረጡና የተጣለባቸውን አደራ መሸከም የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል ማለት ነው።

በሁለተኛ ደረጃ የኮሚቴዎች ጥንካሬ የሚለካው በማንነታቸው ብቻ ላይሆን በተግባራቸውም ጭምር ነው። ስለሆነም ውጤታማ የምስባክ ኪሚቴ የቤተክርስቲያኒቱን ዓላማና የማታመቻምችባቸው አቋማት ለመተግበር የቆመ መሆን ይኖርበታል። አመራር ሰጪ አካላትም እነዚህ አስፈጻሚ አካላት በቃሉ በኩል ተፈጻሚነት ማግኘት ያስባቸውን የቤተክርስቲያኒቱ አውራ ዓላማዎች እንዲተገበሩ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ባሁኑ ጊዜ ምዕመኑ ብቻ ላይሆን የቤተ እምነቱ መሪዎች የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን መሠረታዊ አቋማት በግልጽ የማያውቁ ወይም ግድ የማይላቸው መሆኑ በተግባር ይስተዋላል። ስለዚህ የእያንዳንዱ ቤተ እምነት ዓላማና ከዚያም በሥሩ ያሉ የአጥቢያ

ቤተክርስቲያን አውራ ዓላማዎች በግልጽ ተቀምጠው የመድረክ አገልግሎቶችም ከዚያ ዓላማ አኳያ መቀረጽና መካሄድ አለባቸው። በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ስለ ግልጽ ዓላማና በአቅድ ስለመመራት ተደጋጋሚ ትምህርቶች እንደተሰጡ ይነገራል። በዚህ ርእስ ጉዳይ ላይ ትምህርት አስተማርን እንጂ ቤተክርስቲያን በዕቅድና በዓለማ መመራቷን አላረጋገጥንም። በቤተ ክርስቲያን ዓመታዊ እቅዶቿ ተካትተው መተግበር ያለባቸው ጉዳዮች በውል ተጠነው ፑልፒት ኮሚቴው (የመንፈሳዊ እድገት ኮሚቴው፥ ወይም ፕሮግራሙን የሚያቀናጀው አካል) ለዚያ ግብ እንዲሠራ ነገሮች መመቻቸት አለባቸው።

በሦስተኛ ደረጃ በአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ሙሉ ጊዜያቸውን ለጥተው የሚያገለግሉ የቤተክርስቲያኒቱ አገልጋዮች በአብዛኛው ምስባኮችን ላይ የጎላ ሚና እንዲጫወቱም የአገልግሎቱንም እንቅስቃሴ እንዲቆጣጠሩ ምቹ ሁኔታ መፈጠር አለበት።

ሀ. መጋቢው ያችን አጥቢያ በመንፈሳዊ ጉዞዋ አኳያ ከየት ተነስታ የት እንደምትደርስ የተለመውን ዕቅዱንና ለአጥቢያዋ ያለውን ዓመታዊ ራእይ አብረውት ከሚሠሩ የፑልፒት ኮሚቴ አባላት ጋር አብሮ በማየት አስፈትሾ ራእዱን መተግበር አለበት። ቅደም ተከተል በጠበቀ መልኩ ከፑልፒት የሚፈስ ምግብና ምክር ምዕመኑ እንዲያገኝ ያለማቋረጥ ማረጋገጥ የመጋቢው ፈንታ ስለሆነ ለፑልፒት ኮሚቴው ብርሃን በመፈንጠቅ እንቅስቃሴዎች በሙሉ ወደዚያ ግብ እንዲያመሩ ግንባር ቀደም ሚና መጫወት አለበት።

ለ. እንግዳ ሲጋበዝም በአጥቢያይቱ የፑልፒት ኮሚቴ አቅድ ውስጥ እንዲገባ እንጂ መንፈስ እንዳሳሰበው በሚል ፈሊጥ ከመስመር ለወጣ አደራረግ አጥቢያይቱን አጋልጦ መስጠት ተገቢ አይደለም።

ሐ. በአያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መድረኮች ላይ እንዲያገለግሉ የሚጋበዙ ስዎች እየተጠኑ በየጊዜው እንዲጨመሩና ወደ ፊትም ልዩ ስልጠና እየተሰጣቸው አጥቢያዎች የሚጋብኟቸውን እንዲያዉቁ መደረግ አለበት።

መ. አጥቢያ ውስጥ በሙሉ ጊዜ የተቀበልናቸውን አገልጋዮች እንዳይሰብኩ ሞራላቸውን በመንካት ሥራ ፈት ማድረግን ማቆም አለብን። ለመሆኑ ስንት መጋቢዎች ወይም የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ናቸው በአጥቢያቸው በዓመት

ከአሥር ጊዜ በላይ በመድረክ የሚቆሙ? አርግጥ በገጠር አጥቢያዎች እንደ ሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ያለ ጸጋው ያለው ወይም መድረክ ላይ ደጋግሞ ለመቆም ድፍረቱ ያለው በብዛት ባለመኖሩ ተደጋጋሚ ዕድል ያገኙ ይሆናል። በኩተሞች አካባቢ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች በቋሚነት ከሚያገለግሉባት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ይልቅ የሌሎቹን አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እየዞሩ ሲያገለግሉ ይለተዋላልና በቤታቸው ይከበሩ!!

በዚህ መንገድ የተደፈረውን መድረኳን አስከብራ ምዕመናንን ለሚያንጽ ነገር እንድትጠቀምበት የሚያስችላትን ዘዴ እንድትቀይስ እግዚአብሔር ለመሪዎቿ ማስተዋልን ይስጥ።

የውይይት ጥያቄዎች

1. ምስባክ ኮሚቴን ለውጤታማነት የሚያበቁ ነገሮችን ዘርዝሩ
2. ምስባክ ኮሚቴ እንዳይሳካለት የሚያደርጉትስ?
3. የመንፈሳዊ እድገት ኮሚቴ ወይም መጋቢው ከመድረክ ቀጣይነት ያለው መንፈሳዊ ማእድ ለሕዝቡ እንዲቀርብ ምን ማድረግ አለበት?
4. የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች በቤታቸው የማይከበሩበት ሁኔታ በአገራችን የሚስተዋለው ለምንድነው?
5. በምስባኩ ዘወትር አዲስ ፊት የማየትን ጥቅምና ጉዳት ተነጋገሩበት

3.3 የመጋቢው ሚና በምስባክ ኮሚቴ ውስጥ

በመድረኮቻችንና በምዕመናን ሕይወት ተጓድለዋል ለምንላቸው ነገሮች ለበቡ የመጋቢዎች ሚና አነላነት ነው በሚለው ሃሳብ ዙሪያ በተደጋጋሚ ተነጋግረንበታል። መደጋገሙ ያስፈልገው ትኩረት የነፈግነውን አገልግሎት በውል ማጤን እንዲቻለን ነው። ትኩረት ነፍገነው ስለከረምን በዚህ አገልግት ዙሪያ በቂ ልምድ አልገነባንም። የመጋቢውን ሚና በዝርዝር አንስተን ከመነጋገራችን በፊት የመጋቢነት አገልግሎት ዛሬ በምናየው ሁኔታ እንዲሆን ያደረገው ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ በመመለስ ብንነሳ ሚዛን እንጠብቃለን።

መጋቢ የሚለው ቃል የተሸከመው ስዕል በአብዛኛው የሚያስተላልፈው ቁም ነገር አገልጋዩ ከሚሰጠው መንፈሳዊ ማዕድ ጋር የተያያዘውን እውነታ ብቻ ነው። ይሁን እንጂ በመጋቢው የሚከናወነው አገልግሎት ከዚያ ስለሚጠልቅ አረኛ ማለትን አመርጣለሁ። አረኝነት ስስፋት በሚታወቅበት አገር ብንኖርም ይህንን ተምሳሌ ወደ ጸሎት ቤት ለማምጣት አጅግ ዘግይተናል። እንደውም ባለፉት አምሳ ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለን አገልጋዮች ስለ አረኝነት አገልግሎት የተዛባ ስዕል ስናስተላልፍ ቆይተናል። ዛሬም ቢሆን በብዙዎች ዘንድ መጋቢነት (አረኝነት) በረጅም ዘመን የወንጌላዊነት አገልግሎት የሚደረስበት ሹመት (ሽልማት) ተደርጎ ይወሰዳል።

እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ያፈነገጠ አስተሳሰብ ነው። ምክንያቱም መጋቢነትም ሆነ ወንጌላዊነት ራሳቸውን የቻሉ አገልግሎቶች ናቸውና። ከአንዱ ወደ አንዱ አይታደግም። በጌታ ቸርነት ሁለቱንም ስጦታ የታደሉ ሊኖሩ ቢችሉም በአንዱ መሰላልነት ወደ ሌላው አይወጣም። ወንጌላዊ ተብለው ሊጠሩ ቆይተው መጋቢ የተባሉ ቢኖሩም ጸጋቸውን ለይታ ይህንን ለማድረግ ያረፈደችው እነዚህ አገልጋዮች የሚገኙ ባት ቤተ ክርስቲያን ናት።

በእኛ አገር ሙሉ ጊዜውን ለእግዚአብሔር ሥራ የሰጠውን ሁሉ ወንጌላዊ ማለት ለምዶብናል። ቆይተን ቆይተን ደግሞ መጋቢ ማለት መጥቶብናል። ይህንን ስናደርግ ለመጋቢው ለየት ያለ መኖ (ከፍያ) ስላለናዳን አገልጋዮች ሥልጣን ያለውንና ገቢ የሚያስገኘውን አገልግሎት ያለ ስጦታቸውም ቢሆን እንኳን እንዲመኙ ላይታወቀን ገፋፍተናል። ለዚህ ችግር ማስተዋል የተሞላበት ርምጃ በፍጥነት ካልወሰድን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን ችግር ውስጥ የምንጥል ይመስለኛል። በመሠረቱ «ወንጌላዊነትም ሆነ መጋቢነት ሊተባበሩ እንጂ ሊፎካከሩ አይገባም።»[11] ሁለቱም ለጤናማ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና ለእድገቷ ይጠቅማሉ።

[11] Solomon Kebede Address to Ethiopian Evangelicals Addis Ababa: Meskerem 3,1986EC.

ስለዚህ አቅጣጫ ያለው ስጋቴ እንደ ተጠበቀ ሆኖ አብያተ ክርስቲያናት ጸጋ እየለዩ ሹመት መጀመራቸው የሚያበረታታ ነው። ስለሆነም መጋቢነት ለብርቅዬና ለጥቂት ምርጦች መሆኑ እየቀረ መጋቢ መለየምን ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እየተገነዘቡ መጥተው ዛሬ ዛሬ ብዙ መጋቢያን በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት እየተሸሙ መሆናቸው ይበል የሚያሰኝ ነው። ግና ለማቸው ትልቅ ሥራቸው ትንሽ የሆኑ ከመንጋው ይልቅ የራሳቸውን ጥቅም የሚያስቀድሙ መንጋውን ማብላት ሳይሆን መንጋውን መብላት (ሕዝ 34፡1-6) የተጠናወታቸው አራዊት ብቅ ብቅ እያሉ መምጣታቸው እየታየ ስለሆነ ከዚህ እንድናመልጥ ልባዊ ጸሎቴ ነው። አምላክ በለጣቸው መንጋ ከሚነግዱ አራዊት ያድነን ብሎ መጸለይን ግድ የሚሉ ሁኔታዎች እየተስተዋሉ ነው።

ስለ ሌሎች ሊባል ይህንን ከለማን በቅንንት አገልግሎት ላይ የተሰማራን ከእንዲህ ዓይነቱ ነቀፌታ የጸዳ አገልግሎት ልናገለግል የምንችለው እንዴት ነው? የናፈቅነው ውጤታማ አገልግሎት በእንቅስቃሴያችን በተግባር የሚገለጠው እንዴት ነው?

በምስባክ ኮሚተ ውስጥ የመጋቢው (የእረኛው) አውራ ሚና እጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ ያሉትን ስጦታዎች በቦታቸው በመጠቀምና መልካም ግንኙነትን በማጎልበት ኮሚቴውንና ምዕመናንን ማስተሳሰር ሲሆን። በተጨማሪም ከፕልፒት ኮሚቴ ፊት ፊት እየሄደ ለኮሚቴ ውሳኔ የሚያበቁ ገንቢ ሃሳቦችንና ራዕዮችን ማመንጨት ነው።

ቤተ ክርስቲያን በመዋቅር ተሳስረው ለእዝ ለንለት ጠንካራ ቦታ ለጥተው አለቃና ጭፍራ፥ አዛዥና ታዛዥ፥ አሠሪና ሠራተኛ ለሚለው ከፍፍል የበዛ ትኩረት ለጥተው የሚንቀሳቀሱባት ደርጅት አይደለችም። ይልቁንም ሙሉ ጊዜያቸውን ያልሰጡ ብዙ አገልጋዮችን በማስተባበር የክርስቶስ ሕይወት በተግባርና በተጨባጭ እንዲታይ የሚደክምባት ሕያው አካል ናት። በእንዲህ ዓይነቱ ቦታ ስለ ኃይል አጠቃቀም በስፋት ማውራት ቢቸግርም የእያንዳንዱን አገልጋይ ቦታ ተገንዝቦ ማን ምን ቢያደርግ መልካም ነው የሚለውን ከስጦታ አኳያ ማደላደል የመጋቢው (የሙሉ ጊዜው) አገልጋይ ተቀዳሚ ተግባር መሆን ይኖርበታል። ምንጊዜም ያለ ስጦታቸው ቦታ የያዙ ሰዎች ለአገልግሎት ትልቅ እንቅፋት ይደነቅራሉ። በቤተ

ክርስቲያን ትልቁ መርገም በአንድ አገልግሎት ክፍል ላይ ያለ ስጦታው ተቀምጦ ማንኛውንም የልቀቅልን አቤቱታና ልመና በጉልበቱ አሸንፎ፥ ያንን አገልግሎት ያለተቀናቃኝ ይዞ የሚኖር ግለሰብ ነው፡፡

ማንኛውም ግለሰብ በክርስቶስ አካል ውስጥ ሥፍራ አለው፡፡ ሁነኛ አረኛ የበጎቹን ትክክለኛ ሁኔታ ይገነዘባል፡፡ ስጌታ ኢየሱስ በጎች በሙሉ አንድ ዓይነት አይደሉም፡፡ እያንዳንዳቸውን ነጥሎ ያውቃቸዋል፡፡ ሁኔታቸውንም የሚመጥን እንክብካቤ ያደርግላቸዋል፡፡ ልክ እንዲሁ ስምሪት መስጠት በአረኝነት አገልግሎት ለተለለፍን ሁሉ ቀዳሚ ነገር መሆን ይኖርስታል፡፡ የሚፈልጉትን ሳይሆን የሚያስፈልጋቸውን በማድረግ መስመር ውስጥ አንዲሆኑ መርዳት ይኖርብናል፡፡ ይህን ለማድረግ ስክርስቶስ ጌትነት ሥር ያደረ፥ ክርስቶስን ማእከል ያደረገ አሰራር እንዲሰለጥን ምቹ ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው፡፡ መጋቢው ደግሞ ራስ ከሆነው ጌታ በሚመጣ መመሪያ ሊያገለግል የተሰለፈ ሎሌ ነው፡፡

አገልጋዩ ዲሞክራቲክ ሆኖ የህዝቡን ፍላጎት አስፈጻሚ ለመሆን አልተሾመም ወይም ደግሞ የራሱን ፍላጎት ለማስፈጸም ፈላጭ ቆራጭ (አውቶክራቲክ) ሊሆን አይገባውም፡፡ በተቃራኒው የክርስቶስ ሕይወት በተግባር እንዲታይ ከጌታ በተቀበለው አደራ ተልእኮውን የሚወጣ መሆን አለበት፡፡ መጋቢው ሎሌነቱን በተግባር ማሳየት ይኖርበታል፡፡

ስለሆነም መጋቢው ከምስባክ ኮሚቴው ጋር በመሆን ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በኩል የሚሰናዳውንም ሆነ ከሌሎች ተጋባዥ አገልጋዮች የሚዘጋጅውን ማዕድ እንዲቀበሉ ምእመናንና አገልጋዮች እንዲሁም የኮሚቴ አባሳት ሥፍራቸውን እንዲያውቁ የበኩሉን የበኩሉን በማዋጣት ማነሳሳት አለበት፡፡ ስለሆነም ቀዳሚ ሚናው ሰዎችን በስጦታቸው እንዲሰማሩ ማድረግ ነው፡፡ ይህንን ለማስናወን የምስባክ ኮሚቴ አባላትንም ሆነ ምእመናን ማስታጠቅ ከምንም የሚቀድም የአገልግሎት ድርሻው ነው፡፡

1. የመጋቢው ተልእኮ ለማስታጠቅ (ኤፌ 4:12 ዕብ 13:17)

አካሉ እንዲሰራው የታዘዘውን ሥራ አውራ መሪዎች እንዲጠቀልሉት የጌታ ፈቃድ አይደለም፡፡ የጌታ ፈቃድ አገልጋዮች ሌሎችን

እንዲያገለግሉ ማነሳሳትና ማስልጠን ላይ ትኩረት ቢያደርጉ ነው፡፡ እያንዳንዱ አማኝ የጌታውን ፈቃድ ለመፈጸም ሲተጋ ቤተ ክርስቲያን የሰሳም ቤት፥ የእፎይታ ሥፍራ ትሆናለች፡፡ እንዲሀ እንድትሆን አገልጋዮች ምእመናን የጌታን ፈቃድ በማወቅ እንዲራመዱ መርዳት ይገባናል፡፡ የሙሉ ጊዜ አገልግሎት ቀዳሚ ተልእኮ ሰዎችን ለመልካም ሥራ ብቁ ማድረግ ነው፡፡ በዚህ አኳያ የመጋቢው ሚና ኣሌ የሚባል አይደለም፡፡ መጋቢው በዚህ መስመር ያሰናዳቸው አያሌ ሰዎች ካሉ እንግዳ ትምህርትን የሚያመጣ ተጋባዥ ሲኖር ወዲያውኑ ነጥለው ይለዩታል፡፡ ምክንያቱም መልካሙን ከክፉው ለመለየት ራሳቸውን ስላስለመዱና ስለ በሰሉ ነው (ዕብ 5:14)፡፡

መጋቢው የእያንዳንዱን የአጥቢያይቱን የተሸመ አገልጋይና እንዲሁም የተጋባዥ አገልጋይ ስጦታ ምን እንደሆነ በመረዳት ስጦታቸውን በቦታው ማዋል እንዲችል አብረውት እነማን ቢሰለፉ እንደሚረዱት ለምስባክ ኮሚቴ በይፋ ማሳወቅ አለበት፡፡ በተለይ የምስባክ ኮሚቴ አባላት በአጥቢያ ውስጥ ለሚገኙ ልዩ ልዩ የመድረክ አገልግሎቶችን የሚመለከት ውሳኔ ሊወስኑና ምርጫ ሊያደርጉ የመጋቢው ሃሳብ ለውሳኔ አጋዥ ነው፡፡ የምስባክ ኮሚቴ በአጥቢያ ውስጥ ላሉ ልዩ ልዩ የመድረክ አገልግሎቶች ኃላፊነት የለጣቸው አገልጋዮች ፍላጎት ባጡ ጊዜ ወዲያው ለመድረስና አደራውን ለመረከብ እንዲቻል መጋቢው በተጠንቀቅ መቆም ሲኖርበት የምስባክ ኮሚቴ አባላቱንም ለዚህ ማዘጋጀት አለበት፡፡

በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ የአገልግሎት ስምሪትን ማከናወን ለራሳቸው ከፍተኛ ግምት ሰጥተው አጥቢያን የሚያስጨንቁ አንዳንድ አገልጋዮች አገልግሎት ያለእነርሱ መከናወን እንደሚችል እንዲገነዘቡ ያደርጋቸዋል፡፡ በአንድ ሥፍራ የበዛ ጊዜ ቆይተው አገልግሎትን ርስት ሲያደርጉም እረፍት እንዲወስዱ ለማድረግ እረኛው አብረውት ያሉትን አገልጋዮች በጥልቀት ማወቅ ይኖርብታል (ዮሐ 10:3፣14፣27)፡፡ ከዚህ የተነሳ የመጋቢው ድርሻ በምስባክ ኮሚቴ ውስጥ ወሳኝ ነው፡፡

በተጨማሪ ከመድረክ በዕለተ ሰንበት ወቅታዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሚዛናቸውን የጠበቁ መልእክቶችን በማቅረብ ምእመናን በዓለም ውስጥ ላለቸው የዕለት ተዕለት ጉዞ ያዘጋጃቸዋል፡፡ እሁድ ለምእመናን ታላቁ የመመገቢያ ሰዓት መሆኑን አውቆ ያንን ጊዜ በማስተዋል መጠቀም

እንደሚኖርበት መዘንጋት የለበትም። ምእመናን የሚጠቀሙበትን እውነት ሁሉ በመስጠት የውሰጥ ጥንካሬያቸውን መገንባት አለበት። እንደውም ዓመታዊ እቅድ ወጥቶ ምእመናን በየዓመቱ ሊመገቧቸው በሚገቡ እውነቶች ዙሪያ ተገቢውን ብርሃን አንዲቀበሉ ማመቻቸት ይጠበቅበታል።

በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አደራን የተቀበሰው መጋቢው ሕዝቡ ስለሚመገበው ነገር ክማንም በላይ ሊገደው ይገባል። ስለሆነም እረኛው ልጇን ሰማጥባት ፈላሽና ልዩ ልዩ ምግቦችን እንደምትወስድ እናት÷ ሰራሱ ሊመገበው የቆየውን እውነት ሰምእመናን መጥኖ በማቅረብ ተገቢውን መንፈሳዊ ምግብ በየአሁዱ ሕዝቡን መመገብ አለበት። ይህ ምግብ ቅደም ተከተል ጠብቆ በጽሁፍ የተቀረጸ ሊሆን ይገባዋል። ለእሁድ ሊያዘጋጀው የቆየው ምግብ ውሱ አድሮ ሰቀጣዩ ትውልድ የሚተላለፍ ምእመናንን የሚገነባ መንፈሳዊ ማዕድ ሊሆን ይችል ይሆናል። በብዙ ጥንታዊና ዘመናዊ የእሀት ቤተ ክርስቲያናት አገልጋዮች እየተደነቅን ጽሁፎቻቸውን የምናነብላቸው በማስታወሻ ስላቆዩልን ነው። ምናለ እኛስ ብንጀምረው። በእርግጥ ሃሳብን በጽሁፍ ቀርጸ ማቆየት የሁሱም አገልጋይ ስጦታ አይደለም። ግና መጻፍ የሚሆንልን ብንጀምረው ምናለ?

እስካአሁን በነበረን ልማድ አሁዶቻችንን በተገቢው መንገድ መጠቀም አልሆነልንም። ይፋዊ የማምለክ ነጻነትን አግኙተን በቆይንብቸው እያሌ እሁዶች ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እንደሚገባ እንዳልተጠቀምንበት ጥናቶች ይጠቁማሉ። ስለሆነም አሁዶቻችን ሕዝቡን እንዲሚገባ ልናንጽ ካልተጠቀምንባቸው በክንቱ እንዳይባክኑ ያስፈራል። ስለሆነም መጋቢው በመንፈሳዊ አገልግሎት ሚናው ለሕዝቡ ተከታታይ ምግብ በእርሱም ሆነ በሌሎቹ ተጋባዦች በየአሁዱ መቅረቡን ማረጋገጥ አለበት። ይህንንም በማድረጉ ምእመኑን የማስታጠቅ እደራውን ይወጣል።

2. መልካም ግንኙነትን ማጎልበት (ኤፌ 4:15 25)

ዛሬ ቡብዙ አብያተ ክርስቲያናትና አገልጋዮች መካከል ላለመግባባትና የጎሪጥ ለመተያየት እንዲሁም ለመለያየት ዋና ነገር ሆኖ የምናየው ሞገድ የበዛበት ግንኙነት ነው። ሁነኛ እረኞች አሉባልታ እንዲያይል÷ ወሬ

ምእመኑን እንዲፈታ አይፈቅዱም። ይህ እንዳይሆን ነገርን በብርሃን ያከናውናሉ። ስብርቅዬዎች የሚጠበቅ የተሰየ ምስጢር ስለሌለ አመኔታን በምእመኑ መሐል ይፈጥራሉ። ይህንን በማከናወን በኩል የመጋቢው ሚና ወሳኝ ነው። በአባላትና በልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን ኮሚቴዎች መካከል መተማመንን ለመገንባት ከኮሚቴ ይልቅ ሰመጋቢው ይቀላል። አብዛኛውን ጊዜውን አብሮአቸው ስለሚያሳልፍ ገንቢ ሚና ለመጫወት ይቻሰዋል። መጋቢው ይህንን በማድረግ ለምስባክ ከሚቴው እቅድ የሚመች ሰላማዊ አካባቢን ይፈጥራል። ምክንያቱም መተማመን ፍቅርን ይገነባል ፍቅርም ደግሞ መተማመን ይገነባልና ነው። መተማመን እንዲወነክር ደግሞ በግልጥነት ላይ የተመሠረተ መልካም ግንኙነት የሳላ ድርሻ አለው።

መጋቢው ግልጽነት ያለበት የአፍ ለለፍ ግንኙነትን ሲያዳብር የኮሚቴው አገልግሎት ይቀላጠፋል በኤፌ4:25 .« ተነጋገሩ...». ተብሏልና።

ቃላት ውስን ናቸው። ተሸክመው የሚሔዱትም መልእክትም ውስን ነው። በጽሁፍ የተላለፉ ቃላት እንዳንድ ጊዜ ያልተባሉትን ያስተላልፋሉ። ይህ ሲሆን አለመግባባት ይፈጠራል። በዚህ ጊዜ በጽሑፍ የተቀረጹ ቃላት ለጠብና ትርምስ ምክንያት ይሆናሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ተነጋገሩ አለ እንጂ ተጻጸፉ አላለም። መጻጻፍ የመልእክት ማስተላለፊያ መንገድ ቢሆንም እብረው ባሉና ሊገናኙ በሚችሉ ሰዎች መሐል የሚመረጠው ግንኙነት ግን መነጋገር ነው። ለዚህ ይመስላል ሐዋርያው ዮሐንስ በ2ኛ ዮሐ :12 በእካል ተገኝቶ ከምእመኑ ጋር ለመነጋገር መፈለጉን የገለጸው። ይሁን እንጂ ፊት ለፊት መነጋገር የሌሎችን ስሜትና ማንነት ያገናዘበ ሲሆን ይገባዋል። በተጨማሪም በትክክለኛ መንገድ የሚደረግና የሚነገረውን በፍጹም ግልጥነት ላይ በተመሰረተ ሁኔታ ለማቅረብ መዘጋጀትን በውስጡ ያካተተ መሆን ይኖርበታል። ይህንን ለማድረግ መጋቢው ወሳኝ ሚና ይጫወታል፤ ምክንያቱም አብዛኛውን ጊዜ ከሕዝቡ ጋር ነውና።

መጋቢው ሽፍጥና ድብቅ አጀንዳ እንዲወገድ እውነት በኮሚቴ አባላት እንዲነግስ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ምክንያቱም ብዙዎቹ አምነው ልባቸውን የሚገልጡት ለእርሱ ነውና። በኤፌ 4:25 *«...እውነትን ተነጋገሩ...» ስለተባለ ገንግር እውነት የሚባል ቅመም ሲኖረው ግንኙትን ይገነባል።*

ሰብዙሥቻችን ወይም ለማንኛችንም ቢሆን ሐቁን መናገር ቀላል አይደለም። ተጋብዘን በሄድንበት ቦታ በብዙ ጭንቅ የጨረስነውን ምግብ ጋባኻ ሊጠይቀን «ሌላ ነው» ማለት ለአብዛኞቻችን ቀላል ነው፤ ጉዳዩ ሆድ ሊያውቅ ዶሮ ማታ ሆኖ እያለ። ፊት ሰፊታችን የሚቆመ መልክ ጥፋዎችን፥ ቆንጆ አይደሉህም? ብለው ቢጠይቁን ያለምንም ማወላወል፥ እንዴታ!! የምንልበት ጊዜ ብዙ ነው። ግና ሆድ ሊያውቅ ዶሮ ማታ። በተለይ አወዛጋቢ ጉዳይ ሲነሳ ጥርት ያለውን ማድረግ ጌታ የረዳው ለው ብቻ የሚያከናውነው ነው። ለአብዛኞቻችን ክፋት ባለጠጠ ጊዜ አውነትን መሸፋፈን ወይም መሸሽ ይቀለናል። ያን የምናደርገው ለራሳችን ለግተን ወይም ባለጋራ አንዳይበዛብን በማሰብ ነው። ወይም ደግሞ ሌሎችን አጎዳለሁ ብለን ስንለጋ ነው።

አውነትን መስማት ለሁላችን በቀላሉ የሚዋሃደን ተፈጥሮአዊ ነገር አይደለም። አውነቱን በቀላሉ መተግበር እንቸገራለን። ስንሞክረውም ብዙ ጊዜ ይተናነቀናል። አውነት ቢያምም ግን ይፈውሳል። ስለዚህ አውነቱን መናገር ይበጃል። በአሁኑ ጊዜ « ኤች. አይ. ቪ አንመርመርን » ብሎ ሰው የሚፈራው ለምንድነው? ብለን ብንጠይቅ ሐቁን ፊት ለፊት መጋፈጥ አቅም ስለሚያንስው ነው። ይሁን እንጂ የሌሎቹን ቁጣ ላንፈራ ይተዉናል ብለን ላንለጋ እንዲሁም ይበቀሉናል ብለን ላነጨነቅ ለሐቁ መኖር የእኛ የአገልጋይነት መርሆ ሊሆን ይገባል። መጋቢው በምስባክ ኮሚቴ አባላት መካከል አንዲህ ዓይነቱ አቅም አንዲገነባ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። አውነትን መናገር ወሳኝ የአገልግሎቱ መሣሪያ ነው። ሁሉንም ደስ ሊያሰኝ አይችልምና አምቢ የሚልበትን ጊዜ ማወቅ የአውነተኛ መጋቢነት አንዱ ገጽታ ነው።

መጋቢው ቡድናዊነትን በማስወገድ ትለለር እንዲጎለብት ያደርጋል«....በ ለፌ 4:25» .« እያንዳንዳችሁ» የሚለው ቃል የእያንዳንዱን አማኝ ወሳኝ ሚና ይመለከታልና

ኮሚቴ ውስጥ ትንንሽ ቡድኖች የመፈጠራቸው ነገር ብዙ ቦታ የሚታይ ክስተት ነው። አንዳንዴ የኮሚቴው አባላት ራሳቸው በትንንሹ ተሟድነው መጥተው ከየትኛው ወገን ነህ? ሚናህን ለይ ሊባል ይችላል። በዚህ ጊዜ ሁሉ መጋቢው የገለልተኛነት ቦታውን በኮሚቴው መሐል ጠብቆ

ለትለለር መሥራት አለበት። ገለልተኛ ሊባል አውነትን ጨፍልቆ መሆን የለበትም። ምናልባትም አንዳንዴ ከአውነት ወገን ሊቆም አደላ ሊባል ይችላል። ግን ለሕሊናውና ለመጸሐፍ ቅዱሱ አውነት መኖር ይኖርበታል። ይህ ጊዜ የለለቀን ነው። መንገዱም ለመጋቢው «አልጋ በአልጋ » አይሆንም። በብዙ ልቅሶ በብዙ ምጥ ውስጥ ራሱን ያገኘዋል። ቢሆንም በተቻለ መጠን ሁሉንም ወደ ማለተላለር ደረጃ ለመምጣት መሞከር አለበት። ጌታ ጣልቃ እንዲገባም ያለማቋረጥ ለምልጃ ጸሎት ራሱን መለጠት አለበት። በተጨማሪም እያንዳንዱን ለው ለለሚያሳትፍ ነገር ለንነጋገር ትንሽ ነው ተብሎ የሚታለፍ አንድም ነገር ሊኖር አይገባም።

አንዳንዴ ግንኙነት ሁሉን አቀፍ መሆን ሊያቅተው የፕሮግራም ግጭት ይፈጠራል። ለጥቂቶች ነግረን ሌሎች ይለማሉ ብሎ ማሰብ አያስኬድም። መቼ ነው እንዲህ የወለንነው? ሊባል እንትና አልነገረህም ወይ? ማለቱ አያዋጣም። በተለይ በምስባክ ኮሚቴ አካሔድ ይህ መወገድ አለበት። ሁሉን ያቀፈ «እያንዳንዱ» የተካፈለበት ነገር ሊኖር ግን ነገሮች አይምታቱም። ምን ያገናኘዋል ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው። በውትድርና ላይ የእዙ ለንለለት እያንዳንዱን ሊያሳትፍ ድልና ለርዓት ይረጋገጣል። በጸሎት ቤትም ከጽዳት አገልጋይ ጀምሮ ምን ማድረግ እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው በጠራ ሁኔታ ሊያውቁት ይገባል። የግንኙነት ለንለለቱም ሁሉን ያካተተ ሊሆን ይገባል። በአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ነገሮች ለሙሉ በአባላቱ መታወቅ ይኖርባቸዋል። ያኔ የእያንዳንዱን የአካል ብልት ተሳትፎ ማግኘት ከባድ አይሆንም። ልክ እንዲሁ የምስባክ ኮሚቴ አባላት እያንዳንዳቸው አኩል እንዲሳተፉ በማድረጉ ጉዳይ ላይ የመጋቢው ሚና ቁልፍ ነው።

መጋቢው ከአውቀት ይልቅ ትሀትና ኩኃይል ይልቅ ፍቅር እንዲነለብት በኮሚቴው ቁልፍ ሚና መጫወት አለበት፡

በለፌ 4:15«አውነትን በፍቅር እየተናገርን» አንደተባለ መጋበዊ አውነት በፍቅር መግለጥ አለበት። መጋቢው በየኮሚቴው የጎላ ሚና እንደሚጠበቅበት የታወቀ ነው። በተለይ በምስባክ ኮሚቴ አንደ አባል

የሚጫወተው ሚና ታሳቅ ስለሆነ በዚህ ኮሚቴ ያለው ኃላፊነቱ የላቀ ነው። የምስባክ ኮሚቴ የቤተ ክርስቲያን የኃይል ጣቢያ ነውና። መጋቢው በዚህ ኮሚቴ እውነትን በፍቅር መግለጥ አለበት። በዚህ ጊዜ በመጋቢው እንደበት እውነት መነገር ያለበት ቢሆንም ሊነገር ግን በፍቅር መታጀብ አለበት። ለዚሁ ነው የጌታ ባሪያ ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌ 4:25 እውነትን እንድንናገር እደፋፍሮን በፍቅር እንድናደርገው የሚጋብዘን። ምክንያቱም ያለ ፍቅር የሚነገር እውነት ግትርነት ነው። በተጨማሪም ያለ እውነት የምናሳየው ፍቅር ሁሉ ግብዝነት ነው።

በምስባኩ ኮሚቴ ወይም በመጋቢው የላላ እቋም እንዳንዱ ወደ ምስባክ እንዲመጡ የምንጋብዛቸው እገልጋዮች የሚታይ ስህተት ሲፈጽሙ እንኳን ግድ የለም በፍቅር እንለፈው እንላለን። ይህ ግን እግባብ አይደለም። ምክንያቱም ያለ እውነት የምናሳየው ፍቅር ሁሉ ግብዝነት ነውና። ይህን ሚዛናዊ ለማድረግ የመጋቢው ሚና ወሳኝ ነው። መጋቢው የሚዛን ለው ሆኖ ለጥሪው ትኩረት ሰጥቶ ኩተንቀላቀለ በእጥቢያቱ ምስባክ መቆም የማይገባው ለው እንዳይቆም የበኩሉን ያዋጣል። እነዚህ ሚዛን ጠብቀው በሚክናወኑበት የእገልግሎት መስክ የተሰለፉ በሙሉ እገልግሎታቸው ከትርምስና ከሁካታ ጸድቶ ፍሬ የበዛለት ይሆናል። እሜን!! ለሁላችንም ይሁንልን።

ኢትዮጵያ ውስጥ የምናውቃቸውን መጋቢዎች እነርሱ ሳይወዱ ወደ መዳቢነት ቀይረናቸዋል። ስለሆነም መጋቢው ክመዳቢነት ያለፈ ዕቅዱንና ለእጥቢያዋ ያለውን ዓመታዊ ራእይ አብረውት ክሚሠሩ የፑልፒት ኮሚቴ አባላት ጋር አብሮ በማየት እለፈትሽ ራዕዩን መተግበር እንዳለበት ቀደም ብዬ ማለገንዘቤ ይታወቃል። ራእይ ለኮሚቴ በጅምላ የሚለጥበት ጊዜ በጣም ውስን ነው። ግና ልቡን ወደ ፈጣሪው ባቀና ፈጣሪውን ያለማቋረጥ ለሚለማ መናገር የሚውደው አምላክ ይናገራል። ባለ አደራ በሆነበት እጥቢያ ላሉ ምእመናን መጋቢው ከፍተኛ ኃላፊነት አለበት። ለዚያም የሚሆን የጊዜው ነገር በሰዓቱ ማቅረብ እንዲሆንለት ወይሞ ሌሉቹም መጥተው ያንን አንዲያስፈጽሙ የሚታየው ለው መሆን አለበት። ያንን የታየውን ነገር ለዓመቱም የሚሆነውን የሚያመጣበት የመጀመሪያ ጣቢያ የምስባክ ኮሚቴ ነው። ይህች አጥቢያ የምትኖርለት እውራ ዓላማዋ ይኸ ነው። አኔ እንዲህ

ይታየኛል። እናንተስ? ብሎ ዓለማውን በተመለከተ ጥያቄ ይጠይቃል። ከዚያም አጥቢያቱ ዓላማዋን እንዴት እደምትተገበር መነሻ ሃሳብ ያመጣል።

እጥቢያይቱ ይህንን ዓላማዋን ለማለካት የምትችልበት መንገዱ ይኸ ነው ብሎ መጋቢው የጠራ ዓመታዊ የምስባክ ዕቅዱን ለኮሚቴው ማቅረብ አለበት። ይህ የመጋቢው ራእይ የማይተዝረው መሠረታዊ ችግር እንዳለበት ከታየ ብቻ ነው። ስለሆነም ቢያስፈልግ በሩብ ዓመት ወይም በዓመት ሁለቱ አሊያም የዓመቱን በማቅረብ የምስባክ ኮሚቴ ሃላብ እንዲለግበት ቢያደርግ ጥሩ ጅምር ይሆናል። ቅደም ተከተል በጠበቀ መልኩ ክፑልፒት የሚፈለ ምግብና ምክር ምዕመኑ እንዲያገኝ ያለማቋረጥ ማረጋገጥ የመጋቢው ፈንታ ስለሆነ ለፑልፒት ኮሚቴው ብርሃን በመፈንጠቅ እንቅስቃሴዎች በሙሉ ወደዚያ ግብ እንዲያመሩ ግምባር ቀደም ሚና መጫወት አለበት።

የውይይት ጥያቄዎች

1. የመጋቢው ሚና እንዲሻሻል ምን መደረግ አለበት?
2. መጋቢው በመዳቢነት የተገደበው ለምንድንነው?
3. በምስባክ ኮሚቴ ግንኙነት በተመለከተ የመጋቢው ድርሻ ምን መሆን አለበት?
4. «እግዚአብሔር ለኮሚቴ ራእይ አይሰጥም የሚሉ ወገኖች አሉ ይህን እባባል እንዴት ትገነዘባላችሁ?

3.4 የምስባክ ኮሚቴና የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ

ብዙ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች በተለይም በተለይም መንፈሳዊ እንቅስቃሴን እጥበቀን የምንፈልግ (የጸንጠቆለጤ) እማኞች «ነገር ለኮሜቴ ተለጠ» ለንባል መንፈለ ቅዱስ እንደተረሳ እናስባለን። እርግጥ ነው ያለ መንፈለ ቅዱስ እርዳታ መንፈሳዊ እገልግሎት እክናውናለሁ የሚል ኮሚቴ ካለ ሊታዘንለት ሊፈረድበትም ይገባል። ፍጡር የእግዚአብሔርን ሥራ በራሴ ጉልበት እሠራለሁ ብሎ ካሰበ ትልቅ ጅልነት ፈጽሟል። እንዲህ ዓይነቱም እገልጋይ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ አያውቅም ማለት ነው።

ምስባክ ኮሚቴ የተሳካለት የሚሆነው የእገልግሎት እንቅስቃሴው የሚባረከው ከመረጃ ሳይሆን ከመገለጥ መሆኑን የተገነዘበ እንደሆነ ብቻ ነው።

ይህንን ስንል መረጃ አያስፈልግም ማለታችን አይደለም። መረጃም መነሳጥም የየራሳቸው ሚና አላቸው። የተገለጠው ጉዳይ ሌላ መነሳጥ አያስፈልገውም። በመረጃ የምንሠራቸው በርካታ ሥራዎች እንዳሉ ሁሉ አምበቱ ስሜተ ሕዋሳት ምንም የማይፈይዱበት ጊዜ አለ። ያኔ መነሳጥን የሚጠይቅ ጉዳይ መጥታል ማለት ነው። እግዚአብሔር ልጆቹን ይመራል። እነዚህ በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው (ሮሜ 8፡16) ተብሎ ተጽፏልና። የተሳካለት ምስባክ ኮሚቴ መሪውን ያወቀና ያንንም የተገበረ ኮሚቴ ነው። ነገር በኮሚቴ ተሠራ ማለት ለመንፈስ ቅዱስ ሥፍራን ነፈግነው ማለት አይደለም።

በኮሚቴ ውስጥ እግዚአብሔርን ሳይሆን በኔታቸውን የሚያመልኩ አባላት ሰኮሚቴ ፈተና አይደነቅሩም ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው። ሁሉም አባል አኩል መንፈሳዊ ነው ማለት አይቻልም። ጌታ ሐዋርያት በሚል ስያሜ የእርሱ እጋሮች እንዲሆኑ ከጠራቸው መሐል እንኳን ይሁዳ የሚባል ሰው ነበረ። በእርሱ ምርጫ አንድ ከነበረ በእኛ ምርጫ አናንተው ነምቱ። ይህንን ስል ጌታ ተሳስቷል እንደማልል ትገነዘባላችሁ። እርሱ አንከንየለሽ ነውና። ይሁን እንጂ ማለት የተፈለገው የሚያስቸግሩ ስዎች ምንጊዜም አይጠፉም ነው። በጌታ አገልግሎት እንቅስቃሴ ውስጥ ከታቀፉት መሀል ይሁዳ ቢኖርም የጌታ ተልእኮ አልተጨናገፈም። እግዚአብሔር በጌታ ኢያሱስ ሕይወትና ተልእኮ ላይ መሪ ነበርና። ጌታም በፍጹም ታዛዥነት የአባቱን ፈቃድ ፈጸመ። በኮሚቴ አገልግሎት በመጀመሪያ ሲታወቅ የሚገባው ነገር የመንፈስ ቅዱስን ድርሻ ለእኛ የእኛን ለእርሱ መተው የሚባል አደራረግ አስማስለዱን ነው። እርሱ ይመራል እኛ እንከተላለን። መሪ ያለ ተከታይ ምን ትርጉም አለው? መንፈስ ቅዱስ ይመራል እንጂ አይነዳም። የሚመራውም የሚከተሉትን እንጂ ዳተኞችን አይደለም።

የምስባክ ኮሚቴ አባላት በመንፈበ ታዝዘው እንደ ፊሊጶስ የተላኩትን አንዲፈጽሙ ይጠበቅባቸዋል (የሐዋ 8፡29)። ጉዳዩ በዚህ ጊዜ የብልሃት ላይሆን የምሪት ይሆናል ማለት ነው። ቀደም ብለን የመረጃ አይደለም የመነሳጥ ነው እንዳልን፥ አሁን ደግሞ ነገሩ የጉልበት ሳይሆን የረድኤት ነው እንላለን። ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በለምምነት የሚስሩ ሁሉ ችግር ባጋጠማቸው ጊዜ ጌታ መንፈስ ቅዱስ አብሮአቸው ይወስናል። «እኛና መንፈስ ቅዱስ

ፈቅደናልና.» (የሐዋ15፡29) እንዲሉ ያደፋፈራቸው መንፈስ ቅዱስ በስብስባቸው ተገኝቶ ለዚህ ውሳኔ የሚሆን አቅም ስጥቷቸው እንደነበረ እንገነዘባለን።

መንፈስ ቅዱስ በጊዜው የሚፈልገውን የሚረዱስት የኮሚቴ አባላት ሕዝቡ በወቅቱ ምን እንደሚያስፈልገው ከሚረዳ የእግዚአብሔር መንፈስ ስምተው ወቅታዊ መላን ለሕዝቡ ያቀብላለ። መንፈስ ቅዱስ ኢትየጵያዊው ጃንደረባ በግራ መጋባት ውስጥ አንዳይቆይ የሚያስፈልገውን ተርጓሚ በጊዜው ላከለት። ልክ እንዲሁ መንፈስ ቅዱስ የጊዜውን መልእክተኛ ለሕዝቡ እንዲልክ የምስባክ ኮሚቴ አባላት ለመስማት መፍቀድ አላበቸው። ከመረጃቸው ይልቅ ታላቅ የሆነ ጌታ የጊዜውን መልእክት ለሕዝቡ የሚያመጣውን ለው ወደ እነርሱ በማምጣት ትዕዛዝ ይስጣልና።

ለመመራትና ለመታዘዝ ራሳቸውን ክፍት አድርገው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አደራውን ለመወጣት ስሚተጉ የምበባክ ኮሚቴ አባላት ጌታ ይማልድሳቸዋል (ዕብ7፡25)። ለቅዱሳን የሚያማልደው የእግዚአብሔር ልጅ ጌታ ኢየሱስ ለሕዝቡ በሚበጅ ጉዳይ ላይ ሊቃትቱ ይደግፋቸዋል። መንፈስ ቅዱስም በውስጣችን ሆኖ ለሕዝቡ እንዲሆንለት በምንፈልገው ጉዳይ ስናምጥ በማይነገር መቃተት ፍላጎቱን እንድንተገብር ያግዘናል (ሮሜ 8፡26)። የጌታ ምልጃ የመንፈስ ቅዱስ ረድኤት እውን በሆነበት ቦታ ቅዱሳንን የሚያስተሳስር ነገር ይሆናል። መንፈስ ቅዱስ የእውነት መንፈስ ነው፤ ከእውነት ጋር ያለን ጽኑ ቁርኝት በጠነከረ መንገድ እውን እንዲሆን ይመራናል። መንፈስ ቅዱስ የአንድነት መንፈሰ ነው፤ መለያየት ቤቱን እንዳይከፋፍል ምሪቱን ጠብቀው ለእግዚአብሔር ሥራ የሚተጉትን ልጆቹን ያስተሳስራል። መንፈሰ ቅዱስ እንደ ስሙ ቅዱስ ነው፤ ርኩስት ያስመርረዋል እንዳያዝንም ቅዱሳን የተቀደሱ እንዲሆኑ ለዚህ የሚበጅ ምክርን የሚመክሩ የቅድስና መልእክተኞችን ይልካል (የሐዋ 13፡4)።

ስለሆነም የምስባክ ኮሚቴ አባላት ለሕዝቡ በሳን የሚሻ ቅዱስን መንፈበ መተካት እንደማይችሉ የገባቸው ከሆኑ የእነርሱንና የእርሱን ድርሻ ይገነዘባሉ። ወኪል እንጂ ምትክ እንዳልሆኑ ያውቃሉ። በብስባቸው ለመመራት እንጂ ለመምራት እንዳልሆነ ይገባቸዋል። ለመታዘዝ እንጂ

ፈቃዳቸውን ለመፈጸም አንዳልሆነ በውል ይረዳሉ። ልክ መልእክት ከአምላክ ለመቀበል የፈጣሪን ፊት አንደሚሻ መልእክተኛ የምስባክ ኮሚቴ አባላትም የጊዜው ርዕስ አንዲሁም ለዚህ መሣሪያ የሚሆን አገልጋይ አንዲገኝ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ለመስማማት ከፈለጉ አደራቸው ገብቷቸዋል ማለት ነው። ይህ ከጠፋቸው ግን መንፈሱን የሚያስመርሩ አንገተ ደንዳኖችና ልበ ድፍኖች ስለሆኑ ሁላችንም ልንጮህ ይገባናል። ያኔ የሚያሳርፋን ሁነኛ ለምች ይሰጡናል።

የውይይት ጥያቄዎች

1. ኮሚቴ መንፈስ ቅዱስን አይስማም ይባላል፥ አውነት ነውን? ከሆነስ ለምን? ካልሆነስ ለምች ለምን አንዲህ ይላሉ?
2. መንፈስ ቅዱስ በኮሚቴ አንቅስቃሴ ውስጥ ያለውን ድርሻ በዝርዝር ግለጹና ተነጋገሩበት
3. መንፈስ ቅዱስን የሚሰማ ኮሚቴ ዓይነተኛ ባህሪያት ምን ምን ናቸው?
4. ምስባክ ኮሚቴ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አያስፈልግም የሚሰው አባባል ምን ያህል ያስኬዳል?

3.5 ምስባክ ኮሚቴና ባለአደራነት

የምስባክ ኮሚቴ አባላት አደራውን ከቤተክርስቲያን ብቻ ላይሆን ካምላክ አንደተቀበሉ ከተረዱ ዘወትር ያንን የከበረ አደራ ውጤታማ በሆነ መንገድ መፈጸም ለሰሚቻልበት መንገድ ያስባሉ፥ ይጸልያሉ ተግባራዊ ርምጃም ይወስዳሉ። ባለ አደራነት በውስጣቸው ሲሰርጽ አገልግሎት ተሳክቶና ተውበ አንዲቀጥል የሚከፈለውን ስመክፈል አባላት ይተጋሉ። ይህንን ለመፈጸም የፑልፒት ኮሚቴ አባላት የሚከተሉትን ሰባት አበይት ጉዳዮች ለመፈጸም ይተጋሉ።

የኮሚቴው አባላት በሳልና መንፈሳውያን ሲሆኑና የሁሉም ዕድገት ተመጣጣኝ ሲሆን፥ የምስባክ ኮሚቴው የባለ አደራነት አገልግሎት ከሁሉ በማስቀደም የሚያነጣጥረው የቤተ ክርስቲያን አባላት ጤንነታቸውን

የሚጨምር ምግብ ከምስባክ አንዲያገኙ ምቹ ሆኔታን መፍጠር ነው። ይህንን የሚያደርጉት የቤተ ክርስቲያናቸውን የየወትሮ ትኩሳት እየለዩ ነው። ያኔ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው ችግሯ ምን አንደሆነ፡ አንደሚወገድ በመገንዘብ ትክክለኛ ርምጃ ይወስዳሉ።

ሁለተኛው የምስባክ ኮሚቴው አባላት የባለ አደራነታቸውን ድርሻ የሚወጡበት መንገድ ቤተ ክርስቲያን ያላትንና የሌላትን ለይተው ባላት አቅም አየሮጠች በአካባቢዋ ክርስቲያናዊ ተልእኮዋን በብቃት አንድትወጣ የሚያስችላትን መንገድ በመቀየስ ለአስተዳዳሪዎቿ በማቅረብ ነው። ጤናማ ቤተ ክርስቲያን በሕያውነት መቀጠል የምትችለው አምልኮን መከከለኛ አድርጋ የሚሊዮን ተልእኮን በብቃት የምትወጣበት መንገድ ከታያት ብቻ ነው። አሳት በመቀጣጠል አንደሚቆይ ጤናማ ቤተክርስቲያን በሕይውነት አንድትቀጥል ሕያው አምልኮና ሚሲዮናዊነት አውራ አጀንዳዎቿ መሆን አለባቸው። ስለሆነም የምስባክ ኮሚቴ አንደ ባለአደራ ይህን ለመተግበር የበኩላቸውን ያዋጣሉ። በተጨማሪም ይህን አንዳታደርግ የሚገዳደራትንም ጋይል ይጠቁማሉ።

ሦስተኛው የዚህ ኮሚቴ አባላት ድርሻ አንደ ባለ አደራ ነገርን አርቆ በማየት ቅድመ ትንቢያ ነው። ነገርን አርቆ ከማየት ተለጥአቸው የሚመነጭ ሊመጣ ያለውን አየበለቱ በማቅረብ ቤተ ክርስቲያን አንዱት አንደምታመልጥ ለማሳየት ጥረት ማድረግ ነው። በዚህም ነቢያዊ ተልእኳቸውን ይወጣሉ። ተከላካይ ዘብ ሆነውም የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ለበላተኛ አንዳትጋለጥ የበኩላቸውን ጥረት ያደርጋሉ። ለዚህም ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ያፈላሉ። በዚህ ጉዳይ ከመደበኛ የኮሚቴ ስብሰባ በላይ የሚያስኬድ የጠለቀ ሸክም አንዲኖራቸው ያስፈልጋል።

አራተኛ አባላቱ ቤተክርስቲያን ማተኮር ያለበት ነገር ላይ ብቻ አንድታተኩር የሚረዳ ነገር በየጊዜው ያመነጫሉ። ዓላማዋን ዘንግታ ማድረግ በሌለባት ነገር ላይ ጉልበቷ አንዳይባክን ይደክማሉ። ቅድሚያ ሊሰጠው በሚገባ ዋና ነገር ላይ ጉልበት፥ ገዜና ገንዘብ አንዲውል ማላሰቢያ አንዲቀርብ ያደርጋሉ። ያንንም የስማቸው ሁሉ አስኪለሰች ድረስ ይደጋግማሉ። አያንዳንዱ አባል የቤተ ክርስቲያኒቱን አውራ ራአይ በባለቤትነት አስኪይዘው

ድፈስ ሉማስፈለጉት ተጨማሪ ጥረት ያሳያሉ። በዚህም መንገድ የባለ አደራነት ሽክማቸውን ይወጣሉ።

አምስተኛ የኮሚቴው አባላት ቤተ ክርስቲያን እኔና ለእኔ ብቻ ብላ በተነሡ በሮች ዙሪያ እንዳትኖር በሮቿን ለአካባቢዋ እንድትከፍት የሚሊዮን ተልእኮን የሚያነሳሳና የሚያተሳጥፍ የቸር ሥራ አገልግሎትን ከምስባክ እንዲነገር ያበረታታሉ። በተጨማሪም የክርስቶስን ፍቅር አማኞች በተጨባጭ የሚገልጠብት በጎ ምግባር በቤታቸውና በሥራቸው እንዲገለጥ የሚያደርግ ትምህርት መስጠቱን በቅርበት ይከታተላሉ። የትምህርቱንም ሚዛን መጠበቅ በየጊዜው ያረጋግጣሉ።

ስድስተኛ የምስባክ ኮሚቴ አባላት የሃይማኖት ማጽኛ ትምህርትን በመስጠት ብቻ ላይሆን ሁለንተናዊ አገልግሎት እንዲኖለበት ጥረት ያደርጋሉ። ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን ካለችበት ሕብረተሰብ ጋር እንዴት ባለመንገድ አምንታዊ ትብብር እንደምታደርግ የሚረዷትን መነሻ ጉዳዮች ለመሪዎች በማቅረብ ይኸው እንዲታያቸው ያሳስባሉ።

በመጨረሻም እነዚህ ባለ አደራዎች መንፈሳዊ አገልግሎትን በተመለከተ አጠቃላይ ግምገማ እንዲደረግ ያነሳሳሉ። የቤተ ክርስቲያን አውራ አቅዶቿ ምን ያህል በተግባር ላይ እንደዋሉና እንዳልዋሉ የሚታይበትን ሁኔታ እንዲመቻች ያስገነዝባሉ። የቤተ ክርስቲያንን ተግባሮች እብረው እንዲፈተሽ ካደረጉ በኋላ ያልተተገበሩበትን ምክንያት በሚሰፈር መልኩ በማቅረብ የቤተክርስቲያን ልዩ ልዩ የአገልግሎት ክፍሎች ራሳቸውን እንዲያርሙ ተገቢውን ዕድል ለመፍጠር ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ለመሪዎች ማሳሰቢያ ያቀርባሉ። እነዚህንም ክላይ የተገለጹትን ለባት አበይት ጉዳዮች በማከነወን አምንታዊ የባለ አደራነት ድርሻቸውን ይወጣሉ።

ይሁን እንጂ ክላይ የተገለጹትን እነዚህን ተጨባጭ ድርጊቶች የማክናወኑ ጉዳይ የእንድ ሌሊት ሥራ ባለመሆኑ ባልተሳካላቸው ነገር ፈተና ውስጥ ሊወድቁ ይችላሉ። ስለሆነም እንዳንዴ የምስባክ ኮሚቴ አባላት ለልፋታቸው አምንታዊ ምላሽ ባይገጥማቸው ያንን ችግር በማስተዋል የሚይዙበት ብልሃት ሊያዳብሩ ይገባል። ስገጠማቸው ተግዳሮት መፍትሔ ሊበጅለት እንደሚችል ተገንዝበው በትእግስትና በልብ ሰፋት ችግሩን መያዝም ይጠበቅባቸዋል። ምስባክ ኮሚቴ እንደ ባለአደራ ሊንቀሳቀስ

ከሚገጥሙት ፈታኝ ሁኔታዎች የሚከተለውን አጠር ባለ መልኩ ለማቅረብ እንሞክራለን።

ማንኛውንም አገልግሎት የሚፈታተነው አገልግሎትንም ስኬት የሚነሳው የባለ አደራነት ስሜት ሲጠፋ ነው። ማንኛቸውም ለአገልግሎት የተሰለፉ ቡድኖች እደራቸውን እንዳይወጡ ከሚቋቋሟቸው ነገሮች ዋነኛው አገልግሎትን ግዴታን ለመወጣት የሚወለድ አርምጃ አድርጎ መመልከት ነው። የምስባክ ኮሚቴው አባላት አገልግሎታቸውን የታሪክ አጋጣሚ ወይም አነርሱ ሳይፈልጉ በጫንቃቸው ላይ ድንገት የወደቀ ግዴታ አድርገው ክተመለክቱት አያተርፉም። ሐዋርያው ጴጥሮስ ለመንጋው በእረኝነት ለተሸሙት አንቅስቃሴያችሁ ግዴታን ለመወጣት አይሁን ይላል (1ኛጴጥ5:3-4)። መቼስ ምን ይደረግ? በሚል መድረሻቢስ መረዳት አገልግሎትን መወጣት ስቃይን ያበላል። ክአገልግሎት አንቅስቃሴያችን የሚያበረታታን ነገር ለማየት ሥራችንን እንደ ዕድል ፈንታ ወይም እንደ ባለአደራ ማየት ያግዘናል።

ወገናች!! ጠለቅ ብለን ብናስብ አክ የትልቁ አግዝአብሔርን ባለ እደራ መሆን ታላቅ እድል ፈንታ ነው። ያንን አደራ በታማኝነት ለመወጣት የአርሱን ፊት በጸሎት አየፈለግን ልንተጋ ይገባናል። አገልግሎታችንን እንደ ግዴታ ስናየው ግን እድሚያችንን አንቆጥራለን። «አስቲ ደግሞ አነ አገለ መጥተው በተራቸው ይጣዱ» በማለት ጡረታ መውጣት ይቃጣናል። ስለሆነም በተገኘው አጋጣሚ ነገራችንን መቀየር እንጂ የሚዘልቅ ነገርን ለማቀድ እቅም እናጣለን። ጉዳዩን ቦታ በመቀየር ልንወጣው ብንሞክርም የእይታ ችግር በመሆኑ ተከትሎን ይሄዳል። አገልግሎታችንን ዕዳውን ለመክፈል ተገዶ የሚነዳ፣ ምርጫ ያጣ ተስፋቢስ ሰው እንቅስቃሴ ስናደርገው ጥልቅ ሃዘን ውስጥ ራሳችንን እናገኘዋለን። በአገልግሎታችን ከእፎይታ ይልቅ መታክት ያይላል። ይሁን እንጂ አገልግሎታችንን ወደን በፈቃደኝነት ስናደርገው እኛን ያገዛል፣ ምዕመናንን ይባርካል፣ እግዚአብሔር ይከብርበታል። እኛም እመስግነን እንጠግብም። በዚህ መንገድ ባለአደራ የኮሚቴ አባላት እንድንሆን አምላክ ይደግፈን።

የወይይት ጥያቄዎች

1. ምስባክ ኮሚቴ እደራውን በብቃት ለመወጣት ምን ማድረግ አለበት?
2. ባለ አደራነትና ግምግማ ያላቸውን ግንኙነት አብራሩ።
3. የመሪዎችና የምስባክ ኮሚቴ በራእይ መቆራኘት ጥቅሙን አብራሩ
4. ሁነኛ ባለ አደራነት ማለት ምን ማለት ነው?

3.6 ምስባክ ኮሚቴ እንደ ባለራእይ

በመጽሐፈ ምሳሌ እንደምናነበው «ራእይ በሌለበት ሕዝብ መረን ይሆናል፤ (29:18)። የእግዚአብሔር ሃሳብ በተናቀበት ሰውም አሱን ማዳመጥ ባቆመበት ስፍራ አያሌ አስደንጋጭ ክስተቶች ይሆናሉ። ሰዎች ተከባብረውና ተዛዝነው በመቻቻል መኖር የሚቀላቸው እግዚአብሔር በእነርሱ ኑሮ ውስጥ መካከለኛ የሆነ እንደሆነ ነው። ለመሆኑ ራእይ ማለት ምን ማለት ነው? ራእይ ማለት አግዚአብሔር በወቅቱ ያቀደልንን የሕይወት ዓላማ በትክክል መገንዘብ ነው። ነገሮችን እርሱ ለእኛና ለማህበረሰቡ አንዳየው ለማየት መቻል ነው። አግዚአብሔር ምን ያያል? ቢባል እኛ የማናያቸውን ብዙ ነገሮች ያያል።

ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔር ያየለትን ነገር ከማየቱ በፊት የተቀደለ ነገር የሚያደርግና አምላኩን የሚያለደስት መልካም ሰው እንደሆነ ያስብ ነበር። አግዚአብሔር ለዚህ ወጣት ራእይ ባለየው ጊዜ ግን የሕይወቱ አቅጣጫ ሙሉ ለሙሉ ተቀየረ። ለታየው እውነትም ተገዢውን መስዋዕትነት በመክፈል ለመኖር ቆረጠ። አምላክ ባለየው ጎዳና መጓዝ ቀጠለ። የታየውን ራእይ በሚቃወሙ ሰዎች ተከሶ በንጉሥ ፊት ቀረበ። ንጉሡም ፊት ቆሞ ሊናገር እንዲህ አለ «ንጉስ አግሪጳ ሆይ ከሰማይ ለተገለጸልኝ ራእይ እምቢ አላልሁም» በማለት መለከረ።

ራእይ ለተቀባዩ በሚገባው መንገድ የሚገለጽ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው። ይህም ለግለሰብና ለማኅበረሰብ ሊሆን ይችላል። ለሰሆነም በየትኛውም ጊዜ የአማኞች አረፍት የአምላካቸው ፈቃድ ለእነርሱ ምን እንደሆነ ማወቅ ነው። ይህንን ለመገንዘብ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልምናገለግልበት ቤተ ክርስቲያን አሏያ ብንጠይቅ የምንገነዘበው ነገር ሊኖር ይችላል። የምስባክ ኮሚቴም አንደ ባለ ራእይ ይህንን ጥያቄ ጠይቆ የጠራ መልስ በማግኘት ቤተ

ክርስቲያኒቱ ለየትኛውም ዓመት የምትንቀሳቀስበትን መበመር መቱለም ይሆንለታል። ያም እንደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ራእይ ሊመስድ ይችላል።

እግዚአብሔር ይህን ማኅበረ ምዕመን አንዲያደርግ የሚጠበቅበት ምንድነው? በምድር የመኖራችን ዋና ዓላማ በእግዚአብሔር ቃል እንዴት ተቀምጧል? የምስባክ ኮሚቴው ይህንን ጠይቆ ትክክለኛውን አቡነት ከተረዳ አንዲሁም ያን ዓላማ ከተገነዘበ አርሱ ማየት ነው። ይሁን አንጂ ማየት ብቻ በራሱ በቂ አይደለም። ባለራዕዮችን ልዩ የሚያደርጋቸው ያዩት ነገር አለኪተገበር አረፍት ማጣታቸው ነው። ያዩት አውን አበኪሆን ይጸማሉ፥ ይጸልያሉ፥ ማንኛውንም ወደዚህ ተጨባጭ ድርጊት የሚወስደውን ነገር ያደርጋሉ። ራልፍ ማሆኒ የተባሉት የእግዚአብሔር ሰው እንዳሉት «አምላካዊ ራዕይ የሚሰካ፥ የሚደረበበት፥ ለሌሎቹ የሚያጋሩት አንዲሁም የተጨበጠ ነው»[12]

ምስባክ ኮሚቴ እንደባለራዕይ ይህ አውራ ነገር እንዲኖረው ይገባል። ማየትና መለማት ያቆመ የምስባክ ኮሚቴ በድን ጉባኤ ነው። እይቶም የማይተገብር የምስባክ ኮሚቴ ደግሞ ዳተኛ ነው። ይህ እንዳይሆን ምበባኩ አንደ ባለራዕይ ወደራዕዩ ፍጸሜ የሚኬድበትን መንገድ ማለየት መቻል አለበት። ሌሎች እንዲጨብወልን ልናጋራው የማንችለው ራዕይ የአውን ቅዥት ቢባል ይተላል። ያ ራዕይ ከላይ እንደገለጽነው የተጨበጠ ሊሆን ይገባዋል። ያየውን ለመተግበር የሚንቀሳቀስ የምስባክ ኮሚቴ ሊያቅደ ነገሩን መነሻና መድረሻ ያበጅለታል። ምክንያቱም ማቀድ ማለት ያየነውን በሚበፈር መልኩ ቀርጸ ዳርቻው ከየት እስከየት እንደሆነ መተለም ነውና። ይህ አንቅስቃሴ ውጤታማ እንዲሆን የጠራ ዕቅድን ይጠይቃል።

ከማቀድ ጋር ተቆራኝቶ መታሰብ ያለበት ጉዳይ ማደራጀት ነው። የምስባክ ኮሚቴ እንደ ባለራእይ ማደራጃትን የሌሎች አካላት ኃላፊነት አድርጎ በማየት አነርሱ ይወጡት ማለት የለበትም። ይልቁንም ለምስባኩ የታየውን ራእይ ለሌሎቹ የሚተገብሩ አካላት የማላየት ግዴታ አለበት። ምክንያቱም

[12] Ralf Mahoney The Making of a Leader Burbank : World Missionary Assitance Plan, 1985 (p173)

ማደራጀት ለአጥቢያዋ የምስባክ አስተባባሪዎች የታያቸው ነገር እንዲሳካ የሚኬድበት መንገድ ነውና:: ራእዩን ለማሳካት የምንመርጠው መንገድ፣መሣሪያና ስዎች ከማደራጀት ጋር ይያያዛል:: የትኛው እገልጋይ ራእዩ ቢተገብር የተሻለ እንደሆነ በግላጭ ያመለከተ መሆን አለበት:: ስለሆነም ማን ምን ያድርግ? መቼ ያድርግ? እንዴት ያድርግ? ምን ተጠቅሞ? እንዴት ተወቅሞ? የት ያድርገው? ገንዘቡስ? የሚሉትን በጥንቃቄ መመለስ አለበት::

በዚህ ጊዜ ነው በቡድን መፍስስ ዋነኛ መሆን ያለበት:: ምክንያቱም ወሳኝ የምስባክ እገልግሎት ያለመሪዎች ድጋፍ ግቡን እይመታም:: ያለ ሙሉ ጊዜ እገልጋዮች ጠንካራ ትጋት ይህ የምስባክ እገልግሎት አይሰምርም:: ሽምግልና እና የሙሉ ጊዜ እገልግሎት በውብ ቅንጅት ለእንድ ዓላማ የሚንቀሳቀሱት ብዙ ጊዜ ቢሆንም በዚህ ጊዜ ሊታይ የሚገባው ቅንጅት ከየትኛውም ጊዜ የበለጠ መሆን አለበት:: በዚህ ጊዜ ሽማግሌዎች ንቁ ራእይ እስፈጻሚ እንጂ ገለልተኛ ተመልካች ሊሆኑ አይገባቸውም:: ውጤቱን ባይ ብቻ ሳይሆኑ ለውጤቱ የሚለፉ መሆን ይኖርባቸዋል:: ሉሌዎች እንጂ መኳንንቶች አይደሉምና:: የራእይ ተጣማጅ እንጂ ፈራጅ አይደሉም:: እበረታችና አደፋፋሪ እንጂ ፈንጠር ብለው የቆሙ ነቃፊና ትችት አቅራቢ መሆን የለባቸውም:: የሙሉ ጊዜ እገልጋዩችም ለራዕዩ እቅም እንዲፈጠር በቃሉ የሚያንጹ ጠጋ ብለው መሪዎችን በውሳኔያቸው ያግዛሉ:: የእምነትና የቅንጅት ጉዞ አብረው እያደረጉ መሪዎች አይታቸው እንዲሰፋ ያግዛሉ:: የሙሉ ጊዜ እገልጋዮችና መሪዎች ተደጋግፈው ለራእዩ ተፈጻሚነት የበኩላቸውን ያዋጣሉ::

የውይይት ጥያቄዎች

1. ባለ ራእይ ማለት ምን ማለት ነው? ራእይስ?
2. ኮሚቴ ራእይ ከማየት ይልቅ ራእይ ያፍናል የሚባለው ምን ያህል እውነት ነው? በዝርዝር አስረዱ::
3. ኮሚቴ ራእይ የሚያይና የሚተገብር እንዲሆን ምን ማድረግ አለበት?
4. እግዚአብሔር ለኮሚቴ ራዕይ አይሰጥም የሚለው አባባል ምን ያህል እውነት ነው? ካልሆነስ ሰዎች ለምን እንዲህ ይላሉ?
5. ራእይ በትብብር ሊተገበር የሚችለው እንዴት ነው?

3.7 ምስባክ ኮሚቴ እንደ ጠባቂ

ለምገባ ምቹ ሁኔታን ከመፍጠር ቀጥሎ ያለው የምስባክ ኮሚቴው ኃላፊነት ሕዝቡ ላይ እደጋ የሚያደርሉትን ኃይላት ነጥሎ በማወቅ ሕዝቡን ከእነርሱ መከላከል ነው:: መከላከል ከእጥቂ መጋረድን ወይም ጥቃት ፈፃሚን እንዲመከቱ ማዚጋጀትን ይመለከታል /ኤፌ. 6:18/:: እንደ ምስባክ ኮሚቴ አባላት የቡድን እረኝነት አደራ ተጥሎብናል:: ስለሆነም የቡድን እረኞች ሆነን በምንሰጠው እገልግሎት ልብ ልንለው የሚገባ አውራ ነገር የምንጠብቀው መንጋ ለበላተኛ የተጋለጠ መሆኑን ነው::

ለምሳሌ የትም ሲዘሉ የከረሙ ዋልጌዎች ታማኝ ሚስት የሚገኘው ከጴንጤዎች አምባ ነው በማለት እኛ እካባቢ ያንዣብባሉ:: የልብ ለውጥ ሳይኖር አህቶቻችንን ለማጥመድ ሊያደቡ ቀደም ብለን ልባቸውን በጽድቅ ቃል ካልጠበቅን ችግር ያጋጥመናል:: ነገሩ ጠንከሮ ባልጠበቅነው መንገድ ሊሄድ ያኔ የኛ ድርሻ እንደ እረኛ እነዚህን እራዊት ነጥሎ በማየት ሊበሏቸው ያዘጋጇቸውን የዋሃን ከአፋቸው ማስጣል ነው:: በልዩ ልዩ ነገሮች ሊታለሉ ይችላሉ ብለን የምንገምታቸውን ወገኖች ልብ ሊጠብቃቸው በሚችል የጸጋ ቃል በመሙላት የመከላከል ተልእኮአችንን እንወጣለን:: ያኔ ጠባቂነታችንን በተግባር ለመወጣት የሚያበቃን መስመር ላይ ነን ማለት ነው::

ሐገርን ከጠላት ጥቃት የሚጠብቁ የመከላከያ ከፍሎች የተለያየ ስምሪት እንዳላቸው ሁሉ የምስባክ ኮሚቴም በውስጡ ባሉት አባላት አማካኝነት ህዝቡን ለመጋረድ የራሱን ርምጃ ይወስዳል:: ይህንንም ወቅቱን የሚመጥኑ ወሳኝ የእምነት ማጽኛ ትምህርቶች እንዲለናዱ በማድረግ ይወጣዋል/ቲቶ 2:1-10/:: የምበባክ ኮሚቴ የጥበቃ ሥራውን በልዩ ልዩ መንገድ ያከናውናል:: የተመጣጠነ ምግብ መመገብ ስውነት በበሽታ እንዳይጠቃ እንደሚከላከል ሁሉ መንፈሳዊ ምግብን እንደሚገባ የተመገቡ በሙሉ ለከፉው ጥቃት በቀላሉ አይጋለጡም:: ስለሆነም ዛሬ እንደ እሸን የፈላውን የስህተት እስተምህሮ በመረዳት መንጋውን በጽድቅ እውነት ማስታጠቅ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የማስጣል እንዱ ገጽታ ነው:: ዘረፋው እየተራቀቀ በመጣበት ዓለም ጥበቃው እጅግ እየተራቀቀ መጥቷል:: እኛም እቅማችን የፈቀደውን በሙሉ በማድረግ

የእግዚአብሔር ሕዝብ ከክፉው ተጽእኖና ጥቃት ነጻ የሚሆንበትን ጥበቃ ማጠናከር አለብን።

የምስባክ ኮሚቴ እንደ ጠበቂ ዓይነተኛ ተልእኮው ምእመናን የሚጠበቁበትን ምቹ ሁኔታ መፈጠር ነው ። «ጠላትን ማወቅ ግማሽ ድል ነው» እንዲሉ የአማኝ ጠላቶች እነማን እንደሆኑ ምእመኑ ለይቶ እንዲያውቅ በመርዳት ሌላው ጥበቃን ይወጣል። ጥበቃውን በበለጠ የሚያጠናከረው ደግሞ ተገቢውን መንፈሳዊ ትጥቅ ከምስባክ በማቅረብ ነው። ጠላትን ለማጥቃት የሚቻልበትን መንፈሳዊ ስልጠና መስጠት በበለጠ አማኙ የነቃ ልቦና እንዲኖረው ያደርጋል። ስለሆነም በምስባኩ ላይ በሚፈጸሙ አገልግሎቶች ዙሪያ የሚተገ ሁሉ ምእመናን ከመድረክ ለሚጠበቁበት ሁኔተ በቂ ትኩረት ይሰጣሉ። ለኛም እንደ ምስባክ ኮሚቴ አባላት ምዕመናንን መጋረድ የሁልጊዜ ተግባራችን ይሆናል ማለት ነው።

ስለዚህ መከላከል ስንፈልግ የምናደርገው ሳንፈልግ የምንተወው ጉዳይ አይደለም፣ ይልቁንም የጎልውና ጉዳይ ነው። አረኖ ተከላካይ ወይም ጥቃት ፈፃሚን እንዲመከቱ አስልጣኝ እንደሆነ ሁሉ የምስባክ ኮሚቴ ይህንን በቡድን በመፈጸም የአረኝነት ተልእኮውን ይወጣል። ዘበኝነት የሚለው የአረኝነት ፍቺ መንከባከብንና መጠበቅን ማንነታቸው ላደረጉ አረኞች ዓይነተኛ መግለጫ ነው። በታላቅ ክፍያ እግዚአብሔር የራሱ ያረገውንና ወበት የሰጠውን ሕዝብ ላይደናቀፍ በታማኝነትና በመሰጠት ጉዞውን እንዲቀጥል የማያቋርጥ ጥበቃ ያሻዋል። ሌሎች መጥተው ጸጋቸውን እንዲያካፍሉን መፍቀዱ ባይከፋም ከመጠን ያለፈ ተጽዕኖን በእኛ አሠራር እንዲያመጡ መተው ግን አግባብ አይሆንም።

መንጋውን ማብላት ሳይሆን መንጋውን መብላት ዓይነተኛ ባህሪያቸው የሆኑ አውሬዎች በብዛት በሚገኙበት በዚህ ዘመን ሐቀኛ የምስባክ ኮሚቴ አባላት በሚከፍሉት ዋጋ ሕዝቡን ከእነዚህ ጨካኞች ለማስጣል ታላቅ ጥረት ያደርጋሉ። የቡድን አረኞቹ በእውነተኛ ፍቺ የጌታቸውን ፈለግ ሲከተሉ አበከ ሕይወት መስዋዕትነት ሊያደርሳቸው የሚችል ፈተና ይደቀንባቸዋል። አንዳንዶቹም ሊሰዉ እንኳን ይችላሉ። ሐቀኛ ጠባቂ ከፉው ሲመጣ ከክፉው ጋር ፊት ለፊት ይገናኛል። ስልቱ መንዳት ላይሆን መምራት ነውና። በጥበቃ መሰዋት የአረኝነት ልዩ መለያ ነው። ከመልካሙ አረኖ ለመንጋው ጥንቃቄን

የተማሩ ሁሉ ይህንን የጥበቃ ኃላፊነታቸውን በቸልታ አይመለከቱም። ስለሆነም የምስባክ ኮሚቴ አባላት አደራቸው ምን ያህል የጠበቀና የጠለቀ እንደሆነ ተረድተው የጌታቸውንና የሐዋርያቱን ፈለግ በመከተል እስከሞት በታማኝነት መጓዝ ይኖርባቸዋል /ራዕይ 2፡18/። ይህንን በማድረግ ለሚተገ በሙሉ የአረኞች አለቃ ሲገለጥ ብድራታቸውን ይቀበላሉ /1ኛ ጴጥ 5፡1-4/።

የውይይት ጥያቄዎች

1. የምስባክ ኮሚቴ ጠባቂነቱን እንዴት ይወጣል?
2. መንጋውን መጠበቅ የሚያስከፍላቸው መሰዋእትነቶች ምን ምን ናቸው? በዝርዝር ጻፉና ተነጋገሩባቸው።
3. መንጋውን በመጠበቅ ለተገ ከጌታ ዘንድ ያላቸው ብድራት ምንድነው?
4. ለመንጋው ደንታ ቢስ የሆኑትንስ ጌታ እንዴት ይመለከታቸዋል?

ክፍል አራት የምእመኑ ምላሽ ለመድረኩ

4.1. ምእመኑ እንደ እምላኪ

«ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ (መዝ 122)፡1

አያሌ ምዕመናን በአብዛኛው ወደ ጸሎት ቤት የሚመጡት ጌታ ምን ይናገረኛ ል? በሚል ከፍተኛ ጉጉት እንደሆነ ይታመናል። አሁንና እዚሁ የመኖርን ትክክለኛ ትርጉም የሰጣቸውን አምላክ ÷ በመጪው ዓለም ደግሞ የድንቅ ተስፋ ባለቤት ያደረጋቸውን ጌታ ለማወደስ በመንጓት ወደ ጸሎት ቤት እንደሚመጡ ብዙዎች ይናገራሉ። እነርሱን ከሚመስሉ ወገኖቻቸው ጋር ቢያደርጉት የበለጠ ትርጉም እንዳለው በመገንዘብም ወደ እንድነት የአምልኮ ጣቢያውም ብቅ ይላሉ። አያሌ ምእመናን በግላቸው የውስጥ ዝግጅት አድርገው እንደሚመጡ ሲነገር እንሰማለን። የሕይወታቸውን ጌታ ለመስግነው ሌሎች ደግሞ እንዲያመሰግኑላቸው በመፈለግ ወደ ጸሎት ቤት ብቅ የሚሉ ጥቂቶች አይደሉም።

ይሁን እንጂ ለአርሉ ክብር / 2 /

ባዜምለት ብጮኽለት ብለግድለት

ብዙልስት ግድየለኝም ብለው እንደዘመሩት ዘማሪያን የተከማቸው ሕዝብ ምን እየሆኑ ነው? ብሎ እስኪታዘባቸው ድረስ ራሳቸውን ረስተው አምልኮና ስግደት ለጌታ ኢየሱስ በሚታይ መንገድ ለመስጠት የሚመጡ ብዙዎች ናቸው። የእነርሱ ትኩረት እርሱ ሊከብር ማየት ስለሆነ ለሌላው ደንታ የላቸውም። አንደ ዳዊት አንዳንዶች እስኪናቁ ድረስ ከልባቸው ይህንን ያደርጉታል። ሁሉም በዚህ መንፈስ ውስጥ ናቸው ብሎ መናገር ቢያስቸግርም የአብዛኞቹ ትኩረት በጌታ ደስ መሰኘታቸውን በመግለጥ እርሱን ከፍ ከፍ ማድረግ ነው። አንዳንዶቹም የትናንቱን መልካምነቱን አያስቡ ዛሬም አንዲሁ ይመጣልኛል አያሉ ጌታን ይባርኩታል። በዚህም ጊዜ ጌታ ጨለማቸውን አንዲያበራ፣ ቁጠሮአቸውን አንዲፈታ፣ ጠማማውን ደግሞ አንዲያቃናላቸው በዕለት ተዕለት ርምጃቸውም ፈቃዱን በመፈጸም ራሱን በትሮአቸው አንዲገለጥ ግብጥ ያደርጉለታል። ጌታዬ አንተ የትናንት ብቻ አይደለህም፣ ዛሬም በተለየ መንገድ ትነካኛለህ። ነገም ሁኔታዬን ትቀይራለህ፣ በሚል ልባዊ መስጠት ውስጥ ስውስጥ ከጌታ ጋር ልባዊ ግኑኝነት የሚያደርጉ በርካቶች ናቸው።

ብዙ አምላኪዎች ከመድረኩ (ከመሠዊያው) የሚፈስውን የአምላክ ባርኮት ለመቀበል ታላቅ ጥማት አላቸው። ይሁን እንጂ ሁሉም በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ ብሎ ማሰብ አግባብ አይሆንም። አምላኪ ከመሆን ይልቅ አዋኪ መሆን የሚቀናቸው ምዕመናን ማየት ከጀመርን ውሎ አድሮአል። አዋኪ አምላኪዎች አዘውትረው የሚፈጽሙት ስህተት የሚስተዋለው ለመድረኩ ተቃራኒ ምላሽ በመስጠት ነው። በተደጋጋሚ የሚፈጸሙ ስህተቶችን የሚወክል አንድ ተዛማጅ ምላሌ እናንሳ። የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ በአንድ ወቅት ሠርግ ፕሮግራም ላይ ሲሰብክ ገና ከጅማሬው ሰላምታ ሲሰጥ አንዲት ሴት አሜን አለች። ጉዳዩ ግርታን ስለፈጠረበት የመግቢያ ዓረፍተ ነገሩን ለመጀመር «አንድ የኢንሹራንስ ድርጅት .. ብሎ ንግግሩን ላይጨርስ..» አምላኪዋ «አሜን!! አሜን!!» ማለቱን ተያያዘችው።

ነገሩ እንዲቆም ብሎ ዛሬ ዛሬ ያስቸገረን ተንሳፋፊ አሜን ነው አለ። በዚህም ጊዜ «አሜን! አሜን! አሜን!!» ማለቱን ስትቀጥል ህዝቡ ለማቆም የሚያስቸግር ሳቁን ለቀቀው። ከዚያም እንደምንም ተማጥኖ ሳቁን ካስቆመ

በኋላ መልእክቱን ቀጠለ። ይሁን እንጂ ቦታቸውን ባልጠበቁ አሜኖች እየተንገላታ የዕለቱን አገልግሎት ፈጸመ። ንስሃ የሚጠይቁ ዓረፍተነገሮች ሲነገሩና ልብ ሲነካ የተለመደው ነገር ከንፈር መምጠጥ ወይም ዘለላ ዕንባ ማፍሰስ ነበር። አሁን አሁን ግን የተግሳጽና የዘለፋም ቃል ከመድረክ ሲነገር አሜን!! አሜን!! አሜን!! ማለቱን የለመዱ አዋኪዎች ለመድረኩ እንቅፋት ሲሆኑ ይስተዋላል።

በሌላ ጊዜ ደግሞ «አዋኪ አምላኪዎች» ራሳቸውን የሚገልጹበት መንገድ ድንገተኛ ማንብረቅ ያስበት ከፍተኛ ድምጽ በመጠቀም በአካባቢው ያሉትን አባላት ማስደንገጥ ነው። አልፎ አልፎም ሲያመልኩ ከተሰየሙ ምዕመናን ያልተጠበቀ ተምዘግዛጊ ድምጽ ሲመጣ መልእክታቸውን በድንጋጤና በመደናገር የሚያቋርጡ ስባኪዎች ጥቂት አይደሉም። ጌታ ውስጣችንን ሲነካ ደስታችንን በልዩ ልዩ መንገድ የምንገልጥበት ጊዜ እንዳለ እሙን ነው። ይሁን እንጂ ደስታችን ሌሎችን ሲያሸብርና ድንጋጤ ላይ ሲጥላቸው አይገባም ። ስለሆነም አዋኪ አምላኪዎች ለድምጻቸው መጠን ቢያበጁለት ሌሎችን በምስጋናቸው እንዲተባበሯቸው ያግዛሉ። የሚደረገው ጤና ሆኖ ሁሉን እንደሚያንጽ ከተረዳን ያንን መንገድ ለሁሉ እንደሚጠቅም ማድረግ ይቻላል። በዕብ 10:25 « ለፍቅርና ለመልካም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በእርሳችን እንተያይ» ተብሎ የለ? መተያየታችን ሲያንጸንና የአምላክን ረድኤት ሲያመጣልን ደስታችንን ይጨምራል። ይሁን እንጂ የሚያሸብርና የሚያውክ ሆኖ ሲገኝ ለውን ዛሬስ ባልመጣሁ እናለኛለን። ከሌሎች ጋር የማንጋራው ደስታ ግላዊ ፈንጠዚያ ስለሚሆን ነገራችንን በልክ ማድረግ እንማር።

የውይይት ጥያቄዎች

1. ምእመናን ከአዋኪ አምላኪነት የሚታቀቡት እንዴት ነው?
2. በአምልኮ ምእመናን ድርሻቸውን የሚያበረክቱት እንዴት ነው?
3. ሕያው አምልኮ አውን እንዲሆን የምእምናን ድርሻ ምንድነው?

4.2. ምእመኑ እንደ ተመጋቢ

በየአህጉሩም ሆነ በሌላ ጊዜ ቅዱሳን በተሰበሰቡበት ሥፍራ አማኞች በብዙ ቁጥር ተከማችተው የሚገኙበት ዋና ምክንያት የሚጠቅማቸውን መንፈላዊ ምግብ ለማግኘት ከመጓጓት የተነሳ ነው። ምግብ የናፈቀ ረሃብተኛ ፥ ጥም ያቃጠለው የሚጠጣ ፈሳጊ እንዲሁም ታርዞ ለመልበስ የናፈቀ ሁሉ እነዚህን ወደሚያገኝበት ጣቢያ ሲሄድ በብዙ ጉጉት እንደሆነ ለማንም ግልጽ ነው። ልክ እንደዚሁ እያሌ መንፈላዊ ማዕድና ከሰላ ፈሳጊ ምዕመናን ከምስባክ የሚፈስሰውን በረከት እንደ ተመጋቢ ለማስተናገድ በመጓጓት ወደ ጸሎት ቤት ይመጣሉ። አመጣጣቸው በፕሮግራሙ ፍሰት ውስጥ ተካተው የሚላክላቸውን ባርኮቶች ለመቀበል ባላቸው ጉጉት ነው።

ስለሆነም ቅደም ተከተል ጠብቀው ከመድረኩ የሚፈሱት አገልግሎቶች ረሃባቸውን እንዲያረኩላቸው ጥማቸውን እንዲቆርጡላቸው በጉጉት ይጠባበቃሉ። ከፕሮግራሙ ለውሳኔ የሚያበቃቸውን ትክክለኛ መንፈላዊ እቋም እንዲይዙ የሚደግፋቸውን ምክር ማግኘት ይሻሉ። የሚጸናው የእግዚአብሔር ሃሳብ መሆኑን በእንድም በሌላም መንገድ ስለሚያውቁ ለመንፈላዊ ጉዞአቸው መሳካት የሚበጅ መልካም ውሳኔ መወሰን እንዲቻላቸው ከመካሪዎቹ የተጨበጠ ነገርን ለማግኘት ይፈልጋሉ። በቃሉ እንዳነበብን «በአመራር ጉድለት መንግስት ይወድቃል የመካሮች ብዛት ግን ድልን እርግጠኛ ያደርጋል» (ምሳ11:14 አመት)

እውነት ነው የመካሮች ብዛት ድልን እርግጠኛ ያደርጋል። እንኳን ለግለሰብ ለአገርም ቢሆን ምክር ጠቃሚነቱ እሌ የማይባል ነው። ይልቁንም እግዚአብሔር እንደሚናገርበት በሚታመንበት ሥፍራ ጤነኛ መንፈላዊ እቋም ያለው በሙሉ ከፈጣሪ ጋር ባለው እርምጃ እንዲሁም በዕለት ዕለት እንቅስቃሴው ከአርሱ ጋር በለምምነት ለመራመድ ምክሩን የማይሻ ማን ነው? ምዕመናን እንደተመጋቢ የሚሹት ቀዳሚ ነገር መመከር ነው። ሌላው እንደተመጋቢ የሚናፍቱት ነገር ጌታ በሚፈቅደው መንገድ መጓዝ ወይም ትክክለኛ ምሪት ማግኘት ነው። አማኞች መካሪ የሚፈልጉት ዳዊት እንዳለው ከተመከሩ በኋላ በአርሱ መንገድ እንዲጓዙ ነው «በምክርህ መራኸኝ ፤ኋላም ወደ ክብር ታሰገባኛለህ» (መዝ 73:24 አመት) ።

ምእመናን እንደ ተመጋቢ ዓይተው ከመድረክ የሚጠብቁት ሌላው ነገር ደግሞ መጽናናትንም ነው። ጌታ ዛሬ ካለሁበት ሁኔታ የሚያወጣኝ ነገር ምን ይለጠኛል? ነገሬን እይቶ ልቤን ካከበደ ነገር ያላቅቀኛል በሚል ጉጉት ወደ ጸሎት ቤት የሚጎርፉት ምዕመናን አያሌ ናቸው። ሕይወት የፍልሚያ ጣቢያ ነው። በዚህ ፍልሚያ ምእመኑ አያሌ ጉዳቶች ይደርሱብታል። ከእነዚህ ጉዳቶቹ ለማገገም የሚያስችሰውን ምርኩዝ የሚቀበለው በአብዛኛው ጌታ በፑልፒት በኩል በሚያቀርብለት አገዛ ነው። ጌታ ዛሬ ተናገረኝ፥ ብለው በሙሉ አረፍት ወደየቤታቸው የሚሄዱ ብዙ እንደሆኑ ሁሉ፥ ስላልሆነላቸው ነገር በመከፋት የሚመለሱ ጥቂቶች አይደሉም።

እንዳንድ ጊዜ መድረኩ ይህንን ማፍለስ አቅቶት አያሌ ያልተጠበቁ አስደንጋጭ ክስተቶች ሲያጋጥሙት አምነቴ ይገነባል ብሎ የመጣው ምእመናን ግራ ተጋብቶና ፈራርሶ ለመሔድ ይዳረጋል። አድን ብሎ መጥቶ ሞቶ የሚሄድ የሚያጋጥመበት ጊዜም አይጠፋም። በልቅሶ ፈንታ መጽናናትን በሐዘን ፈንታ ደስታን ያበሳል የሚባለው የአንድነት እምልኮ ጥንቃቄ በጎደለው ሰው እጅ ሲወድቅ የሚያመጣው ጉዳት ቀላል አይሆንም። በጸሎት ቤት ካጋጠማቸው ጉዳት የተነሳ ዛሬም ማገገም ያቃታቸው ጥቂቶች እንዳልሆኑ ይነገራል። ምግብ ፍለጋ ሄዶ መርዝ በልቶ የሕይወት ዘመኑን ጸጸት በሞላበት መንገድ የሚገፋ ጥቂት አይደለም።

ዛሬ ዛሬ ብዙዎች ከአናት ቤተክርስቲያናቸው ምስባክ ይልቅ ወደ ሌላው ሥፍራ የሚሄዱት ረሃባቸውን ማስታገስ የሚችል መልካም ነገር ፍለጋ ነው። ይሁን እንጂ ጠለቅ ያለ ትምህርት እናገኛለን ብለው ራሳቸውን ሲወጡት የማይችሉት ችግር ውስጥ የዘፈቁ በርካቶች ናቸው። በተጨማሪም ትምህርት ፍለጋ ሄደው ባመጡት በሽታ እያሌ ምዕመናንን የሚበክሉ ጥቂቶች አይደሉም። የሚገርመው ይህ የሚሆነው እንደበክሉ እንኳን ሳይታወቃቸው ነው። ሁሉም ነገር አንድ ጸሎት ቤት ውስጥ ተከማችቶ ይገኛል ብሎ ማሰብ ስህተት ነው።

በእንድ ነገር ጠንካራ የሆነ ጸሎት ቤት ሁልጊዜ በሁሉም የተሳካለት ስለማይሆን የማረከንን የምስባክ አገልግሎት ፍለጋ ሔደን ተጎድተን እንዳንቀር

እናስተውል። ትምህርት ስብዙዎቻችን ጠቃሚ ነው። መንፈሳዊ ሕይወትንም ወደ ብስለት ለማምጣት ጠቀሜታው የጎላ ነው። ከፑልፒት የሚመጣን መልካም ትምህርት ፍስጋ የሚንከራተቱ ጥቂቶች እይደሉም። ይህ የሚሆነው ወጥነቱን የጠበቀ ማዕድ ከፑልፒት ስለማይፈስ ነው።

ከእያሌ ጊዜያት ጉጉት በኋላ ነገሮች እንዳሰቡት ሳይሆኑ ሲቀሩ ምእመናን ይህንን እናገኛለን የሚሉስትን ስውር ምስባክ በየመንደሩ ያደራጃሉ። ልብ እንበል!! እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት ለመድረኩ የተሰጠ የተጠና ምላሽ ነው። ይሁን እንጂ ምእመናን በዚህ መንገድ ሄደው የፈሰጉትን የማያገኙበት ጊዜ ብዙ ነው። እንደውም እብዛኛውን ጊዜ እንዲህ ዓይነቱ ስውር የመንደር ምሰባክ ጉዳቱ ያመዝናል። ትርምሰ ተፈጥሮ፥ ጉዳዩ መሪዎች ጋ ደርሶ ፥ የስውር ስብስባዎችን ቤተ ክርስቲያን ስማስቆም ብትነሳ፥ ምሬታቸው ይህ ነው እይባልም። ምናስ ቀደም ብሰው ወደዚህ ከሚወስደን ነገር ቢታደጉን ኖሮ? ይላሉ።

ምሰባኩ በቂ መንፈሳዊ ማዕድ ሳያቀርብ ሲቀር ነገሮች እንዲህ ዓይነት መልክ የሚይዙበት ጊዜ ጥቂት እይሆንም። ምእመኑ እንደተመጋቢ ከምስባኩ የሚጠብቀውን ሲያጣ ለመድረኩ የሚሰጠው ምላሽ ምስባኩን መተው መሆኑን በማወቅ ምስባኩን እንጠንቀቅሰት። ስለሆነም ተጠርተናል የምንል ሁላችን የምእመኑን ወቅታዊ ፍላጎት እያየን በቂ መንፈሳዊ ማዕድ ከመድረኩ እንዲፈስ እንትጋ!! ይህንን ስናደርግ ሕዝቡ የሚፈልገውን ሳይሆን የሚያስፈልገው ላይ እናተኩር። የሕዝቡን ፍላጎት ስበጎ ምላሹ ለማርካት ጥጃ እንደሠራው እንደ አሮን እንዳንሆን እንጠንቀቅ። ምንግዜም ፑልፒቶቻችን የሚመከሩ፥ የሚያስተምሩ፥ የሚያጽናኑ እንዲሁም ስተግባራዊ ርምጃ የሚረዱ መንፈሳዊ ምግብ እያፈሰሱ እንደሆነ በእትኩሮት እንከታተል። ምከንያቱም ምእመኑ ለመድረኩ የሚሰጠው ምላሽ ከእምላኪነት ቀጥሎ ተመጋቢነት ነውና።

የውይይት ጥያቄዎች

1. ምእመኑ ከምሰባኩ ምን ያህል ሚዛን የጠበቀ ምግብ ያገኛል? ካላገኘ ለምን?

2. ምእመኑ እንደተመጋቢ ምን ይጠበቅበታል?
3. ምእመኑ የሚያስፈልገውን ለመመገብ ምን ማድረግ አለብን?

4.3 ምእመኑ እንደ ተባባሪ

ምእመናን ከመድረኩ የሚፈሰውን ስመቀበል የሚመጡ ገለልተኛ ተመልካቾች እይደሉም። ይልቁንም ምስባኩ ላይ የሚሆነው ማንኛውም መንፈሳዊ ድርጊት እንዲሳካ የበኩላቸውን የሚያዋጡ ተሳታፊዎችም ጭምር መሆናቸው ሲዘነጋ እይገባም። ስለሆነም ምእመናን ገና ወደ ጸሎት ቤት ከመምጣቸው እሰቀድሞ ለመድረኩ ምላሽ እንደሚሰጥ ተሳታፊ ውስጣቸውን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል። የእዲስ ኪዳን አገልግሎት ከእንድ አቅጣጫ የሚቀበሉት ብቻ ሳይሆን ማስተዋል የተሞላበት ምላሽ የሚሰጡበት ነው። ምእመናን በእያንዳንዱ የመድረክ እንቅስቃሴ እንደሚተባበሩ ባይታሰብ ከመድረኩ የሚፈሰው ማንኛውም ነገር ምን ትርጉም እለው? ስምሳሌ በሳምንታዊ ፕሮግራሞች እንዲመጡ ባንጠብቅ ለምን ማስታወቂያ እንናገራለን? መዝሙር እንዲዘምሩ መሪ ያደረግነው የእነሱን እምንታዊ ተሳትፎ በመጠበቅ እይደለምን?

በመባ እናመልካለን ሰንልም ምእመናንን በመስጠት ተባበሩ ብለን ግብግ ማቅረባችን መሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ነው። ምእመኑ እንደተባባሪ በእያንዳንዱ ነገር መንፈሳዊ ንቃት ያለበት ርምጃ ቢወስድ እምልኮ ሕይወት ይኖረዋል። ሳምንታዊ የልማድ ተግባራትን ለማከናወን ምንም የውስጥ ዝግጅት ሳያደርጉ የሚመጡ ምእመናን መድረኩ ላይ ጠንካራ ችግር ይፈጥራሉ። ለምሳሌ እንዘምር ሲባል ጸጥ ቢሉ፥ እንጸልይ ሲባል ቢያወሩ፥ እስቸጋሪ ይሆናል። በተለመደው የአሁድ እምልኮና በቤትም ለሚደራጁ ፕሮግራሞች ምእመኑ ምላሹ እምንታዊ ነው። ይሁን እንጂ እስካሁን ከምናውቀው የበለጠ ውበት በፕሮግራሞቻችን ላይ ስመጨመር ምእመኑ ይፋዊ ምላሽ የሚስጥበት መሰመር ልናበጅለት ይገባናል። ምእምኑ የተባባሪነት ምላሽ እንዲሰጥ እንዳንድ የምእመናን ሕብረቶች እንዲህ እይነቱን መንገድ ይጠቀማሉ። ውጭ ለትምህርት በቆየሁባቸው ጊዜያት ምእመናን እንደተባባሪ ሲያደርጉት እይቼ ደስ የሚለኝ ለምድራም የተመኘሁት ነገር

ነበር። በእገራችን እጥቢያዎች ሙሉ ለሙሉ እንተግብረው ባልልም ከጠቀመን ልምዱን እንድንወስድ ድርጊቱን በሚከተለው መልኩ እቀርባለሁ።

«ምእመኑ ጸልዮ፥ ዘምሮ፥ ሰምቶ ፥ እንዲሁም ያለውን
ሰጥቶ ነገር አያበቃም። በዕለቱ አገልግሎት ምን እንደቀረለት
እንዲናገር ዕድል ይሰጠዋል። ይህንን እለከ ስምንት
መቶ ምእመናን ይሰበሰቡበታል የሚባል ጸሎት ቤት ሁሉ
ሲለማመዱት አይቻለሁኝ። ገመድ የለሽ የድምጽ
ማጉያዎች በብዛት ተሰናድተው እስተናጋጆች ምላሽ
ለሚሰጡ ምእመናን ያንን መናገሪያ ያቀብላሉ።
ተናጋሪዎቹ ዕድሉ ለሁሉም እንደማይደርስ ስለሚያውቁ
ንግግራቸው የተመጠነ ነው። በዚያ የትኖው የዕለቱ መንፈሳዊ
ድርጊት እንደነካቸው ጭምር ይናገራሉ። ልምድ
ስላዳበሩም ዝባዝንኬ ሳያበዙ ወደ ሚናገሩት ቁም
ነገር ይሄዳሉ። በዚያም ለሚቀጥለው ተናጋሪ
ተግባራዊ ምላሌነትን ያሳያሉ። በዚህ ጊዜ ምስክርነት
፥ የጸሎት ጥያቄ ፥ እንዲሁም ከመልእክቱም ሆነ
ከእለቱ ያገኙትን ቁምነገር አጥር ምጥን አድርገው
ያቀርባሉ» በዚህም ምላሻቸውን በተግባር ይገልጻሉ።
ለምሳሌ የእለቱ ስብክት ለሚሊዮናዊነት አገልግሎት
የሚያነሳለ ክሆነ በሰማህት መልእክት ልቤ
ስለተነካ ከገቢያ ይህን ያህሉን እስጣለሁኝ ይላሉ።
ሌሎቹም ይህንን ለምተው ከተነሳሉ ያንኑ
ያደርጋሉ። መሪዳት ያለበትን ግለሰብ የሚነካ
ነገርም ስምተው ከሆነ ወዲያው ምላሽ ይለጣሉ።
ባለጠጎች ለሰሆኑ ብቻ ላይሆን የተግባር ለጆችም
ጭምር ስለሆነ ነው። በሌላ አቅጣጫ የሚናዘዙበት ነገርም
ካለ ይህንን የምላሽ ጊዜ በማስተዋል ይጠቀሙበታል።
እንዲህ በማድረጋቸው ያ ጊዜ ምእመኑ ምላሽ የሚሰጥበት
ጊዜ ተብሎ ይጠራ እንደነበር አስታወሳለሁ።
ሰንባኤው እንግዳ ሆኖ የመጣ ለው ሲኖር ቀን ጥቂት ነገር
እንዲናገር ዕድል ይሰጠው እንደነበርም ትዝ ይለኛል»[13]

እንዲህ ዓይነቱ ነገር ከጠቀመን ለእኛ እውድ ተስማሚ አድርጎ መተግበር ይበጅ ይሆናል። ይሁን እንጂ እንዳለ ብንገለብጠው አንዳንድ ምእመኑን በክፋት ማነሳሳት ለሚፈልጉ ሰዎች መሣሪያ እንዳይሆን እፈራለሁ። አፍራሽ ቀዳዳዎችን በመድፈን ምእመኑ ተግባራዊ ምላሽ የሚሰጥበትን ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ነው። እንዴት የሚለው ጥያቄ በየጸሎት ቤታችን ሁኔታ ይወሰናል ብየ እምናለሁ።

በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ምእመናን እርስበርስ ሲገናኙ ምላሽ በመለጠት እንዲተናነጹ የሚያደፋፍሩ ምንባቦችን እናያለን። በ1ኛ ቆር 14 ፡ 27 በምትለበለቡበት ጊዜ ለአያንዳንዱ መዝሙር አለው፥ትምህርት አለው፥ በልሳን መናገር አለው፥ መተርጎም አለው ፥ የሚለው የሐዋርያው ጳውሎስ ንግግር የሚያስረግጠው ምእመናን በተሰበሰቡበት ቦታ በአያንዳንዱ የአካል ብልት ለክርስቶስ አካል መታነጽ የሚሆን መልካም ነገር በብልቶች በሁል እንደሚመጣላቸው ነው። እንዲህ ዓይነቱ የምእመኑ ምላሽ ዛሬም በእኛ ሕይወት በተግባር የሚገለጠው ምእመናን ቦታ በታችንን እውቀን ምላሽ እንድንሰጥ ስንደፋፈር ነው።

እርስበርስ በጥበብ ለመማር የሚቻለው እንዲሁም የሚያንጽና የሚገነባ ተግላጽ ለመለዋወጥ የምንችለው ምእመናን እንደተባባሪ ያሳቸውን ሚና ያጎለበትን እንደሆነ ነው። የምእመናን ድርሻ ለምስባኩ ምላሽ ከመስጠት አኳያ ሲታይ መተባበር እንደሆነ ማወቅ ወደ መድረኩ ለሚመጡ ሰዎች ግልጽ ሲሆንላቸው ይገባል። ግና ስትብብር የከፈትነው በር እሱታዊ እዝማሚያ በሚያሳይበት ጊዜ ደግሞ የሁነኛ አገልጋዮችን ልብ ይሰብራል።

እንዳንድ ምእመናን እባላት እንደ ተባባሪዎች ያሳቸውን ሚና ሲስመ ክተስመረው መስመር እልፈው አትተባበሩ እንኳን ሲባሉ የማይስሙበት ጊዜ አለ። ከቃሉ ያፈነገጡ ጉዳዮችን መድረኩ ሲያስተናግድ እንዳንዶች ትብብር ለመስጠት ወደ ኋላ አይሉም። እንደውም የእንደዚህ ዓይነቶች ምዕመናን እጀብ ነው እንዳንዶችን በመድረክ ከሚፈጽሙት በህተት እንዳይታረሙ እንቅፋት የሆነው። የጠቀሟቸው መስሎአቸው በቤታቸውና በአካባቢያቸው መድረክን ያለናዱላቸዋል። እነዚህም አፈንጋጮች በሕዝቡ ጉያ ተሸሽገው የእልክ ዘመናቸውን ያረዝማሉ። መሪዎችና አገልጋዮችን እምቢ ብሎ ከመጡው ጋር የሙጥኝ የሚያለኝ ትብብር ምእመኑ እንደተባባሪ የሚፈጽመው የክፋት ምላሌ ነው። እንዳንዶች ተዉ እባሌን አትተባበሩ ሲባሉ ያዚያን ተቃራኒ ያደርጋሉ። ምእመናን እንደተባባሪ በጎውን እንጂ ከፋን ከመምስል እንዲታቀቡ መርዳት የበላል አገልጋዮች ኃላፊነት ነው። ያኔ ምእመናንንም እንደታራሚ የበኩላቸውን ለመወጣት ይቻላቸዋል። የተባባሪነት ሚናቸውን በግልጽ ይገነዘባሉ።

[13] Hailu Cherenet Personal Journal Harisonburg April, 1997

የውይይት ጥያቄዎች

1. ምእመኑ ለመድረኩ ትብብሩን ውጤታማ በሆነ መንገድ የሚገልጸው እንዴት ነው?
2. እሱታዊ ትብብር የሚቀነሰበትን መንገድ ግለጹ?
3. የምእመኑን ተጨማሪ የትብብር መንገዶች በመመዝገብ ተነጋገሩባቸው።

4.4 ምእመኑ እንደ ታራሚ

በብሉይ ኪዳን ክቡር ቃሉ ሕዝቡን ለማረም በተደጋጋሚ ወደ እግዚአብሔር ሕዝብ ይላክ ነበር። ይህ የሆነው በጣም ብዙ ጊዜ ነው። ክዚህ ርዕሳችን ጋር ተዛማጅ የሆነውን በነህምያና በህዝቡ ሕይወት የተፈጸመውን ለምሳሌነት እናነሳለን። ክቡር ቃሉ ነህምያና ሕዝቡ ሰንስላ እንዲነሱ ኃጢአታቸውን ገለጠው። ግርዶሽን በማንሳት እውነተኛ ማንነታቸውን ለሕዝቡ ያስረዳቸውን ቃሉን የሰሙ ሁሉ በይፋ ተናዘዙ (ነህ 8:9-18)። በተጨማሪም ለእነርሱ ብጹዎች የሚገዳቸው እንዲሆኑ ብርሃንን ከሕያው ቃሉ በተቀበሉ ጊዜ ለመታረም ራሳቸውን ለጠ። ልክ እንዲሁ ከቃሉ ዙሪያ የሚቀመጠ አማንያን በሙሉ ራሳቸውን እይተው ለመታረምና ክእምላክ ጋር ጤናማ ግንኙነት ለመመሥረት እድል ያገኛሉ። ክላይ በተገለጸው ክፍል ውስጥ ዘመቅሰውም ጊዜ ለሚክሰሉ ፍላጎት የሚሆን ብርሃን ፥ የነገ ተስፋም የሚሆን ድጋፍ ክቃሉ እንደሚገኝ ነህምያና ህዝቡ ተገነዘቡ። ስለሆነም ለመታረም ራሳቸውን አዘጋጁ። በቃሉ አርቃናቸው ተገልጧልና ራሳቸውን መደበቅ አልቻሉም። ስለሆነም አርማቱን በአሽታ ተቀበሉ። በአዲስ ኪዳንም ተጽፎ እንደምናነበው አያሌ የመጸሕፍ ቅዱስ ክፍሎች ምእመኑ በመታረም ከእምላክ ጋር እንዲራመድ የማያቋርጥ ጥሪን ሲያደርጉ እንመለከታለን።
ሐዋርያው ጳውሎስ ሳቴቶ «ብሃይማኖት ጤናሞች እንዲሆኑ በብርቱ ውቀሳቸው»(ቲቶ 1:13) ብሎ እንደ መክረው መንፈላዊ ንጽሕናችን እንዲጨምር ክመድረክ ጉድለቶቻችንን በማሳየት እንድንታረም የሚያስገነዝቡ አያሌ ቁም ነገሮች ይነሳሉ። የእስተምህሮ አቋማችንን የሚፈትሹ ቁም ነገሮች ክመድረክ ሲፈሱ ክቃሉ ያፈነገጠ አቋም ያላቸው ምእመናን ለመድረኩ

መስጠት የሚገባቸው ምላሽ ለመታረም ተግባራዊ ርምጃ መውሰድ ነው። በእንዲህ ዓይነቱ ሰዓት ክመድረኩ ወደኛ የሚፈሰው የእምላክ ምክር ወቀሳን ያዘለ ነው። ወቀሳው እኛን በማሳጣት ላይ ያተኮረ ሳይሆን በመታረም ውበታችን እንዲጨምር ልባዊ ጥንቃቄን የያዘ እንደሚሆን ይታመናል።

ምክንያቱም በመድረክ ላይ የሚቆም ማንም ሕዝቡን ለማሳጣትና ለማዋረድ ዓላማ ያደርጋል ተብሎ አይታሰብምና። ይሁን እንጂ ነገሮች ክበድ ብለው ተግባራዊ እክሄዳችንን ሊፈትሹ የብዙዎቻችን ምላሽ ሁለት መልክ እንደሚኖረው ይገመታል። እንዳንዶቻችን ወዲያውኑ ለመታረም የሚፈቅድ የቅንነት ምላሽ ለመድረኩ ስንሰጥ፥ እልክኝነት የሚያስቸግረን ጥቂቶች ደግሞ ምርምር እንጀምራለን።

ምእመኑ እንደታራሚ ለመድረኩ የሚለጠውን ምላሽ እንደ ምእመን ሆነን ስናስብ የሚያጋጥሙንን እነዚህን ሁለት ዓይነት ምላሾች በመጠኑ ጠጋ ብለን ብንቃኛቸው ክየትኛው ወገን እንደሆንን እውቀን ራሳችንን ወደ እውነተኛው የቃሉ እቋም ለማምጣት እንተጋለን። እሱታዊ በሆነ መንገድ የመጣውን ወቀሳ ለማስተናገድ ክቆረጥን ወደ ማሳደም የሚወስድ እቋም መያዝ ይቃጣናል። ምክንያቱም በተነገረው ነገር የተሰደብን እንጂ ለመታረም ዕድል የተሰጠን አድርገን አንወስድምና። ለምን እንዲህ እንባላለን? ብለን በጠየቅን ጊዜ ሁሉ ምላሻችን አሉታዊ ነው ብሎ ማሰብ እግባብ አይሆንም። ግና እኛም የምናውቀው ሀሊናችን የሚመለክርብንና የሚፈርድብን ነገር እያለ ለመታረም ባንፈቅድ እርሱ ተጨባጭ አሉታዊ እቋም ነው። ይህም በመታረም ክእምላካችን ጋር ጤናማ ሕብረት እንዳናደርግ ይከለክለናል።

እንዳንዱም መንፈስ ቅዱስ ያመጣውን ወቀሳ ምክንያት በመስጠት በግላችን ማምለጥ፥ ሌላውም ደግሞ ትኩረት እንዳይሰጠው ልናደርግ ሁሉ እንችላለን። መልእክተኛውን ኮንነን ማሰፍ የምንሞክርበት ጊዜ ጥቂት አይሆንም። በእንዲህ ዓይነቱ አሉታዊ ምላሽ መክራቸውን ያዩ፥ የተሰደቡ የተዋረዱ እንዲሁም በር የተዘጋባቸው ዘማሪያንና ሰባኪዎች እዚህ ጋ ለማነሳው አሉታዊ ምላሽ ምስክር ናቸው። መታረም የማይፈልጉ አፈንጋጮች ነገሩ ሲከርር እንደ አስጢፋኖስ በመውገር የንጹሐንን መልእክተኞች ሕይወት

አስከማሳለፍም አንኳን ሲደርሱ ይችላሉ (የሐዋ 8:54-60) እንዲህ ዓይነቱ አልታረም ባይነት የሚያስቸግረው ኅሊና ሲደነዝዝ ነው (1ኛጢሞ4:2)::

ግና የሰሙት ከሚያደነድናቸው ይልቅ ሊጠቅሙ የሚሰሙ በመታረምም ከአምላክ ጋር ሰመሆን የሚፈቅዱ በርካታ ናቸው:: እነዚህኞቹ ታራሚዎቹ ናቸው:: የሰሙትን በአዎንታዊ መልኩ የሚያስተናግዱ ቶሎ ብለውም ለመታረም የሚፈቅዱቱ ደግሞ ወደ ትክክለኛው ጎዳና በንስሃ ለመግባት ይፈቅዳሉ:: የጌታ ሃሳብ ሰሁላችን ለመታረም የምንፈቅድ እንድንሆን ነው:: በተለይ ከቃሉ ያፈነገጠ አቋም ሲኖረን ይህንን ፈጥነን በምናደርግ ልጆቹ ጌታ ደስ ይሰኛል:: ዳዊትን እንደልቤ ብሎ የጠራው ለዚህ ሳይሆን አይቀርም፡! የዳዊት አቋም አብዛኛውን ጊዜ ጌታ ሊያዝን ማዘን÷ሲቆጣ መቆጣት ÷ እንዲመለስ ሊፈልግ ምልስ ወዘተ.. ነበረ:: ስለዚህም አንደ ልቤ አለው::

ጌታም ሕዝቡ እንደልቡ እንዲሆንስትና ታራሚ እንዲሆን ይፈልጋል:: ጌታን የሚያሳዝነው መውደቃችን ብቻ ሳይሆን ለመነሳት አለመፈለጋችን ነው:: መሳሳታችን ሳይሆን ለመታረም አለመፈለጋችን ነው:: ድሮም ኃጢአተኛ ሆነን አገኘን÷ አጠበንና ከእርሱ ጋር ሕብረት ፈጠርን:: ታዲያ ቆሸሸን ስንገኝ ለመታጠብና ለመጽዳት አለመፈለጋችን ጌታችንን ያሳዝነዋል:: መንፈሱንም እናስመርራለን:: ለመታረም የሚፈቅዱና «አጠበኝ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ» ለሚሉት ሁሉ ግን አስደናቂ የሕይወት ንጽሕና ይሰጣቸዋል::

ቃሉን በመሰማት ከእርሱ ጋር ለመጣበቅ የሚፈልጉትን ታራሚዎች «አብዝተው እንዲያፈሩ ያጠራቸዋል::» የአስተምህሮ ስህተት ፈጽመን÷ ሞራላዊ ችግር ውስጥ ወድቀን ራሳችንን ስናገኝ ÷ ከመድረኩ ብርሃን ስንቀበል ወዲያውኑ አዎንታዊ ምላሽ ከሰጠን እግዚአብሔር ወዳሰበልን የተሃድሶ መስመር ውስጥ እንገባለን:: ወቀሳው የመጣው ጤና ስለጎደለን ነው:: ስንወቀስ ለመታረም የፈቀድን ታማሚዎች ግን ፈውስ የሚባለው አዲስ የተሃድሶ መስመር ውስጥ እንገባለን:: «እርስ በእርሳችሁ በኃጢእታችሁ ተናዘዙ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለሌላው ይጸልይ» (ያዕ5:16)::

በአዲስ ኪዳን የተጻፉልንን መልእክቶች ይዘት ስንመለከትም በአብዛኛ ው እኛን ለማረም የተሰጡ መመሪያዎችን እንዳካተቱ እንገነዘባለን:: ምእመኑ እንደታራሚ ከመድረኩ ብርሃን ሲመጣለት ለመታረም ፈቃደኛ መሆን አለበት:: ዝማሬዎቻችን እንዲሁም የቃሉ አዋጅ የሚያነጻንን ሥራ ለመሥራት መቻል አሰባቸው:: በቅርብ ጊዜ የሚያርሙን ነገሮች ከመድረክ እየጠፉ ስለመጡ እንዲህ ዓይነቱ ነገር ብርቅ እየሆነ መጥቷል:: የሚያርም ብርሃን እንዲላክልን ያለማቋረጥ መጸለይ አለብን::

በተደጋጋሚ የሚፈጸመው ሌላው ስህተት መልእክት ሲተላለፍ በተለይ ሰባኪው መገለጥ የሚያመጣ ከሆነ ይለዩአቸው የተባለውን ትዕዛዝ በመተላለፍ ጸጥታን ማደፍረስ ነው:: ከቃሉ ያፈነገጠ አንዳንድ ነገር ቢባል እንኳን ለመለየት እስኪያስቸግር ድረስ ግርግር የሚፈጥሩ÷ ትርምስን የሚያበረክቱ ምዕመናን ቁጥራቸው ጥቂት አይባልም:: በርጋታ ማዳመጥን÷ በስርዓት ማምለክን የሚከለክል ነገርን እያየን ከመጣንማ ዓመታት ተቆጠሩ:: ይህንን ለማረም ከመድረኩ የምዕመኑን ኃላፊነት ማስገንዘብ የመድረክ አገልጋዮች ቀዳሚ ተግባር ሊሆን ይገባል:: በእውነተኛና በሳል አማኞች እይታም ዛሬ ያለንበት ሁኔታ የሚያሰጋ እንደሆነ ሲነገር እንሰማለን:: ስለሆነም ታራሚ ሆነን ከአምላካችን ጋር በመስማማት እንድንራመድ ያለንበትን ሁኔታ ጠቁመው «ከወዴት እንደወደቅህ አስብ» እያሉ የሚጠሩንን መልእክቶች በመስማት መታረም ይኖርብናል::

በተጨማሪም መጋቢዎች ዓመታዊ የጊዜ ሰሌዳን አውጥተው የሚያገለግሉትን ህዝብ በሚያስተሳስር የጋራ ዓላማ ዙሪያ ጠንከር ያለ ትምህርት ከመድረክ ለማቅረብ ዕድሉ ካልተሰጣቸው ምዕመኑ እንደተዥጎረጎረ ይቀጥላል:: ስለዚህ ደግመን ደጋግመን እንዳስገነዘብነው መጋቢዎችም ከመዳቢነት ከፍ ያለና የጎላ ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል:: ያኔ ሕዝቡ በቀላሉ አንድ መልክ ይይዛል:: የታረመና የተገራ ስለሚሆን የመጣ ሁሉ እየነዳ ሲያንገላተው አይፈቅድም:: በተጨማሪም ከፉ ደጉን የሚለይ ልቦና አትርፎ የጌታ ስሙ እንዲቅደስ ክብሩ እንዲወደስ የበኩሉን ያደርጋል:: ጌታ ያንን ዘመን ሁላችን አንድናይ ያግዘን::

የውይይት ጥያቄዎች

1. ምአመኑ እንደታራሚ ለመድረኩ ምን ዓይነት ምላሽ አንዲሰጥ ይጠበቅበታል?
2. ምአመኑ አልታረምም ሲል የሚያስከትለው ችግር ምንድነው?
3. ባሬ ባሬ ከመድረኩ የሚያርመን ብርሃን ጠፍቷል የሚባሰው ምን ያህል አውነት ነው?

4.5 ምእምኑ አንደ ገምጋሚ

በብሉይ ኪዳን በዘፍጥረት መጽሐፍ እንደምናነበው እግዚአብሔር አምላክ የሠራውን ሥራ «መልካም እንደሆነ አየ» የሚለው ዓረፍ ተነገር ከግምገማ ጋር ይያዛል። ስው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም ካለ በኋላ የሚበጀውን ለማድረግ ርምጃ መውሰዱ ከግምገማ ጋር የሚገናኝ ተፈጥሮ አለው(ዘፍ 1-2 ይመልከቱ)።

በአዲስ ኪዳንም የእግዚአብሔር ባሪያ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለገልግሎት አጋሮቹ «በከንቱ ሮጫ እንዳልሆን የምሰብክውን አስታውቅኋቸው» ብሎ በተናገረው ሃሳብ ውስጥ ከግምገማ ጋር የሚያያዝ አባባል አለው። ይኸው የእግዚአብሔር ስው ለቆሮንቶስ ሰዎች በሰጠው ምክር ላይ «ራሳችንን ብንመረምር ባልተፈረደብን ነበር» 1ኛቆሮ11፡31 ብሎ ተናግሯል። በዚህም አገላለጽ እንዲሁ የግምገማ ሃሳብ ተንጸባርቆ እናገኛለን። ቃሉ በእንድም በሌላ መልኩ ዙሮ የመቃኘትን ጉዳይ በተመለከተ የሚናገረው ነገር አለ። እኛም ቢሆን በየዕለቱ ግምገማን በሚጠይቁ ሁኔታዎች ውስጥ እናልፋለን። ግና ባሕላችን አላደረግነውም። በመሠረቱ ግምገማ ማለት የተሠራውን ዙሮ ከቃኙ በኋላ ብያኔን መስጠት ነው። ብዙዎቻችን መደበኛ ውን ግምገማ በአሉታዊ ገጽታው ስለምናውቀው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንኳን ማድረጉን ማሰቡንም ጭምር እንጠላለን።

እንኳን ምእመኑ መሪዎችም እንኳን እንዲህ ዓይነቱን ነገር በመደበኛ ሁኔታ የማከናወን ልምድ ያንሰናል። ይሁን እንጂ ጥላቻችን ስሙን እንጂ ድርጊቱን አለመሆኑን ከመንፈላዊ አገልግሎቶች በኋላ የምንሰጣቸው አስተያየቶች ይናገራሉ። ስሙን እንጥላው እንጂ ግምገማን እንጠቀምበታለን።

ለመሆኑ የዛሬ መልእክት እንዴት ነበር? ዝማሬውስ? የእምልኮ መሪውስ? ምን ማድረግ ነበረበት? የትኛውን በተሻለ ሁኔታ አደረገ? ክዛሬው እምልኮ የተሳካው የቱ ነበር? እንዴት? ሌሎቹስ እንዲሳኩ ምን መደረግ ነበረበት? በማለት ከእምልኮ በኋላ አንዳንዶቻችን እንጠይቃለን። እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ጠይቆ መልስ መፈለግ ግምገማ ነው። ይህን ደግሞ ብዙ ጊዜ እናደርገዋለን። ለዚህ ነው የምንጠላው ስሙን ነው ያልኩት።

ምእመኑ በእኔ እይታ ገምጋሚ ነው። ከላይ እንዳልኩት በይፋ እያደርገውም እንጂ በለውር አምላያዎቹን ይዞ ምስባክቻችንን ይቃኛል። በመድረኩ ወረፋ ጠብቀው የወጡት ሁሉ ያሉንን ሰጥተውናል ወይ? ወይም ቤተክርስቲያን አነርሱ ይሰጡአትኋል ያሉትውን ነገር ከእነርሱ አግኝተናል ወይ? በማለት ተገቢ የግምገማ ጥያቄ ይጠይቃል። ምአምናን አንዳንዴም ሲሳሳቱ የሚመስላቸውን የብሶት መግለጫ መንገድ ይከተላሉ። ስለዚህ ምእመናን ስተውም ቢሆን ልክ ሆነው ይገመግማሉ። ግምገማ በምእመኑ ሕይወት የተጨበጠ ሐቅ መሆኑ ግልጽ ሊሆንልን ይገባል። ምአመናን በየአሁዱ ምስባኩ ላይ የሚቆሙትን ወር ተረኞች በታያቸው መንገድ ይመዝናሉ። ዳኝነትም ይለጣሉ። ወገኖች!! «ወጥን ማን ያውቃል ቢባል ቀማሽ ነው አሉ» እንዲሉ ምእመኑ በየፕሮግራሞቹ ምድብተኛ ሆነው ከመጡ በኋላ ይህንን አመጣንልህ የሚሉትን በሙሉ ሙያዊ መመዘኛ ተጠቅሞም ባይሆን አበጥሮ ያያቸዋል። ስለሆነም ምእመኑ እየቀመሰ በግል ቤውስጡ እንዲሁም ከሚመስሉት ጋር የራሱን ዳኝነት ይሰጣል። ምእመኑ እንደ ገምጋሚ ገንቢ በሆነ መንገድ ሃሳፊነቱን እንዲወጣ ቤተ ክርስቲያን ልታደፋፍረው ይገባል።

ቤተ ክርስቲያን ምእመኑን ለነሲብ ፕሮግራም ልትተወው አይገባም። ይልቁንም ዓመታዊ ፕሮግራሞች ምንና እንዴት እንደሆኑ ተገልጸውለት አየጸለየ አንዲጠብቅ መቀስቀስ አለበት። በእስካሁኑ አሠራራችን በየአሁዱ ማን እንደሚመጣ የሚያውቁት በጣት የሚቆጠሩት አገልጋዮች ብቻ ናቸው። ከእነርሱም የተወለኑት ብቻ ናቸው÷ ወር ተረኛው ማን አንደሆነ የሚያውቁት። ውጤትን ለመቃኘት ይህ አሠራር አይበጀንም። በየዓመቱ በሚከናወኑ ፕሮግራሞች ምስባኩ ከየት ተነስቶ የት እንደሚወስደው ምእመኑ

ስለማያውቅ የጠራ ግምገማ ለማድረግ ይቸገራል። ስለዚህ ምእመኑ እንደገምጋሚ የተሳካለት እንዲሆን እንረዳው ዘንድ በተለያዩ የአገልግሎት እንቅስቃሴ የተለለፍነውን ይመለከተናል።

ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህንን እናደርጋለን ተብሎ ቢነገረው ለዝግጅታችን ለኬት ለመጸለይ ራሱን ይለጣል። ከዚያም አደርገዋለሁ ያልነውና ያደረግነውን በጥሞና አብሮን ያያል። ምእመኑ እንደ ገምጋሚ አቃጆችን እንዲያግዝ ራሱንም ለዚያ ተልኦኮ እንዲያለናዳ አደርገዋለሁ ካልነው ምን ያህል እንደቀረ በማየት ገንቢ መረጃ እንዲለጠን ሪፓርታችን ከወጪና ገቢ ያለፈ ነገርን ማካተት አለበት። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኗ ራዕይ ተተግብሯል ወይስ አልተተገበረም? የሚለው ጥያቄ በአስተማማኝ ሁኔታ መመለስ አለበት። ያኔ ምእመኑ የጎን ላይሆን የፊት ለፊት ገምጋሚነቱን በብቃት ይወጣል። በራእይ መጓዝ በሃዲድ ላይ ባለ ጉዞ ይመስላል። ያለሁለት ሚዛናዊ የሃዲድ መለመር ባቡሩን ማስኬድ አይታሰብም። ባቡሩ እንዲሂድ ሁለቱ መስመሮች በቦታቸው መሆን አለባቸው።

ልክ እንዲሁ ልናደርግ የተመኘነው ዓላማችን አንዱ የሃዲዱ መስመር ነው። ልንደርስበት የፈለግነው (የተደረገው) ነገር ሌላው የሃዲዱ መስመር ነው። ያኔ መስመር ላይ ነን። አስበን ÷ ይህንን እናደርጋለን ብለን ÷ ምንም ባናደርግ ራእዩ ጨንግፏል ማለት ነው። ይህንን ሁሉ በተጨበጠና በሚሰፈር መልኩ ለማየት የምእመኑ የገምጋሚነት ሚና ወሳኝ ነው። በአገራችንን አብዛኞቻችን የማጎበረ-ምእመኑን አመራር የምንቀበል ነን። ይሁን እንጂ ምእመኑ እንዲገመግመን አንፈቅድለትም። ምእመናንም ይፋዊ ግምገማን ለማካሔድ መብት ያለን እንደሆነ ባለማወቅ ቅሬታችንን ለመግለጽ ሐሜትና አሉባልታን የብሶታችን መግለጫ አድርገን እንጠቀምባቸዋለን። ከዚህ ይልቅ የቤተክርስቲያንን ዕቅድ በተለይም ከምስባኩ አኳያ ያለውን በውል አጢነን ግምገማን በተመለከተ ገምቢ ሚና መጫወት አለብን።

ከእኛ መሐል ወጥተው እንዲያስተባብሩን የሰየምናቸው የምስባክ ኮሚቴው አባላት ወይም አረኛችን እንዲሆን የሾምነው ግለሰብ መንፈላዊው አገልግሎት እንዲከናወን ካደረጉ በኋላ ገለልተኛ ተመልካች ሆነው እንዲቀመጡ መፍቀድ የለብንም ። ይልቁንም ትናንት የተደረገውን ቃኝተን

ነገ በተሻለ መንገድ ኃላፊነት የተለጠው ክፍል እንደት ሊሠራው እንደሚችል ሥራውን መቃኘትና መገምገምን እንደጥሩ አጋጣሚ እንዲጠቀምበት በጎ ተጽእኖን ማሳደር አለብን።

ምክንያቱም አስተባባሪው ክፍል አገልግሎት ፈጽሞ የተከናወነውን ነገር መለስ ብሎ የማይገመግም ከሆነ የወደፊቱን አገልግሎት ባልታሪመ ወይም ባልተስተካከለ መሠረት ላይ የሚገነባ ይሆናል። ምእመኑ እንደ ገምጋሚ ያልተፈለገ ነገሮች በምስባኩ ላይ እንዳይደገሙ እንደ ግምገማ ያሉትን የማሳወቂያ መንገዶችን በመጠቀም አደራውን መወጣት አለበት። ይህንን ለማድረግ የአጥቢያ ምእመናን ዓመታዊ ስብሰባን እንዲሁም ሃሳብ መለጫ ሳጥኖችን ለዚህ የተቀደስ ተግባር ሊጠቀምባቸው ይችላል። ምእመኑ እንደገምጋሚ ችግሮች ሳያድኑና ሊታረሙ የማይችሉበት ደረጃ ሳይደርሱ በአጭሩ እልባት እንዲበጅላቸው ለማድረግ የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ የሚያስችለውን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።

ግምገማ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አገልግሎት ውጤታማ እንዲሆን የሚያስገኘው ጠቀሜታ እጅግ ታላቅ ነው። ስለሆነም ይህንን አውነት የተገነዘቡ ምእመናን ደግመን ደጋግመን እንደገለጽነው ለመድረክ የሚሰጡት ገንቢ ምላሽ ለምስባኩ መዋብ የበኩላቸውን ገምቢ ሃሳብ ማዋጣት ነው። ስለሆነም ምእመኑ እንደ ገምጋሚ አሉታዊ አዝማሚያዎችን ወደ ጎን ትቶ በአዎንታዊው መንገድ እንዲቀጥል ይመከራል።

ግምገማን መደበኛ በሆነ መልኩ ከእኛ ይልቅ በአሁኑ ወቅት አያሌ መንግሥታዊና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ይገለገሉበታል። ዓላማቸው ይለያይ እንጂ ዞሮ በመቃኘት ትናንት የሠሩትን ሥራ ጠንካራና ደካማ ጎን ለማየት ያላቸውን ቁርጠኝነት ያሳያናል። ምን እንዳለመ ምን ደግሞ እንዳጠፋ ለማየት ኃይለኛ ጉጉት አላቸው። እልፎ አልፎ የጠሉትን ለመጉዳት እንደሚጠቀሙበት ቢታይም ግምገማ በአዎንታዊ መልኩ ጠቃሚ ነው። እኛ ም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የምናደርገውን የመንፈላዊ አገልግሎት ግምገማ መደበኛ ገጽታ አጎናጽፈን ብንጠቀምበት ይበጀናል። ምክንያቱም የጠላነው ሰሙን እንጂ ድርጊቱን አይደለም። የጠላነው መደበኛ መሆኑን እንጂ በተዘዋዋሪ እናደርገዋለን። የጠላነው ይፋ መሆኑን እንጂ በስውር ከሚመስሉን ጋር እናደርገዋለን። ይህ የጎን ባህላችን የሚወገደው መች ይሆን?

የውይይት ጥያቄዎች

1. ምእመኑ ግምገማን በተሻለ መንገድ እንዲጠቀምበት ምን መደረግ አለበት?
2. ምእመኑ እንደገምጋሚ እንዲሆን ብናደፋፍረው የሚከሰት አሉታዊ ነገር ምንድነው?
3. በምእመናን መካከል የጎን ንግግር (የበስተጏላ ሃሜት) እንደግምገማ የማይታየው ለምንድን ነው?
4. የግምገማን ገንቢና አሉታዊ ገጽታ በዝርዝር ተወያዩ

4.6 ምእመኑ እንደ ኃላፊ

አብዛኞቹ የሃገራችን አብያተክርስቲያናት በመዋቅራቸው ምእመናዊውን የአመራር መርህ ተቀብሰው ያንን እንደሚተገብሩት ይሰማል። ይህን በማይቀበሱም አብያተ ክርስቲያናት አካባቢም እንኳን የምእመናን ድርሻ ወሳኝ መሆኑን የሚያመላክቱ ድርጊቶች አሉ። ለምሳሌም ምእመኑ መሪዎቹን እንዲመርጥ ይደረጋል። ይህም የምእመኑን ወሳኝ ሚና በተግባር ያሳያል። ምእመኑ የአመራሩ የበላይ አካል በሚባልበት ሥፍራ መብቱ ሊጠበቅ እንዲሁም እንደባለ ሥልጣን ሊከበር ይገባዋል። በዚህ አይታ ላይ የተመሠረተን ምላሽ ለመድረክ የሚሰጥ ከሆነ አያሌ የሚታረሙ አካላት እንዳሉ መገንዘብ የተሰወረ አይደለም። ምክንያቱም ምእመኑ እንደኃላፊ ከአደናጋሪ ይልቅ መሪን ÷ ከአዝማሪ ይልቅ ዘማሪን የሚፈልግ መሆኑ አይጠረጠርምና።

መጋቢው ከመጻቢነት አልፎ ለምእመኑ የማያቋርጥ እንክብካቤ ከመድረክ መስጠት አለበት። ይሁን እንጂ ይህንን ለማድረግ ባልተቻለ ጊዜ ምእመኑ ያልሆነበትን ምክንያት ምእመኑ ጠይቆ በመረዳት ይህ አውራ የመጋቢው አገልግሎት የሚተገበርበትን መንገድ ማመቻቸት አለበት። በተጨማሪም ለመጋቢው ሁኔታዎች ተመቻችተው መጋቢው ለመመገብ ካልተጋ ርምጃ ለመወሰድ መሰናዶት አለበት። ምእመኑን አረኖውን የምገባ ተልእኮውን እንደሚገባ ባልተወጣ ጊዜ የሚጠበቅባቸውን ያጎደሉ የበታቾቹን እንደሚጠይቅ ኃላፊ ምእመኑ መጋቢውን ለምን ብሎ ሊጠይቀውና አራሚ

የሆነ እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል። ይህ ሲሆን የሚችለው ግን በአገራችን የግልጽነት ባህል እየዳበረ የመጣ እንደሆነ ብቻ ነው።

ምእመኑ በኃላፊነቱ የሚጎድልበትን ብቻ ሳይሆን የሚያጎድለውንም ዓይቶ በጸሎት ቤት መሚሳት ሰላሰባቸው ነገሮች ሊጨንቀው ይገባል። በመድረኩ ሳይ የሚቆሙ ሰዎች ምእመናን ሊያቀርቡት እየቻሉ በጎደለ ነገር ሊሳቀቁ አይገባም። (ለምሳሌ ጀነሬተር መግዛት የሚችሉ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ሆነው እያለ መብራት ሰለ ጠፋ እንቻቻል መባል ያስበት አይመስሰኝም)። ፑልፒቱ በረጅም ሰው ልክ ተስርቶ አጭሮች ሊመጡ ሊያሳጣቸው አይገባም።) ጸሎት ቤቶች አያሌ ባስጠሳችን ይዘው ራሳቸውን አስጨናቂ ነገር ውሰጥ ሊያገኙት ይሰተዋሳል። ምእመናን በጸሎት ቤት የጎደሉ ነገሮችን ለማሟላት ቅድሚያ ከመሰጠት ይልቅ በራሳቸው ፍላጎትና ምርጫ ዙሪያ ባማከለ ወጭ ራሳቸውን ሰሳሚስጡ በቀሳሱ የሚቀረፉ ችግሮች ዓመታት ሊወስዱ ይሰተዋሳል። ምእመናን ለመድረኩ እንደ ኃላፊ የሚስጡት ቀጥተኛ ምላሽ አመራር መሰጠት ነው። በተጨማሪም ጎደሉ የተባሉ ነገሮች በሙሉ የሚሟሉበትንም መንገድ መፈለግንም ጭምር ያካትታል። አመራር መስጠቱን በወኪሎቹ እንደሚወጣው ሌሎች የኃላፊነት ተግባሮቹን ሁሉ በዚሁ መንገድ ይወጣዋል። ስለሆነም ምእመኑ እንደ ኃላፊ አደራውን የመወጣቱ ጉዳይ ለመድረኩ የሚስጠው አንዱ ምላሽ ነው።

የውይይት ጥያቄዎች

1. ምእመኑ እንደ ኃላፊ ለመድረኩ ምላሽ እንዳይሰጥ የሚገዳደሩት ምንድናቸው?
2. ምእመኑ በእርግጥ በብዙ አብያተ ክርስቲያናት የኃላፊነት ድርሻ አለው ወይ? ካልሆነስ ለምን?
3. ምእመኑ በርግጥ መጋቢውን በተግባር የሚጠይቅበት መሰመር ተዘርግቷል? ካልተዘረጋስ ችግሩ ምንድነው?

4.7 ምእመኑ እንደ ጠያቂ

ምእመኑ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ኃላፊነቱን ብዙዎቻችን ከተቀበልን ነገሮች ከቃሉ አፈንግጠው በምሰባኩ ላይ በታዩ ጊዜ የመጠየቅ ሥልጣን እንዳለው መገንዘብ ይኖርብናል። የየትኛውም ክፍል ኃላፊ የመቆጣጠር ÷ የመጠየቅ ÷ የማረም እንዲሁም የመቅጣት መብቱ የተጠበቀ ነው። ስለሆነም ምእመኑ እንደ ኃላፊ ለመድረኩ የሚሰጠው ምላሽ ጠያቂነትን ይጨምራል። ምእመኑ ያፈነገጡትን መቆጣጠር÷ ከመስመር የወጡ እንቅስቃሴዎችን እንዲታረሙ ማድረግ በተጨማሪም አርማቱን የማይቀበሉትን እስከ ማሰወገድ የደረሰ አርምጃን መውሰድ የሚቻለው መሆኑ በውል ሊጤን ይገባል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው እንቅስቃሴ ለቃሉ ማዕከላዊነት በቂ አውቅናን የሰጠ መሆን አለመሆኑን በየጊዜው እንደ ተደራጀ ቡድን ማጣራት የምእመኑ የጠያቂነት ድርሻ ነው። እንደጠያቂ ነገሮች እንደቃሉ ባልተከናወኑ ጊዜ መለስ ብሎ ነገሮች የሚታረሙበትን ሁኔታ መፍጠር ይገባዋል።

ስለሆነም ምእመኑ ታራሚ የሆነውን ያህል አራሚ መሆኑ ጭምር ሊታወቅለት ይገባል። እንዲያገለግሉት መርጦ እንዲሾም የተጠየቀ ህዝብ ጎደለ የሚለውን ነገር ባየ ጊዜ እንደ ኃላፊ የመጠየቅ መብቱን ሊነፈግ አይገባም። ከጥያቄም አልፎ ነገሮችን በጥልቀትና በስፋት በመነጋገር ገንቢ ሃሳብ የሚሰጥበት የውይይት ጊዜ ሊኖረውም ይገባል።

በቃላችን ምእመኑ መብት አለው ብንልም ይህንን መብቱን ብዙዎቻችን ስናከብርለት አንታይም። ስለዚህ በቀሩልን የሕይወት ዘመናት የምእመኑን ምላሽ ከዚህ እኳያ ተገንዝበን ተገቢውን እውቅናና ታዛዥነት ልናሳየው ይገባል። ምእመኑም ይህንን የከበረ ኃላፊነቱን ተገንዝቦ በዓመታዊ ስብሰባ ወቅት ከወጭና ከገቢ ሪፓርት የበለጠ ነገር ለመስማት የሚችልበትን ጥያቄ ማቅረብ አለበት። ሪፓርቱም ዓመታዊ የቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ ሊያስታኘው የሚችል እድል እንዲሰጠው ሆኖ መዘጋጀት አለበት። የሚቀርብለትን ዓመታዊ ሪፓርት በጥሞና አዳምጦ ለመልካም ሥራ እምላክንና በመስክ የለፉትን አመስግኖ መታረም ስሚገባቸው ነገሮች የበኩሉን ምላሽ መስጠት ይኖርበታል። ያኔ ምእመኑ በሚፈለግበት ቦታ ላይ ነው ማለት ይቻላል። ቦታውም የይስሙላ ሳይሆን በእርግጥ ትክክለኛ

እንደሆነ በተግባር አውን ይሆናል። በተጨማሪም ምእመኑ እንደ ጠያቂ ኃላፊነቱን በሚገባ ተወጥቷል ማለት እንችላለን።

የውይይት ጥያቄዎች

1. ምእመኑ ለመድረክ የሚሰጠው ምላሽ እንደ ኃላፊ ጠያቂነት ነው የሚሰው ሃሳብ ልክ ነውን? ካልሆነስ ለምን? ተነጋገሩበት
2. በርግጥ ምእመኑ የመጠየቅ መብት አለውን?
3. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን የጠያቂነት ሚናቸውን በብቃት የማይወጡት ለምንድነው?

ማጠቃለያ

ለአያሌ ዓመታት በቤት ለቤት አገልግሎት ከከረምን በኋላ ይፋዊ የአምልኮ ነጻነት ስናገኝ በውስጣችን የሞላውን አያፈለስን ሰማምለክ በመታደላችን ደስ ብሎናል። ይሁን እንጂ ወደ አደባባይ አገልግሎት ስንወጣ ያልጠበቅናቸው አያሌ ነገሮችም አጋጥመውናል። ምናልባት ስላልተዘጋጀን ነው በማለት ለጊዜው አሉታዊ አዝማሚያዎችን ታገስናቸው። አንዳንዶቹን ባንቀበላቸውም ከጊዜ ጋር ለምደናቸው ተዋህደውናል። በአሁኑ ወቅት እንዳንዶቹ አነጋጋሪ እየሆኑ በመምጣታቸው መድረኮቻችንን በተመለከተ ይህች ጽሁፍ ሚዛናዊ አይታ እንዲኖረን ጥሪዋን ለማስተላለፍ ሞክራለች። መድረኮችን በተመለከተ ሊነሱ የሚገባቸውን ሁሉ አንስታ የማያዳግም ምላሽ እንደሰጠች አይታሰብም። ለመነሻ የሚሆኑ ነገሮችን ለማለት መሞከሯን ጸሐፊው ይገነዘባል።

ምናልባት ከዚህ በኋላ አያሌ ጸሐፍት በዚህ መስመር የጠራ ነገር እንዲያስጨብጡን ለማነሳሳት ለእኛ በታዩን የመድረኩ አንቅስቃሴዎች ላይ መጠነኛ ሃሳቦችን ለማንሳት ጥረት ተደርጓል። ሁሉንም የዳሰሰ ባለመሆኑ ነገ የተሻለ ነገር ይጠበቃል። ትኩረት ስለሚሹ የመድረክ አገልግሎቶቻችን የማይጨንቃቸው በሳል አገልጋዮች ካሉ አንገረማለን። የምእመኑ ምላሽ አንድ ወጥ እንዲሆን ባይጠበቅም ለመድረኩ ስለሚሰጠው ምላሽ ግንዛቤ እንዲያገኙ÷ የመጣ ሁሉ እንዳይነዳው÷ ማንነቱን በውል እንዲያጤን÷ ምእመኑን

የተረዳነውን ያህል ምላሽ ይዤ ሊሆን ይገባል ብለነዋል። ምስባክ (የመንፈሳዊ እንድንት) ወይም ፑልፒት ኮሚቴንም በተመለከተ ሰለጠንክራና ደካማ ጎኑ የታየንን ብለናል። ግና ከዚህ የተሻለ ሥራ በቅርቡ በወጣት፥ የሰላ አእምሮና መንፈሳዊነት ባላቸው ጸሐፊዎች እንደምናነኝ እተማመናለሁ።

ትኩረት የሚሹ የመድረክ አገልግሎቶቻችንን በተመለከተ የተተኮረበት ጉዳይ መታረም ያለበቸው ነገሮች ላይ ነው። ሐዚም ቤት ሰንሄድ ሐዚመ ከጤነኛው ይልቅ ታማሚ የሰውነት ክፍላችን ላይ እንደሚያነጣጥርና ሰለጤነኛው የአካል ክፍሎቻችን ዝርዝር ትንተና እንደማይሰጠን እኛም የሐዚመን የአደራረግ መንገድ ተከትለናል። ሰለሆነም መድረክ አዛባቢ ያለው ጤንነታችን እንዲጨምር አቀራረቡ ታማሚው ማንነታችን ላይ ያተኩራል። ይህ ማለት ግን መድረክቻችን ተሰፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ ላይ ናቸው ማለት እንዳልሆነ ይታወቅልን።

በመድረኩ ወረፋ ጠብቀው የሚያገልግሉትን የማሳጣት ዓላማ የለንም። ምኞታችንና ጸሎታችን ግን በመውቀስ ሰሀተት እንዲታረም መሰመን ነው። የማጋለጥ ተልእኮን እናሰተናግድም፥ በተግላጽ ውበታችን እንዲጨምር መማጠን እንጂ። ምክንያቱም የጠሳነው መንፈስ «ይወቅሳል እንጂ እያሳጣም፥ ይገሰጻል እንጂ እያጋልጥም።» በዚህ ልብ መድረክቻችን በታሳቁ መጽሐፍ ተገልጦ እንደምናየው ይሁኑልን የሚለውን ልባዊ ጥሪ እናደርጋለን። ዛሬ ጉድለታችን ታርሞ መሰብሰባችን የሚያነቃቃ እንዲሆንልን ጥማታችን ነው። እምላክ ይህንን በማድረግ ይደግፈን።

ወዳጂ ሰለሞን ጥሳሁን ዓላማን በተመለከተ እንዲህ ብሏል «አቅጣጫ የተንቀሳቃሽ ፍጡር ሁሉ ጥያቄ ነው። ለአቅጣጫ ግድ የማይሳቸው ግዑዛን ብቻ ናቸው። ሕይወት ደግሞ መሰመር ላይ ዓላማ ሳለው እንቅሰቃሴ በአቅድ የተቀመጠች እንጂ ሜዳ ላይ የተጣለች አጋጣሚ አይደለችም።»[14] ይህም ጽሁፍ ዓላማ አለው። ዓላማውም የመድረክቻችንን የትናንት ገጽታ በጥሞና ተመልክተን ፥ ክሰሀተታቻን ተምረን፥ ዛሬንና ነገን የተሻለ እንድናደርግ ነው። አቅጣጫችን ይሄና ይሄ ብቻ ነው።

[14] Solomon Tilahun Alama Merash Yekristos Betekristian Addis Ababa: Meserete Kristos Church:2003

ዋቢ መጸሀፍት

Bontrager, Edwin G. and Showalter, Nathan D. It Can Happen Today, Scottdale, Herald Press, 1986.

Brown, Paul B.*In and For The World*: Minneapolis: Augusburger, Fortress Press, 1992

Doran, Carol and Troeger, Thomas. *Trouble At The Table : Gathering The Tribes For Worship* ; Nashville, Tennessee: Abingdon Press, 1992. .

Duck Ruth C. *Finding Words For Worship*: Louisville, Kentucky: Westminster John Knox Press, 1995.

Hymnal: *A Worship Book;* Brethren Press, Elgin, Illinois; Faith and life Press, Newton, Kansas; Mennonite Publishing House, Scottdale, PA. 1992.

Kreider, Alan.*Worship and Evangelism in Pre-Christendom*: Cambridge, England, Grove Books Limited, 1995.

Lindgren, Alvin J.. & Shawchuck Norman. *Management for your Church Organization* Resource Press, 1984.

Nouwen, Henri J.M. *Reaching Out: The Three Movements Of The Spiritual Life* : New York: Doubleday, 1986.

Smith, Ebbie C. *Balanced Church Growth,* Nashville, Broadman Press, 1984.

----------*Congregational Discipling.* Mennonite Publishing House, 1997.

Shawchuck, Norman & Heuser, Roger. *Leading the Congregation (caring for yourselves while serving the other people)* Nashville : Abingden press, 1993.

Steinke, Peter L. *How your family Church Works* Bethesda: The

Alban Institute Inc. 1993.

Stevens, Paul R. & Collins, Phil *The Equipping Pastor* Bethesda: The Alban Institute Inc. 1993.

Southard, Samuel & Luecke, David S. *Pastoral Administration.* Texas : Word Book, 1986. (1-190)

Thomas, Everett J. A *Mennonite Polity for Ministerial Leadership.* Newton Kansas: Faith and Life Press, 1996.

White, James F. *Protestant Worship traditions in Transition* Louisville, Kentucky, Westminster John Knox Press, 1989

የአማርኛ መጻሕፍት

ኃይሉ ቸርነት ሕያው ቅብብል (የአሰባበክ ጥበብና ተግዳሮቱ) ንግድ ማተሚያ ቤት 1995

ሰሎሞን ጥላሁን ዓላማ መራሽ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን 1995.

መጽሐፍ ቅዱስ ኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ዩ.ቢ.ኤስ 1954

መጽሐፍ ቅዱስ አዲሱ መደበኛ ትርጉም አይ.ቢ.ኤስ 1993.